# የአባ ባሕርይ ድርሰቶች

## ኦሮሞኛን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ

ጌታቸው ኃይሌ

ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፲፱፻፺፩ ዓ. ም.

**የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው**

**© 2002 by Getatchew Haile, Avon, Minnesota**
**All Rights Reserved**

**Yeabba Bahriy Dirsetoch**

**ISBN: 0-9706663-1-4**

**Library of Congress Control Number: 2002094114**

የመጽሐፉንና የሽፋኑን መልክ እንዲሁም መጠቀሙንና የኢትዮጵያን ካርታ
ያዘጋጀው፡ አምነ አስፋው

የፊት ሽፋን፡ አባ ባሕርይ አገራቸው ጋሞ ሲጠፋና ቤተ ክርስቲያናቸው ሲቃጠል
ከመጽሐፎቻቸው የቻሉትን ተሸክመው ወደ ሰሜን መሰደዳቸውን ያሳያል።

**ይህን መጽሐፍ ለመግዛት**
**ከታች ባለው አድራሻ መጠየቅ ይቻላል።**

**Inquiries can be sent to:**

**Yeabba Bahriy Dirsetoch**
**P.O. Box 113**
**Avon, MN 56310, USA**

**አያት ለመሆን ለበቃሁበት ዕለት ለነሐሴ ፳ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ. ም.**



❧❧

*ምንተኑ አዐስየከ በእንተ ኵሉ ሊተ ዘገበርከ?*
*ወመኑ የሐምየከ እመ ይእዜ ትስዕሮ ለገብርከ?*
*በሰላም እግዚኦ በከመ አዘዝከ::*
*እስመ አዕይንትየ ርእያ÷*
*እንዘ ይመልእ ኀላቄ ኂሩትከ በሊያ::*

❧❧

*Yeabba Bahriy Dirsetoch oromochin kemmimmelekketu leloch sene-doch gara* or *The Works of Abba Bahriy with Other Documents concerning the Oromo*, is primarily a new edition and translation into Amharic and English of the work *Zenahu le-Galla*, a Ge`ez study of Oromo society and Oromo migration into central Ethiopia in the sixteenth century. The author of the text, the monk Abba Bahriy, was an eyewitness to this migration and himself fled his homeland of Gamo when the Galla/Oromo overran and destroyed it. As such, Abba Bahriy's text is an important firsthand account of the social structure of the pastoralist Oromo and the impact of their migration on the existing agrarian communities of central Ethiopia.

To help clarify the original text, the book contains a chapter of selected quotations culled from primary Ge`ez historical sources that expound upon or are otherwise relevant to the sixteenth century migration. Each quotation is accompanied by its Amharic translation.

The book also contains a chapter about the author and his other works.

*Yeabba Bahriy Dirsetoch*... concludes with a bibliography and an index.

# ማውጫ


ቀዳሚ ቃል (ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት) . . . . . 7
መቅድም . . . . . 9
መግቢያ . . . . . 13

ምዕራፍ ፩ - አባ ባሕርይና ድርሰቶቻቸው . . . . . 33
(1) *መዝሙረ ክርስቶስ* . . . . . 34
(2) *"አጭሩ መዝሙረ ክርስቶስ"* . . . . . 47
(3) *መልክዐ ገብርኤል* . . . . . 49
(4) *ሰላመ ቅዱሳን* . . . . . 49

ምዕራፍ ፪ - *ዜናሁ ለጋላ* . . . . . 53
*መግቢያ* . . . . . 55
*ግዕዙ* . . . . . 63
*በአማርኛ* . . . . . 75

ምዕራፍ ፫ - ጋላ/ኦሮሞ . . . . . 95
(1) ጋላ ወይስ ኦሮሞ . . . . . 97
(2) የጋላ ትርጉም . . . . . 97
(3) የኦሮሞ አንድነት . . . . . 98
(4) ኦሮሞዎች ከሌሎች ይለያሉ? . . . . . 99
(5) "ጋላ" ስድብ ነው? . . . . . 102
(6) የጋላ/የኦሮሞ ዜና ለምን ተጻፈ? . . . . . 103
(7) የኦሮሞ ታሪክ ከምንጩ . . . . . 108
(ሀ) መንግሥትና ሕዝብ . . . . . 109
(ለ) የኦሮሞዎች "ሰብአ ትካትነት" . . . . . 118
(8) የመንግሥት አቅምና ኦሮሞዎች . . . . . 123
(9) ኦሮሞዎችን የማስፈር ፖሊሲ . . . . . 138
(10) በአንድ ሀገር ሶስት መንግሥት . . . . . 155

ምዕራፍ ፬ - ትንሣኤ መንግሥት . . . . . 161

አባሪ ፩ - Appendix I - ከአለቃ ታየ ትልቁ መጽሐፍ የተቀዳ . . . . . 171
17. ስለ ነገደ ጋላ . . . . . 171
ጋሎች በሴት ቅናትና መጋደል ይቅር ብለው ሕግ የሰሩበት ምክንያት . . . . . 178
ስለ ጋላ ትውልድ . . . . . 182
የወሎ እስልምና እውነተኛው ታሪክስ እንዲህ ነው . . . . . 186
ስለ ጋላ ተጨማሪ ያፍ ታሪክ . . . . . 188
አንዱ ታሪክ . . . . . 188
ሌላው ታሪክ . . . . . 190
የጋላ ሥራትና ሕግ . . . . . 191
በጋላ ሕግ የደም ሥራት . . . . . 193
18. ስለ ነገደ እናርያ . . . . . 193

አባሪ ፪ - Appendix II
Ethnography of the Galla *(ዜናሁ ለጋላ)* By Abba Bahriy . . . . 195

አባሪ ፫ - Appendix III
Concerning the Galla by Aleqa Tayye . . . . . 215

ዋቢ መጻሕፍት . . . . . 243
መጠቀሚም . . . . . 251

ሥዕሎች

ደራሲውና ሊያ. . . . . 3
ከመዝሙረ ክርስቶስ (BL Or. 534, f. 13a.) . . . . . 12
የኢትዮጵያ ካርታ . . . . . 14
አንቶኒዮ ሴኪ . . . . . 34
ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳ . . . . . 54
ኢግናዚዮ ጉይዲ . . . . . 62
ከዜናሁ ለጋላ (BL Or. 534, f. 1a.) . . . . . 94
አይኬ ሃበርላንድ . . . . . 96
ከዜናሁ ለጋላ (Aeth. 4, f. 1b.) . . . . . 160
አቶ ዓፅመ ጊዮርጊስ (ዓፅሜ/ዓጥሜ) . . . . . 162
አለቃ ታየ . . . . . 170
ቻርልስ ቤኪንግሃም . . . . . 194
ፕሮፌሰር ባይሩ ተፍላ . . . . . 214
ከሰላመ ቅዱሳን (BL Or. 534, f. 168b.) . . . . . 242
ከመዝሙረ ክርስቶስ (BL Or. 534, f. 137a.). . . . . 250

# ቀዳሚ ቃል

**ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት**

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፥ በዚህ ባሜሪካ አገር፥ በሚኒሶታ "ስቴት" ውስጥ በምትገኘው የኮሌጆቪል ከተማ ያለው "የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርሲቲ" ያሰባሰባቸውን፥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን የጥንት ኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት ማይክሮፊልሞች፥ እነሆ ከሃያ አምስት ዓመታት ለበለጠ ጊዜ በማጥናትና በማመሰካከር ቁጥራቸው በዛ ያለ፥ ለሀገራችን የሃይማኖት፥ የቋንቋ፥ የሥነ ጽሑፍ፥ የታሪክና የባህል ጥናት ከፍ ያለ አብነት ያላቸውን ድርሰቶች በመጻሕፍትና በመጣጥፎች መልክ ሊያቀርብ የቻለ ባለሞያ ነው። አሁን ደግሞ ይህንን "*የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፥ ኦሮሞችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ*" የተባለውን ጥናቱን በጥንቃቄ አዘጋጅቶ አቅርቦልናል።

አባ ባሕርይን እስካሁን ብዙዎቻችን የምናውቃቸው፥ በዘመናቸው ከደቡብ ወደ ማህል ኢትዮጵያ በብዛት ተንቀሳቅሰው መስፈር ስለጀመሩት የኦሮሞ ሕዝብ፥ በግዕዝ ቋንቋ በጻፉት መጽሐፋቸው ብቻ ነበር። አሁን ፕሮፌሰር ጌታቸው ባዘጋጀው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ግን፥ ሌሎች አራት የተከበሩ መጻሕፍትም የደረሱ፥ በዘመኑ የትምህርት መስክ እጅግ በጣም የተራቀቁና የበሰሉ ደራሲም እንደነበሩ ከነማስረጃው አጣርቶ ይነግረናል።

አባ ባሕርይ በጊዜያቸው ከነበሩት የግዕዝ ደራስያን ሁሉ በጣም የተለዩ እንደነበሩ ግልጽ ሆኖ ይታያል። እስካሁን ባሉን መረጃዎች መሠረት ሌሎቹ የዘመኑ ደራስያን ያቆዩልን ጽሑፎች በብዛት የሚያተኩሩት በሃይማኖት መጻሕፍት ትርጉምና ትንታኔ፥ በጸሎት፥ በመዝሙሮችና በቅኔዎች ላይ ነበር። እሳቸው ግን በተጨማሪ፥ በዚህ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ባዘጋጁት ጥናት፥ በዘመኑ በጣም አሳሳቢ የነበሩ የሕዝብ ሰፈራ፥ የሰላም፥ የጦርነት፥ የማኅበራዊ፥ የወታደራዊና የፖለቲካዊ ድርጅት ጉዳዮችንም እየተመራመሩና ካገር ሽማግሌዎች መረጃ እያሰባሰቡ መዝግበው ሊያቆዩልን ችለዋል።

ይህ የፕሮፌሰር ጌታቸው መጽሐፍ ለአንባብያን አንድ አዲስ ፈለግ መቀየሱ ጎልቶ ይታያል። ስለኦሮሞዎች ሲጽፍ የአባ ባሕርይን ጥናት ለብቻው ነጥሎ ሳይሆን፥ ከአፄ ገላውዴዎስ ጀምሮ እስከ 20ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ድረስ የነበሩት ነገሥታት ዜና መዋዕል፥ ጸሐፊዎችም የኦሮሞ ሕዝብን በሚመለከት የደረሱትን ሁሉ ከየስፍራቸው አሰባስቦ

እያዋሐደ ነው ያቀረባቸው። ከነዚህም መካከል፥ የአፄ ሱስንዮስ (1600-1625) ዜና መዋዕል ደራሲና የንጉሡ የቅርብ ባለሟል የነበሩት ኦሮሞው ሊቅ፥ አዛዥ ተክለ ሥላሴ ጢኖም ይገኙበታል። ከነዚህም በተጨማሪ፥ በ19ኛው ምእት ዓመት መጨረሻና በ20ኛው መጀመሪያ ላይ የነበሩት አቶ ዓፅሜና አለቃ ታየ በጊዜአቸው ከነበሩ ያገር ሽማግሌዎች ያሰባሰቧቸውም ተካተዋል። የአቶ ዓፅሜ ቀደም ብሎ ስለታተመ፥ ከኢትዮጵያ ጠፍቶ የነበረውን የአለቃ ታየን መጽሐፍ ከኢየሩሳሌም አግኝቶ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ እሳቸው ያዘጋጁትንም በዝርዝር አቅርቦታል። ሌላውም የታወቁት ኦሮሞ የታሪክ ጸሐፊና ሠዓሊ፥ የጎጃሙ ሊቅ አለቃ ተክለ ኢየሱስ/ዋቅጅራ ይጠቀሳሉ።

ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ያሉን የቀድሞ ሰነዶች ሁሉ አንድ ተመሳሳይ ጠባይ አላቸው። የተጻፉት በጦርነትና በትግል ጊዜ ስለነበረ፥ ብዙ የቁጣና የዘለፋ ቃላት ይበዙባቸዋል። አቶ ዓፅሜና አለቃ ታየ ግን በዘመናቸው ይህንን መንፈስ እጅግ በጣም ለማሻሻልና የኦሮሞዎችን አጠቃላይ ባህልና ማንነት በበለጠ አክብሮት ይዞ ለመረዳት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ እንደነበር ከድርሰቶቻቸው ማየት እንችላለን። ይህን ተገቢ እርምጃ ጌታቸው በዚህ መጽሐፍ የበለጠ አዳብሮታል ማለት ይቻላል። እንዲያውም እሱ ተወልዶ የልጅነት ዘመኑን ያሳለፈው፥ በሸንኮራ ወረዳ ከደጎምሲሳ እስከ ቱሉ ፈራና እስከ ሉሜ ድረስ ባሉት የወላጆቹና የዘመድ አዝማድ መኖሪያ አካባቢዎች ውስጥ እየተመላለሰ፥ ከቤት ከጎረቤት ልጆች ጋራ በኦሮምኛ እየተነጋገረና እየተጫወተ ስለሆነ፥ ቋንቋውንና ባህሉን በቅርብ ያውቀዋል፤ ያከብረውማል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡልን ሰነዶች የሚያሳዩን አጠቃላይ ሥዕል፥ ባለፉት 500 ዓመታት ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብ፥ በየሰፈረባቸው አካባቢዎች ሁሉ፥ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋራ በባህል፥ በቋንቋ፥ በሃይማኖትና በትውልድ እየተዋሐደ የመጣ መሆኑን ነው። ይልቁንም፥ የሀገርንና የመንግሥትን ህልውና ጠብቆና አጠናክሮ በማቆየቱ አንጻር፥ ከተራ ገበሬ፥ ነጋዴ፥ ወታደርና ያካባቢ ጎበዝ አለቃ ጀምሮ እስከ ባለ ሙሉ ሥልጣን የመንግሥት የበላይ ጠባቂነት ደረጃ እየደረሰ፥ በባሌቤትነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያስመዘገበ መሆኑን ሰነዶቹ ሁሉ ይመሰክራሉ።

ታደሰ ታምራት

# መቅድም

በጽሑፍ የቆየልንን የባህልና የታሪክ ቅርስ በአማርኛ ለዛሬው ትውልድ ለማሳወቅ ባለኝ ምኞትና እቅድ መሠረት እነሆ ይህንን ሁለተኛውን መጽሐፍ አቀርባለሁ። አንደኛው መጽሐፍ *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ* በሚል ርእስ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. ታትሟል። አምላክ ፈቃዱ እስከ ሆነ ድረስ ጥረቱ ይቀጥላል።

ከታሪክ ጥሩ ጥሩውን እየመረጡ ሊመኩበት ቢገባም ብቻውን ራት አይሆንም፤ የራስንም ፋንታና ግዴታ አይተካም። እንዲያውም እየኰራንበት በዚያው እንድናበቃ ሊያደርገን፥ በዘዴ ካልያዝነውም ከጐረቤቶቻችን ጋራ ሊያቃቅረን ይችላል። በዚያው መጠን መጥፎ መጥፎውን እየመረጡ ቢወቅሱበት የሚወቀሱት ታሪክ አበላሾች ናቸው እንጂ ወራሾቻቸው አይደሉም። የታሪክ ትልቁ ደግነት እዚህ ላይ ነው፤ የሚወረሰው ጸጋው ሲሆን ጸጋ ቢሱ ወራሽ የለውም፤ ከአድራጊው ሰው ስም ጋራ ብቻ ሲነሣ ይኖራል።

እንደ ኢትዮጵያውያን ያለ ወጣ ገባ ታሪክ ያለው ከባድ ሕዝብ የሀገሩን ታሪክ የሚማረው፥ ታሪክ ራሱን ልድገም ሲል የሚስማማ ከሆነ ለማበረታታት፥ የማይስማማ ከሆነ ለመግታት ነው። የአባ ባሕርይን ጥናትና የዘመኑን ታሪክ ያቀረብኩት በዚህ መንፈስ እንድንረዳውና እንድንጠቀምበት በማመን ነው።

ዐወ

አንዳንድ መጻሕፍት ደራሲዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ረቂቃቸውም ታሪክ ሲኖራቸው አያለሁ። የኔው ግን የሚኖረው አልመሰለኝም ነበር፤ አጭርም ቢሆን አለው።

የ"ዘናሁ ለጋኖ"ን ግዕዝ ወደአማርኛ የተረጐምኩት የአሜሪካኖች ዕለተ አኩቴትን (Thanksgiving Day) ከልጆቼ ጋር ለማክበር ወደ ኒው ዮርክ ለመሄድ አይሮፕላን ላይ በነበርኩበት ጊዜ ነበር። ከበዓሉ በኋላ ከመለያየታችን በፊት ምሳ-መሰል የረፋድ ቊርስ አብረን ልንበላና ልንሰነባበት ከአንድ ምግብ ቤት ተቃጠርን። ሁሉም ከያለበት ተሰባስቦ

ቊርሱ እስኪቀርብ ጥቂት እንደተጫወትን፥ አንዳች ነገር ለማውጣት ቦርሳየን ብፈልግ ካጠገቤ አጣሁት። ያጣሁት ለካ የትርጕሙን ረቂቅና ዕለት በዕለት ስለሚያስፈልጉ በኪስ የሚያዙ ሰነዶችን (ጥሬ ገንዘብ፥ የቼክ ደብተር፥ ክሬዲት ካርዶች፥ የመታወቂያ ወረቀት፥ አረንጓዴ ካርድ) በሞላ እንደያዘ ከታክሲው ውስጥ ረስቼው ነው።

የደስታው መንፈሳችን ተሸበረ፤ ታክሲውን ለመፈለግ ምንም ምልክትና ማስረጃ ስለሌለን የመጣውን ከመቀበል በቀር ሌላ ዕድል አልነበረኝም። የጠፋውን ሁሉ ለመተካት ቢቻልም ሂደቱ ቀላል አይደለም። ይልቁንም ኒው ዮርክ መስከረም መባቻ ላይ ከደረሰባት አደጋ ወዲህ "የመታወቂያ ወረቀቴ ጠፋብኝ" ብሎ ለፖሊስ የሚያመለክቱባት ከተማ አይደለችም። የጻፍኩትንም እንደገና መጻፍ ስለማልወድ፥ ብዙ ጊዜ ከቆየና ከተረሳሳ በኋላ ካልሆነ የዘፍሀ ለጋላ ጥናቴን እንደማልቀጥልበት ወዲያው ታየኝ። ያም ሆኖ ልጆቹ ከኔ ይበልጥ ስለተበሳጩ ተጽናንኚ መሆኔ ቀርቶ ሌሎቹን አጽናኝ ሆንኩ።

ሳስበው ቦርሳውን ሊወስደው የሚችል ከኔ ቀጥሎ የተሳፈረው የመጀመሪያው ሰው መሆን አለበት፤ ታክሲ ነጂውማ ተሳፋሪ ከሚ-ቀመጥበት ቦታ ምን ሊያደርግ ይሄዳል? ያ ሰው የሰው ዕቃ ካላጓጓው ለታክስ ነጂው ይሰጠዋል። ታክሲ ነጂው ያለሁበትን ቦታ ስለሚያውቅ የሰው ዕቃ ካላጓጓው ካለሁበት ቦታ ድረስ አምጥቶ ይሰጠኛል። ከማተባቸው በቀር ምንም ተስፋ የሚሰጠኝ ነገር አልነበረም።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ቊርስ መቅረብ ሲጀምር ታክሲ ነጂው ቦርሳዬን ይዞልኝ መጣ።

## ፀጋዓ

መጽሐፉን በመቀምር የጻፈችልኝ ባለቤቴ ምሥራቅ አማረ ናት። እኅታችን ወይዘሮ ማርታ አማረ የፊደል ግድፈት እንዳለበት ለማረም ረቂቁን ስላነበበችልኝ፥ የሥራ ጓደኛዬ ዶክተር ዴቦራ ሸፐርድ (Deborah J. Shepherd) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ሥዕሎች አብዛኞቹን ለኅትመት ስላዘጋጀችልኝ ሁሉንም አመሰግናለሁ።

ፕሮፌሰር ሀብተ ጊዮርጊስ ቸርነት የአማርኛውን ዶክተር እስቲፍን ሄይዝ (Stephen Hayes) የእንግሊዝኛውን ረቂቅ አንብበው የሰጡኝን ሐሳቦች በምስጋና ተቀብየ ጥናቴን የተቻለውን ያህል አሻሽየባቸዋለሁ።

አቶ አምነ አስፋው መጽሐፉን ለመጻፍ ካሰብኩበት ቀን ጀምሮ ወደ ማተሚያ ቤት እስኪሄድ ድረስ አብሮኝ ነበረ። በመቀምር የተጻፈውን እንዲያርምልኝና ለመጽሐፉ ይሸንን መልክ እንዲሰጠው ረቂቁን ካስረከብኩት በኋላ ያደረግኋቸውን ብዙ ለውጦች በስልክና በኢሜል እየተቀበለ ሲያስገባቸው የሚታየው ድካሙና የኔ አሰልችነት ሳይሆን የመጽሐፉ መሻሻል ነበረ። አምነ ብዙ ግልጽ ያልሆኑ ዐረፍተ ነገሮችን

እያገኘ አስለውጦኛል። በዚያ ላይ አባ ባሕርይን በመሰለው የሣላቸው፥ ገጽ 14 ላይ ያለውን ካርታ የነደፈው፥ ማውጫውን ያዘጋጀው፥ ለመጽሐፉ መጠቀም ያወጣለት አምነ ነው፤ ከልብ አመሰግነዋለሁ።

የዚህን መጽሐፍ ረቂቁን እንደጨረስኩ ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ጋራ ድንገት መገናኘታችንንም የመጽሐፉ ሌላው ታሪክ አድርጌ እቁጥረዋለሁ። ፕሮፌሰር ታደሰ ረቂቁን አንብቦ የሰጠኝን የማሻሻያ ሐሳቦች ሳጠናቸው ረቂቁን ሲመረምር መሥመር እንኳን እንዳልዘለለ አሳይተውኛል። ሐሳቦቹን ሁሉንም ከፍ ካለ ምስጋና ጋራ ተቀብዬ በቀጥታ በመቅዳትም ሆነ ከራሴ ሐሳብ ጋራ በማስታረቅ ሲያስቆጨን ሊኖሩ የሚችሉ ስሕተቶችን በጊዜው አርሜባቸዋለሁ። የቀረ ወይም የሳትሁት ነገር ቢኖር ተጠያቂው እኔ ነኝ። ታደሰን የሚያህል የኢትዮጵያ ታሪክ ባለሞያ ይህ ጥናት እንዲታተም መመኘቱ ጥናቱ ወጎን እንደሚጠቅም ያለኝን እምነት አጠንክሮልኛል።

መጽሐፉን ሳዘጋጅ ንብረትነታቸው የብዙ ቤተ መጻሕፍት በሆኑ ሰነዶች ተጠቅሜያለሁ። ባለንብረቶቹ፥ በተለይም የብሪቲሽ ላይብራሪ፥ የቪየና ቤተ መጻሕፍት፥ የዴር ሥልጣን ቤተ መጻሕፍት፥ የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ (ኮሌጆቪል) ቤተ መጻሕፍት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለፈቀዱልኝ፥ አስተዳዳሪዎቻቸውም ስለተባበሩኝ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። ከታተሙ ምንጮች ውስጥ በተለይ ከCSCO መጻሕፍት ብዙ አንቀጾች እያመሰገንኩ ጠቅሻለሁ።

**ማስታወሻ**:

1. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት የዘመን ቁጥሮች ዓመተ ምሕረት (ዓ. ም.) ናቸው፤ አንዳንድ ጊዜ በዓመተ እግዚእ (ዓ. እ.) መጠቀም ግድ ሲሆንብኝ እነዚያን በ "ዓ. እ." አመልክቻቸዋለሁ።
2. ምንጮችን ለማስረጃነት በጎዳጎች ላይ ስጠቅሳቸው መጀመሪያቸውንና ገጾቹን እንጂ ሙሉ አርእስታቸውን አልጽፍም። ሙሉ አርእስታቸውን ለማወቅ የሚፈልግ በየደራሲዎቻቸው ስም ተዘርዝረው ገጽ 243-249 ላይ በ"ዋቢ መጻሕፍት" ስር ያገኛቸዋል።

ጌታቸው ኃይሌ


መዝሙር ዘክርስቶስ ።
ዕብዕ በእሲ ዘኢሐረ ጎበ ፍሞት ካሕድ
ወዘቆመ በእምነተ አብ ወወልድ
ወበሃይማኖተ መንፈስ ቅዱስ ሥላሴ ዋሕድ
ወብዕ በ ካዕበ በአሳተ ፍቅረ ጎዱድ
ዘበልሳኑ ይገኒ ወብርኩ ይሰግድ
ለማርያም ድንግል ድድቱ ኃጥአን ወጥበበ ዓብድ
አንሰ እጌዕ እስክ ለመዊት
በአሚን ዝኩ ትሥልስት
ወከናፍርየኒ እከሥት
አንዘ እነብብ ድርሳነ ማኅሌት
ዘስመ መዝሙረ ኢየሱስ አምሳሉ ለመዝሙረ ዳዊት
ዘኢልቦቱ ሕፀፀ እሐዱ ቃል አምነ ጕልቱ ቃሉ
ወኢይፈደፍድ ፈደለ አምነ ፈደሉ
ባሕቱ ክሂለ ፍጻሜ አምእማዚ አብሔር ሊተ ይደሉ
አስመ ውኡቱ ወጣኒ ወፈጻሜ ኵሉ
መዝሙር ዘክርስቶስ ።
ይለምንት አንገለጉ በሰላም
ሉቃስ ዘበመንፈስ ቅዱ ዘአምቅድመ
አንድርያስ ሄሮድስ ወጲላጦስ ዘርመ
ምስለ ቀያፋ ወሐና ሊቃናተ ኢየሩሳሌም
አኮኑ ኀመ ያጽንዑ ምክረ ክሂወ ደመ

BL Or. 534, f. 13a.

**እስካሁን ከተገኙት የመዝሙረ ክርስቶስ ቅጅዎች አንዱ።**

(**ገጽ** 36–37 **ላይ በከፊል ተቀድቷል።**)

# መግቢያ

*አሐተ ሰአልክም ለእግዚአብሔር ወኪያሃ አኀሥሥ፤*

*ከመ ይስማዕ ሐዘና ወብካያ፥*
*ለሀገራትነ ኢትዮጵያ።*

❖

**እግዚአብሔርን አንድ ነገር ጠይቄዋለሁ፤ እሷንም እፈልጋለሁ፤**
**—— ቅዱስ ዳዊት**

**የሀገራችንን የኢትዮጵያን**
**ሐዘኗንና ለቅሶዋን እንዲሰማ።**
**—— አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ**




**ከተለያዩ ካርታዎች ላይ የተወሰዱ (የቀድሞ) የቦታ፥ የወንዝ(ወ) እና የሐይቅ(ሐ) ስሞች በዘመናዊ የኢትዮጵያ ካርታ ላይ።**

በዚህ መጠነኛ ድርሰት አማካይነት ላንባቢዎች ላቀርብ የምፈልገው፥ ሁለት ነገር ነው -- አንደኛውና ዋናው በዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት **አባ ባሕርይ** ስለኦሮሞዎች የደረሱትን ***ዜናሁ ለጋላን*** ሲሆን፥ ሁለተኛው የደራሲውን ማንነት ሊነግሩን ስለሚችሉት ስለሌሎቹ ድርሰቶቻቸው ያዘጋጀሁትን መግለጫ ነው። ወደ ዋናው ርእሰ ነገሬ ከመሄዴ በፊት ስለ አባ ባሕርይ ለዛሬው ያዘጋጀሁትን አስቀድማለሁ።

የ*ዜናሁ ለጋላ* ርእሰ ነገር "ጋላ" ይባሉ የነበሩት ኦሮሞዎች ስለሆነ የድርሰቴ ትኩረት ርእሰ ነገሩን (የኦሮሞዎችን ዜና) በሚያጐሉ የግዕዝ መምህራን ዘገባዎች ላይ ይሆናል። እንግዲህ የአባ ባሕርይ ***ዜናሁ ለጋላ*** ለዛሬው ድርሰቴ አስኳልና ዋናው ክፍል ከመሆኑም በላይ የደራሲውን ሌሎች ድርሰቶችና ኦሮሞዎች ማእከላዊ ኢትዮጵያን እንዴት እንደወረሱ የሚናገሩ ሀገራዊ ምንጮችን ለማስተዋወቅም ምክንያት ሊሆን ነው።

ስለ ኦሮሞዎች ወይም ስለ "ቤተ ጋላ" ለመጻፍ የበቃሁት ሳላስበው ነው። አሁንም ቢሆን የምጽፈው ለሕዝብና ለወጣት የታሪክ ተማሪዎች የሀገር ውስጥ ሰነዶችን ለማቅረብ እንጂ እንደ ሌሎቹ አንትሮፖሎጂስቶች (ለምሳሌ እንደ ሴኪ እና እንደ ቸሩሊ፥ እንደ ሃበርላንድና እንደ ብራውኬምፐር) ያደረግሁት "የመስክ ጥናት" በጀ የለም፤ ቢኖር "የመጻሕፍት የመስክ ጥናት" ነው። የሆነውም እንዲህ ነው፤ በዘመኑ ፖለቲካ ምክንያት ስለ ኦሮሞዎች አንዳች ውይይት በተነሣ ቁጥር የአባ ባሕርይን *ዜናሁ ለጋላ* በግዕዙም ሆነ ወይም የምዕራባውያን ሊቃውንት በተረጐሙባቸው ቋንቋዎች ባነበቡና ባላነበቡ ኢትዮጵያውያን መካከል የአስተያየት ልዩነት አይ ነበር። ባነበቡትም መካከል ቢሆን ድርሰቱን ሁሉም እንደፈለገው እንዲሆንለት እያደረገ ያየዋል።

ውይይቱ በጥቅምት 27 ቀን 1994 (November 6, 2001) ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴ ለEEDN ያቀረበውን ጽሑፍ ምክንያት በማድረግ ተፋፍሞ ነበር። በዚያን ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን የ*ዜናሁ ለጋላ* ያማርኛ ትርጉም እንዳለኝ ሲጠይቁኝ ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የተረጐሙት ቢኖርም[1]፥ ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴም ሰዎች ("መተክ")

1. EMML 3749, Getatchew Haile, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. IX (1987), p. 127. ረቂቁን ለማግኘት የሚከፈለው ገንዘብ ከሰነዶቹ ብዛት ጋር ሲተያይ ብዙ ነው። መጽሐፉን በምዕራፍ ፪ ላቀረብኩት *ዜናሁ ለጋላ* "መግቢያ" ውስጥ የሚያስፈልገውን ያህል ተችቸዋለሁ።

የተረጐሙለትን ለሕዝብ እንዳሰራጨ ቢነግረንም፥ እስካሁን ያየኋቸው ትርጉሞች ሁሉ ስላላረኩኝ እኔው እራሴ በመሰለኝ ተርጉሜ ልልክላቸው ወሰንኩ። ስተረጉመው ባነበቡት መካከል ያለው ሰፊ የመረዳት ልዩነት ዋናው ምክንያት ዜናሁ ለጋላን ከኢትዮጵያ ታሪክ ተገንጥሎ ብቻውን ስላገኙትና ራሱን የቻለ ሙሉ ታሪክ አድርገው ስላዩት እንደሆነ ገመትኩ፤ ስለዚህ ትርጉሜ ታሪካዊ ማብራሪያ እንደሚያስፈልገው ተሰማኝ።

ማብራሪያውን ለማዘጋጀት ዜናሁ ለጋላ የተጻፈበትንና የተከታዩን ዘመን ታሪክ ነክ የሀገር ውስጥ ምንጮችን፥ በተለየም የነገሥታቱን ታሪክና ዜና መዋዕሎቹን (chronicles)፥ እንደገና ማንበብና መጥቀስ አስፈለገኝ። ኦሮሞዎች ከዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ማህል ኢትዮጵያን ሲይዙ ስለተፈጸመው ተጋድሎ ለምሳሌ የሚሆኑ ጥሬ ምንጮች ስጠቅስ የራሴን አስተያየቶች መስጠቴ አልቀረም። ሆኖም አስተያየቶቼ ሁሉም እነዚህን ያነበብኳቸውን ምንጮች የተመረኮዙ ትዝብቶች ናቸው፤ በማህላቸው ድጋፍ የሌላቸው የአድልዎ አስተያየት የጨመርኩባቸው አይመስለኝም። ስላለፈ ውስጣዊ ሀገራዊ ታሪክ ስጽፍ የሀገሪቱን ነፃነት፥ የሕዝቡን አንድነትና ደኅንነት የሚነካ ድርጊት ካልሆነ በቀር በአድልዎ ምክንያት ለየትኛውም ድርጊት ፈጻሚዎች ነቀፌታም አድናቆትም አይሰማኝም። ምንጮቹ የሚተርኩት **በተለየ** በመንግሥት ሠራዊትና በኦሮሞዎች መካከል በተካሄደው ግጭት ላይ በሚሆንበት ጊዜ፥ ያንን ሳቀርብ ሁለት ዘራፊ አያቶቼ ሌላ ያፈራውን ሲዘርፉ ቢጣሉ ለተዘራፊው (በተለይም ለገበሬውና ለኑጋዴው) ከማዘንና ለሚጠፋው የታሪክና የኪነ ጥበብ ቅርስ ከመቆጨት አልፎ ለማን ያደላል!

ለገለልተኝነቴ በቂ ምክንያት አለኝ፤ ልጆች እናትና አባት ሲጣሉባቸው እንደማየት የሚጠሉትና ከአእምሯቸው እስከመቸም የማይፋቅ አሳዛኝ ነገር የለም። የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን በነገድ ሲጣሉ ሳይ፥ "የኦሮሞዎቹና የሌሎቹ ነገዶች ልጆች ነን እኮ" ስል ለሕዝቡ አንድነት ባለኝ ምኞት "ሰላምን ለመሥራት" ብቻ ሳይሆን ምንጮቹን ሳነብ ያገኘሁትንና ፈላስፋው ዘርአ ያዕቆብ "ያልተሟላ ራስን ማሟላት"[2] የሚለው በራሴና በብዙዎች በማውቃቸው ላይ ሲደርስ በዓይኔ ያየሁትን ለመመስከር ነው።

2. Enno Littmann, *Philosophi Abessini*, CSCO, script, arth., textus series prima t. 31, Paris 1904, reprint, Vol. 18, t. 1, Louvain (1962), p. 16: "እምተክህሎ ለእግዚአብሔር ይፍጥረነ ፍጹማነ ወይረስየነ ብዑዓነ ዲበ ምድር። ወባሕቱ ኢፈቀደ ይፍጥረነ ከማሁ፤ ወፈጠረነ ድልዋነ ለተፈጽሞትነ" ("እግዝአብሔር የተሟላን አድርጎ ሊፈጥረንና በምድርም ላይ ብዑዓን ሊያደርገን ይቻለው ነበረ። ግን እንዲህ አድርጎ ሊፈጥረን አልፈለገም፤ ለመሟላት ዝግጁዎች አድርጎ ፈጠረን እንጂ።")

ረጅሙን ታሪክ ይህን አጭር ድርሰትና የምሰጣቸውን ምንጮች ስናነብ እንደርስበታለን፤ "ያልተሟላ ራስን ማሟላት" ስለሚባለው ፍልስፍና ግን በራሴ በመጀመር ጥቂት መሥመሮች ላስቀድም። ፈጣሪ በጅምር የተወኝን ዕድል አግኝቼ በእድገት ዘመኔ ያሟሉልኝ የህገራችን ትምህርትና የአካባቢዬ ባህል ናቸው። ይህ አጋጣሚ ዕድል የማሟያዬ መጣሪያ ለሆኑት ለመጻሕፍቱ፥ ለሥዕሎቹ፥ ለጸሎት ቦታዎቹ፥ ለቅዱሳት እቃዎቹ እና ለጠቅላላ ባህላዊ ቅርሶቻችን ያልተቆጠበ ፍቅር አሳድሮብኛል። ከነሱ ውስጥ መጥፎዎቹ በቤተ መዘክር፥ ጥሩዎቹ በቤተ መዘክርና በቤተ ትምህርት ከትውልድ ወደ ትውልድ በክብር እንዲተላለፉ እንጂ የትኞቹም ክፉ ነገር እንዲደርስባቸው አልፈልግም። አሁን ካለንበት ለመድረስ ምን ዓይነት ረጂም ጉዞ እንደተጓዝን የሚነግሩን እነዚህ ቅርሶች ስለሆኑ፥ ጥፋታቸው ክስረታችን ነው። አንድ መጽሐፍ ተበላሽ ሲሉኝ የሚታየኝ ህገራዊው ክስረት ብቻ ሳይሆን የስምዖንን *ግብረ ሕማማት* የቀዳውና እንደሱ ያሉት ጸሐፊዎችና ሠዓሊዎች ድካም ከንቱ ሆኖ መቅረት ጭምር ነው።

ስምዖን ከግራኝ አመፅና ወረራ በፊት የነበረ የህገረ ማርያም ገዥ እና ቤተ ክርስቲያኗን ያደሰ ባለጸጋ ነበረ። ግዛቱን የግራኝ ወራሪ ሠራዊት አቃጠለበት፤ እሱንም አባቱን ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስንና ወንድሙን ብእሴ እግዚአብሔርን እንደገደሏቸው ገድለውት ይሆናል። አንዱ ወንድሙ ሠርፀ ዮሴፍ የወለቃ ንጉሥ ነበረ። ስምዖን የደለበ ባለጸጋ ሆኖ ሳለ፥ ስሙ ያልታወቀው የሱ ጸሐፊ በቀዳለት *ግብረ ሕማማት* ጎዳጎች ላይ የጻፋቸው ልመናዎች የተራበና የተራቆተ ሰው እንደነበረ ይመሰክራሉ[3]። የምንኮራበትን የሥነ ጽሑፍ ቅርሳችንን ያወረሱን ባለሟያ አባቶቻችን እንደዚህ የችጋር ማጎደርና ከኢትዮጵያ ጀምረው እስክንድርያና ኢየሩሳሌም በእግራቸው ሲመላለሱ የአደጋው ሁሉ ዒላማ ሆነው ነው።

እንደዚህ ሆኖ የተፈጠረ ቅርስን ጥፋት መስማት ሆድ አይችለውም። ሌላው ምን እንደሚሰማው አላውቅም፤ እንደኔ ታሪካቸውን ታሪኩ የሚያደርገውን ኢትዮጵያዊ ግን አንገቱን ያሳርርበታል። የነዚህ ሰዎች ባህላቸው ባህሌና የኔነቴ አንዱ ክፍል (የተሟላሁበት/የሳለመስኩበት) ሆኗል። አገራችንን የማያት በዚህ ዓይነት ሰው ዓይኖቼ ስለሆነ፥ ታሪኩን ስጽፍ አስተያየቶቼ የፍርድ ጉድለት ቢታይባቸው በራሴ ጉዳይ ላይ ራሴ ዳኛ ስለሆንኩ ነው።

3. EMML 5083, "አዝዝ እግዚአየ ልብስ ለጸሐፊሃ ለዛቲ መጽሐፍ ከመ ኢይዐል ዕራቆ ለበዓላ" ("ጌታዬ፥ ጸሐፊዋ የበዓሏ ዕለት ራቁቱን እንዳይውል ልብስ እዘዝለት"፥ ቅጠል 44ለ)፤ "ርኅበ ወጸምአ ጸሐፊከ፤ አዝዝ እግዚአየ በእንተ ማርያም ፍቅርትከ" ("ጸሐፊህ ተራበ፥ ተጠማም፤ ጌታዬ፥ ስለፍቅርህ ስለማርያም ብለህ (የምበላውን) እዘዝልኝ"፥ ቅጠል 87ለ)።

ይህ ባንድ በኩል ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ አጥቢያችን **ሸንኮራ** ውስጥ ጡጤ እንጦራር ዐማኑኤል ይሁን እንጂ የልጅነቴ ቤታችን እዚያው እሸንኮራ ውስጥ ከ**ሙካ ቶክቻ** እልፍ ብሎ **ደጎምሲሳ** ከሚባል ቦታ ነው። ("ሙካ ቶክቻ" በኦሮምኛ "አንዲት ዛፍ" ማለት ስለሆነና ቀበሌው በምንጃርና በውልንጪቲ በኩል ለአዋሽ ስለሚቀርብ አዬ ዘርአ ያዕቆብ በዓሥራ አምስተኛው ምእት ዓመት ከአዳሉ አሚር/ንጉሥ ከበድላይ ጋራ ስላደረገው ጦርነት ሲጽፍ "ምድረ **አሐዱ ዕፅ**" ("የአንድ ዛፍ ምድር") የሚለው ቦታ[4] ይህንን ስጫወት ያደግሁበትን "ሙካ ቶክቻ"ን ይሆንን እላለሁ።) ከአዲስ አበባ ደጎምሲሳ ለመድረስ በ**ለግ ዳዲ**፥ በ**ጨፌ ዶንሳ** እና በ**ዶቢ** በኩልም ያስኬዳል። "**ጨፌ**" በኦሮምኛ "ሸንጎ"፥ "አደባባይ" ማለት እንደሆነ ይኸንን ድርሰት በማንበብ ስንገፋበት እንደርስበታለን። "**ለግ ዳዲ**" ማለትም "የጠጅ መልካ" ማለት ነው።

ሸንኮራ ብዙ ታሪክ ተፈጽሞባታል፤ ለምሳሌ፥ "አጼ ቴዎድሮስ ሸንኮራ ሰፈሩ የሚባል ወሬ ሲሰማ ነገሩ (ጦርነቱ) እንዳልሰላ (የሸዋ መኳንንት) ባዩ ጊዜ፥... የእግዚአብሔር ፈቃዱ ባይሆን ነው፤ ጌታችንንስ (ወጣት ምኒልክን) አናስማርክም ብለው ተላልከው ወደ አጼ ቴዎድሮስ ይዘው ገቡ"[5]። የሸዋ ራስ ገዝነት ያን ዕለት አከተመ።

ሸዋ ራስ ገዝነቷን በመገፈፏ የተቆጨ "ፀ ሰዎች ተነሥተው ይህ ንጉሥ (አፄ ቴዎድሮስን ነው) የሚሔድበት አይታወቅምና ከአሞራና ከውሻ ከእባብ (ከአለስትዮ) አገር ይዞህ ይሄዳል፤ እንግዲህ የተከተልከው ወታደር ገዝተንሃል፤ ያቡነ ሰላማ ቃል ነው እያሉ በየሰፈሩ እየዞሩ ሲገዝቱ ንጉሡ ሰምተው አሲያዟቸው። ከነዚህ ጋራ የመከሩ በየድንኳናቸው ፀፏ ነበሩ። ሁሉንም አስረው ዕለቱን ተጉዘው ቶራ መስክ ሰፈሩ። ከዚያም አደባባይ (ጉባኤ) አድርገው እነዚያን የወታደር ቄሶች አምጡአቸው አሉ። ይህን ጊዜ አቡነ ሰላማ ከዚያው ተቀምጠው ነበርና፥ እነዚህ ሰዎች እኔ ሳልሾማቸው የማይገባ ሠርተዋል፤ አሁንም ለኔ ስጠኝ፥ በመጽሐፍ በንስሐ ልቅጣቸው። ላንተም እነዚህ በተናገሩት መንግሥትህ አይቀርብህ፤ ክርስቶስ እንደሰጠህ ትገዛለህ፤ አሁንም ተውልኝ፥ ማርልኝ አሉዎ (አሉዋቸው)። ንጉሡም ከምሕረት ወደመዓት ያደላሉና አልተውም አሉ። እንደዚህም ባሉ ጊዜ እነዚያን ሊሞቱ የቀረቡ ሰዎች እንደወጋግራ ከሆነ

4. Kurt Wendt, *Das Maṣḥafa Milād*, p. 18. ዛፉ የነበረው እማህል አውራ ጎዳና ላይ ቢሆንም፥ የበቀለው አውራ ጎዳናው ከመውጣቱ በፊት ሳይሆን አይቀርም። በ1956 ዓ. ም. ስመለስ ደርቆ አገኘሁት። ይኸን ጊዜ የደረቀውም ማገዶ ሆኖ፥ "ይህ ቦታ እኮ ሙካ ቶክቻ የሚባለው እዚህ ጋ አንድ ዛፍ ስለነበረ ነው" እየተባለ ይተረክ ይሆናል።

5. ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፥ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፥ ገ. 48።

ግንድ እያሰሩ ነፍጠኛ ተሰልፎ ቁሞ ነበርና እየቀረበ ተኮሰባቸው፤ በጦርም በጎራዴም ተጨረሱ”[6]::

**“ሸንኮራ”** ማለትም “አምስት ጉብታዎች”፥ ወይም “አምስት ኮርቻዎች” (“ሸን” “ኮራ”) ማለት ሊሆን ይችላል:: እዚያው ሸንኮራ ውስጥ **ሙጢኮራ** (“ሙጢ” “ኮራ”) የሚባል ቦታ እንዳለ ከዚያ (እና ከ**ሙጢ ግላን**) የመጡ ያስታውሳሉ:: ከነዚህ ሁሉ ቦታዎች ጋራ የልጅነት አገሬ የምላቸው ከአጎቴ ጋራ የኖርኩበት **ቱሉ ፈራ** እና የጠመንጃ ያገር ው (የነፍጠኛው) አያቴ ርስት ያለበት (የነበረበት) ሞጆ አጠገብ የሚገኘው **ቢርመጂ** ወይም **ሉሜ** ነው:: (ስለነዚህ የቦታ ስሞችም እዚሁ ድርሰት ውስጥ እንማራለን::)

ምናልባትም እኮ “ደጎ” የተባለው አፄ ዘርአ ያዕቆብ የነገሡባት፥ በኋላም ሐመልማልና “ሉባ ምስሌ” የተዋጉባት ቦታ የት እንደሆነ ያልታወቀው እዚህ “ደጎምሲሳ” እሚለው ስም ውስጥ ተደብቆ ይሆናል (*የዘናሁ ለጋፋን* ክፍል ፱ ተመልከት):: የደጎምሲሳ ጎረቤታችን አባቴ እንዳባቱ የሚያያቸው የጌታ ዲነግዴ ቤተ ሰቦች ነበሩ:: ነፍስ ሳውቅ አባቴ እንደነገረኝ፥ ጌታ ዲነግዴ አቅራቢያችን የሚውለው የሳምንት ገበያ ሲደርስ ከከብቶቻቸው አንዱን በሬ ለመሸጥ ገበያ ይወስዳሉ:: ግን አንዳንድ ጊዜ ገበያ እስኪፈታ እዚያው ውለው በሬውን ሳይሸጡት ይቀሩና መልሰው ያመጡታል:: አባቴ፥ “ጌታ፥ ምነው በሬውን መለሱት? ገገር አጡ እንዴ?” ሲላቸው (እዚያ ጨዋታው ወይ ባማርኛ ወይ በኦሮምኛ ነበር)፥ “የለም ልጄ፤ ገገርስ ሞልቶ ነበረ፤ ግን ስጠይቃቸው በቀየው ለበሬዬ የሚበቃ የመስኖ ሳር ያለው አንድም ሰው አላገኘሁባቸውም፤ ለነሱ ሸጬ በሬዬን ረኅብ ላይ እንዳልጥለው ብዬ መልሼ አመጣሁት” ይሉታል::

በነዚህ ለመሚላቴ አስተዋጽኦ ባደረጉት የኦሮሞ ስም ባላቸው ቦታዎች ሁሉ የሕዝቡን ሰፈራ ሳስታውስ የዛሬዎቹ ወጣቶች ስለ ጎሳዎች የሚናገሩት ስለሌላ ሀገር ይመስለኛል:: እዚያ “አማራው እና ጋላው” ወይም “ሲዳማውና ኦሮሞው” አብሮ ነው የሰፈረው:: እቤት ሁሉም የራሱን ቋንቋ ይናገራል፤ እውጪ ሲገናኙ (ከገበያ ጭምር) ንግግሩን በጀመረው ሰው ቋንቋ ይቀጥላሉ፤ ወይም ያ በዚያ፥ ይኸ በዚህ ቋንቋ እየተነጋገሩ ይግባባሉ:: ዐረፍተ ነገሮቹ አማርኛ ወይም ጋልኛ ይሁኑ እንጂ ከቃላቱ ውስጥ አንዳንዶቹ እዚያ ያሉት እዚህም አሉ፤ እዚህ ያሉት እዚያም አሉ:: **“በስልቻና በቀንቀሎ መካከል ልዩነት የለም”** የሚባለው አነጋገር ከእንደዚህ ያለ ሁኔታ የመጣ ሳይሆን አይቀርም::

አማርኛ በቃላት ብቻ ሳይሆን ዐረፍተ ነገሩም ቢሆን የኦሮምኛ ተጽእኖ ሴማዊነቱን አናግቶበታል:: ጋሼ አበበ ከተማ ከጡት አባቴ (ከኔ አባት) እና ከኔ ጋር ሲነጋገር “አንተ”፥ “አንቱ”፥ “አንቺ” ይለን የነበረውን አሁን ሳስታውሰው የለውጡ ሂደት እንዴት እንደነበረ ያመለክተኛል::

6. እዚያው ገ. 50::

አሮምኛውም አንዳንድ ተመራማሪዎች ኩሳዊ/ካማዊ መሆኑን እስኪጠራጠሩ ድረስ በአማርኛ ተጽእኖ ምክንያት ተመሳሳይ ሁኔታ ደርሶበታል። እንግዲህ፥ ለዚህ ድርሰት ከየምንጩ ስለምጠቅሳቸው ጥቅሶች ማብራሪያ ስጽፍ አስተያየቶቼ የፍርድ ጉድለት ቢታይባቸው በራሴ ጉዳይ ላይ ራሴ ዳኛ ስለሆንኩ ነው።

በዚህ ላይ፥ አባቴ ሲነግረኝ በሚገባ ሳላዳምጠው ቀረሁ እንጂ፥ ትዝ የሚለኝን ያህል ከሆነ፥ ከቅድም አያቶቹ አንዱ በኋላ የአባቴን እናት የያስገኘችውን ልጃቸውን እንኮኮ ብለው በአዳል በኩል ወደ ቡልጋ የመጡ ከአሮምኛ በቀር ሌላ ቋንቋ የማያውቁ ወረሴኼ ነበሩ። የዚያችን ልጅ ዘር ያገቡት (አያቴ) እንደ ተከሉት የእንገሪራር ዐማኑኤል ታቦት የሚከበሩ ካህን ነበሩ። ባንድ በኩል አንኮበሬና ቡልጌ ብሆንም በአንድ በኩል ይኸው እንዲህ ነኝ። ያንኮበሩ ርስታችን የተወሰደው አገሩን ሳላውቀው ነው። አንኮበርንና ቡልጋን የማውቃቸው ከካርታ ላይና ከዚያ ከሚመጡ ዘመዶች ጨዋታ ነው።

ምንም ከተነሣሁበት ዓላማ ቢያርቀኝም፥ የአካባቢያችንን ቦታዎች ሳነሣ አጠገባችን ያለችውን ጉራምባን ሳላስታውስ ብቀር ሰላም ይረፍባቸውና የእቴጌ ጣይቱና የአባቴ ነፍስ ይወቅሱኛል፤ ደግነቱ ይኸኛው ዘገባዬም ታሪክ አልባ አይሆንም። የፋሽስት ወረራ የትውልድ ሀገራችንን ከማስለቀቁ በፊት እዋዜማው ላይ አባቴ ካደረበት የርሐ ሕመም በጉራምባ ማርያም ጠበል ለመፈወስ እዚያ አንድ ሳምንት ያህል ተቀምጠ ነበረ። እንደማስታውሰው፥ በዚያን ጊዜ ከቤተ ሰብ ውስጥ አጠገቡ የነበረ እኔ ብቻ ነበርኩ።

በሕይወቴ ካየኋቸው ቦታዎች ሁሉ እንደጉራምባ በአእምሮዬ ላይ የማይረሳ የደስታና የናፍቆት ትዝታ ማኅተሙን የጣለ ቦታ የለም። "ነገ የራሷ ጉዳይ አለባት" የሚለውን ባለማሰቤ፥ ነፍስ ካወቅሁ በኋላ ተመልሼ ሄጄ ጉራምባን ለመጎብኘት ያለኝን ሐሳብ በማዘግየቴ እጸጸታለሁ። ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ስሄድ እናቴ "ልጄ በሰላምና በጤና ከተመለሰ ከደጅህ አምጥቼ አሳልመዋለሁ" ብላ የተሳለችው ለዶሩ ሚካኤል መሆኑ ቀርቶ ለጉራምባ ማርያም ቢሆን እመርጥ ነበረ። ስላላማከረችኝ ነው እንጂ ለገደልኔቱ ከሆነ ሁለቱም አይተናነሱም፤ ስለት ለመስማቱ ቅድስት ድንግል (ባለምሕረት ኪዳኗ) ትበልጣለች።

ጉራምባ ማርያም ምኞቴን ስለምታውቅ ሄጄ ልሳለማት ሳልችል ጊዜ (የ"*አመ ይትነሥኡ ዕልዋን ፈተወ ይስተይ ማየ እምዐዘቅተ ቤተ ልሔም*" ፍጻሜ ብጤ ሆኖ[7]) "የማን ወዳጅ ምኞቱ ሳይሟላ ይቀራል" ብላ ቤተ ክርስቲያኒቷ የምትገለገልባቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት

7. ዳዊት ታሞ በነበረ ጊዜ ጠላት መንገዷን ከዘጋው ከቤተ ልሔም ምንጭ መጠጣት አማረው። ጭፍሮቹ "የማን ጌታ በውሐ ጥም ይሞታል" ብለው ፈጥነው ተነሡ ...

በማይክሮፊልም ተነሥተው እዚህ እምሠራበት ዩኒቨርስቲ ቤተ መጻሕፍት ቀድመውኝ መጥተው ተከምረው እንዳገኛቸው አደረገች -- ሳላስበው።

እዚያ ገደል ውስጥ ሲወርዱ ውሎ ከሚገኘው ለምለም ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ከመጠን በላይ አድካሚ እንደ ሆነ ግልጽ ሆኖ ሳለ፥ ካልጠፋ ቦታ ለምን እዚያ ታች ወረዱ? የቁልቁለቱ/የዳገቱ መንገድ ጠባብነት ባንድ ጊዜ ከአንድ ሰው በላይ አያስኬድም። ቦታዋን አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ከመኳንንታቸው ጋራ ጎብኝተዋታል። (አፄ ዘርአ ያዕቆብ ደጎ ላይ ከነገሡ በኋላ ያሠራት መካነ ማርያም መስላቸው ይሆን?) ቤተ ክርስቲያኗ እንድትታደስ ሐሳብ ያቀረቡ የተቀደሱትና የታሪኳ እመቤት እቴጌ ጣይቱ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኗን የሠሯት አናጢዎች፥ ገምቢዎች፥ ሠራተኞች በሞላ ከነደሞዛቸው ከአዲስ አበባ ከቤተ መንግሥት ታዘውና ተልከው የመጡ ባለሞያዎች ናቸው። እቴጌ ጣይቱ አለቃ ተክሌን አዲስ አበባ መጥተው ሲያገኟቸው የጉራምባን ሥዕሎች እንዲሥሉ ቀለብ አውጥተውላቸው ነበረ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ብዙዎቹን የጎጃም አብያተ ክርስቲያን በሥዕል ያሸበረቁና የጎጃምን ታሪክ የጻፉ ታላቅ ሊቅ ነበሩ። አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ ከአዛዥ ዛማኔል ጋራ ስለተጣሉ "እቴጌም እንዳልሰላላት ባየች ጊዜ የጉራምባይቱ ማርያም ፈቃዱዋ ባይሆን ነው ብላ" ሳልሄድ ቀረሁ ይሉናል[8]።

ዋና ዋናዎቹንና ብዙዎቹን መጻሕፍት በግዢም በማስቀዳትም ለቤተ ክርስቲያኗ የሰጡ እቴጌ ጣይቱ ናቸው፤ ከነዚህም ውስጥ ዋናው *ተአምረ ማርያም* ሲሆን፥ የሰጠታው ሰነድ እንዲህ ይላል[9]፥

> *ዛቲ መጽሐፍ ዘእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ብእሲቱ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘአጥረየ(ታ) በንዋያ ወመሀበታ ለደብረ ማርያም ዘሀገረ ጉራምባ እንተ ይእቲ ደብረ መድኃኒት ከመ ትኩን ላቲ መርህ ለመንግሥተ ሰማያት በ፲፱፻፬ዓ.ም ዓመተ ምሕረት...።*

❖

> ይቺ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሚስት፥ የኢትዮጵያ ብርሃን፥ የእቴጌ ጣይቱ ናት -- በገንዘቧ ንብረቷ ያደረገቻትና ለመንግሥተ ሰማያት መሪ እንድትሆናት ደብረ መድኃኒት ለምትባለው ለጉራምባ ሀገር ደብረ ማርያም በ፲፱፻፬ዓ.ም ዓመተ ምሕረት የሰጠቻት...።

---

ይጠጣ ዘንድ የወደደውን ውሐ አመጡለት፥ የጎሙስ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ፥ ለምሳሌ፥ *ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያም*፥ (አዲስ አበባ) ፲፱፻፷፭ ዓ. ም.፥ ገ. 206-11።

8. *የጎጃም ታሪክ*፥ EMML 4802, p. 202.
9. EMML 5781, f. 90b.

ማኅተሙም፥ **"ዝማኅተም ዘእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ"** ይላል።

መጽሐፉ የተቀዳው ላስታ ውስጥ አምየ የራሱን መንግሥት አቋቁሞ ለነበረው "ለንጉሥ እልፍዮስ" ነበረ። በአዜ በካፋ ዘመን (በ1718 ዓ. ም.) ሲሸነፍ ንብረቱ ተበታትኖ ይሆናል[10]።

ሌላው መጽሐፍ *ተአምረ ኢየሱስ* ነው። ይኸኛው በተለይ ለቤተ ክርስቲያኗ ከተቀዱት አንዱ ነው። ሰነዱ እንዲህ ይላል[11]፥

> *ዝንቱ መጽሐፍ ዘእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ብእሲቱ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘወሀበታ ለእግዝእትነ ማርያም ዘደብረ መድኃኒት። ወዘአጽሐፎ አለቃ ገብረ ሥላሴ ዘውእቱ ጸሐፌ ትእዛዝ በ፲፱፻፲፪ ዓመተ ምሕረት።*

❖

> ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሚስት፥ የኢትዮጵያ ብርሃን፥ የእቴጌ ጣይቱ ነው -- ለመቤታችን ለደብረ መድኃኒት ማርያም የሰጠቻት። (መጽሐፉን) በ፲፱፻፲፪ ዓመተ ምሕረት ያጻፈው ጸሐፌ ትእዛዙ አለቃ ገብረ ሥላሴ ነው።

ማኅተሙ እንደላይኛው፥ **"ዝማኅተም ዘእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ"** ይላል።

እቴጌ ጣይቱ ለቤተ ክርስቲያኗ ባስቀዱት *አርባዕቱ ወንጌል* ላይ የተመዘገበውን ሰነድ እንደማየው፥ ለቤተ ክርስቲያኗ መገልገያ አልባሳትና የተለያዩ "እቃዎች" ካበረከቱት መካከል በመጀመሪያ ደረጃ እቴጌ ጣይቱ፥ ከዚያ ጃንሆይ (አዜ ምኒልክ)፥ አቶ ሰሙ ንጉሥ (አዜ ቴዎድሮስ ሸዋን ሲወጉ የማድም ገዢ የነበረው[12])፥ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፥ ወይዘሮ አልታየ (የፊታውራሪው ባለቤት)፥ ፊታውራሪ ባልቻ፥ አፈ ንጉሥ (ነሲቡ)፥ አጋፋሪ በየነ (የመጀመሪያው የፖስታ ሚኒስተር)፥ ደጃች ወሰን ሰገድ (የጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክ ልጅ)፥ ልጅ ወልደ ገብርኤል (ንጉሥ)፥ አሳላፊ ድልነሄ ይገኙበታል[13]። ብዙውን እቃ ያመጡት መምሬ ወልደየስ ናቸው። (የቤተ ክርስቲያኗ ጥበቃ የኛ ስለሆነ፥ ሰነዱ "መምሬ ወልደየስ" የሚለው አዜ ምኒልክን አስፈቅደው ሸንኮራ እንጮራር ዐማኑኤልን የተከሉትን የአባቴን አባት መሆን አለበት።)

ይህን ስለአስተዳደጌ የጻፍኩትን ስጀምር፥ "በራሴና በብዙዎች በማውቃቸው ላይ ሲደርስ በዓይኔ ያየሁትን ለመመስከር ነው" ብዬ ነበር።

---

10. I. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyāsu I et Bakāffā*, part II, p. 302.
11. EMML 5782, f. 132ab.
12. ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፥ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፥ ገ. 45።
13. EMML 5783, f. 184ab. እቴጌ ጣይቱ ሌላም ወንጌል በዚሁ 1886 ዓ. ም. (EMML 5784) አስጽፈው ለገዳሙ አበርክተዋል።

ስለሌሎቹ ያነበብኩትንና የሰማሁትን ሁሉ ብጽፍ "ዓለም ራሱ ባልቻለውም" ባይባልም፥ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ይወጣዋል። ሆኖም ሌላው ቢቀር፥ የኮሞዶር ጣሰው ደስታን *የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል* (፲፱፻፺፯ ዓ.ም/1998 ዓ. እ.) እና የአቶ ገብረ ሥላሴ አዳን *ትዝታ ለመታሰቢያ*፥ (አዲስ አበባ) 1990 ዓ.ም. ላንባቢ ላስታውስ።

"ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ካልጠፋ ቦታ ለምን እዚያ ታች ወረዱ?" ብዬ ጠይቄ ነበረ። የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያነብ አባቶቻችን ለምን ገደል ውስጥ እየወረዱ፥ ከተራራ ጫፍ እየወጡ፥ ተራራውን እየቦረቦሩ፥ ደሴት እየፈለጉ ቤተ ክርስቲያን እንደሚሠሩ ሳይጠይቅ መረዳት አያቅተውም። ከቅዱሳት መካናት ውስጥ ብዙዎች ከግራኝና ከኦሮሞ ከሌሎችም ወረራዎች ያመለጡት እንደዚህ ባሉ ቦታዎች በመሠራታቸው፥ ቅርሶቹም የተረፉት እዚያ በመደበቃቸው እንደሆነ በትርጓሜ ራእየ ዮሐንስ ተነግሯል።

## ፩ጋር

ከቅርቡ የትዝታ ጉዞዬ ወደጀመርኩት ወደቅድም አያቶቻችን ዜና ልመለስ። በዘመኑ ፖለቲካ ቀስቃሽነት፥ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ስለኦሮሞዎችና ስለአማሮች መጨካከን ብዙ እንሰማለን፥ ብዙም እናነባለን። የተወለድነው የተበጠበጠው ከረጋና ታሪኩ ተረት ከሆነ በኋላ ስለሆነ ይኸ ለኛ አዲስ ነገር ነው። ኦሮምኛ ተናጋሪዎች እንኳን በሰው ላይ ቀርቶ በከብት ላይ እንኳን የማይጨክኑ፥ እንደማንም ኢትዮጵያዊ ሰላማዊያንና የማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኩያዎች መሆናቸውን እንጂ ማህል ኢትዮጵያን ሲወሩ ስላደረሱት እልቂትና የባህል ውድመት፥ በኋላ በዳግማዊ ምኒልክና በራስ ጎበና ዳጨ ዘመን ደግሞ ያንን ኦሮሞዎች ሲወድቁበት የተንከታከተውን የኢትዮጵያን ማእከላዊ መንግሥት ነፍጠኛው ሲጠግን እዳር አገር እንደበደላቸው የምናውቀው ነገር አልነበረም።

የዚያ የጥገናው ጊዜ በደል እንዲህ እንደዛሬው አንድ ቀን ጥላቻውንና ጥሉን ሊያስገረሽ በሚያስችል ሁኔታ በጠላት ብዕር ተተርኮ የፖለቲካ መርሐ ይወጣዋል ብሎ ማን አስቦት! ታሪኩ እነሱ እንዳፋፋሙት ድንገት ዱብ ሲል ሊቀልቡትም መልሰው ሊወረውሩትም (ማለት፥ ሊቀበሉትም ሊከራከሩለትም)፥ ሊያበርዱትም የማይቻል የእሳት ኳስ ሆነብን! ነፍጠኛው ያጠጣውን ኮሶ መራርነት ከመራርነቱ በላይ እያመረሩ ሲነግሩን፥ (በአባ ባሕርይ ቋንቋ ልጠቀምና) ኢትዮጵያን ከ"አርዌ ከርሥ" (*ዜናሁ...* ክፍል ፰) እንደአሻራት እንኳን ማስታወስ አቃተን።

መላእክት የተፈጠሩ ጊዜ ሳጥናኤል "ፈጣሪያችሁ እኔ ነኝ" ሲል ቅዱስነት እንዳመለጠውና ጥቂቶች መላእክትን እንዳሳሳተ፥ እነዚህ በኢትዮጵያዊነት ዓይን ሲታዩ ቅዱስነት የሌላቸው የጠላት ጸሐፊዎችም የሚያሳስቷቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን አግኝተዋል። ኢትዮጵያ ሰላማዊት እንድትሆንና ልጆቿ ጤናና ብልጽግና እንዲያገኙ ያላት ተስፋና ምኞት የሚፈጸመው ቅዱስ ገብርኤል፥ *"ንቁም በበሥርዓትነ ወንጽናዕ በአሚን"* ("በየሥርዓታችን እንቁም፥ በእምነትም እንጽና") ብሎ ሳጥናኤልን፥ ስብልያኖስን፥ ዲያብሎስን እንዳሸነፈው፥ ተስፋዋንና ምኞቷን "አሜን" ብለን የምንቀበል ልጆቿ፥ "በእኛነታችን እንጽና፤ ብንጣላም ብንፋቀርም እንዳያቶቻችን እርስ በእርሳችን እናድርገው እንጂ፥ ሌሎች አናስገባ" ብለን የኢትዮጵያን ዳግማዊ መንኩታኩት የሚመኙትን ጠላቶቻችንን ስናሳፍር ነው።

እናት ኢትዮጵያ የተሟላች አልነበረችም፤ አያቶቻችን ኢትዮጵያን ያወረሱን ጅምሯን ነው። ለምሳሌ፥ መንግሥቷ የክርስቲያኖች መንግሥት ነበረ፤ ክርስቲያን ያልነበሩ ኢትዮጵያውያን በመንግሥታቸው ፊት እኩል አይታዩም ነበረ፥ ቢታዩም እኩልነቱ አይሰማቸውም ነበረ[14]። አሁንም የክርስቲያን መንግሥት መሆኗ ከቀረ ወዲህም የተሟላች አይደለችም፤ ከሃይማኖት ጋራ ያልተያያዘ ብዙ ጉድለት አለባት። እኛ ወራሾቿ አብረን እንኑርባት ካልን የተቻለውን ያህል ለሁላችንም እንደምትስማማን አድርገን ማሟላት መብታችንና ግዴታችን ጥቅማችንም ነው።

አለመግባባትን ከፈጠሩት ሌላው ዋና ምክንያት የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች "ጋሎች መጤዎች ናቸው ይባላል" የሚሉት ትረካ ነው። እሱ ታዲያ ብናውቅበት ማብራሪያ በመስጠት የሚስተካከል እንጂ የሚያቃቅር አይደለም። አንደኛ፥ ዘመኑን ያለያዩታል እንጂ የታሪክ አስተማሪዎቻችን ሲነግሩን መጤዎች የሚሉት አሮሞዎችን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ነገዶች ሁሉ ነው። ሴማዊ የሚባሉትን ቋንቋዎች የሚናገሩትን በባብ እልመንደብ፥ አሮምኛ የሚናገሩትን በሞምባሳ ወይም በዛንዚባር አድርገው መጡ ቢሉ ልዩነቱ ሆድና ጀርባ ከመሆን የሚያደርስ አይደለም።

---

14. ስለዚህ መሆን አለበት ዶክተር መሐመድ ሐሰን፥ "Christianity, even the Ethiopian variety, just had to be an indicator of a higher level of civilization than a traditional African religion..." ("ክርስትና፥ የኢትዮጵያው ዓይነቱም እንኳ ቢሆን፥ (መጽሐፍ ስላለው) መጽሐፍ ከሌለው ትውፊታዊ አፍሪካዊ ሃይማኖት ይልቅ የከፍተኛ ደረጃ የሥልጣኔ ምልክት ሆኖ ነበረ") ለማለት የበቃው። Mohammed Hassan, *The Oromo of Ethiopia A History 1570--1860* p. 5. መሐመድ ሐሰን በታሪካችንና በታሪክ አጻጻፋችን ተናዶ ይሆናል እንጂ፥ "የኢትዮጵያው ዓይነቱ" ክርስትና የማይናቅ ከማንም ሃይማኖት የማያንስ ጥንታዊና ትልቅ ሃይማኖት እንደሆነ እንደሚያውቅ አልጠራጠርም።

ሁለተኛ፥ አቶ ዐፅሜም አለቃ ታየም “ባለታሪኮች እነዚህ የጋላ ሕዝብ ከእስያ ፈልሰው ወደ ማዳጋስካር እንደ ተሻገሩ፥ ከዚያም ፈልሰው ቦባሳ አጠገብ ከባሕር ወደብ እንደተቀመጡ ይነግሩናል” ይላሉ እንጂ ታሪኩ ይህ ነው አላሉም። ቢሉ ኖሮ እንዲህ ያለ ታሪክ የሚነግሩን እነማናቸው ብለን እንጠይቅ ነበረ።

የጉድሩ ኦሮሞ የነበሩት ሊቅ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ስለኦሮሞዎች ሲጽፉ ከዚህ በታች እንደጠቀስኩት ሁላችንንም ወንድማማቾች አድርገው ነው[15]፥

> እኒህም ጋሎች ጥንት ሀገራቸው ኢየሩሳሌም ነው፤ ኤዶም ሳኤር ይባላል። ትውልዳቸው የአብርሃም የይስሐቅ የኤሳው የኤልፋዝ የወረሞ ዘሮች ናቸው። ይስሐቅ ኤሳውንና ያዕቆብን ወለደ። ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ተቀደሰ፤ ኤሳው ግን ለዚህ ዓለም ተባረከ፤ የብዙ ሕዝብ አባት ሆነ። በኤዶም ምድር በሣኢር ተራራ ተቀምጦ ከከነዓን ዘር ከሔት የልጅ ልጆች አዳ የምትባል አግብቶ ኤልፋ(ዝ)ን ወለደ፤ ኤልፋዝ ቴማንን፥ ኦርማን፥ አማሌቅን፥ ቄነዝን፥ ጋዓትን፥ ቴምናዕን፥ ሱፌን ፯ ወለደ። ከኦርማ ዘር ወረሞ ተወለደ። ወረሞ የተባለም እንዲህ ነው፤ በሞሬት አማራ እንደተባለ ሁሉ በኦርማ ወረሞ ተባለ። አዳ ግን የሔት ልጅ ከኤሳው ወልዳ የብዙ ሕዝብ እናት ሆነች። ስለዚህ ጋሎች በወረሞ ቋንቋ እናት ሲሉ አዳ ይላሉ። ልጆቹዋ እጅግ በዝተዋልና፤ ደግሞ ልጆቹዋ በኢትዮጵያ ከባሕር እስከ ባሕር መልተዋልና።
>
> ነገር ግን (ነቢዩ) መሐመድ በተነሣ ጊዜ ከብት ለማርባት የማይመች ሆነ -- ዘረፋው ኢየበዛ እስላምና ጋላ ሁለግዜ ኢየተዋጉ። የኤሳው ዘር የወረሞ ልጆች ግን ዘላን ሁነው ይኖሩ ነበርና መጀመሪያ ከኢየሩሳሌም ሲመጡ በህንድ ባሕር ተሻግረው ዝንጅ ባሕር (ዛንዚባር?) ከሚባል ስፍራ ተቀምጠው እላም ኢያረቡ ይኖሩ ነበረ። እስከ ሲዳሞ እስከ ወላሞ ኢየመጡ ይሰልቡ ይገድሉ ነበር።

ይኸ የአለቃ ተክሌ ታሪክ እንደሌሎቹ፤ አለቆች ታሪክ ገና ምርምር ያልደገፈው በጽፈት የሰፈረ ያፍ ታሪክ ቢሆንም መልእክቱ በዓይነት ረገድ ከሌሎቹ፤ ጋራ ተመሳሳይ ነው። በነሱ ዓይን ሁሉም መጤ ነው፤ ሁሉም የአብርሃም ዘር ነው።

ኦሮሞዎች ከውጭ መጡ የሚሉ ሌሎች ብቻ አይደሉም፤ ኦሮሞዎችም ይላሉ። ለምሳሌ ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ከኦሮሞ ሽማግሌዎች የሰሙትን “ጋላ ከወደደቡብ መጥቶ ቦረና ገባ የሚለውንም ቃል በአፈ ታሪክ የታወቀውና በጋልኛ የሚነገረው የምርቃት ቃል ሲደግፈው ይታያል” ይሉና “*ውቱባ ማንጃሮ ታኢ፥ ኢጃጃ ሐፊ*” (“የማንጃሮን ወጋግራ ሁን፤ በሕይወት ቁም”) የሚለውን የሽማግሌዎቹን

15. EMML 5403, ff. 61b-62a.

ምርቃት ይጠቅሳሉ[16]። ኦሮሞዎች የክሊማንጃሮ ትዝታ ካላቸው ቀዳማዊ ምኒልክ የተቀበረት እዚያ ነው ከሚለው ያፍ ታሪክ ጋራ ይሄዳል።

ዘመኑንም ቢሆን የኢትዮጵያ ነገዶች (ኦሮሞዎችን ጨምሮ) ኢትዮጵያ የገቡበትን ዘመን ኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ ከመጡበት ዘመን ጋራ ካላምታታነው ቀዳሚውን ከደጋሪው (አልፋውን ከኦሜጋ) ልንለየው አንችልም። እንደሚመስለው፥ ኦሮሞዎች በነገድነት እስከ ዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ድረስ ከኢትዮጵያ ማእከላዊ አስተዳደር ውጪ የሆኑት የሰፈሩበት ደቡቡ በአንዳች በማናውቀው ታሪክ ምክንያትና ዘመን ከኢትዮጵያ አስተዳደር ሲቈረጥ አብረው ቢቈረጡ ነው። ወይም የጀርመን ተመራማሪዎች ሱማሌዎች ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት ከማህል ኢትዮጵያ ተነሥተው ወደዳር የሄዱ ኢትዮጵያውያን ለመሆናቸው ምልክት እንዳገኙ[17]፥ ኦሮሞዎችም በአንድ ዘመን ወደደቡብ የሚያርቃቸው እክል አግኝቷቸው ከኢትዮጵያ ወጥተው ሄደው ይሆናል። ምናልባት ከሁሉም ይልቅ ከፍ ያለ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው አይኬ ሃበርላንድ ከኦሮሞ ጎሳዎች ጠይቆ ያገኘው ይመስለኛል። እንዲህ ይላል[18]፥

> ጋሎች ሁሉ ስለነገዳቸው አመጣጥ የጋራ የሆነ ተረት–መሰል እምነት አላቸው፥ ባሪጋማ ከሚባል አገር እንደመጡ ያምናሉ። ይህንን (ባሪጋማን) "ከባሕር ማዶ" ወይም "ከጠዋት ውጋጋን ማዶ" ብሎ መተርጐም ይቻላል። (ግን) ስለዚህ ቦታ ከዚህ በቀር ሌላ ያቆዩት ነገር የላቸውም።
>
> ይህንን ተረት መሰል ሐሳብ ልተወውና፥ የአያቶቻቸው እውነተኛ የትውልድ ሀገር ባሊ ውስጥ ቀዝቃዛው ደጋ ይመስለኛል።

ሃበርላንድ የ"ባሪጋማ"ን ታሪክ ተረት መሰል አድርጎ "ልተወው" ከማለት ይልቅ አጥብቆ ቢከታተለው የኦሮሞዎች "እውነተኛ የትውልድ ሀገር የት እንደነበረ ለማወቅ የመጀመሪያውን ፈር ያወጣለት ነበረ። "ባሊ ውስጥ ቀዝቃዛው ደጋ" ከባሕረ ገሞ ቀጥሎ ያረፉበት አገር ነው። "ባሪጋማ" ያላዳንች ጥርጥር "ባሕር ገሞ" መሆን አለበት። ዱሮ "ባሕር ገሞ" ይባል የነበረው ሀገር ዛሬ የቱ እንደሆነ እንደሌሎች ብዙ የጥንት ቦታዎች በትክክል ባይታወቅም፥ ከግራኝና ከኦሮሞዎች ወረራ በፊት ለኢትዮጵያ

16. ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፥ *ዜናሁ ለአባ ባሕርይ*፥ EMML 3749, ገ. 6።

17. *Deutsche Forschung Gemeinde*, Vol. 3 (1981), p. 21. ከ1307 እስከ 1336 ዓ.ም. የነገሠው አፄ ዓምደ ጽዮን ጋላ ሀገር ሄዶ እንደነበረ ታሪኩ ይናገራል። መጀመሪያ፥ *"ንጉሥሰ ኀለፈ ወበጽሐ መንገለ ጋላ አመ ፷ወ፭ ለሚያዚያ"* (ንጉሡ ግን አልፎ በሚያዚያ ፷፭ ከጋላ ሀገር ደረሰ)፥ በኋላ ከዚያ "ከጋላ ሀገር" ሲለቅ ደግሞ፥ *"ተንሥአ ንጉሥ ምስለ ሠራዊቱ እምሀገረ ጋላ አመ ሰቡዱ ለሰኔ"* (ንጉሡ በሰኔ ሰባት ከሠራዊቱ ጋራ ከጋላ ሀገር ተነሣ) ያለው ንጉሡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያደረገውን እንቅስቃሴ ሲገልጽ እንጂ ከኢትዮጵያ ውጪ ሄዶ ነበር ማለቱ አይደለም። M. Jules Perruchon, "Histoire des Guerres d'ʿAmda Ṣyon roi d'Éthiopien," pp. 294 and 305.

18. Eike Haberland, *Galla Süd-Äthiopiens*, pp. 4 and 772.

ነገሥታት የሚገብር የኢትዮጵያ ግዛት ነበረ። ለአፄ ይሥሐቅ በተዘፈነው የጥንት አማርኛ ውስጥ ኬራ፥ ዛቶ፥ ወላሞ፥ ባሕር ገሞ፥ ሱፍ ገሞ ለኢትዮጵያ ንጉሥ ፈረስ ገባሪዎች ሆነው ተዘርዝረዋል[19]። የ"ታላቋ ኢትዮጵያ" ታሪክ መጻፍ ተጀመረ እንጂ አልተፈጸመም።

በዚያም ሆነ በዚህ ምክንያት ተቈርጠው ከሆነ፥ በዚያ ተቈርጠው ባሳለፉበት ዘመን እንደ ራስ ዓምዱና እንደ እጨጌ ዕንባቆም ያሉ ብዙ ቤተ ሰቦችና ግለሰቦች ከውጪ (ያውም ከባሕር ማዶ ድረስ) እየመጡ አገሪቱን በባህል፥ በንግድ፥ በፖለቲካ ሲያበለጽጉ[20]፥ ኦሮሞዎች ከቅርቡ ደቡብ አይመጡም ነበር ማለት ይቻላልን? አቶ ዐፅሜም አለቃ ታየም ኦሮሞዎች ወደማህል ኢትዮጵያ መምጣት የጀመሩት በዛጔ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይናገራሉ[21]። በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመን (1263–1277 ዓ. ም.) የኖሩ የሞረቱ መምህር አቡነ ዜና ማርቆስ ዐርፈው የመንፈስ ልጆቻቸው የመንፈቅ ተዝካራቸውን ሲያወጡ "ጋሎች" እንዳስቸገሯቸው በጻድቁ ገድል ተጽፏል[22]። እነዚህ ታሪኮች ሞላው የኦሮሞ ነገድ ከብቱን ይዞ ጓዙን አንሥቶ ማህል ኢትዮጵያ የገባው ያን ጊዜ ነው ለማለት ባያስችሉንም የኦሮሞዎች ሁል ጊዜ ማህል ኢትዮጵያና በመንግሥቱ አስተዳደር ውስጥ መግኘት የቆየ መሆኑን እንድንጠረጥር ያደርጉናል። ብቻ የመንግሥቱን ባህል ተከትለው እንደ እጨጌ ዕንባቆምና እንደ ኦሮሞው አለቃ ተክሌ የክርስቲያን ስም ስለሚይዙ ማን የማን ዘር እንደሆነ ሳይታወቅ ሁሉም "አማራ" ይባላል።

19. Ignazio Guidi, "Le canzoni geez-amariña in onore di Re Abissini," p. 56.

20. የራስ ቢትወደድ ዓምዱ/ዓምደ ሚካኤል ቅድም አያቶች በዛጔ ዘመነ መንግሥት ከየመን የመጡ ይሁዲዎች ነበሩ። ዓምደ ሚካኤል ከዘርአ ያዕቆብ እስከ ናኦድ ዘመን ከማንም ይበልጥ የተከበረና ኢትዮጵያን ያስከበረ ባለሥልጣን ነበረ። ልጆቹም ለራስነትና ለሐስንነት በቅተዋል። ትውልዱን ያወቅነው እንዳጋጣሚ ከተዋት ትንሽ ማስታወሻ ነው፤ Taddesse Tamrat, "The Abbots of Däbrä-Hayq," pp. 112-3; Getatchew Haile, "The Kalilah Wa-Dimnah and the Mazmura Krestos," p. 376-8; Perruchon, "Histoire d'Eskender," pp. 338-9; Sergew Hable-Selassie, "The Ge'ez Letters of Queen Eleni and Libne Dinlil to John, King of Portugal," p. 547-8. እጨጌ ዕንባቆም ከግራኝ ወረራ በፊት ለንግድ ኢትዮጵያ የሚመላለሱ የመናዊ ዓረብ/እስላም ነበሩ። ደብረ ሊባኖስ የሳቸውን ያህል የምታከብራቸው እጨጌዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው። E. J. von Donzel, *'Ĕnbāqom Anqṣa Amin* (*La Porte de la Foi*), Leiden 1969, pp. 17-28; L. Ricci, "Le Vite di Ĕnbāqom e di Yoḥannes, Abbati di Dabra Libānos di Scioa," *Rassegna di Studi Etiopici*, Vol. XIII, pp. 91-120, and Vol. XIV, pp. 69-107.

21. አለቃ ታየ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፥ አዲስ አበባ ፲፱፻፷፬ ዓ. ም.፥ ገ. 62፤ እዚህም ገጽ 171–172 ላይ ተመልከት።

22. EMML 3987, f. 71b., Getatchew Haile, *A Catalogue of Ethiopian Manuscrips*, Vol. IX, p. 270.

ደግሞስ ኦሮሞዎች የቅርብ ጊዜ መጤዎች ቢሆኑ ቅሬታው እምኑ ላይ ነው? ከሌሎች በኋላ መጥቶ ኢትዮጵያን እናት ማድረግና እንደኛ ከሌሎች በኋላ ተወልዶ ኢትዮጵያዊ መሆን አንድ ዓይነት ናቸው። ይኸንን ከማንም ይልቅ የጉዲፈቻን ባህል ያወረሱን አባቶች (የኦሮሞች) ልጆች ነን የምንል ማወቅና ሲሆንም ማስተማር አለብን። ኢትዮጵያንም ሆነ ማንንም አገር እናት ለማድረግ የጊዜ ገደብ የለበትም፤ የደም ግንኙነትንም አይጠይቅም። ኢትዮጵያን ባለታሪክ በማድረግ ረገድም ከሆነ ከዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት እስከዛሬ የተፈጸመው ድርጊት እንደቀላል የሚታይ አይደለም፤ አለጊዜዋ የጠለቀችው የኢትዮጵያ ፀሐይ ቦግ ብላ የወጣችበት ዘመን ነው።

የኢትዮጵያ መምህራን ከውጪ የመጣን ነገዶች ሲያደርጉን ሊያኮሩን እንጂ ሊያዋርዱንና ሊከፋፍሉን አስበው አልነበረም። ይልቅስ መስሏቸውም ሆነ ወይም ለተንኮል፥ እኛን የከፋፈሉን "**ሐበሻ**" ለሚለው ስም የሌለውን ትርጉም እየሰጡ፥ "አቢሲኒያውያን" እና "አቢሲኒያውያን ያልሆኑ" ("ሐበሾች" እና "ሐበሾች ያልሆኑ") ኢትዮጵያውያን እያሉ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚጽፉ ምዕራባውያን ናቸው።

በጥንት ትርጉሙ "ሐበሻ" ሞላ የምሥራቅ አፍሪካን ሕዝብ (አንዳንዴም ከባሕር ማዶ የመጡን) ያጠቃልላል። ታሪክ አበላሾች ግን "አቢሲኒያውያን" ("ሐበሾች") የሚሉት ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎችን (አግዓዝያንን፥ አማሮችን፥ ትግሬዎችን፥ ወዘተ) ብቻ ያደርጉና የኢትዮጵያን ሥልጣኔ፥ ጽሑፋዊ ቅርሳችንን ጨምረው ጠቅልለው ለነሱ ለብቻቸው ይሰጧቸዋል። ይኸም በእንግሊዝኛ የተጻፉትን መጻሕፍት ሁሉ (የነ ዋሊ ሾይንካ ልብ ወለዶችና ግጥሞች ሳይቀሩ) ለእንግሊዞች እንደመስጠት ነው።

በተለይ በትምህርትም ሆነ በሌላ ምክንያት ከሚሲዮናውያንና የኦርቶዶክስ ክርስትና ካልሆነ ሃይማኖት ጋራ ንክኪት ያላቸው ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ ሃይማኖትና የክርስትናው መንግሥት እንደበደሏቸው ስለሚረዱ ይኸንን የምዕራባውያንን አከፋፈል የሀገርንና የሕዝብን አንድነት በሚጐዳ መንገድ ይጠቀሙበታል። ሲጽፉም ሆነ ሌላ ሥራ ሲሠሩ፥ አደገኛ ጥላቻ ያሳያሉ። በምሁርነት ስም የሚጽፉት ሁሉ ምሁራዊ ድርሰት መሆኑ ቀርቶ ለበቀል የሚጣራ ዋይታ ይሆናል፤ የረጋውን የሚበጠብጥ እንጂ የተበጠበጠውን የሚያረጋ ቃል ወይም በቀል ያልቀደመው መፍትሔ አያመጡም። በግራኝ ጦርነትና ኦሮሞዎች ማህል ኢትዮጵያ ሲገቡ ስለደረሰው ጥፋት ሲጽፉ የሚጠቀሙባቸው ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ደስታቸውን የማይደብቁ ናቸው።

ይኸንን ምዕራባውያን "አቢሲኒያውያን" እና "አቢሲኒያውያን ያልሆኑ" እያሉ ያለምንም መሠረት የሚከፋፍሉንን በያዝኩት ርእሰ ነገር ላጥብበውና፥ በታሪክ በደል የተሰማቸው አንዳንድ ኦሮሞዎችም

እንደእስላሞቹ ተቀብለውት፥ "አቢሲኒያውያን" እና "ኦሮሞዎች" እያሉ ይጽፋሉ። የተሳሳቱ ይመስለኛል፤ ምክንያቱም፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲህ በሁለት መደብ ለመመደብ ታማኝ መለኪያ የለንም።

ቢኖረን ኖሮ እናቱ ከጋልኛ ሌላ ቋንቋ የማትናገር አፄ ኢዮአስ (1747-1761)፥ የወለጋው ገብረ እግዚአብሔር፥ የባሌው ጴጥሮስ፥ የጎንደሩ ዐብደላ፥ የሸዋ ኦርቶዶክሱ ገመቹ፥ የጉራጌ ካቶሊኩ ፉላስ፥ የወሎው እስላም በየነ፥ ጸሐፌ ላሕም ቱሉ (በአፄ ኢያሱ ዘመን "ይሉ አይሉ፥ የታል ቱሉ" ይባልለት የነበረው)፥ ከጋላ ነገድና ከሐድያ ወገን የነበረው ብላቴን ጌታ ባስልዮስ (በዚያው ዘመን በጥበቡ፥ በዕውቀቱ፥ በፍርድ አስተዋይነቱ ስም ያተረፈው)፥ "የሐበሻ ንጉሥ" እያሉ ይፈርሙ የነበሩት ትንሹ ራስ ዓሊ ከሁለቱ መደቦች ባንደኛው ብቻ እንደማይቀመጡ ለማየትም ለማሳየትም ይቻል ነበረ።

የዘመነ መሳፍንትን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያነብ በዚያን ዘመን ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት የየጁ መሳፍንት በማንኛውም የስሞች ውሳኔ ኢትዮጵያውያንም፥ ኦሮሞዎችም፥ አቢሲኒያውያንም መሆናቸውን ይገነዘባል፤ ምክንያቱም ታሪኩ እንደሚለው በዚያን ጊዜ የንጉሡ ልትሆን የሚገባት ንጉሣዊት ሥልጣን "በጋሎች እጅ ነበረች" ("ህለወት ሥልጣነ ንጉሥ በእደ ጋላ")[23]።

ዘመኑ አልረዳቸውም እንጂ የጁዎች ሥልጣኑን ይዘው የተቻላቸውን ያህል የሀገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ አልቦዘኑም። የኢትዮጵያውያንን መብት የሀገሪቱን ዳር ድምበር በማስጠበቅ ረገድ ከየትኞቹም የሀገሪቱ ገዢዎች ያነሰ ሥራ አልሠሩም። ግብፆች ትልቁ ራስ ዓሊ የሚተባበሯቸው መስሏቸው ኢትዮጵያን ሊደፍሩ አስበው ነበረ። መኳንንቶቻቸው ሀገሪቷን እስከሞት እንመክትላታለን ስላሉ ዳነች[24]። በኢትዮጵያና በታላቋ ብሪታኒያ መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የወዳጅነትና የንግድ ውል የተፈጸመው በራስ ዓሊ ዘመን ነው[25]።

ከዘመኑ የኢትዮጵያውያን ችግሮች አንዱ የኢየሩሳሌም ገዳማችንን ከነጣቂዎች መከላከል ነበረ። በዚህም ረገድ ራስ ዓሊ እንደሌሎቹ ሥልጣናት ሁሉ በተራቸው ታግለዋል። ከዚህ በታች ያለው ለንግሥት ቪክቶሪያ በ1852 ዓ. እ. በአማርኛ የጻፉላት ደብዳቤ ነው (መግቢያው ብቻ ነው ግዕዝ)[26]፤

23. Conti Rossini, "La cronaca reale abissina," p. 803.
24. እዚያው ገ. 858።
25. Sven Rubenson *et al, Correspondence and Treaties 1800-1854*, pp.178-187.
26. እዚያው ገ. 194። ሳሙኤል ጎባት ኢትዮጵያ ውስጥ የፕሮቴስታንት ሚሺነሪ በነበረበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ጋራ ይተዋወቅ ነበረ። በኋላም የኢየሩሳሌም ጳጳስ ሆኖ ነበረ። ምዕራባውያን ወደ አፍሪካ ሲመጡ ስለሚጀኑ ሰውየው ለራስ ዓሊ የእንግሊዟ ንግሥት ባለሟል ቢመስላቸው አያስገርምም።

እምነበ ርእሰ መኳንንት አሊ ገብረ ንጉሠ ነገሥት እግዚአብሔር ዘይትወሐድ በመለኮት ወይሜለስ በገጻት።

ትብጻሕ ኀበ ንግሥተ እንግሊዝ እንዴት ነሽ፥ በጎ ነሽ የሰማይ የምድሩን ያህል። እኔ ባንች ወዳጅነት ጠንቻለሁ። አንችም በኔ ወዳጅነት ጥኝ። ምነው አንች ሳለሽ ርስቴን መነቀሌ። ሁሉ በየርስቱ ተቀምጦ እኔ ተነቀልሁ። አሁንም ርስቴን እንዳልነቀል አድርጊልኝ። የሐበሻን እጣ መሬቴን ተነቀልሁ። ርስት መነቀል ጥኑ ነገር ነው፥ ርስተ ምድር ርስተ ሰማይ ነውና። በአንች መንግሥት ዘመዴ አይነቀል። ሳሙኤል ጉባ አደራኽን ጠበቃ ሁናቸው ርስቴን አልነቀል፥ ዘመዶቼን አደራ።

የምትወጅውን ነገር ላኪብኝ እሰድልሻለሁ።

ትልቁ ራስ ዓሊም በትውልድ ሀገራቸው በየጁ ሰባት ደብር እንደተከሉ ይነገርላቸዋል። ከነዚህም ውስጥ ጉበርጃ ማርያም፥ ዛምል ጊዮርጊስ፥ ወልድያ ገብርኤል፥ ክቢ ቃሎ ሚካኤል ይገኙባቸዋል[27]።

ኢትዮጵያውያንን "አቢሲኒያውያን" እና "አቢሲኒያውያን ያልሆኑ" ብሎ መከፋፈልና "አቢሲኒያውያን" እና "ኦሮሞዎች" ብሎ መከፋፈል በብሔራዊ ጉዳት ረገድ ተመሳሳይ ናቸው። የመጀመሪያው "አቢሲኒያውያን አይደሉም" የሚባሉትን፥ ሁለተኛው "ኦሮሞዎች" የሚባሉትን ለአቢሲኒያውያን ሥልጣኔ አስተዋጽኦ ያላደረጉ ያደርጓቸዋል።

ሕዝባችንን ከሁለት መደብ መክፈል በአንድነታችን ላይ ፈንጂ መጣል ብቻ ሳይሆን በግለ ሰብም ደረጃ ማንነታችንን እንድንጠራጠር ያደርገናል፤ ለምሳሌ የአቢሲኒያውያንንና የሌሎቹን ስሞች የተለያዩ በማድረግ፥ የሰለሙት ኦሮሞዎች በሌላ አገር ቋንቋ በኮራት "መሐመድ"፥ "ዓሊ"፥ "ሰዒድ" "ዐብደላ" እየተባሉ ክርስቲያን የሆኑት ኦሮሞዎች በሀገር ቋንቋ "ተመስገን" (= "መሐመድ")፥ "በላይነህ" (= "ዓሊ" )፥ "ገብረ እግዚአብሔር" (= "ዐብደላ") ሲባሉ ሊያሳፍሯቸው ይሞክራሉ -- የተገላቢጦሽ። ዘዴያቸው ረቂቅ ስለሆነም፥ የሚያፍርላቸው አልፎ አልፎ ሳያገኙ አልቀሩም።

## ይጋርጃ

ይኸ መጽሐፍ በመሠረቱ አብዛኞቹ ካሁን በፊት የታተሙ ሰነዶች ጥርቅም ነው፤ ብዙ አዲስ ነገር የለበትም። ግን ላላያቸው ሁሉም አዲስ ናቸው። (አዲስነታቸው ግዕዝ ለማያውቁ የታሪክ ተማሪዎችም ነው።) ከሰነዶቹ ውስጥ ለተነሣሁበት ዓላማ የሚሆኑትን እየመረጥሁ ስሰበስብ፥ ምንጮቹ

27. አለቃ ታየ፥ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ*፥ JE692E ገ. 610።

የተደረሱት የኦሮሞዎቹን ወረራ ይቃወም የነበረውን መንግሥትና ተወራሪውን ነባሩን ሕዝብ በሚደግፉ ጸሐፊዎች መሆኑን ሳልረሳ ነው። ያም ሆኖ ጸሐፊዎቹ የአፄውን ጉብዝናና ደግነት፥ የጠላቾቻቸውን በሰይጣን ተመሪነት ይነግሩናል እንጂ የሆነን ድርጊት ዐውቀው ለውጠው ለመመዝገባቸው የሚያስጠረጥረኝ ነገር አላጋጠመኝም። ንጉሡ ሲያሸንፍ ጀግንነቱን፥ ሲሸነፍ ሁል ጊዜ አሸናፊ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ይነግሩናል። ጠላት ሲሸነፍ ክርስቶስ ወገኖቹን ስለረዳ፥ ጠላት ሲያሸንፍ የክርስቲያኖች ኃጢአት ስለበዛ መሆኑ እምነታቸው ነበር። ከዚህ አልፈው ታሪክ ሲያዛቡ አላገኘኋቸውም። የሀገር ውስጥ ምንጮችን የሚያጥላሉ ዘመናዊ ታሪክ ጸሐፊዎች ካሉ ባይመዘገብ የሚወዱት ስለተመዘገበ ነው። እርግጥ፥ ሆን ብለውም ሆነ ወይም አስፈላጊነቱ ሳይታያቸው ቀርቶ ብዙ ታሪካዊ ድርጊቶችን ሳይመዘግቡልን እንደቀሩ መገመት ይቻላል።

ከታሪክ ነገሥቱ ለማስረጃነት ያስፈልጋልና ይበቃል ያልኩትን ያህል በግዕዙ እየጠቀስኩ ሳቀርብ ጥቅሶቹን አንድም ሳላስቀር ወደ አማርኛ እየተረጐምኩ ነው። እነዚህ ጥቅሶች የማስረጃ ምንጭ እና ማብራሪያ ከመሆናቸውም በላይ የዘመኑን አስተሳሰብ ያሳዩናል። በዚያ ላይ የሀገራችንን የታሪክ ሰዎችና ጀአግራፊዋን እንድንማር ያሳስቡናል ብዬ እገምታለሁ። (ግዕዝ የማያውቁ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ጸሐፊዎችም ቢሆኑ በአማርኛ ሲጽፉ የበታ፥ የሰው፥ የሠራዊት የተጻውዖ ስሞችን ከፈረንጅ መጻሕፍት እየቀዱ ወደ አማርኛ ሲመልሷቸው የሚያበላሹትን እንዲያርሙ ይረዳቸዋል።)

በጥቅሶቹ ላይ ሌላም ተስፋ ጥየባቸዋለሁ፤ የነገሥታቱ ታሪክ የተጻፈው በቀላል ግዕዝ ስለሆነ ግዕዝ ለመማር የጠበቀ ምኞት ያለው ጥቅሶቹን አብሯቸው ካለው ትርጉማቸው ጋራ እያስተያየ ራሱን በራሱ ሊያስተምርባቸው ይችላል።

የዘመኑ ነገሥታት ከተለመደው ራሳቸውን የማስተዳደር ሌላ ዋና ኀላፊነት የኦሮሞዎችን ወረራ መግታት ስለነበረ፥ የጥቅሶቹን እናቶች (ምንጮቹን) የሚያነብ ያንዱ ግጭት ታሪክ አልቆ የሌላው ግጭት ታሪክ የሚተካው ብዙ ገጾች ሳይገለበጡ መሆኑን ያያል። እንግዲህ ከነዚያ ውስጥ አለፍ አለፍ እያልኩ ለዚህ ድርሰት የመረጥኋቸው ጥቅሶች በዓይነት ረገድ ሲታዩ ምንጮቹን በትክክል የሚወክሉ ሲሆኑ በመጠን በኩል ግን የትልቅ ታሪክ ብርሃን መጠነኛ ብልጭታ መሆናቸውን እንዳንረሳ አጥብቄ አሳስባለሁ፤ ታሪኩ እዚህ በማቀርባቸው ምሳሌዎች የተወሰነ አይደለም።

ስለ ዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት "የጋሎች ወረራ" ስትጽፍ በዓሥራ ዘጠነኛው ምእት ዓመት "ነፍጠኛው በኦሮሞዎች ላይ ስላደረሰው በደል" አልጻፍክም የሚል ወቀሳ እንደማይነሣብኝ አምናለሁ። እሱ የአባ ባሕርይ *"ዜናሁ ለጋላ"* የማያውቀው ታሪክ ስለሆነ እዚህ ድርሰት ውስጥ ምዕራፍ ሊያገኝ እንደማይችል ግልጽ ነው። ሆኖም እሱንም ቢሆን

የኮሶውን መራርነት ከሰጠው ሽረት ጋራ አመዛዝኖ የሚጽፈው ከጠፋ መጻፉ አያዳግትም::

ይህን ጽሑፍ ሳዘጋጅ የመጣልኝ ሐሳብ ሁሉ ግራና ቀኝ እየጎተተኝ ከተነሣሁበት *ዜናሁ ለጋሳን* የመተርጐም ዓላማ ርቄ ሄጃለሁ:: ለማነው የምጽፈው? ለምሁራኑ የምርምር ድርሰት ለማቅረብ ከሆነ ምርምሩ ይቀረዋል የምላቸውን ብዙዎቹን የጎዳግ ማብራሪያዎችን ማሟላት ነበረብኝ፤ ለሕዝብ ከሆነ ደግሞ ይኸም ይበዛል:: ውጤቱ እነሆ ይህ ሁለት ጌቶችን እኩል የማያገለግልና የሚፈልጉትን ያህል የማያስደስት፥ ታሪካችንን ለመማር የሚፈልገውን ግን ለምንጮቹ "መስተፋቅር" የሚሆን መጽሐፍ ነው::

ምዕራፎቹ በመንፈስ አንድ በአካል ብዙ ስለሆኑ ማንኛቸውንም አስቀድሞ ወይም አቆይቶ ማንበብ ይቻላል፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዲነበብ ብፈልግም፥ ያዘጋጀሁት እንዲያ እንዲሆን አድርጌ አይደለም:: እንዲያውም ስለ አባ ባሕርይ የጻፍኩትንና ራሱን የ*ዜናሁ ለጋሳን* ምዕራፍ አሁን ካሉበት ያሳረፍኳቸው በመቀምር (በኮምፒዩተር) እየጫንኩ ብዙ ካንከራተትኳቸው በኋላ ነው::

# ምዕራፍ ፩

## አባ ባሕርይና ድርሰቶቻቸው

*ወለእመ ሞትኩ ካልአን ይጽሕፉ ዜናየ ወዜና ሉባ ዘይመጽእ። ወባሕቱ ብዑዕ ዘሞተ እስመ አዕረፈ።*

❖

ከሞትኩም ታሪኬንና የሚመጣውን ሉባ ታሪክ ሌሎች ይጽፉታል። ግን የሞተ ብዑዕ ነው፤ አርፏልና።

**አባ ባሕርይ**



**ኦሮሞዎችን ያጠና አንቶኒዮ ሴኪ።**

(ከ *Da Zeila alle Frontiere del Caffa, Viaggi di Antonio Cecchi,* 1886)

ስለ *ዜናሁ ለጋላ* የጻፉ ሁሉ ስለ ደራሲው ስለ አባ ባሕርይ የሚነግሩን ደራሲው በዚች ባጭር ድርሰታቸው ውስጥ ስለራሳቸው ከነገሩን አያልፍም። የሚነግሩን፥ "አባ ባሕርይ የሚባሉ በጋሞ ውስጥ የአንድ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መነኮሴ ነበሩ፤ ስለሳቸው ከዚህ በቀር ሌላ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም" እያሉ ነው[1]።

አሁን እንዳየሁት፥ "የሚታወቅ ነገር የሌለው" ምንጮቹን በሚገባ ሳንመረምራቸው በመቅረታችን ነው እንጂ ብንመረምራቸው፥ ስለ አባ ባሕርይ የሥነ ጽሑፍ አስተዋፅኦ ሌሎቹ የቀድሞ ደራሲዎቻችን ስለጻፉት ከሚታወቀው የማያንስ እናገኝባቸዋለን።

አባ ባሕርይ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ተመራማሪዎች ስማቸውን የዘለሉት[2] ታላቅ ሊቅ ነበሩ። እንደ ሌሎቹ የዘመኑ ጸሐፊዎች ከ*ዜናሁ ለጋላ* ብንጀምር፥ እኝህ ሰው ጋሞ ውስጥ ባንድ (ምናልባትም ብርብር ማርያም በምትባል) ቤተ ክርስቲያን በካህንነትያገለግሉ እንደነበሩ እናውቃለን፤ (የ*ዜናሁ ለጋላን* ክፍል ፪ መደምደሚያ ተመልከት።) ስማቸው አባ ባሕርይ መሆኑ የታወቀውም ይኸው ድርሰት "*ይቤ ባሕርይ*" ("ባሕርይ ይላል") ብሎ ስለደመደመ ነው (የድርሰቱን መጨረሻ ተመልከት)። መጽሐፍ ቀጂዎች ስም ስለሚለውጡ ወይም ስለሚሠርዙ *ዜናሁ ለጋላን* የቀዱልን ሰዎች የአባ ባሕርይን ስም ባለመሠረዛቸው ትልቅ አገልግሎት ሰጥተዋል።

የአባ ባሕርይ ድርሰቶች ብዙዎች ናቸው፤ አንደኛ፥ በ*ዜናሁ ለጋላ* ውስጥና በሌላም ቦታ የሚያደንቁትን የአፄ ሠርፀ ድንግልን ታሪክ[3] ሁሉንም የጻፉት እሳቸው ባይሆኑም የሳቸው አስተዋጽዖ ሳይኖርበት አይቀርም። ሁለተኛ፥ በባዶ ገጾቹ ላይ *ዜናሁ ለጋላ* ተጽፎበት በተገኘው የሎንዶኑ የብራና መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ድርሰቶች (ምናልባት ካንዱ

1. Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, p. xxxvi. ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘንም በቦታው ከምተቸው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ አባ ባሕርይ የጻፉት ሌሎች ከጻፉት የተለየ ነገር ቢኖርበት የገሙ ጎፋ ብርብር ማርያም ካህን ነበሩ ማለታቸው ብቻ ነው፡ EMML, 3749, f. 3a, Getatchew Haile, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. IX (1987), p. 127.
2. ለምሳሌ Guidi, *Storia della Letteratura Etiopica*; Cerulli, *La Letteratura Etiopica*, Milan 1968.
3. Conti Rossini, *Historia Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp. 3-220.

በቀር) ሁሉም የሳቸው ናቸው። መጽሐፉ አሁን ያለው የ1860 ዓ. ም. የጀኔራል ናፒየር ጦር ሠራዊት ምርኮኛ ሆኖ እንግሊዝ አገር ሎንዶን በሚገኘው የእንግሊዝ ቤተ መጻሕፍት (British Library) ውስጥ ነው፤ እዚያ BL Or. 534 የሚል የመታወቂያ ቁጥር ተሰጥቶት ይገኛል[4]። በውስጡ ያሉት የአባ ባሕርይ ናቸው የምላቸው ድርሰቶች ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፤

(1) *መዝሙረ ክርስቶስ*፤
(2) *"አጭሩ መዝሙረ ክርስቶስ"*፤
(3) *መልክዐ ገብርኤል*፤
(4) *ሰላመ ቅዱሳን*።
(5) *ዜናሁ ለጋላ*፤

## (1) *መዝሙረ ክርስቶስ*

*መዝሙረ ክርስቶስ* በማናቸውም ረገድ መጠኑ *መዝሙረ ዳዊትን* ያህላል፤ እንደ*መዝሙረ ዳዊት* 151 መዝሙሮች አሉት። ከዚያም አልፎ፤ መዝሙሮቹ እንደ ግጥም ቤት ይመታሉ። የዳዊት መዝሙሮች በተጻፉበት በጥንቱ በዕብራይስጥ እንጂ በትርጉማቸው ግጥሞች አይደሉም።

መዝሙሩ እንዲህ ሲል ይጀምራል፤ (በቅንፍ የሰጠሁት የፊደሎቹን ብዛት ነው)

***<u>መዝሙረ ክርስቶስ</u>***

*ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ ጎበ ፍኖተ ካሕድ*፤ (18)
*ወዘቆመ በእምነተ አብ ወወልድ*፤ *(15)*
*ወበሃይማኖተ መንፈስ ቅዱስ ሥላሴ ዋሕድ*፤ (20)

4. Wright, *Catalogue of the Ethiopic Manuscripts*, p. 84. ቤተ መጻሕፍቱ አሁን British Library ይባል እንጂ በፊት British Museum ነበር የሚባለው። የ*መዝሙረ ክርስቶስ* ቅጂ ባሁኑ ሰዓት ሌሎች ሶስት እንዳሉ ይታወቃል፤ (1) በርሊን፤ Ms. orient. quart. 996, Hammerschmidt und Six, *Äthiopische Handschriften1*, pp. 220-2፤ (2) ዋሽንግተን ከተማ፤ በኮንግሬስ ቤተ መጻሕፍት (ገና በካታሎግ አልታተመም)፤ (3) EMML 3473, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*,Vol. VIII, pp. 286-9. መዝሙር 18 EMML 2335, ff. 162b-163a ውስጥ ይገኛል፤ እዚያው Vol. VI, p. 384. የዋሽንግተኑን ቅጂ አላየሁትም፤ መጽሐፉን በአቶ ጥሩነህ ፋንታ ስም "Fanta 1" የሚል መታወቂያ የሰጠው አቶ ቡሩክ አብዲ እንደነገረኝ፤ በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ነው። የቀሩት ግን ቀጂ እያወቀም ሳያውቅም አንዳንድ ቦታ አበላሽቷቸዋል።

*ወብዑሪ ካዕበ በእሳተ ፍቅራ ንዱድ፤* (17)
*ዘበልሳኑ ይገኒ ወብርኩ ይሰግድ።* (16)
. . .

❖

**ወደክደት መንገድ ያልሄደ ብዑሪ ነው፤**
**በአብና በወልድ እምነት (ጸንቶ) የቆመም ፤**
**በመንፈስ ቅዱስ ሥላሴ አንድ ሃይማኖትም፤**
**በፍቅሯ እሳት የነደደም ብዑሪ ነው፤**
**በምላሱ የሚያመሰግን ጉልበቱም የሚሰግድ።**
. . .

**አምሳያው *መዝሙረ ዳዊት* ከዚህ በታች ያለው ነው (የፊደሎቹን ቁጥር አስተውል)።**

***<u>መዝሙረ ዳዊት</u>***

*በዑሪ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲዓን፤* (18)
*ወዘኢቆመ ውስተ ፍናተ ኃጥኣን፤ (15)*
*ወዘኢነበረ ውስተ መንበረ መስተሳልቃን፤* (20)
*ዘዳእሙ ሕገ እግዚአብሔር ሥምረቱ፤* (17)
*ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ።* (16)
. . .

❖

**በክፉዎች ምክር ያልሄደ ብዑሪ ነው፤**
**በኃጥአተኞች መንገድም ያልተገኘ፤**
**በዋዘኞችም ሸንጎም ያልተቀመጠ፤**
**ደስታው ግን በእግዚአብሔር ሕግ የሆነ፤**
**ሕጉንም ቀን ከሌት የሚያነብ።**
. . .

*መዝሙረ ክርስቶስ* **እንደ ስሙ የሚመለከተው ክርስቶስንና የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክርስትናን ነው። እንደ ልማድ ሆኖ (ትሕትና) የሀገራችን ደራሲዎች የድርሰታቸው ባለቤት መሆናቸውን ስለማይናገሩ፥ *መዝሙረ ክርስቶስ* "ዘእገሌ" የሚል ባለቤቱን የሚናገር ቃል የለበትም። ግን የአባ ባሕርይ ድርሰት ለመሆኑ በቂ ውስጣዊ ማስረጃ አለበት።**

<u>አንደኛ፥</u> "ለምን እንዲህ አደረገ የሚለኝ ካለ "*ኀሥሥ ውስተ መጻሕፍት*" (ድርጊቴ የሚገባ ለመሆኑ "መጻሕፍትን መርምር" ታገኘዋለህ) የሚለው በዚ*ናሁ ለጋላ* መቅድም የሚገኘው የይቅርታ ፈላጊ (apologetic) አነጋገራቸው እዚህ መቅድም ውስጥም ተደጋግሞ ይገኛል። (ለምሳሌ፥ ቅጠል 10ሀን ብንመለከት "*ኀሥሡ ውስተ መጻሕፍት*" የሚል እናገኝበታለን)።

<u>ሁለተኛ፥</u> እንደ *ዚናሁ ለጋላ* ስማቸው በውስጡ ይገኛል፤ ከመዝሙር 34 ይኸንን እንመልከት (ቅጠል 39ሀ)፤

*ለይትፈሥሑ ወይትሐሠዩ ዘይዜክሩ ስምየ በሠናይ፥*
*ወእለ ዮኀሥሡ ሊተ ሰላመ እንበለ እከይ።*
*እግዚኦ ለገብርከ* ***ባሕርይ***
*ሰሚዓ ቃልየ ኢትትሐየይ።*
*ወሕዋጼየ ኢትትህከይ።*

❖

ስሜን በደግ የሚያስታውሱ ደስ ይበላቸው፥ ይደሰቱም፤
ክፋት የሌለበት ሰላም የሚፈልጉልኝም እንዲሁ።
አቤቱ የአገልጋይህን የ**ባሕርይን**
ቃሌን መስማትን ቸል አትበል።
እኔን መጎብኘት(ህ)ንም አታቋይ።

<u>ሶስተኛ፥</u> አባ ባሕርይ ጋሞ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ያከማቹትን ንብረት ዳዌ የሚባሉ ኦሮሞዎች እንደዘረፉባቸው በ*ዚናሁ ለጋላ* ውስጥ (በክፍል ፪) ሲነግሩን እናገኛለን፥ እዚህም ላይ ደግመውታል። ይህን ከመዝሙር 74 የተቀዳውን እንመልከት (ከቅጠል 71ለ እስከ 72ሀ)፤

*እገኒ ለከ እግዚኦ እገኒ ለከ፥*
*እገኒ ለከ ወእጼውዕ ስመከ፥*
*ወእነግር ኵሉ ስብሐቲከ፥*
*በይነ ዘዐቀብከኒ፥*
*ወበይነ ዘኢገደፍከኒ።*
*ወለዘ ይመጽእ እስእል ኀቤከ፥ ኢትጎድገኒ።*
*ወአስተበቍዓከ ታድኅነኒ፥*
***እምነ እደ ፈያት እለ አቍሰሉኒ፥***
***መሰለቡኒ ዘዘገብክም ለደኃሪትየ።***
***ሚጥ ሊተ ኵሉ ዘነሥአ ጸላኢ እምኔየኑ።***

❖

**አመሰግንሃለሁ፥ አቤቱ አመሰግንሃለሁ፤**
**አመሰግንሃለሁ፥ ስምህንም እጠራለሁ፤**
**ክብርህንም ሁሉ እናገራለሁ፤**
**ስለጠበከኝ፤**
**ስላልጣልከኝም።**
**ስለወደፊቱም እለምንሃለሁ፤ አትጣለኝ።**
**ታድነኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፥**
**ካቆሰሉኝ ሌቦች እጅ፥**
**ለጓላዬ ያከማቸሁትን ከወሰዱብኝ።**
**ጠላት የወሰደብኝን ሁሉ መልስልኝ።**

**አባ ባሕርይ** *መዝሙረ ክርስቶሰን* **የደረሱት እንደ** *ዜናሁ ለጋላ* **በአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት ነው። ይኸንን የሚያደንቁትን ንጉሥ ደጋግመው ከማንሣታቸው በላይ "እግዚኦ ኮነኔከ ሀቦ ለንጉሥ" የሚለውን መዝሙር 71ን ለሱ ነው የሰጡት (ከቅጠል 68ሀ እስከ 69ሀ)፤**

*እግዚኦ ኮነኔከ ምስለ ጥበብ*
***ለንጉሥ ሠርፀ ድንግል** ሀብ፥*
*ከመ በአሠንዮ ይኩንኖሙ ለሕዝብ፥*
*ወይቅንዮሙ ለአሕዛብ።*
*ረሲ በዘመኑ ያንጸፍጽፍ መዓር እምአድባር፤*
*ወሐሊብኒ የኃዝ እምነ አውግር።*
*ወአንብሮ ለቀስም ምስለ ማእረር።*
*ረሲ ሰላመ ለብሔር፤*
*ወሣህለ ለኮሉ አህጉር።*
*በረከተ ዘርእ ወበረከተ ቀምሐ ሥሙር*
*ይረድ አምሳለ ጠል ውስተ ፀምር፥*
*ወከመ ነጠብጣብ ያንጠብጥብ በዲበ ምድር።*
*ይዝነን ምገደ ሀውክ ወፃዕር፤*
*ወይጎዳእ ማዕበለ ትንሣኤሁ ለፀር።*
*ወይኩንን እምጽባሕ እስከ ባሕር።*
*ይረስዩ ሕዝቡ ኮናተ ማዕፀደ ግብር (ኢሳይያስ)[5]።*
*ወይሚጡ ሰይፎሙ ኀበ ምሳር።*
*ይግኔይ ሎቱ ኮሉ ወይግረር።*
*ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያብኡ፤*
*ወነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያምጽኡ፤*

5. ደራሲው ከብዙ መጻሕፍት በብዙው ይጠቅሳሉ፤ ዋና ዋና የሚሏቸውንም ምንጮች በግራ ጎዳግ ይጽፋሉ። ምዕራፍና ቁጥር ግን አይሰጡም። ስቀዳና ስተረጉም የሳቸውን የግራ ጎዳግ በቀኝ በኩል በቅንፍ፥ ምዕራፎቹንና ያልሰጡንን ምንጮች ከሚገኙበት እየፈለግሁ ከግርጌ ጎዳግ እየጠቆምኩ ነው።

*ወለአጽምየ ጥበቡ ኮሎሙ ይትጋብኡ፤*
*እንዘ ይቀድም አሐዱ እምካልኡ::*
*ዳኅነ የዓል ወሠናየ ይቢት እንበለ ሕሰም፤*
*ወዘእንበለ ደቂ ወሕማም::*
*ወይትዓቀብ ዘልፈ በሰላም::*
*አኮኑ በመትከፍቱ ስዩም (ፍትሐ ነገሥት)፤*
*ወስቁል ነፍሰ ኮልነ አምሳለ አዕፁቅ በአም::*
*እስመ ከመ ርእስነ ውእቱ፤*
*ወንሕነኒ አምሳለ መለያልይ ሎቱ::*
*ንስአል ዘልፈ በእንተ ዝንቱ፥*
*ከመ ትንሐይ መንግሥቱ::*
*እመኒ ተህውከት አኮ ለባሕቲቱ፤*
*ወለእመ ሕድአት ኮነ ቦቱ::*
*ኢንትፈለጥ እምነ ክልኤቱ፤*
*እስመ በተዋልጦተ ነፍስ ወንጌሥ ፍጹመ (መጽሐፈ ፈላስፋ)፥*
*ይትዌለጥ ኮሉ ግብር ዘቀደመ::*
*ወከመዝ ንበል ጊዜ ጸሎትነ፥*
*ሣህልከ ወምሕረትከ ይርከብዎ ፍጡነ::*
*ዓዲ ናስተብቍዕ ንሕነ ኮልነ፥*
*ኀበ ዘኮሉ ይእኀዝ እግዚአብሔር አምላክነ፥*
*ከመ ያስተእኀዞ ዕሩያነ፥*
*ክልኤ አብትረ፥ ኀብለ ወሥነ (ዘካርያስ)::*
*ወከመ ሕርቃናስ ይኩንን (መጽሐፈ ፈላስፋ)፥*
*በመጽሐፍ ወሰይፍ ኀቡረ እስከ ለዓለም፥ ለይኩን::*

❖

አቤቱ ፍርድህን ከጥበብ ጋራ
**ለንጉሥ ሠርፀ ድንግል** ስጥ፤
ሕዝቡን በመልካም ይዳኝ ዘንድ፥
አሕዛብንም ይገዛ ዘንድ::
በዘመኑ ማር ከተራሮች እንዲንጠባጠብ አድርግ፤
ወተትም ከኮረብቶች እንዲወርድ::
ቅመምን ከአዝመራ ጋራ አዋሕደው::
አገርን ሰላም አድርግ፤
ዕርቅም በአውራጃዎች ሁሉ (አውርድ)::
የዘር በረከትና የሠመረ የምርት በረከት
ይውረድ፥ እንደዝናም በታጨደ መስክ ላይ፥
እንደ ነጠብጣብ በምድር ላይ ያንጠባጥብ::
የብጥብጥና የጭንቅ ሞገድ ይርጋ፤
የጠላት ትንሣኤ ማዕበልም ጸጥ ይበል::

ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ይግዛ።
ሕዝቡ ጦርን የግብርና ማጭድ ያድርጉ (*ኢሳይያስ*)[6]።
ሰይፋቸውንም ወደ ምሳር ይለውጡ።
ሁሉም ይታዘዙት፥ ይገብሩለትም።
የተርሴስና የደሴቶቹ ንጉሦች እጅ መንሻ ያስገቡ፤
የሳባና የዐረብ ንጉሦችም ገጸ በረከት ያምጡ፤
ጥበቡን ለማዳመጥም ሁሉም ይሰብሰቡ፤
አንዱ ከሌላው እየተሽቀዳደሙ።
ያለምንም ክፉ (ነገር) በደኅና ይዋል፥ በጥሩም ይደር፤
ያለበሽታና ያለሕመም።
ሁልጊዜ በሰላም ይጠበቅ።
በትከሻው ሹም አይደለምን፤ (*ፍትሐ ነገሥት*)[7]፤
የሁላችንም ነፍስ (በሱ ላይ) ተንጠልጥላለች፥ እንደ ቅርንጫፎች በዛፍ ላይ።
ምክንያቱም እሱ ለኛ እንደ ራሳችን ነው፤
እኛም ለሱ እንደ (ሰውነት) አባሎቹ ነን።
ሁልጊዜ ስለዚህ (ጉዳይ) እንጸልይ፥
መንግሥቱ እፎይ እንድትል።
ስትታወክም ሆነ፥
ጸጥታ ሲሰፍንባትም የብቻው አይሆንም ።
በሁለቱም (ጊዜ) አንለይም፤
ምክንያቱም የነፋስና የንጉሥ ፈጽሞ መለወጥ ሲመጣ፥
የቀድሞው ነገር ሁሉ (አብሮ) ይለወጣል (*መጽሐፈ ፈላስፋ*)።
በጸሎታችን ጊዜ እንዲህ እንበል፥
"ይቅርታህና ምሕረትህ ቶሎ ይድረሱለት።"
ደግሞ ሁላችንም ልመና እናቅርብ፥
ሁሉን ወደሚይዝ ወደ እግዚአብሔር ወደ አምላካችን፥
እኩሌች አድርጎ እንዲያሲዘው፥
ሁለቱን በትሮች፥ ገመድንና ውበትን (*ዘካርያስ*)[8] ።
እንደ ሕርቃኖስም እንዲፈርድ(*መጽሐፈ ፈላስፋ*)፥
በመጽሐፍና በሰይፍ በአንድነት ለዘለዓለም፥ ይሁን።

---

6. ኢሳይያስ 2፡ 4።
7. ምንጭ፥ ኢሳይያስ 9፡ 6፤ *መጽሐፈ ቅዳሴ በግዕዝና በአማርኛ*፥ አዲስ አበባ ፲፱፻፺፩ ዓመተ ምሕረት፥ ገ. 53፡ 45፥ "ዘሥልጣኑ ዲበ መትከፍቱ" ("ሥልጣኑ በትከሻው ላይ ነው") የሚለውን ሲያመለክት ነው። ራስ ሚካኤል የሰሜን ኢትዮጵያ (ከሞፈር ውሐ እስከ መረብ) ንጉሥ ሲሆኑ የማኅተማቸው "መፈክር" አድርገውት ነበር፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፥ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፥ ፭ኛ መጽሐፍ፥ አዲስ አበባ ፲፱፻፷፭ ዓ.ም፥ ገ. 35።
8. ዘካርያስ 11፡ 7። "ገመድና ውበት" "ቅጣትና ትክክለኛ ፍርድ" ናቸው።

መዝሙር 20ንም እንመልከት (ከቅጠል 26ለ እስከ 27ሀ)፤

እግዚኦ በኃይልከ ፍጹመ ይትፌሣሕ፥
**ሠርፀ ድንግል መሲሕ ወልደ መሲሕ፥**
ዘይዴቅም ቃሎ በፍትሕ፥
ወይትኃሠይ በረድኤትከ ብዙኅ፤
እስመ በጸሕኮ በበረከት ጽዱቅ::
ወአንበርከ በርእሱ አክሊለ መዊእ ዘያንፀበርቅ፥
ዘክቡር እምጌራ ወርቅ፥
እስከ ፈርህዎ ዘአዜብ ወሠርቅ፥
ወእለሂ ውስተ ባሕር ርኑቅ::
መካሕ ውእቱ ጊዜ ፀብእ::
ወአልቦ አመ ተመውኦ፤ እስመ ልማዱ መዊእ::
ወልድ ጠቢብ ዘልቡ ዲበ የማኑ፤
ወወሬዛ ማእምር ዘውስተ ርእሱ ዓይኑ (መክብብ)::
ሶበኒ ይመውእ ኢይዜኃር በኃይሉ፤
ወኢይትናገር ትዕይርተ በቃሉ::
ወብዙኃን ነገሥተ አግብአ መትሕተ እዱ::
ወአስተጋብኦሙ ለኮሎሙ ፀር ውስተ ማዕዱ (መሳፍንት)::
አክርስቶስ ዕቀባ ለዘመኑ፤ ወስምያ ሥህልተ (ሆሴዕ)::
ወአርኀቅ እምኔሃ መንሱተ::
ወስምዮሙ ለሠራዊቱ ሕዝብየ ሊተ::
ወኢታኅጥኦ ዘሐለየ ተምኔተ፤
እስመ ኪያከ እማዕምቀ ልቡ ይጼወን፤
ወበእምከ ይትመሐፀን::
ትርክቦሙ እዴከ ለፀሩ ወጸላእቱ፤
ወትብልዮሙ ለመዓትከ እሳቱ፤
ለኮሎሙ እለ ይትቃወምዎ ሎቱ::

❖

አቤቱ በኃይልህ በፍጹም ይደሰት፥
**መሲሕ ሠርፀ ድንግል የመሲሕ ልጅ፥**
ነገሩን በፍርድ የሚፈጽም፥
በብዙው እርዳታህም የሚደሰት፤
በእውነተኛ በረከት ደርሰህለታልና::
በራሱም ላይ የሚያንፀባርቅ የድል አክሊል አስቀምጠሃል፥
ከወርቅ አክሊል የከበረ፥
የደቡብና የምሥራቅ (ሕዝቦች) እስኪፈሩት፥
በሩቁ ምዕራብ ያሉትም::
በጦርነት ጊዜ ጀግና ነው::

**የተሸነፈበት ጊዜ የለም፤ ልማዱ ማሸነፍ ነውና።**
**ልቡ ከቀኝ (እጁ) ላይ የሆነ ጥበበኛ ልጅ ነው፤**
**ዓይኑ በራሱ ውስጥ የሆነ ዐዋቂ ጎልማሳም ነው (*መክብብ*)[9]።**
**ሲያሸንፍም በኃይሉ አይታበይም፤**
**በቃሉ ንቀትም አይናገርም።**
**ብዙ ንጉሦችን በእጁ ስር አስገባ።**
**ጠላቶችን ሁሉ ከማዕዱ ሰበሰባቸው (*መሳፍንት*)[10]።**
**ክርስቶስ ሆይ፥ ዘመኑን ጠብቃት፤ "ይቅርታ የሰፈነባት" በላት (*ሆሴዕ*)[11]።**
**ጥፋትን ከሷ አርቅ።**
**ሠራዊቱን "የኔ ሕዝብ ናቸው" በላቸው።**
**ያሰበውን ምኞት አታሳጣው፤**
**በጥልቅ ልቡ አንተን ተጠግቷልና፤**
**በእናትህም ተማፅኗል።**
**ጠላቶቹንና የሚጠሉትን እጅህ ታግኛቸው፤**
**የቁጣህ እሳትም ትብላቸው፤**
**እሱን የሚቃወሙትን ሁሉ።**

**<u>በመጨረሻም</u>፥ አባ ባሕርይ "ንኡስ አነ" እያለ ዳዊት ስለራሱ የሚናገርበት የመዝሙር 151 አምሳያ መዝሙራቸው ውስጥ ስለራሳቸው ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ (ቅጠል 137ሀ)፤**

***ንኡስ አነ እምካህናት፥***
***ረድኦሙ ለመነኮሳት፥***
***ዘደብረ ማርያም ምኔት።***
***ነበብኩ ድርሳነ መዝሙር፥***
***ምስለ ጎልቄ ቃለ ዳዊት ዘየንብር።***
***አዘታነብብ መጽሐፍየ፥***
***በእንተ ጎሠሙ ኢትጌገሥ ሐምዮትየ።***
***አስተስሪ ሊተ ባሕቱ፥***
***ተዘኪረከ ስራሕየ በጎልቆቱ፤***
***እስመ ሶበ ይመልእ ቃል፥***
***ኮነ የሐፅፅ ብየ ጎልቄ ፈደል።***
***ወቦ ጊዜ አመ ይበዝኅ እምቃል።***
***ወአስተዓረይኩ በብዙኅ ጻማ ወገድል፥***
***በመዋዕለ ሠርፀ ድንግል፥***
***አመ ቀተሉ ለፀሩ መሐመድ ንጉሠ አደል።***

9. መክብብ 2፡ 14።
10. መሳፍንት 1፡ 7።
11. ሆሴዕ 2፡ 1-3።

*እንከሰኬ እበል፥*
*ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘእምኔሁ ክሂል።*

❖

ከካህናት ትንሹ ነኝ፥
የመነኮሳቱ ደቀ መዝሙር፥
የደብረ ማርያም ገዳም።
ድርሳነ መዝሙርን (እነሆ) ደረስኩ፥
ከዳዊት ቃል ቍጥር ጋራ የሚተባበር።
መጽሐፌን የምታነብ ሆይ፥
ስለ መጥፎነቱ ልትነቅፈኝ አትቸኩል።
ይቅርታ አድርግልኝ እንጂ፥
በቈጠራው ድካሜን አስታውሰህ፤
ምክንያቱም ቃሉ ሲሞላ፥
የፊደሉ ቍጥር ይጐድልብኛል።
ከቃሉ የሚበዛበትም ጊዜ ነበረ።
በብዙ ድካምና ትግል አስተካከልኩት፥
**በሠርፀ ድንግል ዘመን፥**
**ጠላቱን የአደልን ንጉሥ መሐመድን የገደለ ጊዜ።**
እንግዲህስ (እንዲህ) ልበል፥
"ችሎታ ከሱ ለሆነ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።"

አባ ባሕርይ ድርሰታቸውን በፈለጉት መልክ ለማቀነባበር ሲጥሩ የደረሰባቸውን በዚህ በመዝሙር 151 የነገሩንን ችግር በከፊልም ቢሆን ለማስወገድ ምን እንዳደረጉ በመቅድማቸው እንዲህ ሲሉ ነግረውናል (ቅጠል 7ሀ)፤

*ዘአስተሐመምኩሰ ላዕለ ዝንቱ ድርሳን እንዘ አስተጎሪ ቃሳቲሁ ምስለ ቃሉ ለመዝሙረ ዳዊት። ወእንዘ ኢይዌስክ አሐደሂ ኖጎየተ ላዕለ ኖጎየቲሁ ወኢየሐፅፅ ምንተኒ እምኔሆሙ አላ አስተዋሐድክዎሙ በጎኑልቊ ፍጹም። ወለእመ ተረፈ አሐዱ አው ክልኤቱ ኖጎየት እምነ አሐዱ መሥመር እዌስኮ ኀበ ካልእ መሥመር።*

❖

በዚህ ድርሰት ላይ የደከምኩት ቃሎቹን ከመዝሙረ ዳዊት ቃሎች ጋራ ሳስተካክል ነው። በኖጎያቱ (በፊደሎቹ) ላይ አንድ ኖኔ ሳልጨምር፥ ከነሱ አንዳችም ሳላጐድል በፍጹም ቍጥር አመሳስያቸዋለሁ፤ ግን ካንድ መሥመር ላይ አንድ ወይም ሁለት ኖኔዎች ሲተርፉ ከሁለተኛው (ከሚቀጥለው) መሥመር ላይ ጨምሬያቸዋለሁ።

የደራሲው ችግር መንሥኤው፥ ድርሰታቸውን *መዝሙረ ክርስቶስን የመዝሙረ ዳዊት መመዘኛ* (*መለኪያ*) እንዲሆን መወሰናቸው ነው። ሐሳባቸው አንድ ሰው አንድ የተቀዳ ዳዊት ሲያገኝ ወይም ሲያስቀዳ ጉድለት የሌለበት መሆኑን ለማወቅ ቢፈልግ በሳቸው *መዝሙረ ክርስቶስ* እያቋጠረ እንዲያስተያየው ነው። በዚህም ምክንያት በድርሰት መንገዳቸው ሲጓዙ *መዝሙረ ክርስቶስ* እንደ *መዝሙረ ዳዊት* 151 መዝሙር እንዲኖረው፥ የእያንዳንዱ መዝሙር መሥመርና በየመሥመሩ ላይ ያሉት ፊደላት (ኖኅያት) በብዛት የአቻውን የ*መዝሙረ ዳዊት* መዝሙርን እንዲያህሉ እያደረጉ መራመድ ነበረባቸው። ይህ አልበቃ ብሎ፥ ባሳቸው ትልቅ የባሕረ ሐሳብ ዕውቀት በሞላ ድርሰታቸው ውስጥ ያሉትን ኖኅያት አንድ ጊዜ ለዓሥራ ሶስቱ ወሮችና ለዓሥራ ሁለቱ ከዋክብት፥ አንድ ጊዜ ለሰባቱ የሳምንቶቹ ዕለታትና ለሰባቱ ከዋክብት፥ አንድ ጊዜ ለዓመቱ ሰዓታት እያሉ እኩል አካፍለዋቸዋል። በዚህ ጊዜ ምን ነገር እንደተፈጠረ ይንገሯችሁ፤

> *ወተርፉ ፪፻ ወኪ.ያሆሙ ረሰይኩ ሊተ። ወጸሐፍክዎሙ ቅድመ ገጽየ ከመ ኢይርስዕዎሙ። ወሰመ እሉ ሆህያት ሞት። ወእግዚአብሔር ዘርኑቅ እምኔሆሙ ያርኅቅ ሊተ ኪ.ያሆሙ እስከ አሠምሮ።*
>
> ❖
>
> (ኖኅያቱን ሳከፋፍል) ሁለት ተረፉ፤ እነሱን ለራሴ አደረግኋቸው። እንዳልረሳቸውም ከፊት ለፊቴ ጻፍኳቸው። የነዚያ (የሁለቱ) ኖኅያት ስም "ሞት" ነው። ከነሱ ሩቅ የሆነ እግዚአብሔር እስከ አስደስተው ድረስ ከኔ ያርቃቸው።

ለድርሰት የሚሆኑትን ጥልቅ የጸሐፊነት ሐሳቦቻቸውን ከማውጠንጠን አልፈው ለፊደሎቹ በቍጥር መመጣጠንና ለክፍያው እኩል መዳረስ ሲጨነቁ ጠቃሚ ጊዜያቸውን እንዴት እንዳጠፉ መገመት ይቻላል። የፊደሎቹን ብዛትስ አንድ ባንድ ቈጥረው ይድረሱበት፤ ግን ያንን ቍጥር በዓመቱ ሰዓቶች ለማካፈል የቻሉት ምን ዘዴ ተጠቅመው ነበረ? ይህም ሆኖ የድርሰቱ ሰተት ብሎ መሄድ ልብ ይማርካል።

ከዚህ ከመዝሙር 151 የምናገኛቸው ዋና ዋና የታሪክ መረጃዎች ግን ሁለት ናቸው -- (1) አባ ባሕርይ የደብረ ማርያም[12] ካህን (መነኮሴ)

12. ቸሩሊ *የመዝሙረ ክርስቶስ* እና *የዜናሁ ለጋላ* ደራሲ አንድ ሰው መሆኑን ባለመገንዘብ ደብረ ማርያምን በትግራይና በጣና ደሴቶች ፈልጎ አጣት፤ Cerulli, "The 'Kalila wa-Dimnah'," n. 4, p. 77-8. ሃመርሽሚትም ያንኑ ይዞ በመሄድ ስለ ጣና ደብረ ማርያም ሲጽፍ "ምናልባት አንድ የዚችኛዋ ደብረ ማርያም መነኮሴ ይሆናል *መዝሙረ ክርስቶስን* በአፄ ሠርፀ ድንግል የግዛት ዘመን (1563-97 ዓ. እ.) የደረሰ" ይላል፤ Hammerschmidt, *Äthiopische Handschriften vom Tānāsee1*, p. 60.

እንደነበሩና (2) *መዝሙረ ክርስቶሰን* የደረሱበት ዘመን በአፄ ሠርፀ ድንግል ጊዜ እንደሆነ::

ንጉሥ መሐመድ የሞተው 1569 ዓ. ም. ነው (ሙሉ ስሙ መሐመድ ኢብን ናሲር ኢብን ኡስማን ኢብን በድላይ መሆኑን ቸሩሊ ነግሮናል[13]:: ድርሰቱን አርመው አስተካክለው የቀዱበትን ዘመን ደግሞ በመቅድሙ ውስጥ በዚያ ጊዜ በሚሠራባቸው የዘመን መቁጠሪያ ዘዴዎች ሁሉ አቀነባብረው ጽፈውታል (ቅጠል 12ለ)፤

> *ተፈጸመ ጽሕፈተ ዝንቱ መጽሐፍ አመ፲ወ፬ ዓመተ መንግሥቱ ለመፍቀሬ እግዚአብሔር ንጉሥነ ....፥ በ፳፻ወ፳፬ እምዓመተ ዓለም፥ ወበ፲፻ወ፰፻ወ፯ ወ፱ እም ዓመተ እስክንድር መቄዶናዊ፥ ወእምዓመተ ሰማዕታት በ፲፻ወ፪፻ወ፰ ዓመት፥ ወበ፲፬ወ፯ እምዓመተ አጋር:: ወአሜሃ ፸፯ ዓመት እምልደቱ ለበዓለ መጽሐፍ፤ ይመሐሮ እግዚአብሔር፥ ወይሠሀሎ፤ አሜን::*



> የዚህ መጽሐፍ ጽሕፈት በእግዚአብሔር ወዳጅ በንጉሣችን በ ...19ነኛ ዓመተ መንግሥቱ፥ በ7074 ዓመተ ዓለም፥ በ1893 ዓመተ እስክንድር መቄዶናዊ፥ በ1298 ዓመተ ሰማዕት፥ በ990 ዓመተ አጋር (ሒጅራ) ተፈጸመ:: በዚያን ጊዜ የመጽሐፉ ባለቤት ዕድሜው 46 ዓመት ነበረ:: እግዚአብሔር ይማረው፥ ይቅር ይበለው፤ አሜን[14]::

አባ ባሕርይ የተወለዱት በግራኝ ዘመን በ1528 ዓ. ም. መሆኑ ነው[15]::

አባ ባሕርይ ለሥራቸው በይቅርታ ፈላጊነት ጠባያቸው፥ "*መዝሙረ ዳዊትን* የጻፍኩት በራሴ ቃል ሳይሆን ከመጻሕፍት እያመጣሁ ነው" ይሉና የጠቀሱላቸውን ዘጠና አንድ ዋቢ መጻሕፍት እመቅድማቸው ውስጥ ይዘረዝሩልናል:: እያንዳንዱንም መጽሐፍ ስንት ጊዜ እንደጠቀሱት እዚያው እመቅድማቸው ውስጥ ከነገሩን በኋላ እድርሰታቸው ውስጥ በጠቀሱት ቍጥር ግራ ጎዳግ ላይ ይጠቁሙታል:: ሌሎች ጸሐፊዎችም ምንጫቸውን ከጎዳግ ላይ ሲጠቁሙ ስላየሁ ሥርዓቱ በሀገራችን የተለመደ መሆን አለበት:: የሚያስገርመው የግዕዝን ሥነ ጽሑፍ እንዳለ ማወቃቸው ብቻ ሳይሆን የቱን ሐሳብ ከየትኛው ምንጭ እንዳገኙት ማስታወሳቸው ነው:: ከዘረዘሩልን መጻሕፍት ውስጥ *ራእየ ኤልያስ* እና *ከሊላ ወድምና*

13. Cerulli, "Documenti arabi per la Storia dell'Etiopia," p. 60, nn. 8 and 9.
14. ፮ እና ፯ ስለሚያሳስቱ የደራሲውን እድሜ ከ47 ይልቅ 46 ብዬ ያነበብኩት አጻጻፉን በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት ከብዙ ፸፮ እና ፸፯ ጋራ ካስተያየሁት በኋላ ነው::
15. እነዚህ የተለያዩ የዘመን ቁጠራ ስልቶች እንዴት እንደሚተረጐሙ ለማወቅ *ባሕረ ሐሳብን* ተመልከት::

በግዕዝ መኖራቸው እስካሁን አይታወቅም። እርግጥ የ*ክሊላ ወድምና* ፈለግ ተገኝቷል።[16]

### (2) *"አጭሩ መዝሙረ ክርስቶስ"*

የዚህ ድርሰት ግጥሞች እያንዳንዳቸው ባለአምስት መሥመር ብቻ ሆነው ብዛታቸው ድርሰቱ ተከትሎት እንደሚሄደው እንደመዝሙረ ዳዊት መዝሙሮች 151 ነው። ደራሲው ይህንንም *መዝሙረ ክርስቶስ* ይሉታል፤ (ቅጠል 149ለ)

*በዝንቱ ተፈጸመ ክፍል ኃምስ፥*
*ዘምሳሌሁ ገሲስ፥*
*እንዘ እሰምዮ ለስሙ መዝሙረ ክርስቶስ።*
*ፍዳ አስተሐመምኩ በእንቲአከ ተርጉሞ መዝሙር ቅዱስ፥*
*ሀበኒ አስበ ዘሥጋ ወነፍስ።*

❖

አምስተኛው ክፍል በዚህ አለቀ፥
ምሳሌው መዳሰስ የሆነ[17]፥
ስሙን *መዝሙረ ክርስቶስ* እያልኩት።
ስላንተ ቅዱስ መዝሙሩን በመተርጉም ስለደከምኩ፥
የሥጋና የነፍስ ዋጋ ስጠኝ።

ለድርሰቱ የሚስማማው ለኛም የሚመቸው ስም "ውዳሴ ክርስቶስ" ነበር። ባይሆን ሁለቱ ድርሰቶች በስም እንዳይጋጩ "ረጂሙ" እና "አጭሩ" በሚሉ ቅጽሎች እየለየን ሁለቱን መዝሙረ ክርስቶሶች በዚያው "ወላጃቸው" በሰጣቸው ስም መጥራት ይኖርብናል።

ይህ ድርሰት ደራሲው ሳይታወቅ ተደጋግሞ ተቀድቷል፤ ከ*መዝሙረ ዳዊት* ጋራም ታትሟል[18]። እድርሰቱ ውስጥ አባ ባሕርይን

16. ቸሩሊ ከላይ በቁጥር 12 ስር የተጠቀሰውን "The 'Kalila wa-Dimnah'" የሚለውን ምርምራዊ ጽሑፍ ያዘጋጀው የ*መዝሙረ ክርስቶስ* ደራሲ *ክሊላ ወድምናን* በግዕዝ አላነበበውም፤ እንዲያውም መጽሐፉ ወደ ግዕዝ መተርጐሙ ያጠራጥራል ለማለት ነው። *ክሊላ ወድምናን* እውነትም እስካሁን የግዕዝ ትርጉሙን አላገኘነውም፤ ግን አባ ባሕርይ አልዋሹም፤ ተተርጉሞ እንደነበረ አሁን ማስረጃ ተገኝቷል፤ Getatchew Haile, "The Kalīlah wa-Dimnah," pp. 373-386.

17. ምንጫቸውን የቅዱስ አትናቴዎስን *ትርጓሜ ዳዊት* አድርገው፥ በአምስቱ ሕዋሳት ቁጥር ("ርእይ"፥ "ማየት"፤ "ሰሚዕ"፥ "መስማት"፤ "አጼንም"፥ "ማሽተት"፤ "ጣዕም"፥ በቁሙ፤ "ገሲስ"፥ "መዳሰስ") ከአምስት ከፍለውታል።

18. ለምሳሌ EMML 3996, Getatchew Haile, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. IX, p. 281; Cod. aeth. 46, Six, *Äthiopische Handschriften 2*,

የሚመለከት አጥጋቢ ማስረጃ ለማግኘት ባለመቻሌ የሳቸው ለመሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም። በዚያ ላይ፥ "ድርሰቱ እርግጥ የአባ ባሕርይ ከሆነ፥ የሚያደንቁትን የአፄ ሠርፀ ድንግልን ስም በውስጡ ለምን አንድ ቦታ እንኳን አላነሡትም?" የሚልም ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ ከተነሣ መልሱ ምናልባት መዝሙር 151 ("በእንተ ርእሱ") ውስጥ ይገኝ ይሆናል (ቅጠል 149ለ)፤

*አመ አስተዋደድኩ ዘንተ መዝሙረከ ዘይሜለስ በበሃምሳ፥*
*ንኡስ አነ ወልደ ዓመታት መንፈቀ ሃምሳ።*
*እንዘ ትከድነኒ ክርስቶስ ሞገሰ ጸራቅሊጦስ በዓለ ሃምሳ፥*
*ነፍስየ አዕቢ ከመ አብድዩ ሊቀ ሐራ አካዓብ ሃምሳ።*
*በመዋዕለ ተድላ ሀበኒ ካዕበቶ ለሃምሳ።*

❖

ይኸንን በሃምሳ የሚሠለስ (3 ጊዜ 50) መዝሙርህን ያገጣጠምኩ ጊዜ፥
የአምሳ ዓመት ግማሽ ትንሽ ልጅ ነበርኩ።
ክርስቶስ (ሆይ)፥ በበዓለ ሃምሳ ጸራቅሊጦስ ሞገስ አልብሰኸኝ፥
ነፍሴን ከፍ ከፍ አድርጋት፥ እንደአካዓብ የጦር አለቃ አብድዩ አምሳን እጠፍ።[19]
በተድላ ዘመን የሃምሳን እጥፍ (እድሜ) ሰጠኝ።

ከላይ እንደገመትነው፥ አባ ባሕርይ የተወለዱት በ1528 ዓ. ም. ከሆነና ይኸንን *ሰጭሩ መዝሙረ ክርስቶስን* ሲደርሱ እድሜያቸው "የሃምሳ ግማሽ" (25 ዓመት) ከሆነ የደረሱበት ዘመኑ (1553 ዓ. ም.) ገና የአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን አልነበረም።

ይኸን ድርሰት የአባ ባሕርይ ሊያደርገው የሚችለው ሌላው ማስረጃ ከቅጠል 7ሀ እስከ 12ለ ድረስ ያለው መቅድማቸው የሚመለከተው ሁለቱንም መዝሙሮች መስሎኝ ነበር። ግን ሁለቱ የተደረሱበት ዘመን ስለማይቀራረብ ለማስረጃነት ሊጠቀስ አይችልም።

---

pp. 79-80; *መዝሙረ ዳዊት ምስለ መዝሙረ ክርስቶስ*፡ ሚስቴር አሬን አለቃ ታየ ደረሱት የሚለው *መዝሙረ ክርስቶስ* ይኸንን ቢመስልም ሌላ ድርሰት ነው።

19. ደራሲው የሞከሩት "አከዓብ"ን "አክዓብ" (እጥፍ አደረገ") ከሚል ግሥ አውጥተው በጎብር ለመናገር ነው። ምንጫቸውም ነገሥት ቀዳማዊ 18፡ 3-4፥ "አክዓብም የቤቱን አዛዥ አብድዩን ጠራ፤ አብድዩ እግዚአብሔርን እጅግ ይፈራ ነበር። ኤልዛቤልም የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደለች ጊዜ እርሱ መቶውን ነቢያት ወስዶ አምሳ አምሳውን በዋሻ ውስጥ ሸሽጎ እንጀራና ውሐ ይመግባቸው ነበረ" የሚለው ነው። ግን ግሡ በዚህ መልኩ በግዕዝ ቢኖርም ወይም እሳቸው ቢፈጥሩት "አክዐበ" ("አጠፈ") ወይም "አክዕብ" ("እጠፍ") መሆን ነበረበት፤ የቀጅ ስሕተት ሊኾን ይችላል።

### (3) *መልክዐ ገብርኤል*

የዚህ ድርሰት ደራሲ አባ ባሕርይ መሆናቸውን ለማስረዳት ብዙ ርቆ መሄድ አያስፈልግም፤ ድርሰቱ ቅጠል 150ሀ ላይ የሚጀምረው፥ ድርሳነ መልክዑ ለገብርኤል ***ዘባሕርይ*** (“**የባሕርይ** መልክዓ ገብርኤል ድርሰት”) በሚል ነው። የሰላምታ ግጥሞቹ በዚህ ይጀምራሉ፤

*ሰላም ለዝክረ ስምከ በመጽሐፈ ዳንኤል ዘተጠየቀ፤*
*እስመ ወርኃ ብስራት ቀርበ ወዘመነ ወንጌል አልጸቀ፥*
*ገብርኤል ዘኮንከ ለመገብተ ሐዲስ ሊቀ፥*
*ናሁ ወጠንኩ እግዚኦ ከመ እወድስከ ሕቀ፤*
*ሞገሰ ጸራቅሊጦስ ጸግወኒ ዘይፈጽም ጻሕቀ።*

❖

በመጽሐፈ ዳንኤል ለታወቀው ስምህ[20] መታሰቢያ ሰላም፤
“የብሥራት ወር ቀርቧል፥ የወንጌልም ዘመን ደርሷል”(ብለህ)፥
ለሐዲስ (ኪዳን) ባለሥልጣኖች ሊቅ የሆንክ ገብርኤል ነህ[21]።
ጌታ ሆይ፥ በጥቂቱ ላመሰግንህ እነሆ ጀመርኩ፤
ምኞትን ከመጨረሻ የሚያደርስ የጻራቅሊጦስን ሞገስ ስጠኝ።

ደራሲው ብዙ ላበሠረች ለመልአኩ መላስ ሰላምታ ከሰጡ ከኋላ ልመናቸው ያው ያችኑ ጥቅሚንና ምስጢሯን ተማሪ የሚያውቀውን ነው፤

*ጸግወኒ ርእሰ ሀብታት እንተ ይእቲ አእምሮ፤*
*ምስለ አግዓዚ እግዚእ ዘታሜሪ ገብሮ።*

❖

ዕውቀትን ስጠኝ የሀብቶች ራስ የሆነችውን፤
ከነዛ ጌታ ጋራ እኩል የምታደርግ ባሪያውን።

መንፈሳዊ ድርሰቶች በየቦታው እየተደጋገሙ ሲቀዱ ይህንን ድርሰት ብቻ ከሌላ ቦታ ተቀድቶ አላየሁትም።

### (4) *ሰላመ ቅዱሳን*

በዚህ መጽሐፍ (በOr. 534) ውስጥ አብረው ከተቀዱት ድርሰቶች የመጨረሻው *“ሰላመ ቅዱሳን ሕዝብ፥ ወእማኔ ኦሶሎሙ ሰማዕት ለባሲያነ መስቀል ዘዓርብ”* (“የቅዱሶች ሕዝብ ሰላምታና የዓርብ መስቀል ለባሾች

20. ምንጭ ዳንኤል 8፡ 16፤ 8፡ 21።
21. “ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ” (ሉቃስ 1፡ 31) ብሎ ለቅድስት ማርያም ማብሠሩንና በዚህም ሐዲስ ኪዳን መጀመሩን ለማመልከት ነው።

ሰማዕታት ሁሉ እጅ አነሣሥ") በሚል ርእስ የሚጀምረው ነው። ድርሰቱ **የአርከ ሥሉስ** ድርሰትን ስልት ይከተላል።

ስለ አርከ ሥሉስ ድርሰት የማያውቅ ካለ፥ አርከ ሥሉስ የሚባል ደራሲ ስንክሳሩን ይዞ ከመስከረም አንድ እስከ ጳጉሜን ስድስት ገድላቸው በወሩ ውስጥ በዕለተ ዕረፍታቸው ለተመዘገበው ቅዱሳንና ሰማዕታት ሁሉ ስማቸውን እየጠራ "ሰላም" ብሎ የሚጀምር የግጥም ሰላምታ ደርሶላቸዋል። እነዚህ ግጥሞች ተሰብስበው ለብቻቸው እንዳንድ መጽሐፍና በስንክሳሩም ውስጥ ለየገድሉ ዘገባ መደምደሚያ (ዘርፍ) እየሆኑ በየቦታቸው እየተሰገሰጉ ተጽፈው ይገኛሉ። ይህ ባለ አምስት መሥመር የሰላምታ ስብስብ ርእሱ *"መዝሙረ ፍሥሓን ወጸሎተ ትኩዛን* "(የደስተኞች መዝሙርና የሐዘንተኞች ጸሎት) ሆኖ ሳለ የግጥሙ ስልትና ግጥሞቹም በደራሲያቸው አጭር ስም "አርኬ" እየተባሉ ይጠራሉ[22]።

አባ ባሕርይም ልክ አርከ ሥሉስ እንዳደረገው፥ ስንክሳሩን ይዘው በውስጡ ከመስከረም አንድ እስከ ጳጉሜን ስድስት ገድላቸው ለተመዘገበው ቅዱሳንና ሰማዕታት ለጥቂቶቹ ለብቻቸው፥ ለሌሎቹ ደግሞ የጋራ ባለአምስት መሥመር ሰላምታ ገጥመውላቸዋል። ድርሰቱ የሳቸው ለመሆኑና አርከ ሥሉስን ለመከተላቸው የድርሰታቸው አፍአዊ መልክ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ማስረጃም አለበት። የየካቲቱን ወር ድርሰታቸውን እንዲህ ሲሉ ይደመድሙታል (ቅጠል168ለ)፤

*ለዘብዙኃ አመገብዎ ይትኃሠሥዎ አምጣነ ኮነ፥*
*እምነ ብዙኅ ብዕሉ ከመ አቅረበ **አርክሥ**፥*
*አምኃ ንዴት ንስቲተ ዘአቅረብከ ለነ፥*
*ጻድቃነ የካቲት በሉኒ ተወከፍነ፥ ተፈሣሕ፥ **ባሕርይን**፥*
*እስመ አንተ ኮንከ በውሑድ ምእመን።*

❖

ብዙ ካሠለጠኑት በዚያው ልክ ይፈለግበታል፤
**"ወዳጄችን** ከብዙው ሀብቱ እንዳቀረበ፥
ያቀረብክልንን የደኻነት ትንሽ ገጸ በረከት፥"
የየካቲት ጻድቃን፥ "ተቀብለናል፥ ደስ ይበልህ፥ **ባሕርያችን** ሆይ" በሉኝ፤
"በጥቂቱ የታመንክ ሆነሃልና።" [23]

---

22. ምዕራባውያን *Encomium caelestium et terrestium* ይሉታል፤ ደራሲው እርግጥ አርከ ሥሉስ መሆኑ ነው፤ እኔ ግን እየተጠራጠርኩ ድርሰቱን ከሁለት ቦታ ተችቸው ነበር፤ Getatchew Haile, *The Different Collections of Nägś Hymns*, pp. 16 and 72 እና EMML 2706, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. VII, pp. 100-7.
23. ምንጭ ማቴዎስ 25፡ 23፡ "መልካም አንተ በጎ ታማኝ አገልጋይ በጥቂቱ ታምነሃል።"

"**ወዳጃችን**" እና "**ባሕርያችን**" ብዬ የተረጐምኳቸው "**አርክነ**" እና "**ባሕርይነ**" በግዕዙ ጎብር ናቸው። ግዕዙ ለአማርኛው አይፈቅድለትም እንጂ፥ "የኛ አርከ (ሥሉስ)" እና "የኛ (አባ) ባሕርይ" ብዬ ብተረጓማቸው ምስጢሩ የሚያመለክተው ሁለቱን ደራሲዎች መሆኑ በይበልጥ ግልጽ ይሆን ነበረ።

ይህ ጥቅስ ያስተማረን ሌላው ጠቃሚ ትምህርት አርከ ሥሉስ ከአባ ባሕርይ በፊት እንደኖረ እና፥ በችሎታ ይሁን ወይም በሀብት አይታወቅ እንጂ፥ ከእሳቸው ይልቅ እሱ እንደሚበልጥ ነው። ሆኖም አርከ ሥሉስን ከራሳቸው አብልጠው መናገራቸው የአባ ባሕርይ የትሕትና አነጋገር ሊሆንም ይችላል።

አባ ባሕርይ ይኸንን ድርሰት ደርሰው ሲጨርሱ መቸ እንደደረሱት በዚያው የግጥም ስልት እንዲህ ሲሉ ነግረውናል (ቅጠል 184ሀ)፤

*እምገድለ ቅዱሳን ብዙኃን አስተጋብኡ ጸሐፍተ ስንክሳር ትካት፥*
*በታሰዕ ያወጀ ዓመተ ቡሩካን ሰማዕት።*
*ወእምድኅረ ዓሥር ያወሠላሳ ምእት፥*
*እምአቅማሐ ዝኩ ስንክሳር ቀሰምኩ በበ ንስቲት፥*
*እስመ ለዘመንየ ኢሥህልት ቀንየ ሀኬት።*

❖

ጥንት የስንክሳር ጸሐፊዎች (ስንክሳሩን) ከብዙ ቅዱሳን ገድል፥
በ960 የተባረኩ ሰማዕታት ዓመት ሰበሰቡት።
ከ1300 ዓመት (ዓመተ ሰማዕታት) በኋላ ደግሞ፥
ከዚህ የስንክሳር ምርት በጥቂት በጥቂቱ ቀሰምኩ፤
ምክንያቱም ይቅርታ ያጣች ዘመኔን ብጥብጥ ገዝቷታልና።

ስንክሳሩ በ960 ዓ. ሰ. መደረሱ ልክ ሳይሆን አይቀርም፤ ቅጂዎቹ ግን ብዙ ባይራራቅም የተለያየ ቀን ይሰጣሉ[24] አባ ባሕርይ ያንኑ አያይዘው የነገሩን እርሳቸው ይህንን ድርሰታቸውን የደረሱበት ዘመን (1300 ዓ. ሰ.) 1576 ዓ. ም. መሆኑን ነው።

አባ ባሕርይ በዘጠኙ ለጋላ ድርሰታቸው ውስጥ አንዱን ሳያውቁት አንዱን ዐውቀውት ሁለት ትንቢት ተናግረው ነበረ። ዐውቀው የተናገሩት ትንቢት በሕይወት እያሉ እንደተፈጸመ ነግረውናል (ክፍል ፪ን ተመልከት)። ሁለተኛው ትንቢት ሳያውቁ የተናገሩትና በሕይወታቸው እያሉ የማይፈጸመው "*ለእመ ሞትኩ ካልኦን ይጽሕፉ ዜናየ*" (ከሞትኩ ሌሎች ታሪኬን ይጽፉታል) ያሉት ነው። ለዚያ ትንቢት መፈጸሚያ

24. Wallis Budge, *The Book of the Saints of the Ethiopian Church*, pp. xv-xvi.

የመጀመሪያው ስለሆንኩና እነዚህን መሥመሮች ስለጻፍኩላቸው ራሴን እንደ ዕድለኛ እየቈጠርኩ፥ አባ ባሕርይ ያረፈ ወዳጃቸውን ሲያነሡ "ላዕሌሁ ሰላም" እንደሚሉት "ሰላም ይረፍባቸው" እያልኩና ቡራኬያቸውን እየለመንኩ ለጊዜው እሰናበታቸዋለሁ::

# ምዕራፍ ፪

## *ዜናሁ ለጋላ*

*ልሳኑ ለብእሲ መድሎተ ልቡና ውእቱ፤*
*ለእመ ምሉእ ወሕዑዕ ዘይትዐወቅ ቦቱ::*

❖

**መላስ ነው ልቦና የሚመዘንበት፤**
**ሙሉ እንደሁ ጕደሌ የሚታወቅበት::**

**አባ ባሕርይ**

**የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ሰድስተኛው ክፍለ ዘመን በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለኦሮሞዎች በሰፊው የጻፉ ክቡር አቶ ይልማ ደራሳ::**

(© copyright 2002 by Shimbera Kure Archives)

# መግቢያ

*ዜናሁ ለጋላ* (“የጋላ ዜና”) የሚባለውን አባ ባሕርይ የጻፉትን የኦሮሞ አጭር ዜና ሌሎች ካንዴም ሁለቴ አጥንተው አሳትመውታል። አሁን እኔ በኋላ መጥቼ እንደገና ለማጥናትና ለማሳተም ያሰብኩበት ዋናው ምክንያት ካሁን በፊት የተደረጉት ጥናቶች ለአማርኛ አንባቢዎች በቋንቋቸው ተተርጉመው በጎትመት በሰፊው እንዳልተሰራጩ፥ ድርሰቱ የታሪክ ምንጭ ከሆነም ጥሬ ትርጉም ብቻውን እንደማይበቃ በማየቴ ነው።

*ዜናሁ ለጋላን* ለመጀመሪያ ጊዜ ከአርባ ዓመት በፊት ካነበብኩት ጀምሮ እንደ ኢትዮጵያዊ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ክፍል እንጂ የአንድ ጎሳ ታሪክ አድርጌ ስላላየሁት ይሽንን ድርሰት መነሻ በማድረግ ወይም በሌላ ምክንያት በኦሮሞ ታሪክ ላይ የተለየ ወይም ሌሎች ባደረጉት ላይ ተጨማሪ ጥናት አላደረግሁም። ጎሳዎችንና ነገዶችን ነጥሎ ማጥናት የኔ ሳይሆን ከፋም ለማም ጎብረተሰባዊ መዋቅሮችንና ባህሎችን የሚመረምሩ የአንትሮፖሎጂስቶች መስክ ነው። ለኔ የኢትዮጵያ ታሪክ ያንድ ሀገር፥ ያንድ ሕዝብ፥ ያንድ መንግሥት አንድ ታሪክ እንጂ የየጎሳው ወይም “የየክልሉ” ታሪክ ጥርቅም ሆኖ አይታየኝም።

የአባ ባሕርይ ድርሰትም ቢሆን እኮ ከታሪክነቱ ላይ አተኮርን እንጂ ታሪክ ሊባል የሚገባው ከጠቅላላው ጥናታቸው ውስጥ አንድ ክፍል ብቻ ነው፤ ሌላው፥ ደራሲውም ስለኦሮሞዎች ለመጻፍ ምን እንዳሰኛቸው ገና ድርሰታቸውን ሲጀምሩ፥ “**የነገዱን ቁጥር፥ ሰውን ለመግደል የትጋቱን ነገር፥ የጠባዩን እንስሳነት ለማወቅ ነው**” ብለው መሆኑን እንደነገሩን፥ አንትሮፖሎጂ ነው። “**እንግዲህ እስከዚች ሰዓት ድረስ ወደተውነው ወደበረይቱማ ዜና እንመለስ**” በማለት ክፍል ፱ን አቁመው ያስከተሉት ክፍል ፲ እና “**እንግዲህ ወደ ጋላው ዜና እንመለስ**” በማለት የጀመሩት ክፍል ፳ አንዳችም ታሪክ የለባቸውም። በ*ዜናሁ ለጋላ* ውስጥ ታሪክ ቢኖርበት ስለ ኦሮሞዎች ምርምራዊ ጥናት ሲጻፍ ሊታለፍ የማይገባ ሆኖ የተገኘው ነው።

የኦሮሞ ታሪክማ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ታሪክ በታሪክ ነገሥቱ ውስጥ በሰፊው ተጽፏል። ከሰፊው ባሕር አንድ ሁለት ምሳሌ ለመጨለፍ ያህል፥ አፄ ሠርፀ ድንግል በከሓዲው ባሕር ነጋሽ

ይሥሐቅና ስቦ ባመጣቸው ቱርኮች ላይ ዘምቶ ይሥሐቅን ለመቅጣት፥ ቱርኮችን ዛሬ ኤርትራ እተባለችው ክፍለ ሀገር ውስጥ የያዙትን ምድር ለማስለቀቅ በ1571 ዓ. ም. ወደ ሰሜን ሲዘምት ከወታደሮቹ ውስጥ "ብዙ ጋሎች" እንደነበሩ[1]፥ እንደገና ደግሞ በ1583 ዓ. ም. ተመልሶ ሲዘምት የጦር አለቃውን አስቀድሞ የላከው "ከብዙ ጋላ ጋራ" እንደነበረ[2] ፥ ፈላሻዎች በ1579 ዓ. ም. በጉሸን መሪነት ሲያምፁ "በጦር የሰለጠኑ ጋሎች" እንዳዘመተባቸው[3]፥ አፄ ሱስንዮስ ለመንገሥ የቻለው በመ–ለመላቸው የኦሮሞ ወታደሮች ኀይል እንደሆነ[4] የተጻፈው ከታሪክ ነገሥቱ ውስጥ እንጂ አንዱም *ዜናሁ ለጋላ* ውስጥ የለም። *ዜናሁ ለጋላ* ውስጥ ያሉ ታሪክነት ያላቸው መረጃዎች አብዛኞቹ ታሪክ ነገሥቱ ውስጥ ሲኖሩ፥ አባ ባሕርይ *ዜናሁ ለጋላ* ውስጥ ስለኦሮሞ ኀብረተ ሰብ መዋቅርና አስተዳደር የሚገልጹልን ክፍሎችና አንቀጾች እዚያ ብናገኛቸው በቁንጽል ነው። ምክንያቱ ግልጽ ይመስለኛል፤ ይህ ሌላ ያ ሌላ[5]።

"ዜና" ማለት "ታሪክ" ማለት ብቻ አይደለም፤ ትልቁ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ቃሉን ወደ አማርኛ ሲተረጉሙት[6]፥

> በቁሙ፤ ዝና ጨዎታ ወሬ፤ የተባለ የተነገረ ቃል፤ የኾነ የተደረገ ሥራ፤ ሰው ከሰው አፍ ወይም ከመጽሐፍ የሚሰማው የሚቀበለው እንግዳ ነገር፤ ትንቢት ብሥራት ስብከት፤ ደኅንነት፤ መርዶ ወግ ታሪክ ገድል፤ ደብዳቤ መልክት የመሰለው ኹሉ

ይላሉ። "በቁሙ" ማለት በአማርኛም እንደ ግዕዙ ያው "ዜና" ይሆናል ማለት ነው። መዝገበ ቃላቱና የ*ዜናሁ ለጋላ* ይዞት እንደሚመሰክሩት፥ የ*ዜናሁ ለጋላ "ዜና"* ትርጉሙ "ዜና"፥ "ስለ" ማለትም ይሆናል፤ ስለዚህ የድርሰታቸው ርእስ "የጋላ ዜና"፥ ወይም "ስለ ጋላ" ተብሎ ቢተረጐም ደራሲው ሊያስተምሩን የፈለጉት ምን እንደሆነ በትክክል ግልጽ ይሆንልናል።

*ዜናሁ ለጋላ* በግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ተወዳዳሪ የሌለው የአንትሮፖሎጂ ምርምራዊ ድርሰት ነው። ድርሰቱን ያነበበ፥ "የዚህ ጥናት ጸሐፊ (የአባ ባሕርይ) ኢትዮጵያዊነታቸው የማያጠራጥር ከሆነ የ*ሐተታ ዘዘርኣ ያዕቆብ* ደራሲ (የዘርአ ያዕቆብ) ኢትዮጵያዊነት የሚያጠራጥረው በሁለቱ ደራሲዎች መካከል ምን የጐላ ልዩነት ታይቶ ነው?" የሚል

1. Conti Rossini, *Historia Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, p. 67.
2. እዚያው ገ. 129።
3. እዚያው ገ. 104።
4. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 22ff.
5. ክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ ስለኦሮሞ ለመጻፍ አስበው የዓሥራ አምስተኛውን ምእት ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ አብረው የጻፉት በዚሁ ምክንያት ይመስላል፤ ይልማ ዴሬሳ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ*።
6. ኪወክ ገ. 419።

አስቸጋሪ ጥያቄ ያነሣል። የዘመኑ ምሁራን በዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ከተደረሰ ከማንኛውም ሀገር የምርምር ጽሑፍ የሚጠብቁትን ሁሉ *ዜናሁ ለጋላ* ውስጥ አያጡትም። *ዜናሁ ለጋላ "ጋላ"* ስለሚለው ነገድ አስደናቂ መዋቅር እኚህ ሊቅ ባይጽፉት ኖሮ ሳይታወቅ ይቀር ነበር። የአባ ባሕርይን ሌሎች ድርሰቶች ያነበበ በዚህ አይገረምም። ስለዚህ *ዜናሁ ለጋላን* ትልቅ ጥናት፥ ትልቅ ምንጭ፥ ትልቅ ቅርስ ነው ብሎ ራሱን ድርሰቱን ማሳየቱ ይሻላል።

*ዜናሁ ለጋላ* እናቱ መኖር አለመኖሩ አይታወቅም፤ ግን ሳይጠፋ አይቀርም። ድርሰቱ አጭር ስለሆነ አባ ባሕርይ የጻፉት ከመጽሐፎቻቸው ባንዱ በባዶ ቅጠሎቹ ላይ ይሆናል። ቢገኝ ያ መጽሐፍ ሲገኝ ነው። ድርሰቱ እስካሁን በሁለት ሙሉ ቅጅ ተገኝቷል-- አንዱ BL Or. 534 ውስጥ[7] ከሌሎቹ ድርሰቶቻቸው ጋራ ተቀድቶ ሲሆን፥ ሁለተኛው ነምሳ ቪየና በሚገኘው የቪየና ቤተ መንግሥታዊ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ቁጥር Aeth. 4 በተሰጠው *ገድለ ፊቅጦር* ውስጥ[8] በባዶ ገጾቹ ላይ ተቀድቶ ይገኛል። ከመጀመሪያው እስከ ፲፱ኛው ክፍል የመጀመሪያዎቹ መሥመሮች ድረስ የጐደለው ቁጥጽል ቅጂ በርሊን ቤተ መጻሕፍት ውስጥ የመታወቂያ ቁጥር MS. orient. quart. 996 በተሰጠው *የመዝሙረ ክርስቶስ* ሌላ ቅጂ መጨረሻ ላይ ይገኛል[9]፤ ከBL Or. 534 ላይ የተቀዳ ይመስላል።

የሎንዶኑ እና የቪየናው ቅጂዎች (BL Or. 534 እና Aeth. 4) ከፍ ባለ ደረጃ ይመሳሰላሉ፤ ሆኖም አይተዋወቁም። የተመሳሰሉት አንዱ ከሌላው ቢቀዳ ሳይሆን ሁለቱም ካንድ ምንጭ ቢቀዱ ሊሆን ይችላል። ድርሰቱ በተቈጠሩ ክፍሎች ተከፋፍሎ ሳለ፥ ቁጥሮቹን የቪየናው ቅጂ ሲሰጥ የሎንዶኑ አይሰጥም። ቀጂዎች ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት፥ የዚህም ቀጅ በኋላ በቀይ ቀለም ሊሞላው አስቦ ይሆናል ቦታውን ክፍት ትቶታል። አባ ባሕርይ በክፍል ቁጥር እንደከፋፈሉት አያጠራጥርም፤ ድርሰታቸውን መልሰው የሚጠቅሱት የክፍሉን ቁጥር እየሰጡ ነው (ክፍል ፲፪ን እና ፲፭ን ተመልከት)።

እነዚህን ቅጂዎች ለዚህ ጥናት ስጠቅሳቸው የመጀመሪያውን "ሎ" (ሎንዶን)፥ ሁለተኛውን "ቪ" (ቪየና)፥ ሶስተኛውን ካስፈለገ "በ" (በርሊን) እያልኩ ነው።

የሎንዶኑን ቅጂ ሽላይኸር የሚባል ጀርመናዊ አጥንቶ ግዕዙን ከጀርመንኛ ትርጉሙ ጋራ በ1893 ዓ. እ. አሳትሞታል[10]። ሽላይኸር

7. Or. 534, ff. 1a-3a, Wright, *Catalogue of the Ethiopic Manuscripts*, p. 84 (col. 2).
8. Codex vindobonensis Palatinus, Aeth. 4, ff. 1b-2ab, 103a-104a, and 86b-88b, N. Rhodokanakis, "Die äthiopische Handschriften," p. 69.
9. Ms. orient. quart. 996, ff. 164a-165a, Ernst Hammerschmidt und Veronika Six, *Äthiopische Handschriften 1*, p. 221.
10. Schleicher, *Geschichte der Galla ዜናሁ : ለጋላ* ::

ግዕዙን ያሳተመው ከብራናው መጽሐፍ ላይ እንዳገኘው ሳይሆን የሰዋስዉን ሕግ እየተከተለ ቀጂ ያሳሳተው የመሰለውን ቃል ለሱ ትክክል በመሰለው በቃሉ ሌላ መልክ እየለወጠ ነው። የለወጣቸው ቃላት የቶቹ እንደሆኑና ለምንስ እንደለወጣቸው ሁሉንም በዝርዝር ስለማያሳይ እንኳን እናቱ ራሱ የሎንዶኑ ቅጂ ምን እንደሚመስል ከሽላይኽር ጎትመት ለመረዳት አይቻልም። ራሱ ሽላይኽርም ቢሆን "(ሳሳትም) ከግዕዙ ድርሰት ፊደል እንኳን ሳልቀይር በመቅዳት ነው"[11] ማለቱ በማይገባ ነው። ሁለተኛም፥ የመጀመሪያ ጥናት ስለሆነ ዛሬ የማይደረጉ ብዙ ስሕተቶች አድርጓል።

ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ አንድ ጊዜ ለሥራ ጉዳይ ካይሮ ሄደው ሳለ ዶክተር ሙራድ ካሚል የሽላይኽርን መጽሐፍ ያሳያቸዋል። ያንን በእጃቸው ቀድተው በተቈጠሩ አንቀጾች ከፋፍለው ከአማርኛ ትርጉማቸው ጋራ ለማሳተም በ፲፱፱፱ ዓ. ም. *ዜናሁ ለአባ ባሕርይ ዘጸሐፎ በልሳነ ግዕዝ* በሚል ርእስ ያዘጋጁታል[12]። ለምን እንዳላሳተሙት የሚታወቅ ነገር የለም[13]። ቢታተም ኖሮ ግዕዝ ለማያውቁ የታሪክ ተማሪዎች በፈጥኖ ደራሽነት ከፍ ያለ ጥቅም ይሰጥ ነበረ። የሊቁ ብላታ ትርጉም ወደ እንግሊዝኛ ከተተረጐመው ሁሉ ልቀት አለው ቢባል ትርፍ አነጋገር ይሆናል። ጉዳቱ ከሽላይኽር ጎትመት ላይ መሆኑ ነው። የጎዳግ ማብራሪያቸውም በጣም የተመጠነ ነው።

ኤኖ ሊትማን የሚባለው ጀርመናዊ ሊቅ በታወቀው የኢትዮጵያ ዕውቀት ችሎታው በመተማመንና ሽላይኽር ያላየውን የቪየናውን ቅጅ በመያዝ በሽላይኽር ጥናት ላይ ሊታረሙ የሚገባቸውን ስሕተቶች አርሞ፥ ሊታወቁ የሚገባቸውን በሁለቱ ቅጅዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች አሳይቶ፥ በ1938 ዓ. እ. አንድ መጣጥፍ አቀረበ[14]። ጥናቱ ጠቃሚ ሆኖ ሳለ አንባቢ የሽላይኽርን መጽሐፍና የኤኖ ሊትማንን መጣጥፍ ሁል ጊዜ አብረው ስለማያገኛቸው የእርማቱ ጥቅም ተቀንሶ ነበረ።

---

11. "'Den äthiopischen Text habe ich bis auf die Orthographie unverändert viedergegeben..." እዚያው ገ. iv.
12. ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፥ *ዜናሁ ለአባ ባሕርይ ዘጸሐፎ በልሳነ ግዕዝ*፥ EMML 3749.
13. ከሰጡት ርእስ ለመጠርጠር ቢፈቀድ፥ የዘመኑ ሳንሱር አልፈቀደው ይሆናል። የሌላ ሰው እጅ በያዘው እርሳስ "ጋላ" የሚለው ስም ተቀንፏል፥ "ንጉሣችን" የሚለው ቃል እየተፈለገ "ንጉሥ" በሚል ቃል ተለውጧል፥ ሌሎችም አነጋገሮች ተሠምሮባቸዋል። ሳንሱሩን ያስቆጡት እንዲህ እንዲህ ያሉት ከሆኑ ማብረጃ የማይገኝለት ቁጣ ነበር። የብላታ መርስዔ ኀዘን፥ ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴ የበተነው፥ የኔ፥ እነዚህ ሶስቱ ትርጉሞች ብዙ ቦታ ቢመሳሰሉ አያስደንቅም። ትርጉም፥ ከታወቀበት የሚሳብ ጥያቄ የመመለስን ያህል ባይመሳሰልም ሊቀራረብ ይችላል።
14. Littmann, "Zu A. W. Schleicher's 'Geschichte der Galla'," pp. 389-400.

በመጨረሻ ኢግናዚዮ ጉይዲ የሚባለው ኢጣልያዊ ሊቅ ችግሩን በመገንዘብ ሁለቱን ቅጂዎች አስተያይቶና አስማምቶ ግዕዙን ከፈረንሳይኛ ትርጉሙ ጋራ በ1907 ዓ. እ. እንደ አዲስ አሳተመው[15]። የጉይዲ ሥራ የተጣራ ስለሆነ ከዚያ ወዲህ ግዕዙን የነካው የለም። በዚህ ምክንያት ዛሬ የሽላይኽርን ጥናት ከማስታወስ አልፎ ለጥናት የሚጠቅስ ተመራማሪ ቢኖር የሽላይኽርን ስሕተቶች ያላየና ከሽላይኽር በኋላ የሆነውን ያልተረዳ ብቻ ነው።

*ዜናሁ ለጋላን* ሌሎችም፥ በተለየ ማኑኤል አልሜዳ እና ዋሊስ ባጅ ለድርሰታቸው ተጠቅመውበታል። አልሜዳ የወሰደውን ቤኪንግሃምና ሃንቲንግፎርድ የአልሜዳን ጠቅላላ ድርሰት በእንግሊዝኛ ተርጉመው በ1954 ዓ. እ. ሲያሳትሙ አብረው አሳትመውታል[16]። ዋሊስ ባጅ ግዕዙን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ ከትልቁ ባለሁለት ቅጽ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፉ ውስጥ አስገብቶታል[17]።

ዛሬ የምዕራብ ጸሐፊዎችና በምዕራብ አገሮች የትምህርት ሥነ ሥርዓት የታነፁ ሌሎችም ስለኦሮሞ ታሪክ ሲጽፉ ይኸንን የአባ ባሕርይን ድርሰት የሚጠቅሱት አብዛኛውን ጊዜ ቤኪንግሃምና ሃንቲንግፎርድ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመው ከማኑኤል አልሜዳ ትርጉማቸው ጋራ በ1954 ዓ. እ. ገጽ 111-129 ላይ ያሳተሙትን ነው። ይኸንን የነቤኪንግሃምን ትርጉም የፕሮፌሰር ዓለሜ ድርጅትም አባዝቶ አሰራጭቶታል[18]። ትርጉሙ ግን ስሕተት አልባ አይደለም።

ከሁለቱ ቅጂዎች (BL Or. 534 እና Aeth. 4) ሌላ ስላልተገኘና ሁለቱም ያሉት ከኢትዮጵያ ውጪ ስለሆነ የአባ ባሕርይን ድርሰት በሀገራችን ትምህርት ያደጉ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ጸሐፊዎች፥ በተለየም አቶ ዐፅመ ጊዮርጊስና አለቃ ታየ ገብረ ማርያም፥ አይተውት እንደሆነ ሽላይኽር ወይም ጉይዲ ወይም ሁለቱም ያሳተሟቸውን መሆን አለበት። የነሽላይኽርን ጎትመትንም ቢሆን ማየታቸውን መጽሐፎቻቸው በማያጠራጥር ሁኔታ አያሳዩም።

ይህን የአባ ባሕርይ ድርሰት ለጎትመት ሳቀርብ፥ በግዕዙ አርትዖ ረገድ ጉይዲ ካሳተመው የተለየ ብዙ ቁም ነገር አላመጣሁም። ጉይዲ ግዕዙን ያሳተመው ሽላይኽር ያሳተመውን ለማስተካከል ስለሆነ ብዙዎቹን ስሕተቶች አስተካክሏቸዋል። ኢትዮጵያዊው/ኤርትራዊው ሊቅ ተፍላ ባይሩ የአቶ ዐፅመ ጊዮርጊስን የጋላንና የኢትዮጵያ መንግሥት ታሪክ

15. Guidi, *Historia Gentis Galla*, pp. 221-232.
16. Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, pp. 133-139.
17. Wallis Budge, *A History of Ethiopia, Nubia & Abyssinia*, pp. 603-613.
18. ዓለሜ እሸቴ/መተክ፥ "የጋላ ታሪክ ጸሐፊው - ባሕርይ History of the Galla (Oromo) of Ethiopia by Bahrey."

“የጋላና የሸዋ መንግሥት ታሪክ” በሚል ስም ለውጦና ከእንግሊዝኛ ትርጉሙ ጋራ በ1987 ዓ. እ. ሲያሳትም፥ የጉይዲን ጥረት “(ጉይዲ የሽላይኽርን ጎትመት እንደገና ማሳተሙ) ለትምህርቱ ዓለም የተሻለ ጎትመት ለማቅረብ አስቦ መሆኑ ነው”[19] ያለው የጉይዲን የጥረት ጉልሕ ፍሬ ልብ ባይለው ነው። የሽላይኽር መጽሐፍ ዛሬ በምሁራን የማይጠቀሰው የጉይዲ ጥናት ስላበጠለው (ስለሻረው) ነው[20]።

የጉይዲ የግዕዝ ጎትመት የተመሰገነ ቢሆንም፥ እኔ እዚህ ያቀረብኩት ሁለቱን ቅጅዎች አስተያይቼ ራሴ የደረስኩበትን ግዕዝ ነው። ከአማርኛው ትርጉሜ ጋራ ያሳተምኩት የኔን የአማርኛ ትርጉም የሚያነብ ከፊለገ ግዕዙንም በቅርቡ እንዲያገኘው በማሰብ ነው። ለግዕዙ መሠረት ያደረግሁት የሎንዶኑን ቅጂ ሲሆን ስሕተት ሳይበት ወይ ወደ ቪየናው ቅጂ እሄዳለሁ ወይም እኔው አርመዋለሁ። ሆኖም ያደረግሁትን ለውጥና ሊለወጥ ሲገባው በአንዳች ምክንያት ያልለወጥሁትን ሁሉ በሞላ በግርጌ ጎዳግ አሳይቻለሁ። ይህ የተለመደ ሥርዓት ከመሆኑም በላይ የሎንዶኑና የቪየናው ቅጅዎች ምን እንደሚመስሉ እዚሁ ለማየት የሚያስችል ዘዴ ነው።

ግን አንድ ሕግ ጥሻለሁ። በዚናሁ ለጋላ እና በምጠቅሳቸው ግዕዝ ውስጥ የሚታዩት ነጥቦች የራሴ እንጂ ቅጂዎቹ ላይ ያሉት አይደሉም። በዚያ ላይ በሁለት ነጥብ አልተጠቀምኩም።

ስለ አሮሞች የሚነገረውን በመጠኑም ቢሆን ለማስፋት ስል ካልታተመው ከአለቃ ታየ ገብረ ማርያም ትልቁ መጽሐፍ ውስጥ በመጠኑ ቀድቼ አብሬ አሳትሜዋለሁ (አባሪ ፩ን ተመልከት)። ሁሉም ባይሆን፥ ብዙው አቶ ዐፅሜ ከጻፉት ጋራ ይመሳሰላል፤ የሁለቱም ምንጫቸው አንድ ቢሆን ነው። የአለቃ ታየ ትልቁ መጽሐፋቸው አሁን የሚገኘው ኢየሩሳሌም ባለው ዴር ስልጣን በሚባለው የኢትዮጵያ ገዳም ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነው። የማይክሮፊልም ቅጂው JE692E በሚል መታወቂያ ቍጥር እኔ በምሠራበት በቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ (ኮሌጅቪል፥ ሚኒሶታ) ይገኛል፤ የተጠቀምኩት በሱ ነው[21]። የአቶ ዐፅሜ

19. Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis and His Work*, p. 66: “... supposedly with the intension of availing the academic world of a better edition.”

20. ባይሩ ተፍላ ከላይ የጠቀስኩትን የኤኖ ሊትማንን እርማት በተጨማሪ አይቶና ተጠቅሞበት ቢሆን ኖሮ በጉይዲ ጥረት ላይ እንዲህ ያለ ቃል አይናገርም ነበረ።

21. JE692E ውስጥ የአለቃ ታየን ስም መጽሐፉን በቀዳው ሰው እጅ ተጽፎ አላገኘሁበትም፤ የቁም ጽሕፈቱ ውበትም ከአለቃ ታየ ብዕር ጋራ ፊጽሞ አይመሳሰልም። ታሪኩን የጻፉት እሳቸው ለመሆናቸው ግን አንዳንድ ማስረጃዎች አሉ፤ አንደኛ፥ ጸሐፊው እኔ ብለው የተውትን ሌላ ሰው ታየ የሚል ስም አክሎበታል። ሁለተኛ፥ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ* የሚባለው መጽሐፋቸው እንደገና በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ሲታተም ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት በጻፈው መቅድም ውስጥ ገጽ 20–33 ላይ የተቸው ይኸንን መጽሐፍ መሆኑ ግልጽ ነው። ሶስተኛ፥

መጽሐፍ ቅጅ በመሥሪያ ቤቴ ቢኖርም የተጠቀምኩበት ዶክተር ባይሩ ተፍላ ባሳተመው በፓሪሱ ቅጂ ነው[22]::

*ዜናሁ ለጋላን* አማርኛ ለሚያነቡ ተርጉሜ አማርኛውን ከነግዕዙ ለማቅረብ ከተነሣሁ በኋላ እንግሊዝኛም የጨመርኩበት ምናልባት ይኸንንና የነቤኪንግሃምን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ የሚያነቡ ሰዎች የተለያዩ እንደሚሆኑ በመገመት ነው:: ሆኖም፥ ሁለቱም ወገኖች ሁለቱንም ትርጉሞች ቢያነቡ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፤ ምክንያቱም የነቤኪንግሃም እንግሊዝኛ ውበት የኔ እንግሊዝኛ ለግዕዙ ቅርበት ይታይባቸዋል[23]::

---

በዚህ ተደጋግሞ በታተመው አጭሩ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ነገደ ጋላ እና ስለ ነገደ እናሪያ የተጻፈው መጠኑ መለስተኛ ቢሆንም፥ ያለው ከJE692E ውስጥ ከቀዳሁት ጋራ ቃል በቃል ይመሳሰላል፤ አራተኛ፥ አንድ ሎሬንዝ የንስን የሚባል ጀርመናዊ ዲፕሎማት አለቃ ታየ በርሊን በነበሩበት ጊዜ አብረውት ለሠሩት ለፕሮፌሰር ሚትሾኽ በጁላይ 11 ቀን 1910 ዓ. እ. በጀርመንኛ ከአዲስ አበባ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ፥ "አለቃ ታየ ይፋግ ናቸው፥ በጣም የታመሙ ይመስላል:: ትልቁን የታሪክ መጽሐፋቸውን ጽፈው ለመጨረስ ክረምት ሲወጣ ወደዚህ ተመልሰው ይመጣሉ ይባላል" ይላል፤ Edward Ullendorff, *Studia Aethiopica et Semitica*, p. 155-6.

22. የፓሪሱ የአቶ ዐፅሜ የጋላ ታሪክ ቅጂ በማይክሮፊልም ተነሥቶ እኔ በምሠራበት ዩኒቨርስቲ ቤተ መጻሕፍትም በመታወቂያ ቁጥር EMML 1517 ተመዝግቦ ይገኛል:: ሌሎቹ EMML 2393 እና ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም የግል ቅጅ የተነሣው ናቸው:: የፓሪሱን ቅጂ በካታሎግ የገለጸው ስቴፋን ስትሬልሲን ሲሆን እዚህ ያለውን የገለጸው ዶ/ር ዊልያም ማከምበር ነው:: ባይሩ ተፍላ ስለዚህ ቅጂ ሲጽፍ፥ "የሚያስገርመው ስቴፋን ስትሬልሲንና ጌታቸው ኃይሌ መጽሐፉን ካታሎግ ሲያደርጉ ይህንን (በውስጡ ያለውን) መዛነፍ ልብ ሳይሉት መቅረታቸው ነው" ሲል የኔን ስም ማጥፋቱ በማይገባ ነው፤ Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis*, p. 59. EMML 1517ን ማን ካታሎግ እንዳደረገው በካታሎጉ ውስጥ ተገልጿል፤ Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. V, pp. xi and 19.

23. የቤኪንግሃምና ሃንቲንግፎርድ እንግሊዝኛ ሙሉ በሙሉ ግዕዙን የተመረኮዘ አይደለም:: ወደ ግዕዙ የሚሄዱት ከጉይዲ ፈረንሳይኛና ከሽላይኽር ጀርመንኛ ውስጥ ግልጽ ያልሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው ይመስላል:: በዚያ ላይ የቪየናው ቅጂ መኖሩን ልብ አላሉትም::



**የአባ ባሕርይን ዘናሡ ለጋላ አስተካክሎ ያሳተመ**
**ኢግናዚዮ ጉይዲ።**

(ከ Ignazio Guidi, *Il "Fetha Nagast" o "Legislazione dei Re"*, 1936)

# ግዕዙ

(* የሚያመለክተው የጎዳግ ማስታወሻውን መነሻ ነው:: "ሎ" የሎንዶኑን፥ "ቪ" የቪየናውን ቅጂ፥ "ሎቪ" ሁለቱም ቅጂዎች የተሰማሙበትን ያመለክታሉ::)

ወጠንኩ እጽሐፍ[1] ዜናሁ ለጋላ ከመ አእምር ጎኑልቄ[2] ነገዱ ወግብረ ትጋሁ ለቀቲለ ነፍሳት ወተአንስዖተ ግዕዙ:: ወለእመቦ ዘይብለኒ ለምንት ጸሐፌ ዜናሁ ለእኩይ ከመ ዜና ሠናያን፥ አገብእ ሎቱ ተሠጥዎ ወእብሎ፥ ጎሥሥ ውስተ መጻሕፍት ወትርአይ ከመ ተጽሕፈ ዜናሁ ለመሐመድ ወዜና ነገሥቶሙ ለተንበላት እንዘ ፀር ለነ እሙንቱ በሃይማኖት:: ወጊዮርጊስኒ ወልደ አሚድ ጸሐፌ ዜናሆሙ ለነገሥተ አጀም ዝንጉዓን ዘውእቶሙ እለ አፍሪዶን ወካልአኒሆሙ ነገሥተ ሩርስ ወይሰምይዎሙ በዝንቱ ዘመን ሶፊ::

## ክፍል ፩[3]

ይቤ በዓለ መጽሐፍ ጋላሰ[4] ወፅአ እምዕራብ ወአደወ እምፈለገ ብሔሩ ዘይብልዎ ገለና[5] ጎበ ጽንፈ ባሊ በመዋዕለ ሐፄ ወናግ ሰገድ:: ወክልኤቱ ነገድ ውእቱ ዘይሰመዩ በረይቱማ ወቦረን::

ወወለደ በረይቱማ ስድስተ ውሉደ:: በከሮሩ ይሰመይ ከረዩ፤ ወዳግም መረዋ[6]፤ ወሣልስ ኢቱ፤ ወራብዕ አከቹ፤ ወኃምስ ወረንጢኻ፤ ወሳድስ ሁምበና::

ወለቦረን ይሰመይ[7] አቡሆሙ ሰጲራ:: ወሰጲራ ወለዶ ለዳጨ፤ ወዳጨ ወለዶ ለመጫ:: ወመጫ ወለዶሙ ለዳአሌ ወለጂዳ::

ወክልኤሆሙ አኃው ወለዱ ብዙኃነ አንጋደ፥ ዘውእቶሙ ውሉደ ደአሌ ሆኮ፥ ወዳግም ጭሌ፥ ወሣልስ አቦ[8]፥ ወራብዕ ሱባ:: ወጂዳ ወለዶሙ ለሐካኮ በከሮሩ፥ ወለገኦድሩ[9] ካልኡ፥ ወለሊበን[10] ሣልሱ::

---

1. ሎ እጽሕፍ::
2. ቪ ጐ"::
3. ሎ ባዶ ቦታ ይተዋል እንጂ እንደ ቪ ክፍሎቹንና ቁጥራቸውን አይጽፍም::
4. ቪ "ስ ::
5. ቪ ገላና::
6. ቪ መረዎ::
7. ቪ ይስ"::
8. ቪ አቦ::
9. ቪ ወለጉ"::
10. ቪ "ቦን::

ወካዕበ ወለዶሙ ዳጨ ለዳጭ ወሰመዮሙ[11] በስመ ዚአሁ፥ ወለኮኖ ወለበቾ ወለጅሌ።

ወእሉኒ ወለዱ አንጋደ ብዙኃን። ወዝውእቱ[12] አስማቲሆሙ፤ ደቂቀ በቾ፥ ዑሩ ወኢሉ። ወደቂቀ ዳጭ፥ ሶዶ አቦ ጋላን። ወውሉደ ኮኖ፥ ሰቅሰቅ[13] ሊበን[10]። ወውሉደ ጅሌ፥ ኤላ አቦ ወልኢስ።

እሉ ኮሎሙ ይሰመዩ ቱለማ እስመ ብዙኃን እሙንቱ። ወኮኑ ይፀብኡ ኀቡረ። ወእምድኅረ ገኑዱይ[14] መዋዕል ተጋአዙ ወተፈልጡ በበይናቲሆሙ በከመ ተፈልጡ አብርሃም ወሎጥ ሶበ በዝኃ እንስሳሆሙ እስከ ተበሀሉ[15] ንትፈለጥ እመ አኮ አንተ የማነ ወአነ ፀጋመ። ወእመ አኮ አነ የማነ ወአንተ[16] ፀጋመ። ወኮነ በከመ ኮነ።

ወካዕበ[17] ነገደ ዳአሌ[18] ክልኤቱ፥ ዘውእቶሙ ጭሌ ወሆኮ፥ ወዓዲ ክልኤሆሙ ነገደ ጅዳ፥ ሊበን ወገኦድሩ[19]፥ ተፈልጡ እምአኀዊሆሙ ወተሰነአዉ ወተሰምዩ አፍሪ በዘመነ ሉባ ዘይሰምዮ[20] ቦረን አምቢሳ፤ ወበርቱማ ይሰምዮ[21] ሮባሌ።

ወካዕበ ተሰነአዉ ሐካኮ ወልደ ጅዳ ወደቂቀ ደአሌ አቦ ወሱባ፥ ወተሰምዩ ሰደቻ በዘመነ ሉባ ዘይሰመይ ቢርመጂ። ወእሉሂ ወለዱ ብዙኃን አንጋደ ወዝአስማቲሆሙ፤

ውሉደ ጭሌ፥ ገላም ወቦ[22]፡
ወውሉደ ሆኮ፥ ኪረሞ እሙሩ ጂዳ፤
ወውሉደ ሊበን፥ ዋሊሶ ኮታዌ አምዬ፤
ወውሉደ ገኦድሩ[23]፥ ሲርባ መሎል ጨረቃ፤
ወነገደ ሐካኮ፥ አቦ ሐርሱ ሊሙ፤
ወነገደ ሱባ፥ ሐገለባቦ ጩራ፤
ወነገደ አቦ፥ ሰዮ አቦኖ ቱምኤ ሌቃ።

ወእሉ ኮሎሙ ሶበ ተፋቀሩ ይሰመዩ መጫ። ወሶበ ተፃልኡ ይትበሀሉ አፍሪ ወሰደቻ። ወለእመ ኮሎሙ ኃብሩ ምስለ ቱለማ ይሰመዩ ሰጲራ[24]።

ወቦረንሂ[25] ወለደ ዓሠርተ ወክልኤተ ደቂቀ። በኮሩ ዳጨ፥ ወዳግም ጅሌ፥ ወሣልስ ኮኖ፥ ወራብዕ በቾ፤ እሉ ይሰመዩ ቱለማ[26]፤

11. ቪ ወስመዮ ።
12. ቪ ወዝ ውእቱ።
13. ቪ ሳቅስቅ።
14. ቪ ጉ"።
15. ተባ" ለማለት።
16. ሎ ወአነ።
17. ቪ ወከ"።
18. ሎ ደ"።
19. ቪ ወጉ"።
20. ቪ "ስ"።
21. ቪ ይሳ"።
22. ቪ አቦ።
23. ቪ ጉ"።
24. ቪ ሳጲራ።
25. ቪ ወቦረን ሂ።
26. ቪ ትሉማ።

ኃምስ ሀካኩ፥ ሳድስ አቦ፥ ወሳብዕ ሱባ፤ እሉ ይሰመዩ[27] ሰደቻ፤ ሳምን ጭሌ፥ ታስዕ[28] ሊበን፥ ወዓሥር ጐድሩ[29]፥ አሠርቱ ወአሐዱ ሆኩ፤ እሉ ይሰመዩ[27] አፍራ።

## ክፍል ፪

ወዳዌ ዘአጥፍኣ[30] *ለበጥረ አሞራ[31] እምሰብአ ቦረን ውእቱ። ወቦ ዘይቤ እምካልእ ረከበ[32] ምክንያተ በእንተ ተፃብኦቱ ምስለ ቦረን። ዝንቱሰ[33] ዜና የዋህ[34]፥ ወኢኮነ ጽድቀ። ወመጠይቅሰ ይብል አመ ወፅኡ እምሀገሮሙ አኮ ኮሎሙ ዘወፅኡ፤ አላ ተርፈ ዘፈቀደ፥ ወወፅአ ዘፈቀደ፤ እስመ አልቦ እግዚአ ዘይኤዝዞ፥ አላ ዘአደሞ ልቡ ይገብር።

ወእሉ ዘተርፉ እምቦረን ወፅኡ እምሀገሮሙ በፍኖተ ኬራ[35]። ወመረደ ቦሙ ፋሲል፤ ወቀተልዎ[36]። ወአሜሃ ወጠነ ዳዊ ፀቢአ ክርስቲያን።

ወአሜሃ ተነበየ ጸሐፌ[37] ዝንቱ ታሪክ እንዘ ይብል፥ እፈርሆ ለቀታሌ ፋሲል፤ እስመ ጥዕመ ደመ ክርስቲያን፤ ወውእቱ አጥፍኦሙ ለበጥራ አሞራ[38] ወወጅ። ወኮነ በከመ ቃሉ፤ እስመ መንፈሰ ትንቢት[39] ኢይርሕቅ እምካህናት። ወለዝንቱ ነቢይ ሰደዶ ዳዊ ወአጥፍአ ሀገሮ ዘገሞ ወማህረከ ኮሎ ዘአጥረየ።

ንግባእኬ ኀበ ዜና በረይቱማ ዘኃደግናሁ እስከዛ ጊዜ።

## ክፍል ፫

ወወለደ ከረዩ ስድስተ ውሉደ። ወኮኑ አንጋደ ብዙኃነ ወኃያላነ። ቀዳሚሆሙ ሊበን፥ ወዳግም ወሎ፥ ወሣልስ[40] ጅሌ[41]፥ ወራብዕ አቦ፥ ወሐምስ ሱባ፥ ወሳድስ በላእ።

ወወለደ ወሎ ስድስተ ውሉደ፥ ዘውእቶሙ ወረ ቡኮ፥ ወረ ጐራእ[42]፥ ወረ ኖሌኤሉ፤ እሉ ሀለዉ በስመ ወሎ፤ ወረ ከረዩ፥ ወረ ኢሉ፥ ወረ ኖሌአሊ፤ እሉሂ ፫ ይሰመዩ ሰደቻ። ወተፈልጦሙሰ እምአመ ቀተልዎ ለአቦሊ። ወይእዜ ገብሩ ዕርቀ በላዕሌነ፥ ተሰካተዩ፥ ወተካየዱ።

---

27. ፬ ይስ"።
28. ፬ ታሰዕ።
29. ፬ ጉ"።
30. "ፍኣ ለማለት ።
31. ፬ ለበጥራምራ።
32. "ረኪቦ"፥ ወይም "ወውእቱ ረከበ"፥ ወይም "ወዘይቤ እምካልእ ረከበ" ለማለት።
33. ፬ ዝንቱ ሰ።
34. ፬ ውእቱን ይጨምራል።
35. ፬ ኬራ፥ EMML 7109 ኳራ።
36. ፬ ወቀተዎ።
37. ፬ ጸሐፈ።
38. ፬ ምራ።
39. ሎ ትዕቢት።
40. ሎ ወሳድስ።
41. ፬ ጀሌ።
42. ፬ ጉራዕ።

## ክፍል ፬

ወመረዋ አያ ወለዶሙ ለአና ወለዑሩ ወለአበጢ። ወከማሁ በዝኑ ደቂቆሙ ወደቂቀ[43] ደቂቆሙ[44]፤ ወከኑ አንጋደ ብዙኃነ፤ ወይሰመዩ አስማቲሆሙ በበነገዶሙ።

ወአልቦሙ ንጉሠ[45] ወኢእግዚአ ከመ ካልእ[46] ሕዝብ እለ[47] ይትኤዘዙ ለሉባ እስከ ፷ ዓመት። ወድኅረ ፷ ዓመት ይሠየም[48] ካልእ ሉባ ወይሰዓር ቀዳማዊ። ከመዝ ይገብሩ በበዘመኑ።

ወብሂለ ሉባስ ዘተገዝሩ በ፩ ዘመን። ወሥርዐተ ግዝረቶሙስ ከመዝ ውእቱ፤ እስመ ሶበ ይሠዐር ሉባ ያወፅኡ ስመ ለርእሶሙ ኮሎሙ በርቱማ ወቦረን፥ በከመ ይሰመዩ[27] ሐራ ንጉሥ ሥሉስ ኃይሌ በድል ፀሐይ ወጊዮርጊስ ኃይሌ።

## ክፍል ፭

ወከማሁ ዘተገዝረ[49] አመ ወጠነ ፀቢኦታ ለባሊ ይሰመይ[27] ሜልባሕ። ወስመ አቡሁ[50] ኢየአምር እስመ አልቦ ዘይነግረኒ።

## ክፍል ፮

ወዳግማይ ሉባ ተሰምየ[51] ሙደና። ወለዝንቱኒ ጅበና ስመ አቡሁ። ወውእቱ ዘዓደወ ፈለገ ወቢ።

## ክፍል ፯

ወሣልስ ሉባ ተሰምየ ኪሎሌ። ወውእቱ ፀብአሙ ለቄላተ ደዋሮ ዘከመ አደል መብረቅ ወዘቄላቲሃ።

## ክፍል ፰

ወራብዕ ሉባ ተሰምየ ቢፎሌ። ወውእቱ ዘአጥፍአ[30] ለደዋሮ በምልዓ። ወወጠነ ተዋብኦተ ፈጠጋር።

ወወጠነ ፄውዎተ ሰብእ፤ ወረሰዮሙ አግብርተ፤ ወሰመዮሙ ገበር። ወወጠነ ሰትየ ኮሦ። ቀዳማውያንሰ ሉባ ዘዘከርናሆሙ ይቀትሉ ሰብአ

43. ቪ "ቄቀ።
44. ቪ ደቄ"።
45. ቪ "ሥ።
46. ቪ ካልአን።
47. "አላ" ወይም "እለ ይትኤዘዙ አላ" ለማለት።
48. ሎ ይሰመይ።
49. ቪ "ዘረ።
50. ቪ "ሁሰ ።
51. ቪ ተስ"።

ተባዕተ ወአንስተ፤ ወይቀትሉ አፍራሰ[52] ወአብቅልተ። ወኢያትረፉ[53] ዘእንበለ አባግዐ[54] ወአጣሌ ወአልህምተ[55]። ወኢይቀትሉ በመድኃኒት አርዌ ከርሦሙ፤ አላ ይውሕዝ በአቀኒያጺሆሙ ከመ እንስሳ።

## ክፍል ፱

ወኃምስ ሉባ ተሰምየ ምስሌ። ውእቱ ዘቀተሎ ለጎርጎ አሞራ። ወተፃብአ ለሐመልማል በደኃ[56]። ወአጥፍአሙ ለኵሎሙ አህጉራት፤ ወተሠልጠ ላዕሌሆን፤ ወቦአ ምስለ እንስሳሁ። ወቀደምትሰ ጋላ ኮነ ይፃባእ ወፂአ እምወቢ ወይትመየጥ ህየ።

ወኪያሁ ፀብኡ ንጉሥነ አጽናፍ ሰገድ ተንሢኦሙ እምዓሣ[57] ዘነብ። ወአመ ይወርድ ኑር ሀገሮ እምድኅረ *ዘገብረ ገብረ[58] ውእቱ ተራከቦ በቅሩበ[59] ኀዘሌ ወቀተለ መብዝኀተ ሠራዊቱ ዘአልቦ ኀልቈ። ወእምአመ ወፅአ ጋላ ሀገርነ አልቦ ዘሞቱ ዘከመ ሞቱ አሜሃ። ወእምሠራዊተ አውሣ ዘሀለወነ ንዝክሮሙ[60] በጊዜሁ ይበዝኑ ሠራዊተ ኑር ዘተቀትሉ አሜሃ። እስመ ፈደዮሙ እግዚአብሔር በቀለ ደሞሙ ለአግብርቲሁ ዘከዓዉ በመጅ[61]።

ወዝንቱ ምስሌ ወጠነ ተፅዕኖ ፈረስ ወበቅል ዘኢኮነ እምቅድሜሁ፥ እስከ ይቤሉሙ ለሉባ ዘቀደምዎ፤ ለእለ ኮኑ የሐውሩ በ፪ ወ፫ እግር ረሰይክዎሙ ይሑሩ በ፬ እግር። ወብሂሎቱሰ በ፫ እግር በእንተ ዘይትመረጐዙ ከኖናቶሙ ሶበ ደክሙ በፍኖት።

## ክፍል ፲

ወኃምስቱሰ ሉባ እለ ዘከርናሆሙ ኰነኑ ፴ ዓመተ፤ ወኢተገዝሩ ውሉዶሙ። ወነበሩ እንዘ ይወግሩ ቈላፋን ውሉደ ወአዋልደ፤ እስመ ከመዝ ሕጎሙ። ወሶበ ተገዝሩ የሐፅኑ ውልደ። ወለአዋልድሰ[62] ዓዲ ይወግርዎን እስከ ፪ ወ፫ ዓመት እምድኅረ ተገዝሩ።

## ክፍል ፲፩

ወእምድኅረ ፮ ሉባ[63] ተገዝሩ ውሉዱ ለሜልባሕ። ወተሰምዩ ሐርሙፋ። ወውእቱ ቀተሎሙ ለጊዮርጊስ ኃይሌ በቀጭኖ። ወቦረንሂ ይሰምዮ ዱሉ። ውእቱ ዘአጥፍአሙ[64] ለገኘ[65] ወለአንጐት[66] ወለአምሐራ።

52. ቪ "ስ።
53. ቪ ወኢያተርፉ።
54. ሎ ቪ "ዕ።
55. ቪ "ምት።
56. ቪ ግልጽ አይደለም።
57. ሎ ዓሣ።
58. ቪ ገብረ ዘገብረ።
59. ቪ በቅሩቡ።
60. ቪ ንዘከሮሙ።
61. EMML 7109 በመኧር።
62. ቪ ወአዋልድ ሰ።
63. ቪ ግልጽ አይደለም።
64. ሎ "አሙ።
65. ቪ "ኘ ።
66. ቪ "ጎት።

ውእቱ ዘወጠነ ፀቢኦተ[67] በጌምድር[68]። ወሐርሙፋ ዘበርቱማ ፀብኦ ለበጌምድር[69]፤ ወቀተሎ ለዋካ እጉሁ ለሐርቦ። ወአሜሃ ነበበ ሐርሙፋ ቃለ ትዕይርት[70]፤ ወይቤ። ለሲዳማ እለ ይለብሱ ባሕረ አጽደፍክምሙ ባሕረ።

## ክፍል ፲፪

ወእምድኅረ[71] ፷ ዓመት ተሥዕረ ሐርሙፋ ወተሰይመ ሮባሌ ወልደ ሙደና፥ ዘተጽሕፈ[72] ስሙ በክፍል ስድስቱ[73]። ውእቱ ዘአጥፋአ[74] ለሸዋ። ወወጠነ ፀቢኦታ ለጐጐምም[75]።

ወሎቱ ፀብእዎ ሐዌጌ በዝዋይ። ወቀተሉ[76] ብዙኃነ እምኔሁ[77]፤ ወማኅረኩ አልህምቲሁ[78] ወኮኑ[79] ብዙኃን አብዕልተ እምነ ውእቱ ምህርካ።

ወውእቱ ቀተሎ ለአዝማቺ[80] ዘርአ ዮሐንስ ርእሰ መኳንንት ላዕሌሁ ሰላም።

ወበውእቱ መዋዕል ኮነ ሶሊ ወቢዳሮ ኢላላ በነገደ ሱባ ዘቦረን።

ወእምድኅረዝ[81] በ፷ ዓመት ፀብእዎ ሐዌጌ ለሮባሌ ዘአበጠ በወይና ደግዓ ወቀተልዎ እንበለ አትርፎ። ቦዘይቤ ተርፉ ዘይበዝኑ[82] እምኀ ወበጽሑ ሀገሮሙ ለዜና።

## ክፍል ፲፫

ወእምድኅረ ፷ ዓመት ተሠይመ ቢርመጀ ወልደ ኪሎሌ ዘአጥፍአ[74] ለደዋሮ። ወዝንቱ ቢርመጀ ዘቦረን ገብረ ወልታ ዘአነዳ ላህም መጠነ ቆሙ፤ ወፀብአሙ ለማያ ሰብአ ቀስት፤ ወሞአሙ ሶበ ኃጥኡ ዘይነድፍዎ፤ እስመ ተወልተወ[83] አነዳ ላህም ይቡሰ።

ወዓጽአቆ ለአዝማቺ ደኅረኅት መልአከ ኀይሉ ለንጉሥ[84]፤ ወቀተሎሙ ለእለ ዜናይ ወወዓልያኒሁ[85]። ቅድመሰ[86] ኮነ ይመውኦ ብዙኃ ጊዜ። ባሕቱ በፈቃደ እግዚአብሔር ኮነ በእንተ ዘኢተፈጸመ ዕዳሆሙ።[87]

67. ሎ "ቱ።
68. ቪ በጌ ምድር።
69. ቪ ለቤጌ ምድር።
70. ቪ "ይንት።
71. ቪ ወእምኅረ።
72. ሎ ወተ"።
73. ቪ ፮።
74. "ኣ ለማለት።
75. ቪ ለኅ"።
76. ቪ "ትሉ።
77. ቪ "ኒሁ።
78. ቪ "ተ።
79. ሎ "ነ።
80. ሎ "ቸ።
81. ሎ "ረ።
82. ዘኢ"?
83. ቪ "ው።
84. ቪ ላን"።
85. ሎ ሁለተኛው ወ ግልጽ አይደለም፥ ቪ ወዓል"።
86. ቪ "ስ።
87. ቪ ዕዳኛ"።

ለክርስቲያን፤ ተሞአ መዋኢ፥ ወአጥፍኣ ለአርእኘ[88] ሀገረ ሚመቱ። ወቀተሎሙ ለእለ ጋቶ ወበትሮ ወበድሌ ወዓምዶ ወካልአኒሆሙ። ወኮኑ በድወ እሉ[89] ፪ አህጉር ዘኮሎሙ ነዳያን ይብዕሉ በጎቤሆሙ።

ወቢርመጀ ዘበርቱማ ፀብኣ ለደምብያ ወቀተሎ ለአቦሊ እምዘመደ መንግሥት፤ ወለሠምረ አብ ባሕር[90] ነጋሽ ወካልአኒሁ።

ወዝንቱ ኮነ ጎበ ኢሀለዉ ንጉሥነ ዘኃያል በምግባሮሙ ወጠቢብ በምክሮሙ። ሶበሰ ነበሩ በደምብያ እምበጽሑ ለቢርመጀ ዘበጽሑ ለሮባሌ። ባሕቱ ከመ ይኩን መዊእ በተባርዮ አርትዓ እግዚአብሔር ፍኖቶሙ ለንጉሥነ ጎበ ዳሞት። ወረከቡ መዊአ ጎበ ሐሩ፤ ወተመውኡ መኳንንት ጎበ ኢሀለዉ።

## ክፍል ፲፬

ወቢርመጀ ዘቦረን ዓገታ ለምድረ ዳሞት። ወዜወወ ሰብአ ወእንስሳ[91] ሶበ ረከባ ለሀገር እንዘ አልቦ ዘያድኅን ወዘይባልሕ።

ወአሜሃ ኮነ ደጅ አዝማቺ ዓስቦ። ወተማከረ ምስለ አጎዊሁ። ወአስተጋብአ ሠራዊተ፤ ወደገኖ። ወበጽሐ ጎበ ሀለወ[92] ይትካፈል ምህርካሁ። ወዓገትዎ ጎሩያን ወመስተዕእናን በመስለስት[93]፤ ዝብሂል ዓገቶሙ በ፫ አውራሪ። ወጌየ ጋላ፥ ወተቀትለ።

ወመብዝኀቱ ተኃብኡ ውስተ በዓት ስፉሕ። ወአስተጋብአ ዕፀወ፤ ወአንደደ ውስተ አፈ በዓት። ወብዙኃን ወዕኡ እምፍርሃተ[94] እሳት፤ ወተአስሩ፤ እስከ[95] አምጽኡ ሎቱ ወወሀብዎ ለወልደ መንግሥት ዘተዜወወ ምስለ ብዙኃን ዒውዋን። ወለእለ ሞቱ መተሩ[96] አርእስቲሆሙ[97]፤ ወበዝኃ እምኀሩልቊ[98]፤ ወዓቀበ ሀገሮ።

ወእምድኅረዝ እስከ አመ የኃልፍ መዋዕለ ዕብሬቱ ለቢርመጀ ወእደ እግዝአብሔር ዓዲሃ ልዕልት ወእስከ ዓዲ ኢተፈጸመ ዕዳዎሙ ለክርስቲያን። እመኒ ተዓቀቡ በመዋዕለ ቢርመጀ ሀለወ ያጠፍኦሙ[99] ደኃራይ[100] ሉባ ዘንዜክሮ ድኅረ በገጸ መካኑ።

## ክፍል ፲፭

ወእምዝ ተሥዕረ ቢርመጀ ወተሠይመ ሙልአታ ወልደ ቢፎሌ። ወገብረ ዱላጉቶ በጐኅም። ወፍካሬሁ ለዱላጉቶ ጸብአ ጉትያ ውእቱ። እስመ ጋላ

88. ቪ "ጥ ይመስላል።
89. ሎ የለውም።
90. ቪ "ረ።
91. ቪ "ሳሳ።
92. ቪ ሀላወ።
93. ቪ "ልስት።
94. ቪ "ት።
95. ቪ "ኮ።
96. ቪ "ረ።
97. ቪ እር"።
98. ቪ "ኑ"።
99. ያጥ"?
100. ቪ ዳኅራይ።

ሶበ ተገዝሩ በ፩ ዘመን ያወፅእ ስመ ለርእሱ በከመ ንቤ በርእሰ ክፍል ፬ ። ወይፀብእ አሐደ ሀገረ ዘኢፀብእዎ[101] ቀደምቱ። ለእመ ቀተለ ሰብአ ወአራዊተ ዓቢያነ ይትላጸይ ኮሎ ርእሶ፤ ወየኃድግ ንስቲተ ሥዕርተ በማእከለ[102] ድማሁ። ወዘኢቀተለሰ ኢይትላጸይ እስከ ይትመነደብ በቅማል። ወበእንተዝ ይተግህ[103] ለቀቲሎትነ።

ወበውእቱ መዋዕል መከሩ ሐቄጌ ከመ ይሑሩ ምድረ ዳሞት። ወእንዘ ሀለዉ በፍኖት ሰምዑ ከመ ፀብአ ጋላ ምድረ ጐጥም÷ ወከመ ዐርጉ እሞሙ ንግሥት ደብረ አብርሃም ይፀወኑ ህየ።

ወዊዘሮ ተውዳዳ እኅተ አበዊሆሙ ነገሥታት አጽናፍ ሰገድ ወአድማስ ሰገድ ላዕሌሆሙ ሰላም። ወሶበ በጽሐ ኀቤሆሙ ጋላ ግብተ በጊዜ ኢትኃዘብዎ ደንገፁ ኮሎሙ ሰብአ ሀገር፤ ወተዘርዉ ሠራዊቶሙ። ወወልዶሙሰ[104] ዘይልህቅ ተኃየለ ላዕለ ጋላ እለ ቀርቡ ኀበ ዕሙ፤ ሰደዶሙ[105]÷ እስመ ወሬዛ ውእቱ ወይትዌደስ በኃይሉ። ወተመይጠ ወአኀዘ እደ እሙ ወአዕረጎሙ ኀበ ደብር ነዋኅ ዘስሙ ጅበላ።

ወሐቄጌሰ ኀደጉ ፍኖቶሙ ወተመይጡ በጉጉዓ[106] ኀበ ሀሎ ጋላ፤ ወቦኡ ምስለ ሠራዊት። ወኃደጉ ሥርዐተ አበዊሆሙ ነገሥታት፤ እስመ ኮነ ልማዶሙ ሶበ ይበጽሑ ኀበ ፀብእ ይፈንዉ መስተቃትላነ ወይቀውሙ ምስለ ኀሩያን ሰብአ አፍራስ ወእግር፤ ይቄድስዎ ለዘበደረ ወይኬንንዎ ለዘተድኅረ[107]።

አሜሃሰ ቀደሙ ንጉሥነ እምኃያላን ወተኃየሉ። ወሶበ ርእዩ ዘንተ ሠራዊት ሮጹ፤ ወተአርወዩ ላዕለ ጋላ። ወቀተሉ ኮሎ[108] እንበለ አትርፎ። ወመብዝኀቱ ተነጽሐ ውስተ ጸድፍ እስከ ኮነ[109] ሰብአ ሀገር ወመስተገብራን ይቀትልዎሙ በኀበ ረከቡ።

ወአዘዙ ከመ ይምትሩ አርእስቲሆሙ ለጋሎች[110]። ወመልአ ውስተ አዶራ÷ ዘውእቱ መካን ስፉሕ።

ወአውረድዎሙ ለኢቴጌ ወለዊዘሮ ቴዎዳዳ[111] እምነ አድባራት ዘኮኑ ውስቴቱ። ወተቀበልዎሙ በክብር።

ወሶበ ርእዩ ብዙኆሙ ለአርእስተ ፀር እለ ተመትሩ ተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሐ። ወአእኰትዎ ለእግዚአብሔር ዘሜመ መንፈሰ መዊእ ላዕለ መሲሑ።

ወአልህምትሰ ዘአንገፉ እምእደ[112] ጋላ ሜጡ ሎሙ ለእለ ተማኅረኩ።

---

101. ቪ ዘይፀ"።
102. ቪ "ላ።
103. ሎ ይት"።
104. ቪ ወው"።
105. ሎ ሰደደዶሙ።
106. ቪ በጉጉአ።
107. ቪ ለዘ ተድ"።
108. ሎ ጋሎ ።
109. ቪ ኮኑ።
110. "ች ለማለት።
111. ቪ ቴው"።
112. ሎ ላዕለ።

## ክፍል ፲፮

ወእምድኅረዝ መከሩ ንጉሥነ ያርትዑ ፍኖቶሙ፤ እስመ ይገብሩ በከመ ሐለዩ፥ ወይፈጽሙ በከመ ነበቡ። ወሖሩ ወጅ ለፀቢአ ጋላ *ዘስሙ ዳዌ። ወጋላሰ ይሰምዮ ጋላ[113] ዘድኅር። ወሰብእሰ ይሰምይዎ ዳዌ በእንተ ዘአድወዮሙ።

ወምክንያተ ሐዊሮቶሙሰ[114] ህየ እስመ መሰሎሙ ዘይሁበሙ ሰልፈ፥ ወኢይጐይይ። ወሶበ በጽሑ ኀበ ይቤልዎሙ ሀሎ ዝየ ኃጥእዎ፤ ኀሠሡ ወኢረከቡ መካኖ።

ወሶበ ኃጥኡ ምህርካ እንስሳዊ ወፀብአ ሥጋዊ መከሩ ከመ ይፃብኡ ምስለ ሰይጣን ወይማህርኩ እምኔሁ ነፍሳተ አሕዛብ። ጸውዕዎሙ ለእናርያ ወለቦሻ ወለጎመር። ወይቤልዎሙ ኩኑ ክርስቲያነ። ወኮኑ፤ ወተጠምቁ ጥምቀተ ክርስትና።

## ክፍል ፲፯

ወሙልአታ ዘወርድአያ ሶበ ፀብአ ሀገሮ ለራስ ወልደ ክርስቶስ[115]። ሞአ[116] ወአንገፈ ምህርካሁ፤ ወቀተለ ብዙኃ እምኔሁ። ወለመንፈቁ ዲገኖሙ እስከ ተነጽሑ በጸድፍ። ወዓቀበ ሀገረ እስከ ይትመየጡ ሐዌጌ። ወሶበ ተመይጡ ሐዌጌ[117] ረከብዋ ለሀገር ዕቅብተ[118] በትጋሁ ለወልደ ክርስቶስ ወበተፃብኦቱ። ወበእንተዝ ረሰዮ እግዚአ ለቤቱ ወአኰነኖ[119] ላዕለ ኵሉ[120] መንግሥቱ።

## ክፍል ፲፰

ወሙልአታ ዘቦረን አጽሐቦሙ ለክርስቲያን ዘዳሞት፤ ወዘረዎሙ ወአጥፍአ ሀገሮሙ። ወኮኑ በድወ በዘመኑ ምድረ ሽዋ ወዳሞት።

ወዘጸሐፍኩሰ ምዕረ መዊኦተ ጋላ ወምዕረ መዊአ ክርስቲያን ልማደ መጽሐፍ ውእቱ ዘይቤ ዮም ለከ ወጌሠም ለካልእከ። ወመዊእኒ ትከውን ጊዜ[121] ለዝንቱ ወጊዜ[122] ለዝክቱ። ወዘይመውእሰ ኵሉ ጊዜ ፩ እግዚአብሔር ዘላዕለ ኵሉ። ወሀገርሰ[123] ገብአት ውስተ እዴሁ፤ ወአልቦ ዘተርፈ።

ወእምአመ[124] ተጽሕፈ ዝንቱ መጽሐፍ ኮነ ፯ ዓመተ ሚመቱ ለሙልአታ ወልደ ቢፎሌ። ዓዲሆሙ ድልዋን ለተገዝሮ[125] ወለሚመት

113. ቪ የለውም።
114. ቪ "ሙ ሰ።
115. ቪ ክሶስ።
116. ቪ ሞአ።
117. ቪ የለውም።
118. ሎ "በተ።
119. ቪ ወአኮ"።
120. ቪ ኩሉ።
121. ቪ ጌዜ
122. ቪ ወጌዜ።
123. ቪ "ስ።
124. ቪ ወአመ።
125. ሎ ለተግ"።

ዘደቂቀ ምስሌ። ወዘይከውን በዘመኖሙ እምነ አጽባዕት ወቀትል ለእመ ሐዮኩ እጽሕፎ ድኅረ። ወለእመ ሞትኩ ካልአን ይጽሕፉ ዜናየ ወዜና ሉባ ዘይመጽእ። ወባሕቱ ብፁዕ ዘሞተ እስመ አዕረፈ።

## ክፍል ፲፱

ወይትኃሠሡ ማእምራን ተኃሥሦተ ብዙኃ ወይብሉ በእፎ ይመውኦነ ጋላ እንዘ ንሕነ ብዙኃን ወብዙኅ ንዋየ ፀብእነ። ቦእለ ይቤሉ አብሐ[126] እግዚአብሔር በእንተ ኃጢአትነ። ወቦ ዘይቤ በእንተ ተከፍሎቱ[127] ሰብእነ ኀበ ፲ ጸታ፤ እምኔሆሙ ፱ ጸታ ኢይቀርቡ[128] ኀበ ፀብእ[129] ወኢየኃፍሩ በፍርሃቶሙ። ወባሕቱ ዓሥራይ ጸታ ይፃባእ ወይትቃተል መጠነ ተክህሎ።

ወለእመ ብዙኅ ኅልቊነ ውኁዳን እሙንቱ እለ ይክሉ ተፃብኦ፥ ወብዙኃን እለ ኢይቀርቡ ኀበ ፀብእ።

፩ እምኔሆሙ ነገደ መነኮሳት እለ አልቦሙ ኅልቈ። ቦዘይመነኵስ[130] በናእሱ ሶበ ኄጥዎ መነኮሳት በጊዜ ትምህርቱ ከመ ጸሐፌ[131] ዝንቱ ታሪክ ወእለ ከማሁ፤ ወቦ ዘይመነኵስ[130] እምፍርሃት[132] ፀብእ።

ካልእ ነገድ ይሰመዩ ደብተራ፤ ይትመህሩ መጻሕፍተ ወኵሉ[133] ግብረ ክህነት፤ ይጠፍሑ በእደዊሆሙ ወያጽሕሱ በእገሪሆሙ። ወኢየኃፍሩ በእንተ ፍርሃቶሙ። ወይነሥኡ አርአያ እምሌዋውያን ወእምካህናት፥ ዘውእቶሙ ደቂቀ አሮን።

ሣልስ ነገድ ይሰመዩ ኀጕን ሐጸና ወኀጕን መዓሠሬ፤ የዓቅቡ ፍትሐ[134] ወይትዓቀቡ እምተፃብኦ።

ራብዕ ነገደ ደጋፎቺ[135] ዘአንስትያ መኳንንት[136] ወዊዛዝር፥ እደው ኃያላን ወወራዙት ጽኑዓን ኢይቀርቡ ኀበ ፀብእ፤ ወይብሉ ወዓልያነ አንስት ንሕነ።

ኃምስ ነገድ ይሰመዩ ሽማግሌ ወገዜ[137] ወበዓለ ርስት፤ ይከፍሉ ምድሮሙ ለመስተገብር ወይኤዝዝዎ፤ ወኢየኃፍሩ በእንተ ፍርሃቶሙ።

ሳድስ ነገድ መስተገብራን፤ ይውዕሉ ኀበ ገራህት ወአልቦሙ ሐልዮ ለተፃብኦ።

ሳብዕ ነገድ እለ ይትበቀዑ በነጊድ ወይረብሑ ለርእሶሙ።

ሳምን ነገድ ጠቢባን ዘከመ ነህብት ወጸሐፍት ወሰፋይያን ወፀራብያን ወእለ ይመስልዎሙ[138]፤ ኢየአምሩ ተፃብኦ።

126. ቪ. አብሐ።
127. ቪ. "ሎትነ።
128. ቪ. "ቅረቡ።
129. ቪ. ሰብእ።
130. ቪ. "ኩስ።
131. ቪ. "ፈ።
132. ቪ. "ቲ።
133. ቪ. ወኩሎ ።
134. ሎ ፈታሐ።
135. ሎ "ቸ።
136. ቪ. መኳ"።
137. ሎ ወጊዜ።
138. ቪ. ይም"።

ታስዕ ጸታ አዝማሮቺ ወበዓለ ቀንደ ከበሮ ወበዓለ በገና እለ ይሬስይዎ ተግባረ ለስኢል። ይባርክዎ ለዘወሀቦሙ፤ ወይሁብዎ ስብሐተ ብጹለ ወውዳሴ ጽሩዓ። ወለእመኒ ረገምዎ ለዘከልኦሙ ኢይከውኑ[139] ዕዳ እስመ ይብሉ ሕገ ብነ። ወነዋኃ ይርኅቁ እምፀብእ።

ዓሥራይ ጸታ እለ ይእኅዙ ኵናተ ወወልታ ወእለ ይክሉ ተግብኦ፤ ወይተልዉ አሠረ ንጉሥ ለረዊጽ። ወበእንተ ውኅደቶሙ ለእሉ[140] ጠፍኦት ሀገርነ።

ለጋላሰ አልቦ በኀቤሁ እምእሉ ፱ ጸታ እለ ዘከርናሆሙ። ወኮሉሙ ምሁራነ ፀብእ፤ እምንኡሱ[141] እስከ ዓቢዩ። በእንተዝ ያጠፍአነ ወይቀትለነ።

ወእለሰ ይብሉ ይቀትለነ በትእዛዘ እግዚአብሔር ነሥኡ ምክንያተ እምተመውኦተ ደቂቀ እስራኤል ወጥፍኦቶሙ በእደ ነገሥተ ፋርስ ወባቢሎን። ወይብሉ እመሰ መስተፃብእ ይመውእ[142] መኑ እምሰአለ[143] ረድኤተ[144] እምእግዚአብሔር ክቡር ወልዑል። ወእመኒ ብዙኅ ይመውኦ ለውኑድ እምኮነ ብጹለ ቃለ መጽሐፍ ዘይቤ ፩ ያነትያሙ ለ፲፱ ወክልኤቱ ይሰድድዎሙ ለእልፍ።

ወለእመ እሙን ቃሉሙ ለመስተጋዕዛን ቀዳማውያን አው ለደኃራውያን አንትሙ ተአምሩ አማእምራን።

## ክፍል ፳

ንግባእኬ ኀበ ዜናሁ ለጋላ።

ለንኡስ ሕፃናት ይሰምዮሙ መ·ጫዕ። ወለእለ ይልህቁ ይሰምዮሙ ኤልማን። ወእምነ እሉሂ እለ ይልህቁ ይሰምዮሙ ጐርባእ፤ ዘይወጥኑ ተግብኦ።

ወለወራዙት እለ ኢተገዝሩ ይሰምዮሙ ቈንደላ፤ እለ ይገብሩ ሥዕርተ ርእሶሙ ከመ ጎራ ወይሰምይዎ ከለላ። ወለእመ ቀተሉ[145] ሰብአ ወነጌ ወአንበሳ ወአርዌ ሐሪስ ወጐሽ ይትላጸዩ ንስቲተ ሥዕርተ ማእከለ ድማሆሙ። ወዘኢቀተለሰ ኢይትላጸይ። *ወለእለ ነሥኡ አንስቲያ ኢይትላጸዩ[146] እመ ኢቀተሉ።

ወበመዋዕለ ሙልአታ በልዑ ጐሽ[147]። ወይቤሉ እመሰ በላዕናሁ ላህም ውእቱ ኢንትላጸይ ርእሰነ *እመ ቀተልናሁ። ወመንፈቆሙ ይቤሉ በቃለ ትዕይርት ኢንትላጸይ ርእሰነ[148] እመ ቀተልናሆሙ ለሰብአ ሸዋ ወአምሐራ እስመ አልህምት ነባብያን እሙንቱ፤ ወኢይክሉ ተግብኦ።

139. "ኖሙ ለማለት።
140. ሎ በ።
141. ሎ "እሱ።
142. ቨ. ይውእ።
143. ቨ. "ላ።
144. ቨ. "ት።
145. ቨ. ቀተሎ ።
146. ቨ. የለውም።
147. ሎ "ሽ።
148. ቨ. የለውም።

ወኮሉ ጋላ እመኒ ሉባ ወእመኒ ቀንዶላ[149] ዘኢነሥኡ ብእሲተ ይሰመዩ ቄሮ። ወየኃድሩ በፅ ቤት፡ ቄሮ ዘሉባ ምስለ ሉባ፡ ወዘቄንደላ ምስለ ቄንደላ፤ ወቄሮ ዘገበር ምስለ ገበር።

ወይሠይሙ[150] መጠነ ፫ ሰብእ እምኔሆሙ ለሰሪሐ ሰቄላ፤ ወይሰምይዎሙ አጀርቱ።

ዓዲ ይሠይምዎሙ ለጠቢሐ አልሀምት ወይሠመዩ ቀልታ።

ወካዕበ ይሰመዩ[151] ፪ ሰብአ እለ ይጠብሱ ሥጋ ወይመትሩ ወይሁቡ ለኮሉ ዕሩየ በበምታር፤ ወይብልዎሙ[152] ዋጆ።

ወካዕበ ይሠይሙ ፫ ዕደወ ለሐሊበ ወትወት እምአልሀምት[153] ኮሉ፤ ወስሞሙ ሐለብዶ።

ዓዲ ይሠይሙ ፪ ለቀዲሐ ወትወት፤ ወይሁቡ ለለፅ ፅ በመስፈርት፤ ወስሞሙ ጥኒቶ።

ወካዕበ ይሠይሙ[154] ፯ ሰብአ ለአእትዎ አልሀምት፤ ወየኃሥሡ ዘጠፍአ፤ ወስሞሙ በርባዶ።

ወዓዲ የኃርዩ ፪ እምኔሆሙ ወይሠይምዎሙ[155] ከመ ይግሥጹ ወይቅሥፉ ለዘየሐውር[156] ኀበ ብእሲት፤ ወይሰመዩ ጎርሳ። ወዝንቱ ተዓቅቦቶሙ አኮ ለጽድቅ[157] አላ[158] ከመ ይኩኑ ንቁሃነ ወትጉሃነ ለተቃትሎ። ወዘሰ አውሰበ ይሔሊ በዘያሠምራ ለብእሲቱ።

ወካዕበ ይሠይሙ መጠነ ፲ ሰብእ ለነዲአ አልሀምት ወስሞሙ ጠውቱ[159]። ወዘፈቀደ እምኔሆሙ ነሢአ ብእሲት ይትፈለጥ ወይነብር በቤቱ፤ ወይሰምይዎ ጅልሂካ።

ወለአረጋዊ[160] ይሰምይዎ ምልጉዶ። ውእቱኒ ኢየአርፍ እምተፃብአ[161] ለእመ ኢደከመ በሕቁ ከመ አኀዊነ ዘጰ[162] ወአባ ሐራ።

ወአልቦ ከማነ ዘረከበ ፀረ ዘይተግህ ለገቢረ እከይ። ወአልቦ ከማነ ዘረከበ እግዚአ ወንጉሠ ዘይተግህ ለገቢረ ሠናይ። እግዚአብሔር ይዕቀቦ[163] እስከ ዘመን ነዋኅ ወመዋዕል ጕንዱይ፤ ይቤ ባሕርይ። ። ። ።

149. ሎ ቪ።
150. ሎ "የሙ።
151. ይሠየሙ ለማለት።
152. ቪ "ዎዎሙ።
153. ቪ "ት።
154. ቪ "የሙ።
155. ቪ ወሠምይዋሙ።
156. ቪ ለዘ የ"።
157. ሎ ለጻ"።
158. ቪ የለውም።
159. ሎ ጣ"።
160. ቪ ወላአረጋዌ።
161. ሎ ለተ"።
162. ዘጰራቅሊጦስ።
163. ቪ ለገብሩን፡ ሎ ክፍት ቦታ ይጨምራሉ።

# በአማርኛ

(በቅንፍ ውስጥ ያሉት ቃላት ግዕዙ ውስጥ እኩያ ሳይኖራቸው ትርጉሙን አማርኛ ለማስመሰል የገቡ ናቸው።)

የነገዱን ቁጥር፥ ሰውን ለመግደል የትጋቱን ነገር፥ የጠባዩን እንስሳነት ለማወቅ የጋላን ዜና ልጽፍ (እነሆ) ጀመርኩ። "የክፉውን ዜና እንደ ደጎች ዜና ለምን ጻፈ?" የሚለኝ ካለ፥ "በሃይማኖት ጠላቶቻችን ሆነው ሳለ የመሐመድ ታሪክና የእስላሞች ነገሥታት ታሪክ እንደተጻፈ ታይ ዘንድ መጻሕፍትን መርምር" ስል መልስ እሰጠዋለሁ። ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድም[1] የዝንጉዓን[2] የኢራን[3] ነገሥታትን፥ ማለት የእነ አፍሪዶንንና[4] የሌሎቹን የፋርስ[3] ነገሥታት ታሪክ ጽፏል። በዚህ (ባለንበት) ዘመን ሶፊ[5] ይሏቸዋል።

---

1. ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ በ1205–1273 ዓ. እ. የኖረ የዓለምን ታሪክ እስከ 1260 ዓ. እ. በዓረብኛ የጻፈ ቅብጢ/ግብፃዊ ነው። ("ቅብጢ" የግብፅ ክርስቲያኖች መጠሪያ ስም ነው።) መጽሐፉን አባቶቻችን ወደግዕዝ የተረጐሙት በ1290 ዓ. ም. ይመስላል። የዓለምን ታሪክ የሚያውቁት ከ25 በማያንሱ የታሪክ መጻሕፍት ሲሆን፥ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ፥ ዲያቆን አቡሻክር፥ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን፥ ዮሐንስ መደብር፥ ዮሐንስ ጳጳስ ዘኒቂዩ፥ ሰዒድ ወልደ በጥሪቅ፥ ማርቆስ ወልደ ቀምበር፥ ዮሐንስ ዘደማስቆ፥ ወልደ መነኮሳት የጻፏቸው ናቸው። የጳጳስ ዮሐንስ መጽሐፍ በግዕዝ መገኘት የግዕዝ ምንጮችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋጋ ካሰጧቸው ምክንያቶች አንዱ ሆኗል። ጳጳሱ የጻፈው ዐረቦች ግብፅን እንደያዙ የሆነውን በቅርብ ሆኖ የተመለከተውን ታሪክ ሲሆን፥ ድርሰቱ ወደግዕዝ ከተተረጐመ በኋላ ዋናው ጠፍቷል፤ ሌላ ቅጂም አልተገኘም። የኛ ሰዎች ወደግዕዝ ባይተረጕሙት ኖሮ ያ ሁሉ የታሪክ ዕውቀት ይጠፋ ነበር።
2. ደራሲው ዝንጉዓን የሚሉት የባቢሎንን ሕዝብ ነው። ምንጫቸውም ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ ነው፤ ለምሳሌ፥ EMML 21, f. 40b, Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. I, p. 23.
3. ደራሲው የዓረቦችን አነጋገር ተከትለው ፋርሶችን ዐጀም ይሏቸዋል። ዓረቦች በነገድ ዓረብ ያልሆነ፥ አረመኔ የሆነ እና ኢራኖችን ዐጀም ይሏቸዋል። ፋርስ የኢራኖች የቀድሞ ስም ነው።
4. አፍሪዶን ስለሚባለው የኢራን መንግሥት፥ H. Masse, "Farīdun," *The Encyclopaedia of Islam*, Vol. II, Leiden 1991, p. 798, ላይ ተመልከት።
5. ሶፊ በእስላም ሃይማኖት ውስጥ ያለ ልዩ እምነት ነው።

## ክፍል ፩

(የዚህ) መጽሐፍ ባለቤት[6] (እንዲህ) ይላል፤ ጋላው በአፄ ወናግ ሰገድ[7] ዘመን ከምዕራብ[8] ወጥቶ ገለና[9] የሚሉትን የሀገሩን ወንዝ ወደባሊ[10] ዳርቻ ተሻገረ። እሱም በረይቱማ እና ቦረን የሚባሉ ሁለት ነገድ ነው።

በረይቱማ ስድስት ልጆች ይወልዳል፤ በኵሩ ከረዩ ይባላል፤ ሁለተኛው መረዋ፥ ሶስተኛው ኢቱ፥ አራተኛው አከቹ፥ አምስተኛው ወረንጢሻ፥ ስድስተኛው ሁምበና (ይባላሉ)።

ቦረኖች አባታቸው ሰዲራ ይባላል። ሰዲራ ዳጨን ይወልዳል፤ ዳጨ መጫን ይወልዳል። መጫ ደአሌን እና ጂዳን ይወልዳል።

(እነዚህ) ሁለቱ ወንድማማቾች ብዙዎች ነገዶች ወለዱ። እነሱም፥ የደአሌ ልጆች (እነ) ሆኮ፥ ሁለተኛ ጭሌ፥ ሶስተኛ አቦ፥ አራተኛ ሱባ ናቸው። ጂዳ በኵሩን ሐካኮን፥ ሁለተኛውን ጉድሩን፥ ሶስተኛውን ሊበንን ይወልዳል።

---

6. "ደራሲው" ማለታቸው ነው -- "እኔ" ወይም "የዚህ ታሪክ ጸሐፊ" በማለት ፈንታ። የተለመደ አጻጻፍ ነው።
7. ወናግ ሰገድ በ1500-1533 ዓ. ም. የነገሠው የልብነ ድንግል የንግሥ (የዙፋን) ስም ነው። (ግራኝ መንግሥቱን እንዳናወጠበት ይታወሳል።) በግዕዝ "ልብን"፥ "ስኒን" ማለት "ዕጣን" ማለት ስለሆነ "ዕጣነ ድንግል"ም፥ "ስኒነ ድንግል"ም ይሉታል። "ወናግ" ማለት "አንበሳ" ማለት ስለሆነ "ወናግ ሰገድ" ማለት "አንበሳ ሰገድ"፥ አንበሳ ሳይቀር የሚሰግድለት ማለት ነው።
8. ኦሮሞዎች ወደማህል ኢትዮጵያ የገቡት ከኢትዮጵያ ደቡባዊ ምሥራቅ ተነሥተው ወደሰሜን እየተጓዙ ነው። "ከምዕራብ" የሚለው ቃል ወይ የደራሲው ነው ወይም የቀጂው ስሕተት ሊሆን ይችላል። የደራሲው ከሆነ አዲስ ነገር አይደለም፤ ጸሐፊዎቹ አንዳንድ ጊዜ ማእዝንን (የጂኦግራፊን አቅጣጫ) የሚያመለክቱ ቃላትን እንደመሰላቸው ይጠቀሙባቸዋል። የፀሐይ መውጫን አንዳንድ ጊዜ ምዕራብ እንደሚሉት ዲልማን ቀደም ብለው ከተቀዱ መጻሕፍት ውስጥ ለምሳሌ ኢሳይያስ 11፡ 11፥ 45፡ 6ን አግኝቷል፤ Dillmann, *Lexicon linguae aethiopicae*, col. 964. ሁለተኛም፥ "ከምዕራብ ወጥቶ" ሲሉ "ወደ ምዕራብ ወጥቶ" ማለታቸው ሊሆን ይችላል። አባ ባሕርይን ያባረሯቸው ከጋሞ ከሆነ ማህል ኢትዮጵያ የመጡት ከደቡብ በኩል ነው።
9. "ገላና" የሚባሉ ሁለት ወይም ሶስት ወንዞች እንዳሉና ወንዞቹ እነዚያ እንደሆኑ አንዳንድ ጸሐፊዎች ያመለክታሉ -- "ገላና ሰገን" እና "ገላና ዱሌ"። አቶ ብርሃኑ ለሜሶና አቶ ታቦር ዋሚም እነዚያ መሆናቸውን ተቀብለዋል፤ *የኦሮም ሕዝብ ታሪክ* ፥ ገ. 36። በቪየናው ቅጂ ውስጥም ቃሉ "ገላና" ነው። ግን "ገለና/ገላና" በኦሮምኛ "ወንዝ" ማለት ስለሆነ፥ የደራሲው አነጋገር "ገለና የሚለውን የሀገሩን ወንዝ" ማለት ሳይሆን አይቀርም። "ገላና ሰገን"፥ "ገላና ዱሌ" ማለትም "የሰገን ወንዝ"፥ "የዱሌ ወንዝ" ማለት ሊሆን ይችላል።
10. ይህ ጠቅላይ ግዛት (ወይም አውራጃ) ዛሬ "ባሌ" ይባላል እንጂ ቀደም ያለው ዘመን የታሪክ ምንጮች እንደሚያሳዩት፥ "ባሊ" ነበር የሚባለው።

ደግሞ ዳጨ (እነ) ዳጭን -- (እነዚህን) በራሱ ስም ጠራቸው -- (እነ) ኮኖን፥ በቾን፥ ጅሌን ይወልዳል::

እነዚህም ብዙዎች ነገዶች ወለዱ፤ ስማቸውም ይህ ነው፤ የበቾ ልጆች ዑሩ እና ኢሉ፤ የዳጭ ልጆች ሶዶ፥ አቦ፥ ጋላን፤ የኮኖ ልጆች፥ ሰቅሰቅ፥ ሊበን፤ የጅሌ ልጆች ኤላ፥ አቦ እና ልኢስ[11] ናቸው::

እነዚህ ሁሉም ብዙዎች ስለሆኑ ቱለማ[12] ይባላሉ:: አብረው ይወጉ ነበረ:: ከብዙ ዘመን በኋላ ተጣሉና አብርሃምና ሎጥ ከብታቸው በበዛ ጊዜ፥ "ወይ አንተ በቀኝ እኔ በግራ፥ ወይም እኔ በቀኝ አንተ በግራ እንለያይ" እንደተባባሉና እንደተለያዩ እርስ በርሳቸው ተለያዩ፤ (በዚያን ጊዜ) እንደሆነ (አሁንም) ሆነ::[13]

ደግሞ የዳአሌ ሁለቱ ነገድ፥ ማለት ጭሌና ሆኮ፥ እንደዚሁም ሁለቱ የጅዳ ነገድ፥ ሊበንና ጉድሩ[14]፥ ከወንድሞቻቸው ተለዩና ቦረን "አምቢሳ"[15] በሚለው -- በርቱማ "ሮባሌ"[15] በሚለው -- ሉባ[16] ዘመን ጎብረት ፈጥረው "አፍራ"[17] ተባሉ ::

---

11. በግዕዝ "ወ" ዋፄ አያያዥ (መስተጻምር) ስለሆነ በአማርኛ "ና" ወይም "እና" ተብሎ ይተረጐማል፤ ወይም ሳይተረጐም ይቀራል:: በግዕዝም በአማርኛም አንዳንዶቹ መስተዋድዶች እንደ "ወ" ነጠላ ሥጌዎች ሲሆኑ፥ ከሚያዋድዱትና ከሚያጻምሩት ቃል ጋራ አብረው እንደሚጻፉ ይታወሳል:: ያ የሚጻመረው/የሚዋደደው ቃል የታወቀ ሲሆን መስተዋድድ ወይም መስተጻምር እንዳረፈበት ወይም እንዳላረፈበት ማወቅ አያስቸግርም:: ያልታወቀ ከሆነ ግን ችግር ይፈጠራል:: ለምሳሌ እዚህ ቦታ "አቦ እና ልኢስ" ያልኩት ግዕዙ "አቦ ወልኢስ" ያለውን ነው፤ ግን "ወልኢስ" የጀመረበት "ወ" የቃሉ ክፍል ከሆነ የጅሌ ልጆች "ኤላ፥ አቦ፥ ወልኢስ" ሊሆኑ ነው:: ይኸ ችግር በተለይ የሚፈጠረው ደራሲዎች ስም ሲዘረዝሩ አንዳንድ ጊዜ በ "ወ" አንዳንድ ጊዜ ያለ "ወ" እያጻመሩ በመዘርዘራቸው ነው:: ይኸንኑ አንቀጽ ተመልከት::
12. አነጋገሩ የሚያመለክተው "ቱለማ" ማለት ብዙዎች ማለት መሆኑን ነው::
13. ዘፍጥረት 13፡ 9፤ በከብት ብዛት (በሚጥጫ/ቻ) ተለያዩ ማለታቸው ነው::
14. "ጐድሩ" እና "ጉድሩ" አንድ ናቸው:: የተለያዩ ያስመስላቸው የ "ግ" ጣጣ ነው:: "ትርጉም/ትርጉም"፥ ጉራጌ/ጉራጌ፥ "ጐጃም/ጎጃም" የሚለውን ተመልከት::
15. "አምቢሳ"፥ "ሮባሌ" የሠራዊት የስልጣን (ሹሞች ለራሳቸው የሚያወጧቸው አዲስ) ስሞች ናቸው:: ከሚቀጥሉት ክፍሎች እንደምናየው፥ ሌሌች ስሞችም አሉ:: ሐሳቡ "ወናግ ሰገድ" ከሚለው ጋራ ይስማማል:: አሮሞዎች ወደኢትዮጵያ ግዛት ሲመጡ የኢትዮጵያ ንጉሥ የልብነ ድንግል የዙፋን ስም "ወናግ ሰገድ" እንደነበረ ክፍል ፩ ላይ ተነግሮናል፤ "ወናግ ሰገድ" ማለት "አንበሳ ሰገድ" ማለት ስለሆነ "አምቢሳ"ን ከአንበሳ/አምበሳ ጋራ ለማያያዝ ያጓጓል፤ ግን አይያያዝም::
16. ጎብረት ሰቡን ስምንት ዓመት እንዲመራ አብሮ በመገዘር የሚሾመው ትውልድ "ሉባ" ይባላል:: ክርስቲያኖቹ ንጉሡን "መሲሕ"፥ "ሥዩም"፥ "ቅቡዕ" እንደሚሉት፥ "ሉባ" ማለት "ግዙር" ("የተገዘረ") ትውልድ ማለት ነው::
17. "አፍራ" የሚለው ቃል "አፉር" ("አራት") ከሚለው የተወለደ ስለሆነ "አራትዮ" ወይም እነ አራት (ወይም እንደነ እለ አሚጻ "እለ አርባዕቱ") ተብሎ ሊተረጐም ይቻላል:: እነሱም፥ (1) ጭሌ፥ (2) ሆኮ፥ (3) ሊበን፥ (4) ጉድሩ ናቸው::

ደግሞ የጅዳ ልጅ ሐካኮና የደአሌ ልጆች አቦ እና ሱባ "ቢርመጂ" በሚባለው ሉባ ዘመን ጎብረት ፈጥረው "ሰደቻ"[18] ተባሉ። እነዚህም ብዙዎች ነገዶች ወለዱ። ስማቸው ይህ ነው፤

የጭሌ ልጆች ገላም፥ ወቦ/አቦ[19]፤
የሆኮ ልጆች ኪረሞ፥ እሙሩ፥ ጂዳ፤
የሊበን ልጆች ዋሊሶ፥ ኮታቄ፥ አምዬ፤
የጉድሩ ልጆች ሲርባ፥ መሎል፥ ጨረቃ፤
የሐካኮ ነገድ አቦ፥ ሐርሱ፥ ሊሙ፤
የሱባ ነገድ ሐገለባቦ፥ ጩራ፤
የአቦ ነገድ ሶዮ፥ አቦኖ፥ ቱምኤ፥ ሌቃ (ይባላሉ)።

እነዚህ ሁሉም ሲፋቀሩ "መጫ"[20] ይባላሉ፤ ሲጣሉ "አፍሬ" እና "ሰደቻ" ይባላሉ። ሁሉም ከቱለማ ጋራ ሲያብሩ "ሰጲራ"[21] ይባላሉ።

ቦረን ደግሞ ዓሥራ ሁለት[22] ልጆች ይወልዳል። በኵሩ ዳጨ ነው፤ ሁለተኛው ጅሌ፥ ሶስተኛው ኮኖ፥ አራተኛው በቾ፤ እነዚህ (አራቱ) "ቱለማ" ይባላሉ፤ አምስተኛው ሀካኮ፥ ስድስተኛው አቦ፥ ሰባተኛው ሱባ፤ እነዚህ (ሶስቱ) "ሰደቻ" ይባላሉ፤ ስምንተኛው ጭሌ፥ ዘጠነኛው ሊበን፥ ዓሥረኛው ጉድሩ፥ ዓሥራ አንደኛው ሆኮ ናቸው፤ እነዚህ (አራቱ) "አፍሬ" ይባላሉ።

---

18. "ሰደቻ" የወጣው "ሰዲ" ("ሶስት") ከሚለው ቃል ስለሆነ "ሶስትዮ" (እነ ሶስት፥ እለ ሰለስቱ) ተብሎ ሊተረጐም ይቻላል።
19. የሎንዶኑ (ሎ) ቅጅ "ወቦ"፥ የቪየናው ቅጂ "አቦ" ነው የሚለው፤ በምርጫ ጊዜ ስላለው ችግር ከላይ ቁጥር 11ን ተመልከት። ሌላው አጻጻፍ የሚያመጣው ችግር "ም" እና "ን" ከ"በ" ዘር ሲቀድሙ ዘሩ ይውጣቸዋል። ለምሳሌ "አቦ" በመሠረቱ "አምቦ" ሊሆን ይችላል።
20. "ሲፋቀሩ" ማለት "ሲተባበሩ" ማለት ነው። ስያሜው እንደሌሎቹ ቁጥርን የሚከተል ስላይደለ፥ እነዚህ ጎሳዎች "መጫ" የተባሉት ሃያ ስለሆኑ ነው ብሎ "መጫ"ን "ሃያዮ" ("እነ ሃያ") ብሎ መተርጐም አይቻልም፤ "መጫ" ከ"ዲግደማ" ("ሃያ") ጋራ ግንኙነት የለውም።
21. "ሰጲራ" ኦሮምኛ መሆኑ ይገርማል። ቃሉ ግዕዝ ከግሪክ የወሰደው ሲሆን ትርጉሙ "ጭፍራ" ማለት ነው። የኦሮሞ ሽማግሌዎችም ስሙን የሚያውቁት አይመስሉም። ብላታ መርስዔ ጎዘን እንዲህ ይላሉ፤ "አባ ባሕርይ ሰጲራን የነገድ ራስ አድርጎ ሲጽፍ ስለራያ ምንም የጠቀሰው ነገር የለም። አንዳንድ (የኦሮሞ) ባላባቶች እንደሚተርኩትም የነገድ ራስ የሚሉት ራያን ሲሆን፥ ሰጲራ የተባለውን ስም ግን እንደማያውቁት ይገልጻሉ።" (EMML 3749, p. 57)። ይኸ "ኦሮሞዎች ከፖርቱጋሎቹ ጋራ ግንኙነት አላቸው" የሚባለው ትረካ ትንሽ እውነትነት ሳይኖረው አይቀርም።
22. የተዘረዘሩት ዓሥራ አንድ ብቻ ስለሆኑ ዓሥራ አንድ ለማለት ይሆናል፤ ወይም የዓሥራ ሁለተኛው ልጅ ስም ሳይጻፍ ቀርቷል።

## ክፍል ፪

በጥረ አሞራን[23] ያጠፋ ዳዌ ከቦረን ሰዎች ነው፤ ከሌላ ነው የሚልም አለ፤ (ከሌላ ነው የሚል) ከቦረን ጋራ መዋጋቱን ምክንያት ይሰጣል። ይኸ ግን ሞኝ ነገር ነው፤ እውነት አይደለም። አስረጂ ግን (እንዲህ) ይላል፤ "(ጋሎች) ከሀገራቸው የወጡ ጊዜ የፈለገ (እዚያው) ቀረ፥ የፈለገ ወጣ እንጂ ሁሉም አልወጡም።" ምክንያቱም (ሁሉም) በልቡ ያሰኘውን ያደርጋል እንጂ የሚያዛቸው ጌታ የለም።

እነዚያ ከቦረን (ተቈርጠው) የቀሩት (በኋላ) ከሀገራቸው በኴራ[24] መንገድ ወጡ። ፋሲል ዘምቶባቸው ነበረ፤ ገደሉት። በዚያን ጊዜ ዳዌ ክርስቲያኖችን መውጋት ጀመረ።

በዚያን ጊዜ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ[25] "የፋሲልን ገዳይ እፈራዋለሁ"[26] ሲል ተነበየ፤ ምክንያቱም የክርስቲያን ደም ቀምሷልና፤ በጥራ አሞራንና

---

23. በጥረ አሞራ (በጸር አሞራ) የሠራዊት ስም ነበረ። በኋላም ሠራዊቱ የሠፈረበት ሀገር በስሙ ተጠርቷል። ሰውና ሕዝብ ስሙን ለሀገር፥ ሀገር ለሕዝብና ለሰው መስጠት በኛ አካባቢና በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ ነው። በጥራ አሞራ (በጥራሞራ) ጉራጌ ውስጥ ወይም አጠገብ ነው።

24. ለጥንት ነገሥታት ለነአዜ ይሥሐቅ በተገጠመላቸው ዘፈን ውስጥ "ኴራ ይንገር፥ ፈረሱን የሚገብር" የሚል ስላለበት "ኴራ"ን እንደ ሀገር/ነገድ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፤ Guidi, "Le canzoni geez-amariña", p. 56። የቪየናው ቅጂ "ካራ" እንደሚል አይተናል። ሌሎች አንዳንድ ምንጮች ጎራ ይላሉ። "ኴራ" የሚባለው ቦታ ሻሸመኔ አጠገብ ያለው ኮዮራ ነው የሚባለውን ብርሃኑ ለሜሶና ታቦር ዋሚ (*የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ*፥ ገ. 55) ተቀብለውታል። አቶ አምበሉ ከበደ በገሙ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት በዳኝነት ያገለግሉ በነበረበት ጊዜ ስለጨንቻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም. በጻፉት ማስታወሻ ላይ ጨንቻ ጥንት "ነራ" ይባል እንደነበረ ከሀገሩ ሽማግሌዎች የሰሙትን መዝግበዋል፤ EMML 5731, f. 114a. ዳዌ አባ ባሕርይን ጋሞ በነበሩበት ጊዜ የዘረፋቸው ዛሬ ጨንቻ በፊት ነራ/ኴራ በሚባል ቦታ አቅጣጫ መጥቶ ሊሆን ይችላል። ከአርባ ምንጭ በደቡብ ምሥራቅ አምሳ ኪሎሜትር ያህል ርቆ ኮይራ የሚባል ቦታ/ነሳ አለ። ከዚያ ደቡቡ "ቦረና አሮሞ" ስለሆነ፥ ለኴራ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚው እሱ ነው፤ ዳዌ ከቦረን ሰዎች እንደሆነ አባ ባሕርይ ነግረውናል። Bender, *The Non-Semitic Languages of Ethiopia*, p. 298። ለማንኛውም ስለዚህ ቦታ አንዳች አስተያየት ስንሰጥ አባ ባሕርይ የሰጡን ስም "ኴራ" መሆኑን ሳንዘነጋ መሆን አለበት። "ኮዮራ" ወይም "ኮይራ" ስላላሉ፥ "ኴራ" እንዴት "ኮዮራ" ወይም "ኮይራ" ሊሆን እንደሚችል ሳናስረዳ "ኮዮራ" ወይም "ኮይራ" ነው ማለት አይፈቀድልንም።

25. እንደ በፊቱ "(የዚህ) መጽሐፍ ባለቤት" አላለም፤ ከላይ ቍጥር 6ን ተመልከት። "ይቤ ጸሐፌ ዝንቱ ታሪክ" የጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድም ቋንቋ ነው።

26. አፄ ሠርፀ ድንግል በነገሡ በሶስተኛው ዓመት ፋሲልን የዳሞት ገዢነት ሾሞት ነበረ፤ ባመቱ ተጣልተው ተዋጉ፤ ተሸነፈ፤ ዜና መዋዕል EMML 7109, f. 58b። ሱስንዮስ ለመንገሥ ሲያምፅ የመንግሥቱ ሠራዊት ወራሲ ልጁን ያዕቆብን

ወጅን[27] አጠፋቸው። እንደ ቃሉም ተፈጸመ፤ ምክንያቱም የትንቢት መንፈስ ከካህናት ዘንድ አይርቅም። ይኸንንም ነቢይ ዳዊ አባረረው፤ የገሞ አገሩንም አጠፋው፤ የአካበተውንም ሁሉ ማረከ(በት)።

እንግዲህ እስከዚች ሰዓት ድረስ ወደተውነው ወደበረይቱማ ዜና እንመለስ።

## ክፍል ፫

ከረዩ ስድስት ልጆች ይወልዳል። ብዙዎችና ኃይለኞች ነገዶች ሆኑ። ከነሱ የመጀመሪያው ሊበን ነው፤ ሁለተኛው ወሎ፥ ሶስተኛው ጅሌ፥ አራተኛው አቦ፥ አምስተኛው ሱባ፥ ስድስተኛው በላእ ናቸው።

ወሎ ስድስት ልጆች ይወልዳል፤ እነዚህም ወረ ቡኮ፥ ወረ ጐራእ፥ ወረ ኖሌኤሉ -- እነዚህ በወሎ ስም አሉ -- ወረ ከረዩ፥ ወረ ኢሉ፥ ወረ ኖሌአሊ ሲሆኑ፥ እነዚህ ሶስቱ ደግሞ "ሰደቻ" ይባላሉ። የተለዩት አቦሊን የገደሉ ጊዜ ነው[28]። አሁን በኛ ላይ እርቅ አድርገው አሜሩ፤ ቃል ኪዳን ተጋቡ።

## ክፍል ፬

መረዋ አያ አናን፥ ዑሩን፥ አበጢን ይወልዳል። (የነሱም) ልጆቻቸውና የልጆቻቸው ልጆች እንደዚሁ በዝተው ብዙዎች ነገዶች ሆኑ። ስማቸው በየነገዳቸው (ስም) ይጠራል።

ለስምንት ዓመት ለአንድ ሉባ ይታዘዛሉ እንጂ እንደ ሌላ ሕዝብ (የሚታዘዙት) ንጉሥም ጌታም የላቸውም። ከስምንት ዓመት በኋላ ሌላ ሉባ ይሾማል፤ የፊተኛው (ሉባ) ይሻራል። በየዘመኑ እንደዚህ ያደርጋሉ።

ሉባ ማለት በአንድ ዘመን የተገዘሩ ማለት ነው።[29] የአገዛዘራቸው ሥርዓትም እንደዚህ ነው፤ አንድ ሉባ ሲሻር በርቱማና ቦረን ሁሉም ለ(የ)ራሳቸው ስም ያወጣሉ፤ (ልክ) የንጉሥ ሠራዊት "ሥሉስ ኃይሌ"፥ "በድል ፀሐይ"፥ "ጊዮርጊስ ኃይሌ" እንደሚባሉት።[30]

---

አጅበው፥ "ፋሲልን ያሸነፍነውና ያዋረድነው እኛ አይደለንምን" ብለው ፎክረውበት ነበረ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ገ. 86። ጐጃምና ዳሞት የተያያዙ ናቸው።

27. ጉራጌ ውስጥ ወይም አጠገብ።

28. አቦሊ የሞተው ሠርፀ ድንግል በነገሠ በ22ተኛው ዓመት (በ1576 ዓ. ም.) ነው፤ ጌታቸው ኃይሌ፥ ባሕረ ሐሳብ፥ ገ. 248። ገዳዩም "ጋላ ወሎ" ነው፤ ዜና መዋዕል፥ EMML 7109, f. 59ab.

29. "በአንድ ዘመን የተገዘሩ" ሲሉ ሉባ ማለት "አንድ የግዝር ትውልድ" ማለት መሆኑን በግልጽ ያስረዳል።

30. ለጦር ሠራዊት ክፍሎች እንደዚህ ስም መስጠት እስከቅርብ ጊዜ የተለመደ ነበረ። ታሪክ ነገሥቱና ሌሎችም ምንጮች እንደሚያመለክቱት በተጨማሪ እነዚህ ትዝ ይሉኛል፤ "አፍሮ አይገብ"፥ "አቄትገር"፥ "ቀኦርባን"፥ "ስናን"፥ "ዳማ"፥ "ነፋኝ

## ክፍል ፩

እንደዚሁ ባሊን መውጋት በጀመረበት ጊዜ የተገዘረው "ሜልባሕ" ይባላል። የአባቱን ስም አላውቅም፣ ምክንያቱም የሚነግረኝ (አስረጂ) የለም።

## ክፍል ፪

ሁለተኛው ሉባ "ሙደና" ተባለ። የዚህ (ሉባ) የአባቱ ስም ጅበና ነው። የወቢን ወንዝ የተሻገረ እሱ ነው።[31]

## ክፍል ፫

ሶስተኛው ሉባ "ኪሎሌ" ተባለ። እንደ አደል መብረቅና[32] እንደቄላዎቿ (ያሉትን) የደዋሮን[33] ቆላዎች ወጋቸው።

## ክፍል ፬

አራተኛው ሉባ "ቢፎሌ" ተባለ። ደዋሮን በመላዋ ያጠፋ እሱ ነው። ፈጠጋርንም[34] መዋጋት ጀመረ።

ሰው (ማርኮ) ማጋዝ ጀመረ፣ አገልጋዮች አደረጋቸው፣ "ገበር" አላቸው። ኮሶ መጠጣት ጀመረ። (ከላይ) የጠቀስናቸው የፊተኞቹ

---

ዘገር"፣ "ማንደበል"፣ "ሳንደር"፣ "በፀር ዋጀት"፣ በፀር ሾተል፣ "ቀስተ ንህብ"፣ "አደል መብረቅ"፣ "ቢለማ"፣ "ቤርሳ"፣ "ጨፈንታ"። በዚያ ላይ "ጎይላት"፣ "አርባብ" እያሉ በነገደ መላእክት ስምም የሚጠሯቸው ነበሩ።

31. ከኢትዮጵያ ግዛት የገቡት ግን የወቢን ወንዝ ከመሻገራቸው በፊት ነው።

32. "አደል መብረቅ" በመሠረቱ የጦር ሠራዊት ስም ነው። እዚህ ግን "እንደ አደል መብረቅና እንደ ቄላዎቹ" ሲል የሚያመለክተው ሠራዊቱ የሰፈረበትንና ቄላዎቹን ነው።

33. ደዋሮ ከጨርጨር እስከ አሩሲ (አርሲ) ያለው አገር ይመስላል። ኡሎ ዐፅሜ አሁን ሶዶ የተባለው ነው ይላሉ። ግን ግራኝ ሲያምፅ መጀመሪያ የመታው ደዋሮን ስለሆነ ለአዳል ቅርብ መሆን አለበት። ገዳማቸውን ደብረ አሰቦትን ጨርጨር ውስጥ የቆረቆሩት የአቡነ ሳሙኤል ዘወገግ ገድልም የሚያመለክተው ይህንኑ ነው፤ Kur, *Actes de Samuel de Wagag*, p. 84 ። ከድርሳነ ዑራኤል አንዱን አንቀጽ ብንተረጉመው እንዲህ ይላል፣ "ከዚህ በኋላ (ዑራኤል) ወደፀሐይ መውጫ ሄደ፣ ከደብረ ጽባሕ ላይም ወጣና የደብረ ያግሙንና የደብረ ጎዝሎን ገዳሞች ሁሉ ቀደሳቸው። ደብረ አሰቦት ላይ ሲወጣ ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ዑራኤልን እንዲህ ሲል ነገረው፣ ይቺን ደብር ቶሎ ባርካት፣...። በዚህ ጊዜ ቶሎ ቀደሳት ደብሯንም ደብረ ወገግ አሏት።"

34. ፈጠጋር በቡልጋና በጉራጌ ማህል ያለው አገር ይመስላል፣ ምንጃርን ይጨምራል።

ሉባዎች ግን ሰውን፥ ወንዱንም ሴቱንም፥ ይገድሉ ነበረ። ፈረስም በቅሎም ይገድሉ ነበረ። ከበግ፥ ከፍየል ከከብት (ከላምና ከበሬ) በቀር (ምንም) አይተውም ነበረ። የሆዳቸው አውሬ[35] እንደእንስሳ በቋንጃቸው ላይ ይወርዳል እንጂ በመዳኒት አይገድሉትም ነበር።

## ክፍል ፱

አምስተኛው ሉባ "ምስሌ" ተባለ። ጐን አሞራን[36] የፈጀ እሱ ነው። ሐመልማልን[37] ደጎ ላይ ወጋው፤ አገሮቹን ሁሉ አጥፍቶ ሠለጠነባቸው። ከነከብቱም ገባ(ባቸው)። በፊት ግን ጋላው ከወቢ እየወጣ ይዋጋና ወደዚያ ይመለስ ነበረ።

ንጉሣችን አጽናፍ ሰገድ[38] ከዓሣ ዘነብ ተነሥተው ወግተውት ነበር። ኑር የሠራውን ከሠራ በኋላ[39] ወደ ሀገሩ ሲወርድ ጎዘለሎ አጠገብ ገጠመው። ቀጥር የሌለውን አብዛኛውን ሠራዊቱን ፈጃቸው። ጋሎች ወደሀገራችን ከመጡ ጀምሮ በዚያን ጊዜ እንዳለቁት አላለቁም። ያን ጊዜ የተገደሉት የኑር ሠራዊትም በጊዜው ከምናነሣቸው ከአውሣ ሠራዊት ይበዛሉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በመጅ ያፈሰሱትን የአገልጋዮቹን የደም በቀል (አስ)ከፈላቸው።[40]

---

35. በመዳኒቱ ስም በኮሶ የሚጠራው እርጥብ ሥጋ ሲበሉ የሚይዘው ትል።
36. "ጐን አሞራ" እንደ "በጥራ አሞራ"፥ በመሠረቱ የሠራዊት ስም ነበረ።
37. ሐመልማል የአፄ ናኦድ (1488-1500) የልጅ ልጅ ነው። ሐመልማል ያዘመተው ሠራዊት ጐን አሞራ ሊሆን ይችላል።
38. አጽናፍ (አጥናፍ) ሰገድ የአፄ ገላውዴዎስ (1533-1551) ስመ መንግሥት ነው።
39. ኑር ሙሐመድ አልሙጃሂድ የግራኝን አልጋ ከነሚስቱ የወረሰ የአዳል ኢማም ነበረ። (የአዳል ኢማሞች የመሾም የመሻር ሙሉ የውስጥ ሥልጣን ስለነበራቸው የግዕዙ ምንጮች "ንጉሥ" ይሏቸዋል።) ገላውዴዎስን ወግቶ አሸንፎታል። ደራሲው "የሠራውን ከሠራ በኋላ" የሚሉት አፄ ገላውዴዎስን ካሸነፈና ብዙ ሕዝብ ከፈጀ በኋላ የንጉሡን አንገት ቆርጦ ቸብቸቦውን በዘንግ ጫፍ ይዞ መሄዱን በቁጭት ለማስታወስ ነው። (የንጉሡን ራስ አልባ ሰውነት አምኃራ ሳይንት ውስጥ ባሠራት በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቀበሩት፤ ራሱን በኋላ አምጥተው ሸዋ ውስጥ ገሚ ከሚባል አገር ከወንድሙ ከአቤቶ ያዕቆብ መቃብር አጠገብ ቀበሩት።)
40. ደራሲው "በጊዜው ከምናነሣቸው" ያሉትን አንሥተውት ቢሆን ብዙ ታሪክ ይነግሩን ነበረ። የገላውዴዎስን ታሪክ የጻፉት እሳቸው ከሆኑ ያንን ማለታቸው ሊሆንም ይችላል። ሆኖም አዳሎች (እስላሞች) እና ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ምድር ላይ አያልቁ እልቂት እንደተላለቁ ይህ አንቀጽና ሌሎችም ብዙ ምንጮች ይጠቁማሉ። አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች "በመጅ ያፈሰሱት ደም" የሚለው አዳሎች አፄ ገላውዴዎስን የገደሉ ጊዜ የፈሰሰውን ነው ይላሉ፤ ልክ አይመስለኝም። ሌሎቹ ምንጮች፥ የራሱ የገላውዴዎስ ታሪክ ሳይቀር፥ ንጉሡ የተገደለበትን ቦታ "ነጭ ሣር" ይሉታል። ደራሲው፥ "እግዚአብሔር በመጅ ያፈሰሱትን የአገልጋዮቹን የደም በቀል አስከፍሏቸዋል" የሚለውን ዐረፍተ ነገር ሊጽፉ ከሚገባው ቦታ ትንሽ ስላራቁት ያሳስታል እንጂ ይኸኛው የሚነግረን

ይህ ምስሌ (በጋሎች ዘንድ) ከሱ በፊት ያልተደረገውን በፈረስና በበቅሎ መቀመጥ ጀመረ[41] -- የፊተኞቹን ሉባዎች "በሁለትና በሶስት እግር የሚሄዱትን በአራት እግር እንዲሄዱ አደረግኋቸው" እስኪላቸው ድረስ። በሶስት እግር ማለቱ በመንገድ ሲደክሙ ጦራቸውን ስለሚመረኮዙ ነው።

## ክፍል ፲

ያነሣናቸው አምስቱ ሉባዎች አርባ ዓመት ገዙ። ልጆቻቸው አልተገዘሩም ነበረ። ወሸላዎቹ (አባቶች) ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ይጥሉ ነበረ፤ ምክንያቱም ሕጋቸው እንደዚህ ነው። (አባቶች) ሲገዘሩ ወንዶች ልጆችን ያሳድጋሉ። ሴቶቹን ልጆች ግን ከተገዘሩ በኋላም ሁለትና ሶስት ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ (የሚወልዷቸውን) ይጥሏቸዋል።[42]

## ክፍል ፲፩

ከአምስቱ ሉባዎች (አመራር) በኋላ የሚልባሕ ልጆች ተገዘሩ፤ "ሐርሙፋ" ተባሉ። ይህ (ሐርሙፋ) ጊዮርጊስ ኃይሌን ቀጭኖ ላይ ፈጃቸው። ቦረን "ዱሉ" ይለዋል። ገኝን፥ አንጐትን፥ አምሐራን ያጠፋቸው እሱ ነው።[43]

በጌምድርን መውጋት የጀመረ እሱ ነው። የበርቱማ ሐርሙፋ በጌምድርን ወጋ፤ የሐርቦን ወንድም ዋካንም[44] ገደለው። በዚያን ጊዜ ሐርሙፋ በስድብ ቃል (እንዲህ) ሲል ተናገረ፤ "ባሕር የሚለብሱትን ሲዳማዎች ከባሕር ገፈተርኳቸው።"[45]

---

በ1570 በወይናደጋ መጅ/መዣ ወንዝ ላይ ከአበጠ ጋራ ያደረጉትን መተላለቅ ይመስለኛል፤ የክፍል ፲፪ን መጨረሻ ተመልከት። የመንግሥቱ ሰዎችም፥ "የአበጠን ጋላ ያሸነፍን እኛ ነን አኮ" እያሉ ሱስንዮስን አስፈራርተውበታል፤ የሱስንዮስ ታሪክ ገ. 86.

41. ዛሬ በፈረሰኝነት የሚታወቁ አሮሞዎች ለካ ፈረስ ግልቢያ የተማሩት ማህል ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ነው።

42. ግዝረትን የምናያይዘው ከሕፃናት/ከልጆች ጋራ ስለሆነ፥ ድርሰቱም "ልጆቻቸው አልተገዘሩም" በማለቱም፥ መልእክቱ ሊያሳስተን ይችላል። ድርሰቱ የሚናገረው ስላልተገዘሩ አባቶች እንጂ ስለልጆች አይደለም። ወንዶቹ ልጆች ሳይገዘሩ ያድጉና ወሸላ እንደሆኑ ልጅ ይወልዳሉ፤ ወሸላ አባት የወለደው ልጅ የትም ይጣላል፤ ሕጋቸው ነው። ከተገዘሩ በኋላ የተወለደ ልጅ ወንድ ከሆነ ያሳድጉታል፤ ሴት ከሆነች የተወለደችው የአባቷ ግዝራት ሁለት ወይም ሶስት ዓመት ሳይሆነው ከሆነ ትጣላለች። ይኸንን ባህል አዛዥ ጢኖም በሱስንዮስ ታሪክ ውስጥ መዝግበውታል፤ ገ. 215፤ እዚህም ገጽ 150-151 ላይ ተጠቅሷል።

43. በአቀማመጥ እነዚህ ሶስት አገሮች (ገኝ፥ አንጐት፥ አምኃራ) የተያያዙ ነበሩ ማለት ነው።

44. የቤገምድር ገዥ ይመስላል።

45. ለክርስትና የሚጠመቁትን ማለቱ ነው፤ አነጋገሩ በግዕዝ ምንጮች የተለመደ ነው።

## ክፍል ፲፪

ከስምንት ዓመት በኋላ፥ ሐርሙፋ ተሻረና ስሙ (እላይ) በክፍል ስድስት የተጻፈው የሙደና ልጅ ሮባሌ ተሾመ። ሸዋን ያጠፋት እሱ ነው። ጎጃምን መውጋት ጀመረ።

ሐፄ ዝዋይ ላይ ወጉት[46]። ብዙ (ሰው) ፈጁበት፤ ከብቱንም ማረኩበት። በምርኮው ብዙዎች በለጸጉ(በት)።

ሰላም ይረፍበትና የመኳንንቱን ራስ፥ አዝማች ዘርአ ዮሐንስን፥ የገደለው እሱ ነው[46]።

በዚያን ዘመን በቦረኑ ነገድ በሱባ (ዘንድ) ሶሊ እና ቢዳሮ ኢላላ ሆነ።[47]

---

"ሲዳማ" የሚሉት ክርስቲያኖችን ከሆነ በዚያን ጊዜ ሲዳማዎችም እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ (ለምሳሌ እንደ ጉራጌ፥ ትግሬ) ክርስቲያኖች እንደነበሩና ክርስትና በደቡብ ተስፋፍቶ እንደነበረ ያሳያል። ሃበርላንድ ያዘጋጀውን ቤተ ክርስቲያኖች የነበሩበትን ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ ተመልከት፤ Haberland, *Untersuchungen*, p. 246. ሃበርላንድ ኢትዮጵያውያን የክርስትና አስተማሪዎች ክርስትናን በደቡብ አስፋፍተው እንደነበረ ለማሳየት ያደረገው ረጂም ንግግር እዚህ ላይ ሊታወስ ይገባል። "Altes Christentum in Süd-Äthiopien." አባ ባሕርይም አገራቸው ጋሞ እንደነበረ ነግረውናል። የደራሲውን ነገድ ከአነጋገራቸው ለማወቅ ባይቻልም የእሳቸው እዚያ መገኘት አገሩ ትልቅ ማኅበረ ክርስቲያን እንደነበረበት ያመለክታል። አባ ባሕርይን ያህል ሊቅ ባለበት ቦታ ትልቅ ተማሪ ቤትም ይኖራል። አቶ ዐፅሜ እንደነገሩን፥ ከፋ ውስጥ ደኑ አሮሞዎችን ከነከብታቸው አላስገባ በማለቱ ከአሮሞ ዱላ የተረፉ አንፊሎች እስከ አፄ ምኒልክ ዘመን ድረስ ክርስቲያኖች ነበሩ፤ ዐፅሜ/ባይሩ ተፍላ፥ *ቦጋላ ታሪክ*፥ ገ. 164፤ Bender, *The Non-Semitic Languages of Ethiopia*, p. 298. "ማያ" የሚባሉትም ነገድነታቸው በምን እንደሆን አይታወቅም፤ በሃይማኖት ከሆነ እንደ ክስታኒ ጉራጌዎች ክርስቲያኖች ነበሩ፤ "አፅእምነ ማያ ዘስሙ ምክሀ ጊዮርጊስ ወልደ ዓስቦ" ("ከማያዎች ውስጥ አንድ ስሙ ምክሀ ጊዮርጊሰ የሆነ የዓስቦ ልጅ") የሚለውን ከዮሐንስ/አእላፍ ሰገድ ታሪክ ውስጥ ገ. 39 ላይ ተመልከት።

46. "ሐፄ" (ንጉሡ አፄ ሠርፀ ድንግል) ሮባሌን (አምቢሳን?) የወጋው በነገሠ በ10ኛው ዓመት (በ1565 ዓ.ም.) ነው፤ ዜና መዋዕል EMML 7109, f. 59a ። "ሐፄ" ማለት "ጃንሆይ" ማለት ነው። የሠርፀ ድንግል ታሪክ ጸሐፊ የነገረን አዝማች ዘርአ ዮሐንስ መሞቱንና ሎሌዎቹ እንዳይበተኑ ንጉሡ አጽናንቶ ከሎሌነት አውጥቶ በባለርስ ወታደርነት (በጨዋነት) እንደከተባቸው እንጂ እንዴት እንደሞተ በግልጽ አይናገርም፤ የሠርፀ ድንግል ታሪክ ገ. 45።

47. የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጉም በሰዋስዉ መሠረት ልክ ቢሆንም፥ መልእክቱ ግልጽ አይደለም። በዚህ አነጋገር "ሱባ" የሚባሉ "ብዙ" (ከአንድ በላይ) ነገዶች አሉ፤ አንዱ የቦረኑ ነው። ("ነገደ ሱባ ዘቦረን" ማለት "የቦረኑ ነገደ ሱባ" ማለት ነው።) ሌሎቹ ጥያቄዎች አንደኛ፥ "ኢላላ" ማነው ወይም ምንድን ነው?፤ ሁለተኛ፥ "ሶሊ እና ቢዳሮ" መሆን ወይም መደረግ ምን መሆን/መደረግ ነው? ያም ሆነ ይህ፥ እንደ ግዕዙ ከሆነ፥ በቦረኑ ነገደ ሱባ ዘንድ ኢላላ ሆኗል/ተደርጓል። ትርጓሜውን ሰዋስዉ አይፈቅድም እንጂ፥ ቢፈቅድ "ሶሊ" እና "ቢዳሮ" የቦታ ስሞች (ተራሮች?) ሆነው

ከዚህ በኋላ በአምስት ዓመቱ ሐፄ የአበጊን ሮባሌ ወይና ደግዓ ላይ ወጉትና (ምንም) ሳያስተርፉ ፈጁት::[48] "ከዓሥር የሚበልጡ ተርፈው ለዜና ሀገራቸው ደርሰዋል" የሚሉም አሉ::

## ክፍል ፲፫

ከስምንት ዓመት በኋላ፥ ደዋሮን ያጠፋው የኪሎሌ ልጅ "ቢርመጂ" ተሾመ:: ይኸ የቦረኑ ቢርመጂ በቁመቱ ልክ የሚሆን የበሬ ቆዳ ጋሻ አበጀና ወስፈንጥረኞች የሆኑትን ማያን ወጋቸው::[49] የሚነድፉት (አካል) ስላጡ(በት) አሸነፋቸው፤ ምክንያቱም ሰውነቱን በደረቅ የበሬ ቆዳ ጋርዶ ነበረ::

የንጉሡን የጦር አለቃ አዝማቺ ደኑረሳትንም[50] አስጨነቀው:: እነ ዜናይንና ሎሌዎቹን ገደላቸው:: ቀድሞ ብዙ ጊዜ ያሸንፈው ነበረ:: ግን የክርስቲያኖች ፍዳ ስላላለቀ በእግዚአብሔር ፈቃድ (እንዲህ) ሆነ:: አሸናፊው ተሸነፈ፤ የሹመት ሀገሩን አርእኝን አጠፋት:: እነ ጋቶን፥ በትሮን፥ በድሎን፥ ዓምዶን እና ሌሎችን ገደላቸው:: ደኾች ሁሉ የሚበለጽጉባቸው እነዚህ ሁለቱ አገሮች ምድረ በዳ ሆኑ::[51]

---

ለኢላላ (ለጠላት ጥበቃ) መጠቀሚያ ሆነዋል:: "ኢላላ" በአማርኛ "ይላላ" ("ስለላ") ሆኗል:: ግን "ሶሊ እና ቢዳሮ የሚባሉ ሁለት ዓይነት (የ)ኢላላ (ለቅሶ ወይም ማስጠንቀቂያ) ሆነ/ተደረገ" ማለት ሳይሆን አይቀርም:: አንዱን ትርጉም ያሳሰበኝ ታሪኩና አቶ አምሀ አሰፋው ከነገረን የ"ይላላ ደነባ" ለቅሶ ናቸው:: ታሪኩ በዚሁ ክፍል "ሐፄ ዝዋይ ላይ ወጉት:: ብዙ ፈጁበት፤ ከብቱንም ማረኩበት" የሚለው ነው፤ ስለለቅሶው አምሀ አሰፋው *ይላላ ደነባ* በሚል ርእስ በ1995 ዓ. እ. ያሳተመውን መጽሐፍ ተመልከት:: ስለ ማስጠንቀቂያው የሞረሹ ደወል "በደሩ" ይባል እንደነበረ ሴኪ ነግሮናል፤ Cecchi, *Da Zeila alle frontiere del Caffa*, Vol. II, pp. 327-8, n. 1. and Vol III, p. 123.

48. አፄ ሠርፀ ድንግል አበጊን ደግዓ ላይ የመታው በ1570 ዓ. ም. ነው፤ *ባሕረ ሐሳብ* ገጽ 248:: የሱስንዮስ ታሪክ ጸሐፊ እንደሚነግረን መኳንንቱ ድሉን እንደ ታላቅ ድል ይመኩበታል፤ "የአበጊን ጋላ ያሸነፍንና ምንም ሳናስተርፍ የፈጀነው እኛ ነን እኮ" ይላሉ ገ. 86:: ይህ የሆነው አዝማች ዘርአ ዮሐንስን ጋላ በገደለው በአምስት ዓመት ከሆነ፥ አዝማች ዘርአ ዮሐንስ የሞተው በ1565 ዓ. ም. (ከ1570 ላይ 5 ቀንስ) መሆኑ ነው::

49. "ማያ" የሚባሉ ኢትዮጵያውያን በቀስት መንደፍ የታወቁ ነበሩ:: በቄላውም በደጋውም የሚኖሩ ነገዶች ነበሩ፤ ዛሬ የሉም:: ከላይ ቍጥር 45ን ተመልከት::

50. ደኑረሳት የታወቀ ጀግና አዝማች (ጄኔራል) ነበረ:: በፈላሻ ላይ ዘምቷል፤ የሠርፀ ድንግል ታሪክ ገ. 91:: ትግሬ መኮንን (የትግሬ ገዥ) እና ባሕር ነጋሽ (ዛሬ ኤርትራ የተባለው አገር ገዢ) ሆኖ ደኸኖ (ምጽዋ አጠገብ) ሁለት ጊዜ ዘምቷል፤ እዚያው ገ. 128-133:: ሱስንዮስ ሲያደንቀው "በፋሲል፥ በአዜ፥ በመሐመድ፥ በይስሐቅ ዘመን ከነበሩት (ጀግኖች) ውስጥ ከደኃረሳትና ከበርናባስ በቀር እስከ ዛሬ ማን አለ?" ይላል፤ የሱስንዮስ ታሪክ ገ. 88::

51. አንዱ ሀገር አርእኝ ሲሆን ሁለተኛው ሀገር የቱ እንደሆነ አልተገለጸም፤ ሰርግት ሊሆን ይችላል፥ ወይም አርእኝ የሁለት ወረዳዎች (ሀገሮች) ስም ነበረ::

የበርቱማው ቢርመጇ ደምብያን ወጋትና ልዑል አቦሊን፥ ባሕር ነጋሽ ሠምረ አብን፥ ሌሎችንም ገደላቸው።

ይህ (ሁሉ) የሆነው በሥራቸው ኃይለኛ፥ በምክራቸው ጥበበኛ የሆኑት ንጉሣችን በሌሉበት ነው። በደምቢያ ኖረው ቢሆን ኖሮማ በሮባሌ ላይ የደረሰው በቢርመጇ ላይ ይደርስበት ነበረ። ነገር ግን ድል ተራ በተራ እንዲሆን እግዚአብሔር የንጉሣችንን መንገድ ወደ ዳሞት አቀናው። በሄዱበት ድል አገኙ[52]፤ በሌሉበት ደግሞ መኳንንቱ ተሸነፉ።

## ክፍል ፲፬

የቦረኑ ቢርመጇ ዳሞትን ከበባት። ሀገሪቷን የሚያድንና የሚያስጥል የሌለ ሆኖ ሲያገኛት ጊዜ ሰውና ከብት አጋዘ።

በዚያን ጊዜ ደጅ አዝማቹ ዓስቦ ነበረ። ከወንድሞቹ ጋራ ተማከረና ሠራዊት ሰብስቦ ተከታተለው፤ ምርኮውን ሲካፈል ደረሰበት። ምርጦች (እግረኞች) እና ፈረሰኞች በመስለስት፥ ከበቡት፤ ይህ ማለት በሶስት የወራሪ ሰልፍ ከበባቸው ማለት ነው። ጋላው ሸሸ፤ ተፈጀ።

አብዛኞቹ ከአንድ ሰፊ ዋሻ ውስጥ ተደበቁ። (ሠራዊቱ) እንጨት ሰበሰበና ከዋሻው በራፍ ላይ አነደደው። ብዙዎቹ እሳቱን ከመፍራት የተነሣ ወጡና ታሰሩ -- ከብዙዎች ግዞተኞች ጋራ የተጋዘውን ልዑል አምጥተው እስኪያስረክቡት ድረስ።[53] የሞቱትን ራስ ራሳቸውን ቈረጧቸው፤ (ችብችቦው) ለቀኑጥር በዛ። (እንደዚህ አድርጎ) ሀገሩን ጠበቀ።

ከዚህ በኋላ የቢርመጇ የተራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ (ሀገር ተጠብቃለች)። ግን የክርስቲያኖች ዕዳ እስካላለቀ ድረስ አሁንም (የምትቀጣ) የእግዚአብሔር እጅ ገና ከላይ እንደተዘረጋች ነች[54]፤

52. የዳሞት ዘመቻ የተደጋገመ መሆን አለበት፤ እንዲያውም አፄ ሠርፀ ድንግል የሞተው ከዚያ ዘመቻ ሲመለስ በመንገድ ላይ ድንገት ታሞ ነው፤ *ባሕረ ሐሳብ* ገጽ 248፥ የሱስንዮስ *ታሪክ* ገ. 8።

53. ወይም "የተጋዘውን ልዑል ከብዙ ግዞተኞች *ጋራ* አምጥተው እስኪያስረክቡ ድረስ"። እንዲያውም ይህ አተረጓጐም ለግዕዙ የበለጠ ባይቀርብም *ታሪኩ* ከመዘገበው *ጋራ* አብሮ ይሄዳል። "ልዑል" በሚል ቃል የተረጐምኩት "ወልደ መንግሥት" ያለውን ነው። ቃል በቃል ቢተረጐም "የመንግሥት ልጅ" ይሆን ነበር፤ ግን ዘመናዊ አማርኛ አይሆንም። ዝርዝሩ በራሱ በንጉሡ በሱስንዮስ *ታሪክ* ተመዝግቧል፤ ገ. 5-6። የሱስንዮስን ስም ሊጠራው ያልፈለገው ደራሲው ሳይሆን ቀጂው ሊሆን ይችላል። ምክንያቱ ምናልባት ሱስንዮስ ከነገሠ በኋላ ቤተ ክርስቲያኗን ስለከዳና ካቶሊኮችን ስላመጣ ይሆናል። *ዜናሁ ለጋላ* የሠርፀ ድንግል *ታሪክ* ሆኖ ሳለ የባለታሪኩ ስም አንዴም ያልተነሣው ለኛ የደረሰው (ሁለተኛው ወይም ሶስተኛው) ቅጂ የተቀዳው በሱስንዮስ ዘመን ስለሆነ ይመስለኛል። *መጀመሪያ* አባ ባሕርይ የጻፉት የራሳቸው ቅጂ ይኖራል፤ ከዚያ ላይ አንድ ሰው ቀድቶለታል፤ ለኛ የደረሰው ያ አንድ ሰው ከቀዳው ላይ የተቀዳው ይመስላል።

54. ኢሳይያስ 5፡ 25።

በቢርመጂ ዘመን ቢጠበቁም በኋላ በቦታው የምናነሣው የኋለኛው ሉባ ያጠፋቸዋል::

## ክፍል ፲፩

ከዚህ በኋላ ቢርመጂ ተሻረና የቢፎሌ ልጅ ሙልአታ ተሾመ:: እጐጉም ላይ ዱላጉቶ አደረገ:: የዱላጉቶ ትርጉሙ "የቁንጮ ውጊያ" ነው::[55] ምክንያቱም ጋሎች በአንድ ዘመን ሲገዘሩ በክፍል አራት መጀመሪያ ላይ እንዳልነው ለራሳቸው ስም ያወጣሉ:: እነሱም የፊተኞቹ (ሉባዎች) ያልወጉትን አንድ ሀገር ይወጋሉ:: ሰውና ትላልቅ አራዊት ሲገድሉ ሞላ ራሳቸውን ይላጩና በጭንቅላታቸው ማህል ላይ ቁንጮ ያስተርፋሉ:: ያልገደለ በቅማል እየተሰቃየ አይላጭም:: ስለዚህ እኛን ለመግደል ይተጋል::

በዚያን ዘመን ሐዌጌ ወደዳሞት ለመሄድ ወሰኑ:: በመንገድ ላይ እንዳሉ ጋላ ምድረ ጐጉምን እንደወጋ፥ እናታቸው ንግሥቲቱ መጠጊያ ፈልገው ደብረ አብርሃም እንደወጡ ሰሙ::

ሰላም ይረፍባቸውና የአባቶቻቸው የንጉሦቹ የአጽናፍ ሰገድና የአድማስ ሰገድ እጎት ወይዘሮ ቴዎዳዳም (እዚያ ነበሩ):: ጋላው ድንገት ባላሰቡት ሰዓት ቢደርስባቸው የሀገሩ ሰው ሁሉም ደነገጠ፤ ሠራዊታቸውም ተበተነ:: ታላቁ ልጃቸው[56] ግን ወደናቱ በቀረቡት ጋሎች ላይ አይሎባቸው አባረራቸው፤ ምክንያቱም በኃይሉ የሚመሰገን ጐልማሳ ነው:: ተመልሶ የእናቱን እጅ ይዞ ጅበላ ከሚባል ረጅም ተራራ ላይ አወጣቸው::

አፄጌም መንገዳቸውን ትተው ጋላው ወዳለበት በጥድፊያ ተመለሱ፤ ከሠራዊታቸው ጋራ ደረሱ:: የአባቶቻቸውን የነገሥታቱን ሥርዓት ተዉት:: (የነገሥታቱ) ልማድ ከውጊያ ሲደርሱ ተዋጊውን ይልኩና ከምርጥ ፈረሰኞችና እግረኞች ጋራ ቁመው የሚጣደፈውን ያመሰግናሉ፥ ወደኋላ የሚለውን ይቀጣሉ::

---

55. ስለባለ ቁንጮዎች (ቁንጫቸውን "ከለላ" ስለሚሉ ቄንደላዎች) የመጀመሪያ ውጊያ፥ ክፍል ፲፩ንና ፲፭ን አስተያይ:: "ዱላጉቶ" ትርጉሙ "የቁንጮ ጦርነት" ማለት ሲሆን ቃሉ የወጣው ከ"ዱላ" ("ጦር") እና ከ"ጉቶ" ("ቁንጮ") ነው::

56. "ንግሥቲቷ" ወይም እቴጌይቱ የሠርፀ ድንግል ሚስት አይደለችም፤ እናቱ ነች:: እቴጌነት ሚሞት ስለሆነ ባሏ ንጉሡ ቢሞትም ከወራሲው ጋራ ፍቅር ከሆኑ ሹመቷን አይነካባትም:: ሠርፀ ድንግል እናቱን ሥሉስ ጎይላን (አድማስ ሞገሳን) ይወድም ያከብርም ነበረ:: "ታላቁ ልጃቸው" የሚለው የንጉሡን ሳይሆን የዌዘሮ ቴዎዳዳን ልጅ ነው:: "ተመልሶ የናቱን እጅ ይዞ ጅበላ ከሚባል ረጅም ተራራ ላይ" ከማውጣቱ በፊት የንጉሡ እናት "መጠጊያ ፈልገው ደብረ አብርሃም" ሄደው ነበረ:: ንጉሡማ እንዲህ ያለ የደረሰ ጀግና ልጅ ቢኖረው አልጋውን የስምንት ዓመቱ ልጅ አፄ ያዕቆብ አይወርስም፥ ወርሶም መንግሥቱን አያስወስድም (ማለት፥ ሱስንዮስ አይቀማውም) ነበረ::

ያን ጊዜ ግን ንጉሣችን ከኀይለኞች ቀድመው ኀይል አሳዩ። ሠራዊቱ ይኸንን ሲያይ እየሮጠ በጋላው ላይ አውሬ ሆነበት። ሁሉንም አንዳች ሳያስተርፉ ፈጁት። አብዛኞቹ ገደል ገቡ -- የሀገሬው ሰውና ገበሬዎቹ በአገኙበት ቦታ እስኪገድሏቸው ድረስ።

የጋሎቹን ራስ እንዲቈርጡ ትእዛዝ ሰጡ። (ቸብቸቦው) ሰፊውን ቦታ አዶራን ሞላው።

ኢቴጌንና ወይዘሮ ቴዎዳዳን ካሉበት ደብሮች (ተራሮች) አወረዷቸው፤ በክብርም ተቀበሏቸው።

የተቈረጠውን የጠላትን ራስ ብዛቱን ባዩ ጊዜ ከፍ ያለ ደስታ ተደሰቱ። በመሲሑ ላይ የድል መንፈስ ያሳረፈውን እግዚአብሔርንም አመሰገኑት።

ከጋላው እጅ ያስጣሉትን ከብትም ለተማረኩባቸው መለሱላቸው።

## ክፍል ፲፮

ከዚህ በኋላ ንጉሣችን መንገዳቸውን ሊያቀኑ ወሰኑ፤ ምክንያቱም እንዳሰቡት ያደርጋሉ፤ እንደተናገሩት ይፈጽማሉ። ዳዌ የሚባለውን ጋላ ለመውጋት ወደ ወጅ ሄዱ። ጋላው (ዳዌን) "የኋለኛው ጋላ"[57] ይለዋል። ሰዎች ግን ስላሳመማቸው "ዳዌ"[58] ይሉታል።

(ንጉሡ) ወደዚያ የሄዱበት ምክንያት (ዳዌ) በውጊያ የሚገጥማቸው፥ የማይሸሽ ስለመሰላቸው ነበር። "እዚህ አለ" ከአሏቸው ቦታ ሲደርሱ አጡት፤ (ያለበትን) ቦታውን ፈልገው አላገኙትም።

እንስሳዊ ምርኮና ሥጋዊ ውጊያ ሲያጡ ጊዜ ከሰይጣን ጋራ ለመዋጋትና የአሕዛብን ነፍስ ሊማርኩበት ወሰኑ፤ የእናርያን፥ የቦሻን፥ የጎመርን ሰዎች ጠሩዋቸውና፥ "ክርስቲያኖች ሁኑ" አሏቸው። ሆኑ፤ የክርስትና ጥምቀት ተጠመቁ።[59]

---

57. አነጋገሩ ኦሮሞዎች ኦሮሞችን "ጋላ" የሚሏቸው ያስመስላል፤ ካሉ ከክርስቲያኖቹ ሰምተው ሊሆን ይችላል፤ ወይም እውነትም የነሱ መጠሪያ ኖሯል። ግን ይህን የሚለው የሎንዶኑ ቅጂ ብቻ ስለሆነ የሰዋስው ስሕተት ባይኖርበትም፥ በአከራካሪ ጉዳይ ላይ ባንድ መስካሪ ከማያጠራጥር ውሳኔ ላይ ለመድረስ አይቻልም። ከቪየናው ቅጂ ውስጥ (በቀጂ የጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት) መሥመሩ በሙሉ ሳይቀዳ ቀርቷል።

58. በግዕዝ "ደዌ" ማለት "በሽታ" ማለት ነው። ግን ታዲያ ለምን "ደዌ" አላሉትም? ሲያሾፉ ይሆን? ሁለተኛም፥ ዳዌ እና ጃዊ የአንድ ጎሳ የተለያዩ መጠሪያዎች ለመሆናቸው ማስረጃ የለንም። እንዲያውም አይደሉም ማለቱ ለእውነቱ ይቀርባል፤ ምክንያቱም፥ "ጃዊ" ማለት "እባብ" ማለት ስለሆነ አባ ባሕርይ ይወዱትም ይጠቀሙበትም ነበር።

59. ዘመኑ መጋቢት 27 ቀን 1575 ዓ. ም. ነው፤ *ባሕረ ሐሳብ* ገ. 248።

## ክፍል ፲፯

የወርድአያ ሙልአታ የራስ ወልደ ክርስቶስን (የግዛት) ሀገር በወጋ ጊዜ አሸነፈውና ምርኮውን አስጣለው፤ ብዙም ገደለ። ግማሹንም ገደል እስኪገቡ ድረስ አሳደዳቸው። ሐዌጌ እስኪመለሱ ድረስ ሀገሩን (እንዲህ) ጠበቀ። ሐዌጌ ሲመለሱ ሀገሪቷን በወልደ ክርስቶስ ትጋትና ውጊያ ተጠብቃ አገኟት። በዚህ ምክንያት የቤታቸው ጌታ አድርገው በመንግሥቱ ሁሉ ላይ አሰለጠኑት።

## ክፍል ፲፰

የበረን ሙልአታ የዳሞትን ክርስቲያኖች አዳከማቸው፤ በታኑናቸው፤ አገራቸውን አጠፋው። በሱ ዘመን ሸዋና ዳሞት ምድረ በዳ ሆኑ።

አንድ ጊዜ የጋላን ድል፥ አንድ ጊዜ የክርስቲያንን ድል ብጽፍ፥ "ዛሬ ላንተ፥ ነገ ለሌላህ" የሚለው የመጽሐፍ ልማድ ነው።[60] ድልም አንድ ጊዜ ለዚህኛው፥ አንድ ጊዜ ለዚያኛው ነው። ሁልጊዜ የሚያሸንፍ የሁሉ በላይ የሆነ አንድ እግዚአብሔር (ብቻ) ነው። ሀገሪቱም በእጁ (በጋላው እጅ) ገባች፤ የተረፈ የለም።

ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ የቢፎሌ ልጅ የሙልአታ ሹመት ሰባት ዓመት ሆኖታል።[61] ለምስሌ ልጆች (ነገድ) ግዝራትና ሹመት ገና በመዘጋጀት ላይ ናቸው። በዘመናቸው የሚሆነውን ውጊያና እልቂት በሕይወት ካለሁ በኋላ እጽፈዋለሁ። ከሞትኩም ታሪኬንና የሚመጣውን ሉባ ታሪክ ሌሎች ይጽፉታል። ግን የሞተ ብዙዕ ነው፤ አርፏልና።

## ክፍል ፲፱

ዐዋቂዎች (እንዲህ እያሉ) ብዙ ምርምር ይመራመራሉ፤ "እኛ ብዙዎች፥ የጦር መሣሪያችን ብዙ ሆኖ ሳለ ጋላ እንዴት ያሸንፈናል?" ይላሉ። "በኃጢአታችን ምክንያት እግዚአብሔር ፈቀደለት" የሚሉ አሉ። "ሕዝባችን ከዓሥር ጸታ ስለተከፈለ ነው። ከነሱ ውስጥ ዘጠኙ ጸታ ከውጊያ አይቀርቡም፤ በፍርሃታቸውም አያፍሩም። ዓሥረኛው ጸታ ግን የተቻለውን ያህል ይዋጋል፥ ይጋደላል" የሚልም አለ ።

ቀኙጥራችን ብዙ ይሁን እንጂ ውጊያ የሚችሉ ጥቂቶች፥ ወደ ውጊያ የማይቀርቡ ብዙዎች ናቸው።

ከነሱ ውስጥ አንዱ፥ ቀኙጥር የሌላቸው የመነኮሳት ወገን ነው። እንደዚህ ታሪክ ጸሐፊና እንደሱ ብጤዎች በልጅነቱ በትምህርት ላይ ሳለ መነኮሴዎች ሲደልሉት የሚመነኮስ አለ፤ ውጊያ ፈርቶ የሚመነኮስ አለ።

60. ምንጩ አልታወቀም።
61. 1586 ዓ. ም. መሆኑ ነው።

ሁለተኛው ወገን ደብተራ ይባላሉ:: መጻሕፍቱንና የክህነትን ሥራ ሁሉ ይማራሉ፤ በእጃቸው ያጨበጭባሉ፤ በእግራቸው ያሸበሽባሉ.[62]:: ስለፍርሃታቸው አያፍሩም:: ምሳሌነትን የአሮን ልጆች ከሆኑት ከሌዋውያንና ከካህናት ይወስዳሉ::[63]

ሶስተኛው ወገን ጣጉን ሐጸና እና ጣጉን መዓሠሬ ይባላሉ:: ፍርድ ይጠብቃሉ፤ ከውጊያም ይጠበቃሉ::

አራተኛው ወገን የመኳንንት ሚስቶችና ወይዛዝሮች[64] ደጋፎች ናቸው፤ ጎይለኛ ወንዶች፥ ጠንካራ ጎልማሶች (ሆነው ሳለ) ወደውጊያ አይቀርቡም:: "የሴቶች ሎሌዎች ነን" ይላሉ::

አምስተኛው ወገን ሽማግሌ፥ ገዜ፥ በዓለ ርስት ይባላሉ፤ መሬታቸውን ለገበሬ አካፍለው ያዝዙታል፤ በፍርሃታቸው አያፍሩም::

ስድስተኛው ወገን ገበሬዎች ናቸው፤ እርሻ ላይ ይውላሉ፤ ስለውጊያ አንዳችም ሐሳብ የላቸውም::

ሰባተኛው ወገን በንግድ የሚጠቀሙና ለራሳቸው የሚያተርፉ ናቸው::

ስምንተኛው ወገን እንደ አንጥረኞች፥ ጸሐፊዎች፥ (ልብስ/ቆዳ) ሰፊዎች፥ አናጢዎች ያሉ እና እነዚህን የሚመስሉ ጥበበኞች ናቸው፤ ውጊያ አያውቁም::

ዘጠነኛው ጸታ ልመናን ሥራ ያደረጉ አዝማሪዎች፥ ባለከበሮዎች፥ ባለበገናዎች ናቸው:: የሰጣቸውን ይባርኩታል፤ ብጡል ምስጋናና ውዳሴ ከንቱ ይሰጡታል:: ያልሰጣቸውን ሲራገሙት እዳ አይሆንባቸውም፤ ሕጋችን ነው ይላሉ:: ከውጊያ በረጅሙ ይርቃሉ::

ዓሥረኛው ጸታ ጦርና ጋሻ የሚይዙ፥ ውጊያ የሚችሉ፥ "ለሩጫ የንጉሡን ፈለግ"[65] የሚከተሉ ናቸው:: በነዚህ ጥቂትነት ምክንያት አገራችን ጠፋች::

ጋላ ግን እነዚህ ያነሣናቸው ዘጠኝ ወገኖች የሉበትም:: ሁሉም ከደቂቅ እስከ ልሂቅ ለውጊታ የሠለጠኑ ናቸው:: ስለዚህ ያጠፉናል፥

62. በበዓላት ቀን ከቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ የሚያደርጉትን ወረብ ማለቱ ነው::
63. የብሉይ ኪዳን ካህናት::
64. "ወይዛዝር" የቤተ መንግሥቱ ሴቶች (ልዑላቱ) ናቸው:: (ጥንት ወንዶችም በቃሉ ይጠሩበት ነበረ::) ንጉሡ አፄ ሠርፀ ድንግል ይህንን ትንተና ከሰማ በኋላ "ደጋፎች"ም በውትድርና እንዲያገለግሉ ዐዋጅ አስነግሯል ይባላል::
65. "አሰረ ንጉሥ ለረዊጽ" ምንጩ መኃልይ 7: 5 ነው:: ግን አባ ባሕርይንና ሌሎቹንም መምህራን እንደመሰላቸው "አሰር" እዚህ ላይ "ፈለግ" (ስም) ማለት አይደለም፤ "ጠፈረ" (ግሥ) ማለት ነው:: ሆኖም "ፈለግ" መስሏቸው ንጉሥ ሲያጠፋ ጥፋቱን እንዲያርም አስተያየት የሚሰጥበት፥ ሲያሳምር የሚመሰገትበት ለንጉሥ ብቻ የሚሰጥ "አሰረ ንጉሥ" የሚባል የቅኔ ዓይነት ፈጥረዋል፤ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ፥ መጽሐፈ ቅኔ፥ (አዲስ አበባ) ፲፱፻፭ ዓመት እምድኅረ ልደቱ ለክርስቶስ፥ ገ. 8.

ይፈጁናል። "(ጋላው) በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይፈጀናል" የሚሉ የእስራኤል ልጆችን መሸነፍና በፋርስና በባቢሎን እጅ መጥፋታቸውን ምክንያት ያመጣሉ። "ተዋጊ የሚያሸንፍ ቢሆንማ ኖሮ ክቡርና ልዑል ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ማን እርዳታ ይለምን ነበረ? ብዙዎች ጥቂቶችን ቢያሸንፉ፥ 'አንዱ አንዱን ሺ ያባርራቸዋል፤ ሁለቱ ዓሥሩን ሺ ያሳድዷቸዋል'[66] የሚለው የመጽሐፍ ቃል ከንቱ በሆነ ነበር" ይላሉ።

ዐወዋቂዎች ሆይ፥ የሚታመነው የመጀመሪያዎቹ ወይም የኋለኞቹ ተከራካሪዎች ቃል እንደሆነ እናንተ ታውቃላችሁ።

## ክፍል ፰

እንግዲህ ወደ ጋላው ዜና እንመለስ።

ትናንሾቹን ልጆች "ሙጫዕ" ይላቸዋል፤ በለጥ የሚሉትን "ኤልማን" ይላቸዋል። ከነሱ የሚበልጡትን፥ መዋጋት የሚጀምሩትን "ጐርባእ" ይላቸዋል።

ያልተገዘሩትን ጎልማሶች--የራስ ጠጉራቸውን እንደ ጎራ[67] የሚያሽሙና "ከለላ" የሚሉትን--"ቄንደላ"[68] ይላቸዋል። ሰው፥ ዝሆን፥ አንበሳ፥ አውራሪስ፥ ጎሽ ሲገድሉ ከማህል ራሳቸው ላይ ቁንጮ (ትተው) ይላጫሉ፤ ያልገደለ ግን አይላጭም።[69] ሚስት ሲያገቡም ካልገደሉ አይላጩም።

በሙልአታ ዘመን ጐሽ (ስለ)በሉ፥ "ከበላነው ከብት ነው፤ ስንገድለው ራሳችንን እንላጭ" አሉ። ግማሾቹም በስድብ አነጋገር፥

66. ዘዳግም 32፡ 30።

67. ሶስቱም ቅጅዎች በግልጽ "ጎራ" ይላሉ። ጉይዲ "ጎራ" (ወታደር) ብሎ ለውጦታል። እርግጥ ወታደሮች በዚያን ዘመን መለዮዋቸው የጠጉራቸው አሠራር እንደነበረ ከግራኝ አነጋገር ለመረዳት ይቻላል፤ ግራኝ ለወረራ ያሰለፋቸውን ወታደሮች የጦር ዘዴ ሲነግራቸው፥ "ጠጉራችሁን እንደ ክርስቲያኖች ብነይ ደዋ ("የደዋ ልጆች"?) አሽሙ" ማለቱ በግልጽ ባይገባም ወታደሮች የተለየ የጠጉር አበጣጠር እንደነበራቸው ይጠቁማል፤ Basset, *Histoire de la conquête de l'Abyssinie*, Vol. I, p. 327, for the text, and Vol. II, p. 436, for the translation.

68. ቄንዳላ አማርኛም ነው፤ ለምሳሌ፥ መኃልይ 5፡ 11ላይ "ቄንዳላው የተዝረፈረፈ ነው" የሚለውን ተመልከት።

69. እዚህ ላይ ቀጂዎቹ የተሳሳቱ ይመስላሉ። ሁለቱም የሚሉት እንደ ሳዱላ "ከማህል ራሳቸው ላይ ትንሽ ጠጉር ይላጫሉ" ነው። ለእውነቱ የሚቀርበው ግን እንደ ቁንጮ "ትንሽ ጠጉር ትተው ይላጫሉ" ማለቱ ነው፤ ክፍል ፲፭ን ተመልከት። ግራኝ በዘንተራ ጦንነት ሲወድቅ፥ "እንግዴህስ አንተ ከሞትክልን ጠላት ጠፋልን" ቢሉት፥ "እኔ መቸ ሞትኩ ቁንጪም ቁንጪም ልጆች ወልጃለሁ" አለ የሚባለውም ተጨማሪ ማረሚያ ነው፤ Caquot, "Histoire Amharique de Grāñ et des Gāllās," p. 129.

“የሸዋንና የአምሐራን ሰዎች ስንገድል ራሳችንን አንላጭ፤ ምክንያቱም እነሱ የሚናገሩ ከብቶች ናቸው፤ መዋጋት አይችሉም” አሉ።

ጋላ ሁሉ፥ ሉባም ሆነ ቀንዶላ፥ ሚስት ያላገቡት “ቄሮ”[70] ይባላሉ። የሉባው ቄሮ ከሉባ ጋራ፥ የቄንደላው ከቄንደላ ጋራ፥ የገበሩ ቄሮ ከገበር ጋራ በአንድ ቤት ይኖራሉ።

ሰቄላ (ሰቀላ) ለመሥራት ሃያ የሚያህሉ ሰዎች ይሾማሉ፤ “አጀርቱ” ይሏቸዋል።

ደግሞ ለበሬ አረዳ ይሾማሉ[71]፤ (እነዚህ) “ቀልታ” ይባላሉ።

ደግሞ ሥጋ የሚጠብሱ እና እየቈረጡ ለሁሉም በቀኙጥ በቀኙጥ እኩል የሚያድሉ ሁለት[72] ሰው ይሾማሉ፤ “ዋጆ”[73] ይሏቸዋል።

ደግሞ የሁሉንም ላሞች ወተት የሚያልቡ አምስት[72] ወንዶች ይሾማሉ፤ ስማቸው “ሐለብዶ”[74] ነው።

ደግሞ ወተት ለመቅዳት ሁለት[72] ይሾማሉ፤ ለያንዳንዱ በመለኪያ ያካፍላሉ፤ ስማቸው “ጥሂቶ” ነው።

ደግሞ ለከብት እገዳ ሰባት ሰዎች ይሾማሉ፤ (እነዚህ) የጠፋውንም (ከብት) ይፈልጋሉ፤ ስማቸው “በርባዶ”[75] ነው።

ደግሞ ከማህላቸው ሁለት ይመርጡና ወደሴት የሚሄደውን እንዲገሥጹና እንዲቀጡ ይሾሟቸዋል፤ (እነዚህ) “ጎርሳ”[76] ይባላሉ። ይህ (ከሴት) መጠበቃቸው ለጦርነት የነቁ የተጉ እንዲሆኑ ነው እንጂ ለጽድቅ አይደለም። ያገባ የሚያስበው ሚስቱን የሚያስደስትበትን (ነገር) ነው።[77]

ደግሞ (ሲጓዙ) ከብት የሚነዱ ዓሥር የሚሆኑ ሰዎች ይሾማሉ። ስማቸው “ጠውቱ”[78] ነው። ከነሱ ውስጥ ሚስት ለማግባት የፈለገ ይለይና በቤቱ ይኖራል፤ “ጅልሂካ”[79] ይሉታል።

---

70. “ቄንዳላ” የሚለውን ቃል አማርኛ ያደረጉትን አባቶች ምሳሌ በማድረግ “ቄሮ”ን "bacheler" ለሚለው የእንግሊዝ ቃል መተርጐሚያ ማድረግ እንችላለን። እነሱም ወስደውት ይሆናል፤ “ነፋኝ ዘገር” የሚባለው ሠራዊት ሲፎክር፥ “ዘገር ቂሮ ሳይዋጋ ድል ይነሳ” ያለውን ከዮሐንስ/አእላፍ ሰገድ ታሪክ ውስጥ ገ. 20 ላይ ተመልከት።
71. ቀልታዎቹ ስንት እንደሆኑ በቀኙጥ ያልተናገረው ቀኙጥን ቀጂ በስሕተት ቢገድፈው ይሆናል።
72. የቀኙጥሮቹ ማነስ የጎሳዎቹን መጠን ያሳያል። ጎይላቸው ብዛታቸው ሳይሆን መደራጀታቸው ይመስላል።
73. ዋዳ (ጠበሰ) ከሚለው ግሥ የወጣ።
74. “ሐለብዶ” “አላቢዎች” ማለት ከሆነ “አለበ” ከሚለው አማርኛና “ሐለበ” ከሚለው ግዕዝ ጋራ ያለው ግንኙነት ታሪካዊ እንጂ አጋጣሚ ሊሆን አይችልም።
75. “በርባዳ” “ፈለገ” ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
76. “ጎርሳ” ማለት “መካሪ” ማለት ነው።
77. አንደኛ ቆሮንቶስ 7፡ 33።
78. “ጠውቱ” “እረኛ”።
79. “ጅልሂካ” “ሚስት ያገባ እረኛ”።

ሽማግሌውን "ምልጉዶ"[80] ይሉታል። እሱም ቢሆን እንደወንድሞቻችን እንደ ዘጸ[81] እና እንደ አባ ሐራ[82] በጣም ካልደከመ ከውጊያ አያርፍም።

ክፋት ለማድረግ የሚተጋ ጠላት እንደኛ ያገኘ የለም። ደግ ለመሥራት የሚተጋ ጌታና ንጉሥም እንደኛ ያገኘ የለም። እግዚአብሔር እስከ ረጅም ዘመንና ብዙ ጊዜ ይጠብቀው፤[83] ይላል ባሕርይ።

80. "ምልጉዶ" "ሽማግሌ"። እነዚህን ሁሉ የኦሮሞ ቃላት ቤኪንግሃም እና ሃንቲንግፎርድ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመዋቸዋል፤ C.F. Beckingham and G.W.B. Huntingford, "*Some Records of Ethiopia*," pp. 111-129. (የጎዳግ ማስታወሻዎቹን ተመልከት።)

81. የሽማግሌው ስም ዘጸራቅሊጦስ ነው፤ በሠርፀ ድንግል ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ ተነሥተዋል። በዚያን ዘመን ስምን እንደዚህ ማሳጠር ይወዱ ነበረ፤ ዓስቦ (ዐስበ)፥ ዓምዶ (ዐምደ)፥ ተዝካሮ (ተዝካረ)፥ መንገዶ (መንገደ)፥ ጎደሮ (ጎደረ)፥ ክፍሎ (ክፍለ) ይሉ ነበረ። ልማዱን ከኦሮሞዎች ወስደውት ይሆናል፤ "ጢኖ"፥ "በርባዶ"፥ "ሐለብዶ" የሚለውን ተመልከት።

82. አባ ሐራ ድንግል ካቶሊኮቹን በመቃወም ለቅድስና በቅተው ገድል ተጽፎላቸዋል፤ EMML 69, William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. I, p. 71.

83. ንጉሡ አፄ ሠርፀ ድንግል ነበረ።



BL Or. 534, f. 1a.

**እስካሁን ከተገኙት የዜናሁ ለጋላ ቅጅዎች አንዱ::**

(ገጽ 63-66 ላይ ተቀድቷል::)

# ምዕራፍ ፫

## ጋላ/ኦሮሞ

*ዱሜሳ ታኢ፥ ዋቃ ኡዊሳ፤*
*ጨቆርሳ ታኢ፥ ለፈ ኡዊሳ።*

❖

**ደመና ሁን፥ ሰማዩን አልብሰው፤**
**ሰርዶ ሁን፥ መሬቱን አላብሰው።**

**የኦሮሞ ሽማግሌዎች ምርቃት**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ኦሮሞዎችን ያጠና አይኬ ሃበርላንድ።**

(**ፎቶግራፍ አንሺ**: Karl Heinz Striedter, Frobenius-Institut)

# ፫

*“ዜናሁ ለጋላ”*ን እና ስለኦሮሞዎች የሚባለውን በይበልጥ ለመረዳት መነጋገሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች እንዳስፈላጊነቱ በዚህ ምዕራፍ ባጭሩም በረጂሙም እየተቸሁ አቀርባቸዋለሁ።

## (1) ጋላ ወይስ ኦሮሞ

ኦሮምኛ ተናጋሪዎች “ጋላ” የሚለውን ስም ከመጥላታቸው በፊት ጀምሮ የነገድ ስማቸው “ኦሮሞ” እንደሆነ ይናገራሉ። ሌሎችም ኦሮሞ እንዲሏቸው ዛሬ ገፋ በት እንጂ ስሙ ከጥንት የኖረ ለመሆኑ ባዔ ምኒልክ ዘመን የነበሩ አቶ ዐፅሜና አለቃ ታየ ይመሰክራሉ። የታሪክ ምንጮቹ ግን፥ በዚያውም ተያይዞ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሌሎችም፥ የሚጠሯቸው “ጋላ” እያሉ ነው። በዚህ ድርሰቴ ውስጥ ሁለቱ ስሞች እየተፈራረቁ ቢመጡ “ጋላ” የምንጮቹ “ኦሮሞ” የኔ አጠራር ሆነው ነው።

## (2) የጋላ ትርጉም

“**ጋላ**” ማለት ትርጉሙ ምን እንደሆነ አይታወቅም፤ የማይታወቀውን ለማወቅ ብዙዎች (ዘመናዊ ጸሐፊዎች ሳይቀሩ) ሲሞክሩ ይታያሉ። አንደኛ፥ ቀደም ብለው የወጡ የሕዝብና የቦታ ስሞች ትርጉማቸው በጊዜው ሳይመዘገብ ከቀረ ወይም በቋንቋችን ውስጥ ሕያው ካልሆነ የተጻውያ ስም ቢሆኑም እንደ “ዛፍ”፥ “ጠላ”፥ “ፈረስ” የዘመን ርዝመት ትርጉማቸውን ደብቆባቸዋል። ግን እንደሰው ስም እንደ “አሰፋ”፥ “መሐመድ”፥ “ገለታ”፤ እንደቦታ ስም እንደ “አህያ ፈጅ”፥ “ነጭ ሣር”፥ “ዶሮ ማነቂያ”፥ “አሐዱ ዕፅ” የተጻውያ ስሞች ስለሆኑ ትርጉማቸው ያልጠፋ እየመሰለን ለማወቅ እንፈልጋለን። ስንፈልግ ሰዉ ዝም ብሎ የፈጠረውን ትርጉም እናገኝና እውነት አድርገን እንይዘዋለን[1]። “ጋላ”፥ “አማራ”፥ “ሸዋ”፥ “ጐጃም”፥ ወዘተ በሚሉት ስሞች ላይ የደረሰው ይኸው

1. የኔ ብጤው መምህርም “ይኸንን የፈጠራውን ታሪክ ለዕውቀቱ ያህል ዕወቁት፤ እንደ እውነተኛ ታሪክ መተረካችሁን ግን ተዉ” ቢለን እሺ አንለውም። ለምሳሌ፥ “ጠመንጃ” ማለት “ጠብ መንጃ” ከሚለው የመጣ ነው የሚለውን ማስጣል አልተቻለም። ዘመኑ የመምህር ቃል የማይከበርበት ዘመን በመሆኑ፥ “ጠመንጃ”/ “ጠበንጃ” የቱርክ ቃል ሆኖ ከኛ የደረሰው በዓረብኛ በኩል ነው፤ የዚህን የቱርክ ቃል ትርጉም “ጠብ መንጃ” ለማድረግ መጀመሪያ ቱርኮችን አማርኛ ተናጋሪዎች ማድረግ ያስፈልጋል” ቢባልም ብዙ ሰሚ አልተገኘም።

ነው፤ እውነተኛ ትርጕማቸው እስካሁን አልተገኘም። "ዛፍ" ለምን "ዛፍ" እንደተባለ ምክንያት ቢኖረውም፥ ያንን ምክንያት አሁን እንደማናውቅ፥ ለእነዚህ ነገዶችና ቦታዎች ለምን ይኸ ዓይነት ስም እንደተሰጣቸው የሚታመን ዕውቀት የለንም።

"ጋላት" የሚል የግዕዝ ቃል አለ፤ ግን "ጋላ" ከግዕዙ "ጋላት" ጋራ ግንኙነት ይኑረው አይኑረው እርግጠኛ አይደለሁም። በግዕዝ "ጋላት" ብዙ ቍጥር ሆኖ ትርጕሙ "ጭፍሮች" ማለት ነው። ወደኋላ ዘመን የተጻፉት ካልሆኑ በቀር ቀደም ያሉት ምንጮች ኦሮሞዎችን ባንድም በብዙም "ጋላ" ይሏቸዋል፤ ብዙዎቹን "ጋላት" ("ጭፍሮች") ወይም "ጋሎች" የሚሏቸው ሁሌም ባይሆን አብዛኛውን ጊዜ የቅርቡ ዘመን ምንጮች ናቸው፤ ስለዚህ "ጋላ" የ"ጋላት" ነጠላ ቍጥር ነው ለማለት አያስደፍርም። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም "ጋላ"ን እና "ጋላት"ን ሳያያይዙ ለየብቻቸው የመዘገቧቸው ስለዚህ ነው[2]።

ይህም ሆኖ፥ "ጋላት" የ"ጋላ" ብዙ ቢሆን ተስማሚው ነው፤ ምክንያቱም አንደኛ፥ የስሙን ጥንታዊነት ያሳያል፤ ሁለተኛም፥ ምንጮቹ "ጭፍራ" የሚለውን ከኦሮሞዎች የተወሰደ ቃል አድርገው ትርጕሙ "የእሮምታ፥ በአንድነት የግር ብሌ ሰልፍ" ማለት እንደሆነ ይናገራሉ። "በጭፍራ አምሳለ ጋላ" ማለት "እንደ ጋላ በጭፍራ (በተናጠል ሳይሆን በአንድነት፥ በእሮምታ ለመውጋት መሰለፍ)" ማለት ነው።

የግዕዙ ምንጮች እስላሞችን "እስላም" ወይም "መለሳይ"፥ ኦሮሞዎችን "ጋላ" ስለሚሏቸው "ጋላ" የሚሉት ክርስቲያንም እስላምም ያልሆነውን ነው ያሰኛል። ግን ኦሮሞ ያይደሉትንና ክርስትናን ወይም እስልምናን ያልተቀበሉትን ሌሎቹን ኢትዮጵያውያን "ጋላ" አይሏቸውም። "ጋላ" የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የጋራ ቋንቋ ያላቸው ሰዎችም (የነገድም ስም) መሆኑ አያጠራጥርም። ክርስትናን ወይም እስልምናን የተቀበሉትንም ባህላቸው፥ ቋንቋቸው ኦሮምኛ እስከሆነ ድረስ "ጋላ" ይሏቸዋል።

### (3) የኦሮሞ አንድነት

ሆኖም ይህ ሁሉንም "**ጋላ**" ብሌ ጠቅላላ አጠራር ኦሮምኛ ተናጋሪዎች አንድ ቤት (**ቤተ ጋላ**) ለመሆናቸው ማስረጃ አይሆንም። ታች ታች ግብጽ (Lower Egypt) በአስቄጥስ ገዳማት የሚኖሩትን መነኮሳት ከምዕራብ በኩል እየመጡ የሚዘርፏቸውን በርበሮች መጽሐፎቻችን "በርበር የሚባል ጋላ" ይሏቸዋል[3]። በርበሮችንና ኦሮሞዎችን በአንድ ስም እንዲጠሯቸው ያደረጋቸው ምንድን ነው? "ፈረንጅ" እንደማለት ነው፤ ለኛ ይምሰለን እንጂ ፈረንጆች የምንላቸው ሁሉ አንድ ቤት (**ቤተ ፈረንጅ**) አይደሉም።

2. ኪወክ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ገ. 317።
3. ለምሳሌ፥ *ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያም*፥ ገ. 206–11።

ሌላ ምሳሌ፥ ከአውሮፓ መጥተው አሜሪካውያን የሆኑት ("ፈረንጆች") ቀድመዋቸው አገሩን የያዙትን "ኢንዲያንስ" ("ህንዶች") ይሏቸዋል። "ህንዶቹ" ግን "ህንዶች" መባላቸውንም ሆነ እንደ አንድ ሕዝብ መታየታቸውን አይቀበሉም። ተስማሚው ምሳሌ ግን የዓረቦች ሁኔታ ነው። አንድ ቋንቋ (ዓረብኛ)፥ አንድ መንፈሳዊ መሪ (ነቢዩ መሐመድ) አላቸው፤ ሲጀምሩም ብዙ ጎሳ ግን አንድ ነገድ ወይም አንድ ሕዝብ ነበሩ። በኋላ እንደ ሱዳን ያሉትን ሌሎች ሕዝቦች ሃይማኖታቸውንና ቋንቋቸውን በማውረስ አሳረቧቸው (ዓረቦች አደረጓቸው)። ምንጮቹ የኦሮሞዎቹን ሁኔታ በዚህ መልክ ነው የሚያቀርቡት፤ ለምሳሌ፥ "ጋላ ዘይብልዎ ቦረን" ("ቦረን የሚባል ጋላ") ማለት "ጣሊያን የሚሉት ፈረንጅ" ወይም "ናቫሆ የሚሏቸው ህንዶች" እንደማለት ነው። አለቃ ታየ ገብረ ማርያምም ይህን ልብ በማለት <u>የሚባለውን</u> ሲነግሩን፥

> ከዚያ (ጌታቸውን አዝማች እንድርያስን ከገደሉበት) ዘመን ጀምሮ እስከ አፄ መለክ ሰገድ (ሠርፀ ድንግል) ዘመን ድረስ በክርስቲያንና በጋላ መሀከል ሁለግዜ ጠብና ጦርነት፥ ሁከት፥ መጋደልም ሆነ፤ ስለዚህም እነዚያ በጋላን ወንዝ ስለነበሩ ጋላ ተባሉ። የጋላ ወገንም ሁሉ በጥቅሉ በዚህ ስም ጋላ ተባለ። ጥንት ግን የጋሎች በጥቅሉ ባንድ የሚጠሩበት ስም አልነበራቸውም፤ ባባቶቻቸው ስም በየነገዳቸው በርቱማ ቦረና ይባሉ ነበር ይላሉ

ብለው ነግረውናል[4]። ይህ እምነት የነበረው ኦሮሞዎች አንድ ስም ቢኖራቸው ባይኖራቸው ልዩነት በማያመጣበት ዘመን ስለሆነ ታሪኩ ሊታመን የሚችል ይመስላል፤ ፖለቲካ የለበትም።

ሆኖም ባህልን፥ በተለየም ቋንቋን፥ መገመቻ ካደረግን ኦሮምኛ ተናጋሪዎች አንድነት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፥ አንድ ስም ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፥ ሲጀምሩ አንድ ዓይነት ሕዝብ ነበሩ። አባ ባሕርይም እንዳንድ ሕዝብ ነው የሚያይዋቸው።

### (4) ኦሮሞዎች ከሌሎች ይለያሉ?

ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ከታዩበት ጊዜ ጀምሮ "ሲዳማ" ከሚሉት ሕዝብ ጋራ (ከሲዳሞች፥ ከአማሮች፥ ከአገዎች፥ ወዘተ) በፍቅርም በጠለፋም ይጋቡ ነበረ። በሃይማኖት ካልሆነ "ሲዳማዎች" "ጋሎችን" በዘር እኩዮችና ተመሳሳዮች እንጂ ልዩዎች ወይም ከፍተኞች ወይም ዝቅተኞች አድርገው አላዩዋቸውም። ቋንቋቸው ኩሳዊ ወይም ካማዊ ስለሆነ ለሱማሌዎች፥

4. JE692E, p. 582. ከአዝማች እንድርያስ ጋራ ስላደረጉት ግጭት የሚባለው ከዚህ ቀጥሎ (ቁጥር 6 ውስጥ) ተጽፏል። ስለ JE692E ገጽ 60፥ ጎዳማ ቁ. 21ን ተመልከት።

ለአገዎች ለቤጃዎች በአንደኛ ደረጃ፤ ቋንቋቸው ሴማዊ ለሆነ ለአማሮች፥ ለትግሬዎች፥ ለጉራጌዎች፥ ለአደሬዎች እና ቋንቋቸው አሜታዊ ለሆነ ለአሜቶዎች፥ ለጊሚራዎች፥ ለጃንጁሮዎች በሁለተኛ ደረጃ ያቀርባቸዋል። ኩሳዊ/ካማዊ፥ ሴማዊ፥ አሜታዊ እነዚህ ሶስቱ በከፍተኛ ደረጃ "ወንድማማች አባት ቋንቋዎች" መሆናቸው ነው። የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ዝምድናቸው የአንድ አባት ወይም የአንድ አያት ልጆች እንደመሆን ማለት ነው። የረጅም ጊዜ ምርምር ያደረገውን ጀርመናዊውን አይኬ ሃበርላንድን፥ "ዛሬ የሰሜንና የደቡብ ባህላዊ ተቃርኖ ቢጎላም፥ ኢትዮጵያ አንድ አንድነት ያለው ባህል አገር ሆናለች"[5] ከሚል እምነት ያደረሰው የሕዝቡ መዛመድ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ሁለት ነገሮች ማስታወስ ያስፈልጋል፤ አንደኛ፥ ኩሳዊ/ካማዊ ቋንቋዎች ከአፍሪካ ውጪ ተናጋሪ የላቸውም። ፍጹም አፍሪካውያን ናቸው። የውጪ ለመሆን ሐሜት እንኳን ቢመጣ ከአፍሪካ ውጪ ተናጋሪ ባላቸው በሴማዊ ቋንቋዎች እንጂ በኩሳዊ/ካማዊ ሊመጣ አይችልም። ሁለተኛ፥ አሮምኛ ከሱማልኛ፥ ከቅማንትኛ (ከአገውኛ) ወዘተ ጋራ ያንድ አባት ልጅ ከሆነ አሮሞዎቹን ከነዚህ ለይቶ በቅርብ ጊዜ ከወዲያ ማዶ መጡ ለማለት ያስቸግራል።

አይኬ ሃበርላንድ ስለ ጋዳ ሥርዓት የሰጠውን (ከታች በጎዳግ ቁጥር 28 ስር የጠቀስኩትን) አስተያየት እዚህ ከጠቀስኩለት ጋራ አቀራርበን ብናየው የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለ አንድ ትልቅ እንቆቅልሽ ሊፈታልንም ይችላል። እንደምናስታውሰው፥ የአክሱም "ነገሥታት" ስም "እለ" የሚል መነሻ አለው፤ ለምሳሌ፥ "እለ ዓሚዳ"፥ "እለ አለዳ፥ "እለ አዝጓጓ"፥ "እለ ገበዝ" የሚባሉትን "ነገሥታት" እናስታውስ። የ"እለ" ትርጉሙ "እነ" ነው፤ ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። ሁለተኛ፥ በዚህ ቃል ከሚጀምሩ ስሞች

5. Haberland, *Untersuchungen*, p. 219. ሃበርላንድ በደቡብ ኢትዮጵያ ክርስትና ተስፋፍቶ እንደነበረ ለማስረዳት ንግግር ሲያደርግ ደግሞ እግረ መንገዱን እንዲህ ይላል፤ "Die so häufig zu findende Apostrophierung der Amhara als "Semiten" im rassischen und auch im kulturellem Sinne ist rein Phantasie. (Es ist unmöglich, einen linguistischen Namen auf den rassischen Befund zu übertragen). Die meisten Völker Äthiopiens, wie z. B. die Galla oder die Kaffa oder die Agau -- die Urbevölkerung Nord-Äthiopiens --, haben das gleiche Aussehen wie die Amhara und Tigray" ("ይኸ ብዙ ጊዜ የሚገኘው አማሮችን በዘርና በባህል ረገድ ከሴማውያን ማገጣጠም ፍጹም ቅዠት ነው። (አንድን የቋንቋ ስም ወደ ዘር ግኝት ማስተላለፍ አይቻልም።) አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለምሳሌ ጋሎች ወይም ከፍኞች ወይም -- ሰሜን ኢትዮጵያን በጥንታዊ ሕዝብነት የያዙ -- አገዎች መልካቸው ያው የአማሮቹና የትግሬዎቹ ዓይነት ነው።") Eike Haberland, "Altes Christentum in Süd-Äthiopien", p. 3.

ጋራ አብሮ የሚሄደው ግሥም ብዙ ቍጥር ነው፤ ለምሳሌ፥ "ነግሡ" (ነገሡ)፥ "ሞቱ" (ሞቱ) ይላል።

"እለ" እና ግሡ የሚያመለክቱት ብዙነትን ከሆነ፥ ይህ አክሱማዊ የግዝ ስም አወጣጥ አባ ባሕርይ በክፍል 4 ስለ ሉባ ከጻፉልን ኦሮማዊ የግዝ ስም አወጣጥ ጋራ ተመሳሳይ ነውኮ። እነዚህ ስሞች የነገሥታቱ ሳይሆኑ እንደ "ሥሉስ ጎይሌ"፥ እንደ "ሜልባሕ" የግዝው ሠራዊት ስሞች ይመስላሉ። "ግሡ ብዙ ቍጥር የሆነው ንጉሡን ለማክበር ነው" የምንለው ቢቸግረን ነው፤ በግዕዝ ሲጻፍ ንጉሦችን በብዙ ቍጥር ግሥ ማክበር የተጀመረው በቅርብ ጊዜ ነው።

ዛጌዎችም ተመሳሳይ የዓውደ ግዛት (ጋዳ) ሥርዓት ሳይኖራቸው አይቀርም። ለምሳሌ፥ የግዛት ዘመናቸው የተመዘገበ ሁለት የነገሥታት ዝርዝር አለ። ባንደኛው ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት 11 "ነገሥታት" 7ቱ፥ በሁለተኛው ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት 9 "ነገሥታት" 8ቱ 40 40 ዓመት ገዝተዋል። ይህ 40 ዓመት ዓውደ ግዛት መሆን አለበት። አለዚያማ ይህ ሁሉ ተመሳሳይነት እንዴት አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። የጸሐፊዎች ፈጠራ ነው የሚል ትርጉም መስጠትም አያረካም።

ባጭሩ፥ ኢትዮጵያ ሀገርነቷ የነገደ ኩሳ ነው፤ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ቋንቋቸውን ገፈፍ አድርገን ብናያቸው አብዛኞቹ አገዎችና ቤጃዎች ናቸው፤ ልብ አላልነው እንደሁ፥ በጌምድር ማለት ምድረ ቤጃ ማለት ነው። አንዳንድ የታሪክ ምንጮች በጌምድርን እንደ "አገው ምድር" "በጀ ምድር" የሚሉትን እናስታውስ። የግዕዙና የዐረብኛው ምንጮች ኢትዮጵያንና ሐምን/ካምን አንድ ያደርጓቸዋል።

ይኸ ስለቋንቋዎች አመሠራረት ነው። ዛሬ ማን የማንን ቋንቋ ቋንቋዬ ብሎ እንደያዘ ለማወቅ ወደ ታሪክ፥ ወደ አንትሮፖሎጂ፥ ወደ አርኬዎሎጂ መሄድ ያስፈልጋል። በዚያን ጊዜ ኦሮሞነትና አማራነት ከዳቦው ውስጥ እርሾው ሆነው የቀረው ትልቁ የዳቦው ክፍል የኢትዮጵያ ነገዶች ውሕደት ሆኖ ያገኘዋል። የምርምሩን ውጤት ለማወቅ የሚጓጓ በጌምድርን፥ ጎጃምን፥ አምኃራን፥ ወለቃን፥ ፈጠጋርን፥ ያጥለቀለቁት ኦሮሞዎች አማራ እንደሆኑ፤ ኦሮሞዎች ደቡቡን ስላጥለቀለቁት ጉጂ፥ እናርያ፥ የአሩሲ ሐድያዎች ኦሮሞዎች እንደሆኑ ይረዳል። እዚህ ድርሰት ውስጥም በመጠኑ አንዳንድ ምልክት እናገኛለን።

"የምናገረው ቋንቋ የጥንት አያቶቼ ቋንቋ ነው" የሚል ሊሳሳትም ላይሳሳትም ይችላል፤ በጭለማ ማነጣጠር የሚሉት ዓይነት ነው። ክቡር አቶ ዐማኑኤል አብርሃም በትዝታቸው መጽሐፍ ውስጥ ባባቴም በናቴም ኦሮሞ ነኝ ያሉት ወላጆቻቸው ኦሮምኛ ሲነጋገሩ ስላገኟቸው መሆን አለበት። ቋንቋዎቻችን እንደልብስ የሚቀያየሩ ሆነዋል፤ በበጋው ወራት እንዳንቸገር ሰውን በክረምት ወራት በለበሰው ልብሱ አንከፋፍለውም።

### (5) "ጋላ" ስድብ ነው?

አንድ ቋንቋ የሚናገር ሕዝብ ሌላ ቋንቋ የሚናገውን ሕዝብ የሚጠራበት ስም ይኖረዋል። ያንን ስም ወይም ከተጠሪዎቹ ያገኘዋል፥ ወይም በአንዳች ምክንያት ይፈጥረዋል፥ ወይም "በመዝገበ ቋንቋ" ውስጥ ካሉት ቃላት አንዱን የሚስማማ የሚመስለውን ቃል ይመርጠዋል። "አፍሮ አይገብ"፥ "ሥሉስ ኃይሌ"፥ "ኃይላት"፥ "አርባብ"፥ "ቍርባን" ወዘተ እያሉ ለጦር ሠራዊቶቹ የሚሰጧቸውን ስሞች እናስታውስ። ያ እንዲህ ሆኖ የወጣው የሕዝብ ስም በኋላ በአንዳች ታሪክ ምክንያት ("**ጀግናው የእገሌ ሕዝብ**") እየተባለ መደነቂያ ወይም ("**አይ የእገሌ ሕዝብ ነገር**") እየተባለ መሰደቢያ ይምሰል እንጂ ሲወጣ "**እገሌ**" ይህን ዓይነት ትርጉም እንዳለው ማስረጃ አይገኝም።

እርግጥ ጠላት የጥላቻ ስምም ያወጣል፤ አባ ባሕርይ እንደነገሩን፥ ለቦረን ኦሮሞዎች አንዱ ክፍል "ዳቄ" የሚለውን ስም ያወጡላቸው ኦሮሞዎቹ ሳይሆኑ ሌላው ሕዝብ ነው (የድርሰታቸውን ክፍል ፲፫ ተመልከት)። ይህ የነገድን ስም ስድብ አድርጎ አነጋገር ደግሞ ብዙ ነገዶች በሚኖሩበት አገር ዐዋጅም የማያቆመው በሕይወት (በነገድነት) የመቆያ የሰው ልጅ ጠባያዊ ዘዴ (survival) ነው። ሆኖም፥ "ጋላ" ለስድብ የወጣ ስም ለመሆኑ ምንም ማስረጃ የለንም።

ዛሬ "ጋላ" ስድብ ነው ሲባል እሰማለሁ እንጂ ባደግሁበት አካባቢም ሆነ በማውቃቸው ምንጮች ዘንድ ቃሉ እንደ ማንኛውም የሕዝብ ስም ገለልተኛ መጠሪያ እንጂ ስድብነት የለበትም። ባደግሁበት አካባቢ እረኞች ስንከባበር በአማርኛ "አማራ" እና "ጋላ"፥ በኦሮምኛ "ሲዳማ" እና "ኦሮሞ" እንባባላለን፤ ስንናናቅና ስንሰዳደብ ደግሞ "ጋሎ ..." እና "ሲዳምቲቲ እነና ... " እንባባላለን። ቤተሰቦቻችን ተቈጥተው አቁሙ የሚሉን "ጋላ"፥ "ሲዳማ" መባባሉን ሳይሆን "ጋሎ" እና "ሲዳምቲቲ" መባባሉን ነው።

በነገዱ የተሰደበ ሁሉ የነገዱን ስም ቢለውጥ ዓለም ዝብርቅርቋ ይወጣ ነበረ። ጎሳዎችና ነገዶች ዝብርቅርቃቸው ቢወጣ ሳይሻል ይቀራል? በአሁኑ ዘመን ብዙ አማሮች "አማራ" እንዲባሉ አይፈልጉም። ምክንያታቸው ግን ኦሮሞዎች "ኦሮሞ እንጂ ጋላ አትበሉን" ከሚሉበት ምክንያት የተለየ ነው፤ "አማሮች" አማራነታቸውን አይክዱም፤ አማራ መባልን የማይፈልጉት ጎሰኝነት ኢትዮጵያዊነትን ሲቀናቀን ስላዩ ነው እንጂ ስድብነቱን ለመሸሽ አይደለም። አማሮች፥ ኦሮሞዎች ኦሮሞ መባልን የሚፈልጉትን ያህል አማራ መባልን አይፈልጉትም። ምርጫቸው ኢትዮጵያዊ መባል ነው። ግን አማሮች ኦሮሞዎችን ራሳቸው ኦሮሞዎቹ በፈለጉት ስም ለመጥራት ሲጥሩ፥ እነሱ አማሮቹ አማራ መባልን እንደማይፈልጉ እያወቁ "አማራ" ይሏቸዋል።

የ"ጋላ" ሕዝባዊ ትርጉሞችም ቢሆኑ እውነትነት ባይኖርባቸውም **ደጋጎች** ናቸው። አንዱ፥ "ነቢዩ መሐመድ እስልምናን እንዲቀበሉ ቢልኩባቸው (ለእነማ?) መልክተኞቹ ሲመለሱ ለነቢዩ ያመጡላቸው መልስ ነው፤ በአፍሪካዊ ዐረብኛ፥ **"ጋል ላ"** ("እምቢ አለ") የሚለው ነው። (በዐረባዊ ዐረብኛ ቢሆን "ቃለ ላ" ይሆን ነበረ።) ሌላው፥ "ነገዱ የመጣው ገላን ከሚባል ከሀገሩ ወንዝ ስለሆነ በወንዙ ስም ጋላ ተባለ" የሚለው ነው። ያም ይኸም ስድብ የለበትም።

ያም ሆነ ይህ፥ ዛሬ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች "ጋላ ስድብ ነው፤ ስትጠሩን ኦሮሞ በሉን እንጂ ጋላ አትበሉን" ካሉ ፈቃዳቸው ይሁንላቸው።

ኦሮሞ መባል ትክክል ቢሆንም በአማርኛ ስንነጋገር በደስታ እንድንጠቀምበት ተገንጣይ ኦሮሞዎችን እንዳያስታውሰን ኦሮሞዎች ነን የሚሉ አስፈላጊውን ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ሁለተኛው ድክመት ሌላ ቋንቋ እየተናገሩ አማርኛን እናርም ማለት ነው። ጀርመኖች ጀርመን አትበሉን፥ ስዊድኖች ስዊድ አትበሉን አይሉም፤ ሁሉም በመሰለው ሲጠራቸው ተቀብለውታል። እነሱ ግን ራሳቸውን ለራሳቸው ባወጡት ስም ይጠራሉ። ዋናው ነገር ከመግባባቱ ላይ ነው። እርግጥ አንድ ሰው በኦሮምኛ ሲነጋገር "ጋላ" ቢል አያምርበት ይሆናል።

ከላይ እንደጠቀስኩት ወደኋላ ዘመን የተጻፉት ካልሆኑ በቀር ምንጮቹ "ጋላ"ን ላንድም ለብዙም ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ፥ "ወመጽአ ጋላ" ሲሉ እንደሁኔታው "ጋላ መጣ" ወይም "ጋሎች መጡ" ማለታቸው ሊሆን ይችላል። ስለዚህ፥ ዜናሁ ለጋላን እና ከምንጮቹ የምቀዳቸውን ሌሎቹን የግዕዝ ጥቅሶች ስተረጉም ከ"ጋላና" እና ከ"ጋሎች" አንዱን የምመርጠው እንደ ሁኔታው ለአማርኛ ተስማሚውን ነው። ለግዕዙ የተቻለውን ያህል ለመቅረብ ስል በነጠላ አነጋገር "ሕዝቡ" እንደሚባለው፥ "ጋላው" የምልበትም ጊዜ አለ።

### (6) የጋላ/የኦሮሞ ዜና ለምን ተጻፈ?

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ የብዙ ነገዶችና ጎሳዎች ሀገር ሆና ሳለ በግዕዝ ስላንዳቸውም ተለይቶ ኦሮምኛ ስለሚናገሩ ኢትዮጵያውያን (ስለ ጋላ) የተጻፈውን ያህል አልተጻፈም። ከሌሎቹ ይልቅ ስለኦሮሞ በይበልጥ ለማወቅ የቻልነው በምን ምክንያት ነው? በሌላ አነጋገር፥ ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ስለሌሎቹ ጎሳዎች ያንን ያህል የግል ዜና ያልጻፉልን ለምንድን ነው?

መልሱ ቀላል ይመስለኛል። ጸሐፊዎቻችን ስለ ሌሎቹ ጎሳዎች ብዙ ያልጻፉልን የመጻፍ ፍላጎት ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን ስለነሱ ብዙ የሚያውቁት ስለሌላቸው ነው። ሌሎቹ ጎሳዎች ወይም ነገዶች ኢትዮጵያውያን የሆኑት ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ከመገኘታቸው በፊት ነው።

ጸሐፊዎቹ እነዚህን ጎሳዎችና ነገዶች ኢትዮጵያ ውስጥ አገኟቸው እንጂ ወደ ኢትዮጵያ እንዴትና በየት በኩል እንደመጡ አላዩም፤ ያየም አላገኙም። እንዲህ ከሆነ ስለማያውቁት ነገር ምን ብለው ይጻፉልን? "የኢትዮጵያውያን አባታቸው ኢትዮጲስ ይባል ነበረ። የነገደ ዮቅጣን፥ የነገደ ኩሳ ልጆች በዚህ ወጥተው በዚያ ወርደው ኢትዮጵያ ሰፈሩ፥ ወዘተ" የሚሉ ታሪኮች ሁሉ ያላየ፥ ያልሰማ የነገረን ገና የምርምር ማስረጃ ያልደገፋቸው ከአፍ ወደ አፍ የተላለፉ ቅርሶች ናቸው፤ የአንድ ሰው የአንድ ዘመን ጣፋጭ ፈጠራ ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙ ያፍ ታሪኮች በምርምር መስቀልኛ ጥያቄ ሲወጠሩ በድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት ይንኮታኮታሉ። ቅርሶች ስለሆኑ ግን ከመዝገብ አይፋቁም።

ስለኦሮሞዎች የምናውቀው ከዚህ በፍጹም የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ስለነሱ የተጻፈው ወደ ማህል ኢትዮጵያ ሲገቡና ከገቡም በኋላ ምን እንዳደረጉ ባዩ የዓይን ምስክር ታሪክ ጸሐፊዎች ነው። *የዜናህ ለጋላ* ደራሲ ክፍል ፩ ላይ፥ "እንደዚሁ ባሊን መውጋት በጀመረበት ጊዜ የተገዘረው (ሉባ) ሜልባሕ ይባላል። የአባቱን ስም አላውቅም፤ ምክንያቱም የሚነግረኝ የለም" ያሉትን እዚህ ላይ እናስታውስ።

ይኸም ሆኖ፥ ስለ ኦሮሞዎች ካፍ ታሪክ የሚቈጠር ብዙ ተጽፏል። ሁለቱ እንዲህ ይላሉ[6]፤

6. (1) EMML 7346, ff. 13a-14a; (2) EMML 1521, pp. 55-6, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. V, p. 20. አፄ ገላውዴዎስ ግራኝ እንደሞተ የፖርቱጋልን ሰዎች (ካቶሊኮቹን) አገር ሰጥቶ ማስፈሩ እርግጥ ነው። እነሱም ስለገላውዴዎስ ሲናገሩ፥ "ግራኝን ለማሸነፍ እንድንረዳው ሃማኖቴን በናንተ ሃይማኖት እለውጣለሁ ያለውን ቃል አጠፈብን" ይሉ ስለነበረ፥ ለበቀል ኦሮሞዎቹን አርፈው ከተቀመጡበት አስነሥተውበት ይሆናል። አፄ ፋሲል "ካገሬ ውጡ" ቢላቸው ወንድሙን ማሳመፃቸው በታሪክ የተመዘገበ ነው። የካቶኛኛሊኮቹ ጳጳስ ሲባረሩ፥ "እግዚአብሔር የሐበሾችን እምቢተኛነት ለመቅጣት መጀመሪያ በግራኝና በአደል እስላሞች እጅ የጣላቸውን ዱላ እና አለንጋ አሁን ለጋሎች እንደሰጣቸውና እነሱም የበለጠ ጨካኝ መቅሠፍቶችና የዚህ ያልለዘበ መንግሥት አውዳሚዎቹ እንደሚሆኑ ገልጸላቸዋል"፤ እሳቸውም "የሀገሪቷን መንግሥቶችና አውራጃዎች የሚወሩና የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ፈጽሞ ለመውደም የሚያደርሱ ጥቁር ጉንዳኖች አሉ" ብለው እርግማንና ትንቢት እንደተናገሩ የሳቸው ሰዎች መዝግበውላቸዋል፤ Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, p. 135. አለቃ ታየ ስለኦሮሞዎች የሚነገሩትን እውነት ያልሆኑ ታሪኮች የሚሏቸውን በብዙው ሰብስበዋል። እዚያ የወይዘሮዋ ታሪክ የተለያየ ትረካ አለው፤ አንዱ እንዲህ ይላል፤ "ባፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን (1307-1336) በሃይማኖት የተነሣ እጨጌ ፊልጶስ ረግመውት በሀገራችን ጽኑ ረኀብ ሆነ። በዚያን ጊዜ የቸገራት ሴት ወይዘሮ (ልዕልት) በፈጠጋር ነበረች። ደግሞ አዝማች እንድርያስ የሚባል የደዋሮና የከተታ መኰንን ነበረ። የሱም ላሎ የሚባል የላም ራስ ባሪያ ነበረው። ያቺ ሴት ወይዘሮ ቢርባት ወተት ቢያጠጣኝ ብላ ለላሎ አደረችለት። እሱም ምሽት አደረጋት፤ ፬ ወንዶች ፫ ሴቶች ልጆች ወለደችለት። ስማቸውንም የወንዶቹን

(1) አዝማች እንድርያስ የሚሉት መኰንን (አገረ ገዢ) የአርእኝ፥ የደዋሮ፥ የፈጠጋር ጌታ ነበረ። (የዚያን ጊዜውን) የላም ራሱን ("ላም ራስ" የወረዳ ገዥ የማዕረግ ስም ነው) ላሌ ይሉት ነበረ። ደኻ ወይዘሮ (ልዕልት) ብታድርለት ሚስት አደረጋት። ልጅ ብትወልድ ትልቁን ከረዩ አለው። ተከታዩን ሜጫ አለው፥ ሶስተኛውን ቱለማ አለው፥ አራተኛውን ወሌ አለው።

እሊህን አራቱን ምድር እየማሰች፥ ጨርቅ እየጐዘጐዘች አሳደገቻቸው። እዚያ ሰይጣን አደረባቸው፥ ሌላ ቋንቋ (ኦሮምኛ መሆኑ ነው) ያናግራቸው ገቦመር። ከሰው ሳይገናኙ አደጉ። ካደጉም (በኋላ) አባታቸውን እያስከተሉ የሰው ከብት (መቀማት) በፍየልና በበግ ገቦመሩና ፈረሱን ላሙን (ከብቱን) ያገኙትን ሁሉ ይቀሙ ገቦመር።

ሰው ሁሉ ተሰበሰበና እጌታ(ቸ)ው ዘንድ አቤት አቤት አለ። ጌታቸው ቢሰማ ተዉ አላቸው፥ ስንኳን ይተዉ የጌታቸውን ግትል (ከብት?) አስቀሩ። ላሙን ይዘው ጋላ የሚሉት ወንዝ አለ፥ ዱር እዚያ ገብተው ዐመፁ። ጌታ(ቸ)ው ሰዉን ክተቱ አለና ተዋጋቸው፥ ድል ነሡና ጌታቸውን ገደሉ፥ ሰውንም ፈጁት።

ከዚያ ወዲያ የሚቆም (የሚቋቋማቸው) ጠፋ። (አገሩ) በ፩ ዓመት መገር ድረስ ጠፋ። በ፪ ዓመት ደራ አደረሰው። በአፄ ኢያሱ ዘመን ወለቃ፥ ሸግላ፥ ወሎ አምሐራ እስከ መልዛ ጠፋ።

(እነሱም) በወንዙ ስም ጋላ ተባሉ።

(2) በሠርፀ ድንግልም ዘመን ጋላ ተነሥቶ ክርስቲያንን ሁሉ ይዋጋቸው ጀመር። እሱም በጥቂት ዘመን እረብቲልና በረታባቸው።

የጋላም አመጣጥ ታሪኩ እንዲህ ነው። ባፄ ገላውዴዎስ ዘመን ነፍጥ ይዞ የመጣ ፈረንጅ ግራኝ ከሞተ በኋላ ከገላውዴዎስ ጋራ ወደ ሸዋ ሄደ። ያፄ ልብነ ድንግልን ላም (ከብት) እየጠበቁ ገላን በሚባል አገር ወንዝ ዳርቻ ከሚኖሩ ዘላኖች ጋር ይኖር ጀመር። ከነዚህም ወገን ሚስት አግብቶ ፪ ልጆች ወለደ። እነዚህም በዘላኑ ቤት አደጉ፥ በጥቂት ዘመን አካለ መጠን አደረሱ፥ ጐለመሱ። እነሱም በዘላኑ ቤት በአዳል ከሚኖሩ ከእስላሞች ወገን አገቡ፥ ፯ ልጆች ወለዱ። እነሱም ፲፪ ነገድ (ሆኑ)። ገላን በሚባል አገር ወንዝ ስለኖሩ ጋላ ተባሉ። ሸዋን፥ አማራን፥ ወለቃን፥ ጐጃምን፥ ዳሞትን፥ በጌምድርን፥ እንደርታን፥ ላስታን ሁሉ ወረሱ። ክርስቲያንን ሁሉ ዙሪያውን ከበቧቸው።

---

ከረዩ፥ ትሌማ፥ መጫ፥ ወሌ አላቸው። ሴቶችንም አልኮ፥ ዱረቲ፥ አያንቱ አላቸው" (JE692E, p. 564). ሌላው ታሪክ ሴት ወይዘሮዋን "ያጼ መለክ ሰገድ የእጎት ልጅ ነኔት (መኒት/መና እሥራኤል) የምትባል"፥ ላሌን ደግሞ "ከጥቁር ምድር ማርኮ ያመጣው" ይላቸዋል፥ እዚያው ገ. 570። የዚህን ታሪክ ሌላ ትረካ ካኩት *የኢትዮጵያ ዓመታዊ መጽሔት* ውስጥ በ፲፱፻፸፱ ዓ. ም. አሳትሞታል፥ Caquot, "Histoire Amharique de Grāñ et des Gāllās," pp. 124-132.

ስለ ኦሮሞ የሚታመን ዜና የተጻፈልን ምክንያቱ የኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ ሲመጡ ጸሐፊዎች ስላዩዋቸውና አመጣጣቸው የመንግሥቱና የክርስቲያኑ ሕዝብ ወገን የሆኑ ጸሐፊዎችን ለጽሕፈት የሚጋብዝ ሆኖ ስለተገኘ ነው።

ኦሮሞዎች ከደቡብ (ምናልባትም ከደቡብ ምሥራቅ) ተነሥተው ወደ ማህል ኢትዮጵያ የገቡት የሕዝብ ንቅናቄ ከሚወስደው ዘመን ጋራ ሲተያይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው። ሲገቡ ጉዟቸው ከፍ ባለ ጥድፊያ ነበረ። በ1570 ዓ. ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ጋራ ተጋጭተው በአፄ ሱስንዮስ ዘመን (1600-1625) አገሩን እስከ ትግሬ ድረስ እንደአጥለቀለቁት፥ ሕዝቡንም እንደአርበደበዱት እንመልከት[7]፤

> *ወእምድኅረ ኀልፈተ ክረምት በወርኃ ጥቅምት ኮነ ሁከት ዓቢይ በውስተ ኵሉ ሀገረ መንግሥት ። ወተሰምዓ ከመ ከረዩ በምልኡ ወረደ መንገለ ትግሬ፥ ወመረዋ ወፅዓ መንገለ በጌምድር፥ ወከመ ኢቱ ወቦረን ይፈቅዱ ፀቢአ ጐዣም።*

❖

> ክረምት ካለፈ በኋላ በጥቅምት ወር በመንግሥቱ ሀገር[8] ሁሉ ትልቅ ሁከት ሆነ፤ ከረዩ በሙሉ ወደ ትግሬ እንደ ወረደ፥ መረዋ ወደ በጌምድር እንደ ወጣ ኢቱና ቦረን ጎጃምን ሊወጋ እንደሚፈልግ ተሰማ።

ኦሮሞዎች ወደሰሜን ሲገፉ መንገዱ የቀናቸውና ሀገሪቷን በአጭር ጊዜ ውስጥ ያጥለቀለቋት ስለተደራጁ እንጂ ተቃዋሚ ስላልነበረባቸው ወይም "ሰርዶ ሁን መሬቱን አላብስ" ተብለው በመመረቃቸው ያገኙት የቁጥር ብዛት የወረሩትን አገር ሕዝብና የጊዜውን መንግሥት ለማሸነፍ የሚያስችላቸው ሆኖ አይደለም። ቁጥራቸውን አቅም ያደረገላቸው አሸንፈው ከወረሩት ሕዝብ ያጠፉትን አጥፍቶ የተረፈውን ኦሮሞ የማድረግ ችሎታቸው ነው። አንድ አገር በያዙ ቁጥር "ሲዳማ" ከሚሉት ነባር ሕዝብ ግማሹን ደምስሰው የቀረውን ቋንቋቸውንና ባህላቸውን በማውረስ እንደነሱ ኦሮሞ ያደርጉታል፤ "ሲዳማነቱ" ይቀራል፤ ከተወራሪነት ወራሪነትን ስለሚመርጥም ኦሮሞ ሆኖ አብሮ ወረራ ይወጣል። ለምሳሌ ዛሬ ከኦሮሞ ነገድ ውስጥ ገብተው የሚቈጠሩት እነ

7. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 165.
8. "ሀገረ መንግሥት" ("የመንግሥት ሀገር") የሚሉት "ዳር አገር" የማይሉትን፥ ማእከላዊው መንግሥት (ንጉሡ) የራሱን ሰው በነጋሪት (በዐዋጅ) የሚሾምበትን ክፍለ ሀገር ነው፤ ሁለቱን አስተዳደሮች አንዱን "ሀገረ መንግሥት" ሌላውን "ምድረ ግብር" ይሏቸው እንደነበረ በዘርአ ያዕቆብ ታሪክ ውስጥ ይታያል፤ Perruchon, *Les Chronique de Za'a Yâ'eqôb*, p. 15. ንጉሡ የሁለቱም አስተዳደሮች የበላይ መሆኑን ለማመልከት "ንጉሠ ጽዮን፥ ንጉሠ ነገሥት

ሰዮ፥ አቦኖ፥ ቱምኤ፥ ሌቃ፥ ሐገለባቦ፥ ኦቦ፥ ሐርሱ፥ ሊሙ ኦሮሞነታቸው "በጥምቀት" እንጂ በዘር እንዳይደለ ብላታ መርስዔ ኀዘን ይናገራሉ። ይኸ ልክ የአማራ ባህል (ቋንቋውና ሃይማኖቱ) በሀገሪቱ ሰሜንና ማእከል እየተስፋፋ ሌሎቹን አማራ እንዳደረጋቸው ማለት ነው።

ማስረጃ የለኝም እንጂ ለኦሮሞዎች ድል አድራጊነት ሌላም ምክንያት እጠረጥራለሁ። ሕዝቡ የመንግሥቱ ጨቋኝነትና ዘራፊነት ስለመረረው ኦሮሞዎች እንዲመቱት ረድቶ ይሆናል። ታሪክ ጸሐፊው የአግዛዙን መራርነት ሲመዘግብ እንዲህ ይላል[9]፥

> ዘድንግል (1596-7) በነገሠ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሰዎች ፪ በጉንት ሠራላቸው፤ ፪ ዕዳ ፋቀላቸው፤ ፩ ዕዳ አንበሳ ወደቅ ነው። በቀኝ በግራ ጐኑ የተመሰገነው ከብት በንጉሡ ማኅተም ኢየተተኰሰ ለንጉሡ ይሆን ነበረ። (ዘድንግል፥) "ይህ ዘረፋ ነው፤ እንደ ዓቅሙ ኢየተቋጠረ (ቀረጡን) ፍሪዳ ይክፈል" አለ።
>
> ፪ተኛ ዕዳ ገብሮ ገብሮ ሲደኸይ የግብር መሬት ለገዢ ሰጥቶ በጤና መሄድ አልነበረም። የሚከፍለው ገንዘብ አጥቶ ሁለንተናውን ሲጨርስ ልጁን ለግብር ያሳልፍ (ይሰጥ) ነበረ። ልጅ የሌለው ከነምሽቱ ራሱ ባሪያ ሆኖ ይገዛ ነበረ። አጼ ዘድንግል ግን "ሰው ባሪያ፥ ምድር እናሪያ አይሁን፤ ምድር ባሪያ፥ ሰው እናሪያ ይሁን" ብሎ አዋጅ ነገረ። ግብር ሲቸግረው መሬቱን ለገዢው ጥሎ ይህድ እንጂ ብሎ።

"አንበሳ ወደቅ" ሲሉ ሞአ አንበሳ ከትልቁ በሬ ላይ ጉብ አለ ማለታቸው ነው። ከብቱ "የተመሰገነ" ከሆነ ሁሉም ይወሰድበታል። ከብት በድብቅ ማድለብ አይቻልም።

የዜናሁ ለጋሳን ክፍል ፲፱ ስናነብ እንደምንረዳው ምድሩ የነጌቶች ሆኖ ገበሬው ተጋዝቶ ገባር ይሆን ነበረ። የአፄ ዘድንግል ትልቁ "በጉንት" መገበር ያልቻለ መሬቱን ለቆ ይሂድ ማለቱ ነበረ፤ አልሆነለትም። መኳንንቱ ገባር ሊያሳጣን ነው ብለው በጦር ልብ እራሱን ብለው ገደሉት።

ይኸ ወንጀል ይፈጸም የነበረው በክርስቲያኑ አገር ነው። ሌላውማ እንደ "ጎንካ እና እንደ ሻንቅላ" ያለው ዘወትር ባሪያ

---

ዘኢትዮጵያ" ይባል ነበር፤ Perruchon, "Histoire des Guerres d'Amda Ṣyon," p. 280. ሀገረ መንግሥት/ጽዮን ዳሞትን፥ ደምቢያን፥ ስሜንን፥ ጎጃምን፥ ሸዋን፥ ትግሬን፥ ምድረ ባሕርን ("ኤርትራን") ይጨምራል። ሀገሮቹ በዓምደ ጽዮን ታሪክ ውስጥ ተዘርዝረዋል፤ እዚያው ገ. 280-1። በሁለቱ አስተዳደሮች መካከል ያለው ልዩነት የዳራጎሮቹ የራሳቸው ፈላጭ ቈራጭ ባላባት ነበራቸው። "በእስላም ባሕር ውስጥ የክርስቲያን ደሴት" የሚሉት አነጋገር የሚያመለክተው ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን ሳይሆን በተለይ ንጉሡ በዚህ "ሀገረ መንግሥት/ጽዮን" በሚባለው ክፍለ ሀገር የዘረጋውን አስተዳደር መሆኑ ነው።

9. *የጎጃም ታሪክ*፡ EMML 5403, ff. 63b-64a.

የሚታደንበት ጫካ ነበረ። ታዲያ እንዲህ ያለውን መንግሥት የሚያርበደብድ ጎይል ቢመጣ ተገፊው ምን ይላል? በግራኝ ወረራ ጊዜና በኛስ ሕይወት ተመሳሳይ ነገር አልደረሰምን?

ኦሮሞዎች ያሸነፉትን እያስገደዱ አገልጋይ ("ገበር") ማድረግንም የወሰዱት ከጠላቶቻቸው ሊሆን ይችላል። ቃሉ/ስሙ ለአማርኛ አዲስ አይደለም። አፄ ይሥሐቅ (1406-1421) የተዘፈነለት ምክንያት አንዱ ዘምቶ ብዙዎችን "ገበር" ስላደረጋቸው ነበር[10]፤

ስንቱን እቄጽር።
የሐላባ ገበር።
የጣይቶ ገበር።
የላቦላ ገበር።
ስንቱን እቄጽር።
የጉዴላ ገበር።
ሲፈክር ነበር።
ስንኳን ለአምሐራ ገርር (ወታደር)።
ሰማይ ቢከነበል።
እናቆም (እናቆማለን) ሲሉ ነበር በጸር (በጦር)።
ሲፈክሩ ነበር።
አጠፋዋቾ ለዝክር።

## (7) የኦሮሞ ታሪክ ከምንጩ

ኦሮሞዎች ከዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ጀምረው ወደ ማህል ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት አገሪቱን ቀደም ብለው በያዙት ሕዝቦች፥ በተለየም በላያቸው በተቋቋመው በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ስለተፈጸመው ግጭት በይበልጥ ለማወቅ የሚፈልግ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ጀምሮ ከግራኝ በኋላ የተነሡ ነገሥታትን ታሪክ እና ዜና መዋዕላቸውን[11]፥ በተጨማሪም የአቶ ዐፅሜን መጽሐፍ[12] (ስድባቸውን እየናቀ) ማንበብ ይኖርበታል። ኦሮሞዎች ከየት ተነሥተው በየት በኩል ወደማህል ኢትዮጵያ እንደገቡ በአማርኛ ከተጻፉት ውስጥ ሊጠና የሚገባው ሆኖ ያገኘሁት ክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ የጻፉትን ነው[13]።

10. Guidi, "Le canzoni geez-amariña", p. 59.
11. ብዙውን ለቅሜ *ባሕረ ሐሳብ* ውስጥ አስፍሬዋለሁ።
12. Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis and His Work*. ዶ/ር ባይሩ የአቶ ዐፅሜን መጽሐፍ ለጎትመት ሲያዘጋጅ ሽልማት የሚያሰጥ ሥራ ሠርቷል፥ ግን የመጽሐፉን ርእስ ባይለውጠው ደግነት ይሆንለት ነበር።
13. ይልማ ዴሬሳ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፥ ገጽ 212 ላይ የሚጀምረውን ምዕራፍ 40ን ተመልከት። ክቡር አቶ ይልማ በዚህ መጽሐፋቸው ውስጥ በኦሮሞዎች ላይ ጠብ

እነዚህን ምንጮች ሳይመረምር ምዕራባውያንና በሚሲዮኖቻቸው ያደጉና ሌሎችም ለኦርቶዶክስ ክርስትና ጥላቻ የሚሰማቸውና እንደ ጠላት የሚያዩዋት የጻፏቸውን "የኦሮሞ ታሪክ" የሚያነብ እነዚህ ዘመናዊ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያን ሕዝብና አገራቱን የቱን ያህል እንደበደሉ ልብ አይለው ይሆናል። እነዚህ ጸሐፊዎች "የኦሮሞ ሽማግሌዎች ጠይቀን ያገኘነው ነው" የሚሉትን እውነት ይሁን ሐሰት ማመሳከረ እንደማንችል ያውቃሉ። ለዚህ ትውልድ የጊዜው ትልቁ እንቅፋት ታሪክ ነገሥቱና ዜና መዋዕሎቹ በግዕዝ መሆናቸውና ቢተረጐሙም ያሁኑ ትውልድ በሰፊው በማያውቃቸው የምዕራባውያን ቋንቋዎች መተርጐማቸው ነው። የተተረጐሙትም ቢሆኑ የምርምር መጻሕፍት ስለሆኑ የሚገኙት በታላላቅ ቤተ መጻሕፍት እንጂ በሕዝብ የመጻሕፍት መደብር አይሸጡም።

የኢትዮጵያን ታሪክ ከምንጩ የሚያነብ ከሁሉ አስቀድሞ በክርስቲያኑ መንግሥት ባለሥልጣኖችና በሚገዙት ሕዝብ መካከል ሁል ጊዜ ግጭት እንደነበረ ያያል። ከዚያም የኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ አመጣጥ ለምን "የመንግሥቱ ወገን የሆኑ ጸሐፊዎችን የሚጋብዝ ሆኖ" ተገኝቷል እንዳልኩ ይረዳል። ከዚህ በታች ከዋናዎቹ ዘመን (ከዓሥራ ስድስተኛው እስከ ዓሥራ ስምንተኛው ምእት ዓመት) የታሪክ ምንጮች ለዚህ አጭር ጥናት ለምሳሌነት የሚበቁትን ያህል በጥቂቱ እጠቅስላቸዋለሁ።

### (ሀ) መንግሥትና ሕዝብ

የሕዝብና የመንግሥት ግጭት መሠረታዊ ምክንያት፥ ከቤተ መንግሥት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ገዢው ድረስ ያሉ ባለሥልጣኖች ወታደሮቻቸውን፥ ሎሌዎቻቸውን፥ ባሮቻቸውን ጨምሮ ብዙ ስለሆኑ፥ በተለይ ድርቅ ሲገባ፥ ለነሱና ላግበሰበሱት ሠራዊታቸው ቀለብ፥ ለፈረሶቻቸው መኖ ማቅረብ ሕዝቡን ስለሚከብደው አልፎ አልፎ አልገብርም ይል ስለነበረ ነው። በዚያ ላይ ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋራ በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ነገዶች

---

አጫሪ ሱማሌዎች ናቸው እንጂ ኦሮሞዎችስ ሰላማዊ ሕዝቦች ናቸው የሚሉትን አስተያየት ሰላማዊነታቸውን ከኤኮኖሚ ሥርዓታቸውጋራ እያስተያዩ የሚገባውን ያህል አላብራሩትም። አቶ ብርሃኑ ለሜሶና አቶ ታቦር ዋሚ *የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ* በሚል ርእስ ያሳተሙትን መጽሐፍ ሳነበው የተረዳሁት እነሱም እንደገለጹት የመጽሐፉ "ዋና ዓላማም የኦሮሞ ሕዝብ መፍለቂያና ጥንተ መኖሪያ በዚህች የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መሆኑን የሚያረጋግጡ የታሪክ ማስረጃዎች ማቅረብ ነው" (ገ. 41)። መጽሐፉ ከመታተሙ በፊት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ክፍል መምህራን ካዩት፥ ቢቀሩ የደራሲዎቹን የተቀደሰ ዓላማ የማያደናቅፉትን አነጋገሮች እንዲያስቀሩና ዜናሁ ለጋላንም ከግዕዙ የሚተረጐምላቸው ሰው እንዲፈልጉ ወይም ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን የተረጐሙትን (EMML 3749ን) እንዲያነቡ ለምን ሐሳብ እንዳላቀረቡላቸው ግልጽ አይደለም።

ሰብላቸው ቢሠምርላቸውም አቅም ካገኙ (ወይም ያገኙ ሲመስላቸው) አንገብርም ይሉና መተላለቅ ይመጣል::

ለምሳሌ ከፈላሾች ጋራ ከሆኑት ግጭቶች ውስጥ አንዱን ዘገባ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ታሪክ እንቅዳ[14]፥

*ወበውእቱ ወርኃ ክረምት ተንሥአ ደዌ በከተማ ወሞቱ ብዙኃን ሰብእ በውእቱ ደዌ:: ወእምቅድመ ዝንቱ ኮነ ምክረ ሐዜጌ ከሪሞ ከመ ይሖር ለፀቢአ ጋላ እኂዞ እምአንጎት እስከ ግድም ወኢፋት ወፈጠጋር ወደዋሮ::*

*ወዘንተ ምክረ ዐቀመ ወአጽንዓ ምስለ ኵሉሙ ሥዩማን ዘለፈ ወለፈ ጊዜ አስተፋነዎሙ ለለ ብሔሮሙ፥ ወባሕቱ ይመስለነ ዘይቤ እግዚአብሔር በውእቱ ጊዜ ኢኮነ ምክርየ ከመ ምክርክሙ ወኢኮነ ሕሊናየ ከመ ሕሊናክሙ::*

*ዘንተሰ ዘንብል እስመ በፈቃደ ዚአሁ ዘትሜግብ ኩነታተ ዓለም ኮነ ሙራደ ሐዜጌ ድኅረ ኃለፈ ክረምት መንገለ ፈላሻ፥ ወተርፈ ፀቢአ ጋላ:: ወምክንያተ ተኃድኑቱሰ ለውእቱ ምክር በእንተ ፀብአ ጋላ ናየድዕ በዝየ::*

*መጽአ መልእክት ዘይብል አትረፈ ረዳኢ ፈንዎተ ጸባሕት ዘይቤ ለሐዜጌ እንዘ ሀለዉ በጉባኤ እፈኑ ግብርየ ብዙኃ እክለ ወመዓረ አልሀሞተሂ ወአባግዓ ከማሁ አልቦ እምዝ ኮኑ ኢወሀበ ምንተኒ::*

*ወዘንተ ሰሚዖ ነደ ልቡ ከመ እሳት:: ወሶቤሃ ወጠነ ምክረ ከመ ይፅብአሙ ለፈላሻ ወይኅድግ ፀቢአ ጋላ:: ወለአከ ኀበ ኵሉሙ ጨዋ ውእበ ሠየምተ ትግሬ ከመ ይብጽሑ በዕድሜ ዘዓደሞሙ:: ወምስለ ዝኒ ኮነ ይብል፥ ይኄይሰኒ እትበአስ ምስለ ዕድወ ደሙ ለእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ እምእሑር ለፀቢአ ጋላ:: ዘንተ ምክረ አጽንዓ በወርኃ ክረምት...::*

*ወበይእቲ ዕለት ወረዱ ሽዋዳ ብዙኃን ሰብአ እግር ወመስተጽዕናን አፍራስ ወማኅረኩ ብዙኃ አልሀምተ እስላም ወክርስቲያን ዘተመይጡ እምክርስትና ኀበ አይሁድና፥ እስመ ነበሩ ልኢኮሞ ኀበ ሐዜጌ እንዘ*

14. Conti Rossini, *Historia Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp 84-6. የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ከልዩ ልዩ የአገው ጎሳዎችና ከሌሎችም ጋራ ይጣሉ ነበር፥ ፈላሻዎቹን የሚመለከተውን ጥቅስ በተለይ የመረጥሁት "ፈላሾች ፈላሻ የተባሉት ርስታቸውን ተነቅለው ፈላሲዎች እንዲሆኑ ስለተፈረደባቸው ነው" የሚለው ትክክል አለመሆኑንና እንዲያውም የሚያጓጓ ርስት እንደነበራቸው በዚያው ለማሳየት ነው:: ሱስንዮስ "የወንድጌ እና የለግ ሰዎች ግብር ከማግባት እንደለገሙ በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ "ሠራዊቱ እንዲዘርፋቸው" እንዳዘዘ ሠራዊቱም "ብዙ ከብቶች" እንደማረኩ የሚያሳየውን ጥቅስ ገጽ 131-135 ላይ ተመልከት:: ገጽ 31 ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፥ "በከተማ ረኀብ በገባ ጊዜ ፋሲሎ ሐዜጌ ዘንድ መጥቶ እንዲህ ሲል ምክር አቀረበ፥ 'እነሆ ከተማው ተራበ ዘረፋ ልወስዳቸው መውጣቴ ነውና የከተማው ሰው ይከተለኝ' ሐዜም እሺ አሉ (ተስማሙ)::"

ይብሉ ናሁ መጻእነ ኀበ እግዚእነ ምስለ አልህምቲነ ወአንስቲያነ ወደቂቅነ። ህላዌሆሙሰ እምቅድመዝ ኮነ ኀበ ምድረ ምልክናሁ ለረዳኢ።

ወበፈቃደ እግዚአብሔር ተሰነአወ ምጽአተ እሉ ምስለ ሙራደ እሉ ኃያላን ከመ ትትዓወቅ ኂሩተ እግዚእነ በአግብኦተ ንዋዮሙ ለእሉ እምድኅረ ተማኀረኩ፣ ዘመደ እክልኒ ብዙኀ ተዘርፈ በይእቲ ዕለት። ወባሕቱ ኢፈቀዱ ነሢኦቶ ለዳንኤላ ወዘይመስሎ እንበለ ስርናይ ወጽሩይ እክል ዘከማሁ። ለእሉሰ እለ ተማኀረኩ አግብኦ ሎሙ በግዘት ኮሎ ንዋዮሙ ዘተነሥኦ። ወኢያመክነየ እንዘ ይብል ሚላዕሌየ እመ ነሥኡ ሠራዊትየ ክርስቶሳዊያን ንዋየ እስላም ወፈላሻ። ኦለዛቲ ኂሩት ዘትመስል ኂሩተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘያሠርቅ ፀሐየ ላዕለ ኄራን ወእኩያን ወያዘንም ዝናመ ላዕለ ጻድቃን ወኃጥኣን።

ወበሳኒታሁ በዕለተ ዓርብ ወዓልነ በህየ፣ ወፈነዎ ለአዛዥ ሐሊቦ ቅድመ ገጹ ከመ ይጺሕ ፍኖቶ ወይምላእ ኮሎ ማዕምቀ። እስመ አንሀሉ ፈላሻ በውእቱ መዋዕል ወአጥፍኡ ፍኖተ ከመ ኢይሖርዎ አብቅልት ወአፍራስ። ወበይእቲ ዕለት አስተራትዓ አዛዥ ሐሊቦ መብእሰ ወጕጻገጻ ወረሰዮ መጽየሕተ ርቱዓ።

ወበሳኒታሁ ዘውእቱ ዕለተ ቀዳም ተንሥአ እምህየ ወረሰየ ፍኖቶ መንገለ ለርዊ ወሰፈረ በጻርጻ። በይእቲ ዕለት አልቦ ዘተዓቅፈ ወአልቦ ዘድኅነ በፍኖት እምሰብእ እስከ እንስሳ እስመ የማነ እግዚአብሔር ትሜግብ ፍኖተ ዝንቱ ንጉሥ። ወበዕለተ ሰንበት ወዓልነ ኀበ ሰፈርነ በዕለተ ቀዳም።

ካሌፍሰ እኀወ ረዳኢ ወጠነ ያውጂ በእሳት አብያተ ምስለ ኮሉ ዘውስቴቱ። ወእክለኒ ዘህሎ በገራህት አውዓየ፣ እስመ ጻዕደወ በውእቱ ጊዜ ወበጽሐ ለማእረር። ከሳስስተኒ ኀበ ተከምረ አውዓየ እንበለ ምሒክ። ዘንተሰ ዘይገብር እስመ ይመስሎ ዘይትመየጡ ሶበ ኃጥኡ ሲሳየ፣ ወኢያእመረ ከመ ፈትሐ ቦቱ እግዚአብሔር።

ንሕነሰ ሶበ ርኢናሃ ለህገር እንዘ ኮለንታሃ ሥርጉት በሐመልማለ ዘርእ ወፍሬ ማእረር ተነደፍነ በፍቅራ ወፈቀድነ ነቢረ ውስቴታ በከመ ይቤሎ ጴጥሮስ ለእግዚእነ በደብረ ታቦር፣ ይኄይሰነ ንንበር ዝየ።

ኢንጎድግ ትንቢተ ቃሉ ለረዳኢ ዘተነበየ አመ መጽአ ኀቢሁ ሐርቦ። ወውእቱ ከዊኖ ጅደን ፈነወ ሠራዊቶ ምሁራነ ፀብእ ኀበ ሽዋዳ ዘዘረፍዎ ሰብአ ሐዌጌ። ለይእቲሰ ፈለግ ዘህለወት በማእከል አልቦ ዘተህበለ ዓዲዎታ።

ውእተ አሚረ ለአከ ቃለ ትዕይርት ኀበ ሐርቦ እንዘ ይብል፣ ኦኃያል አዝማች ሐርቦ ነያ ቅድመ ገጽከ ምድረ ርስት እንተ ትውኀዝ ሐሊበ ወመዓረ። አፍጥን መጺአ ወኢትትህከይ ከመ ትትዋረሳ ወትትካፈል አዕጻዳቲሃ።

ሐርቦሰ አርመመ ወኢያውሥአ ምንተኒ አላ አግብአ ለዘ ይኴንን ጽድቀ። ሶበኒ ተቃተሉ ሠራዊቱ ጸንዕዎሙ ፈላሻ በውእቱ ዕለት፣

ወአንትዕዎሙ ለሠራዊተ ሐርቦ ወይገንዎሙ እስከ ማእከለ ዓቀብ። ወባሕቱ ኢተሐገሉ እምኔሆሙ እንበለ ፩እምዐበይተ ሕዝብ። ዝንቱ ኮሉ ከዊኖ ተመይጠ ሐርቦ ብሔሮ በዳጎን ወበሰላም።

ወበብዙኅ ዓመታት ፍዳ ይእቲ ትዕይርቱ መጽአ ንጉሥ ጎየል መለክ ሰገድ ጎበ ስሜን። ዝንቱሰ ምጽአቱ ይመስል ከመ ዘይቤሎ ለረዳኢ ለአከ ጎበ ሐርቦ ከመ ይምጻእ ጎቤከ። ወህየንቱሁ ናሁ መጻእኩ ከመ እትካፈል አዕጻዳቲከ፤ ዘኢኃሠሥከኒ ረከብከኒ፤ ወዘኢጸዋዕከኒ ተሰጠውኩከ፤ ከመ ዘይብል ዘንተ ይመስል ምጽአተ እግዚእነ ጎበ ፈላሻ። እስመ ተህውከት ኮላ ሀገር እምግርማሁ በከመ ተብህለ አድለቅለቃ ለምድር ወሆካ።

ወበዕለተ ሰኑይ ተንሢአነ እምጻርዳ ሰፈርነ በሠሉስ ጎበ ቅሩበ አምባሁ ለካሌፍ። ወጎዳጣን ሕዝብ ወረዱ ቁሳ እንበለ የአዝዘዎሙ። ወሶቤሃ አርአዮሙ ብዙኃ ወልታ ወከሩናተ፤ ወባሕቱ ኢመጽአ ጎቤሆሙ ውእቶሙኒ ኢሖሩ ጎቤሆሙ። ወተፋርሁ በበይናቲሆሙ። ከተማሆሙኒ ገብሩ በአንጻሪሁ ዘሪፎሙ እክለ። በይእቲ ሌሊት አልቦ ዘተህበለ ቀሪበ ጎቤሆሙ ለአሕስሞ እምሰብአ ፈላሻ፤ እስመ ሞገሰ ግርማሁ ለዝንቱ ንጉሥ ትተልዎሙ፤ ወመልአኩ ይትዐየን ዓውደሙ። ዝንቱ ኮሉ ኮነ አመ ፳ወ፬ለወርኃ ጥቅምት። ስፍራሰ ዘሐዜጌ ምድረ ደግዓ ውእቱ፤ ወብዙኅ ቍሩ።

ወበሳኒታሁ በዕለተ ረቡዕ ወረዱ ሐዜጌ እመልዕልት ጎበ መትሕት ከመ ይፅብእዎ ለካሌፍ። ወአትረፍዎሙ በስፍራ ለዶባ ሥልጣን (ወ)ሳዊሮስ ምስለ ብዙኅ አፍራስ ወነፍጥ ወምስለ ብዙኃን ሰብአ ወልታ። ሐዜጌሰ ወሪዶሙ ገብሩ ከተማ ጎበ ሰፈሩ ሰብአ ትማልም። ዝንቱሰ ኮነ አመ፴፱ሁ ለወርኃ ጥቅምት።

ወፍኖተ ይእቲ ዕለት ኮነ በ፫ጸታ። ለእለሰ የሐውሩ በሣልሳይ ፍኖት ተንሥኡ ላዕሌሆሙ ፈላሻ፤ እስመ አእመሩ ከመ ኢሀሎ ሀየ ዝንቱ ንጉሥ መዋኢ ወሖረ እንተ ካልእ ፍኖት። ወሶቤሃ ተነየለ ላዕሌሆሙ ፊቅጦር ወልደ አዛዥር ፋኑኤል። ወቀተለ ብዙኃ እምኔሆሙ ወአወፈየ ለሐዜጌ መጠነ ፫ሸብሸበ። ዝውእቱ ቀዳማይ መዊአቱ ለእግዚእነ ወጥንተ ተመውአቶሙ ለፈላሻ።

ወቤተ ይእተ ሌሊተ ለጸቢሐ ሐሙስ እንበለ የሀብ ንዋመ ለአዕይንቲሁ ወኢድቃሰ ለቀራንብቲሁ እንዘ ይኄሊ ወይመክር ዘከመ እፎ ይፅብአ ለካሌፍ ወዘከመ እፎ ያወርዶ እመልዕልተ ደብር ዘተጸወነ ቦቱ። ወበይእቲ ዕለተ ሐሙስ አንግሀ ገይሰ፤ ወሖረ ከመ ይፅብአ ለካሌፍ።

ወእምዝ ፈነዎሙ ለመስተቃትላን በ፫ፍናዎት። ወእንተ ታሕታይ ፍኖት ሖረ አዛዥር ሐሊቦ ምስለ ባሕር አሥባ። ወኮኑ ቅድመ ገጹ ደኃረኅት ጐሣም ኑጋሽ ምስለ ውራን። ወበለፌ እሉ ኮኑ ቍርባን ኃያላነ ዝንቱ ንጉሥ እለ ኢይመይጡ ገጸሙ እምደርብዮ ከሩናት ወእምውግተረ እብን ወነፍጥ ወአጎፃ። ለዕሉ ኮሉሙ ፈነዎሙ ምስለ ብዙኅ ነፍጥ በበ ነገዶሙ ወበበ ሕዘቢሆሙ። ውእቱሰ ቆመ አንጻረ

ገጹ ለካሌፍ ጎበ ተዓየነ ምስለ ሠራዊቱ። ወዓቅመ ርጎቀቱሰ ለህላዌሆሙ የአክል መጠነ ፮ምዕራፍ አው ይበዝኍ። ወምስለ ዝኒ ጸድፍ ዓቢይ ማእከሌሆሙ ዘኢይትከሃል ይዕድውዎ።

ወኮነ ዐቢይ ፀብእ በይእቲ ዕለት ማእከለ ሠራዊተ ዝንቱ ንጉሥ ወማእከለ ፈላሻ። ወተዓብኦቶሙሰ ለሰብአ ካሌፍ ኮነ በአእባን እንዘ ያመረግሑ ላዕሌሆሙ ይክልእዎሙ ዓረገ እመትሕት ጎበ መልዕልት። በዘ ከመዝ ግብር ጐንደየ ሰዓተ ነዋኃ፤ ወጊዜ ፮ሰዓት አዘዘ ዝንቱ ንጉሥ ይውግሩ መዳፍዓ። ወበውግረተ ፩መድፍዕ አውደቅዎ ለጸዋሬ ዓላማ ወለአሐቲ ብእሲት ዘነበረት ተኃቢኣ ታሕተ ዕፅ።

ውእተ ጊዜ ተህውከ ካሌፍ ወኮሉ ሠራዊቱ፤ ወተፈትሐ ኮሉ ሠራዊተ ፀብኡ። እስመ መሰሎሙ ዘወድቀ ላዕሌሆሙ መብረቅ እምሰማይ። ወዶብዓ ሥልጣንኒ ወረደ ጎቤሆሙ እመንገለ መልዕልት፤ እስመ ነበረ ተሪፎ በላዕላይ ሰፍራ ለዓቂበ በር። ወተራድኡ በበይናቲሆሙ ዘየማን ወዘጸጋም ዘመልዕልት ወዘመትሕት።

ካሌፍሰ ኃጥአ ልቡናሁ፤ እስመ አምሠጠ ልቡ እምብዝኃ ፍርሀት። ወሶበ ተመንደበ እምኮለሄ ዓረገ ጎበ ዐቢይ ጸድፍ ምስለ ጎዳጣን ወዓልያኒሁ። ጎበ ዝንቱሰ ጸድፍ አልቦ ዘዓረገ እምቅድመዝ አላ ዳእሙ አዕረገዶ ፍርሀቱ ለዝንቱ ተሐባሊ።

ወሠራዊተ ፀብኡሰ እለ ተፈልጡ እምኔሁ እምግርማ መድፍዕ ወእምፀብአ ኃያላኒሁ ለዝንቱ ንጉሥ እለ ይመስሉ ኃያላነ ዳዊት ዘአስተማሰለ መጽሐፍ ሩጸቶሙ በሩጸተ ንስር ወጽንያሙ በጽንዓ አንበሳ። ውእተ ጊዜ መንፈቆሙ ወድቁ በአሩናት፤ ወመብዝኃቶሙ ተወርዉ ውስተ ጸድፍ (እንዘ) ይጐይዩ። ወእምእንስሳሂ እለ ከመ አልህምት ወአባዕር ወአብቅልት ወአእዱግ ወኢኃደጉ ሕያወ አላ ዳእሙ አሕጕሉ በከመ ተብህለ ወቀተለ በኮሮሙ ለግብጽ እምሰብእ እስከ እንስሳ። እስመ አውገዘ አባ ንዋይ ከመ ኢይምሐኩ እደ ወአንስተ አእሩገ ወሕፃናተ ወኢያትርፉ ኮሎ ዘየሐውር በእግር።

ዕፁብ ዜና ዘኮነ በይእቲ ዕለት ለአሐቲ ብእሲት ዘተማኅረከት እንዘ ያመጽኣ ፩ብእሲ አሲሮ እዳ ምስለ እዱ። ወሶበ ርእየት በጥቃሓ ዓቢየ ጸድፈ እንዘ ተሐውርአ አዶናይ ርድአኒ ብሂላ ተወርወት ውስተ ጸድፍ ወተማልአቶ ምስሌሃ እንበለ ፈቃዱ ለውእቱ ብእሲ ዘአሰረ እዳ ምስለ እዱ።

❖

በዚያ የክረምት ወራት በሰፈሩ በኽታ ተነሥቶ በበኽታው ብዙ ሰዎች ሞቱ። ከዚህ ቀደም ብሎ የአፄ ውሳኔ ክረምቱን አሳልፎ ጋላን ከአንካት አንሥቶ ግድም፥ ይፋት፥ ፈጠጋር፥ ደዋሮ ድረስ ለመውጋት ለመሄድ ነበረ።

ይህንን ውሳኔ ከዚህም ከዚያም ሹሞች ጋራ ወደየሀገራቸው ሲሸኛቸው አጽድቆና አጽንቶ ነበረ። ግን እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ

“ምክሬ ከምክራችሁ ጋራ አይደለም፥ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ ጋራ አይደለም”[15] ያለ ይመስለናል።

ይህንን ያልነው፥ የዓለምን ሁኔታ በምታስተዳድር ፈቃዱ ምክንያት ከክረምት በኋላ የአዜጌ ዘመቻ ወደፈላሻ ስለ ሆነ ነው፤ ጋላን መውጋት ቀረ። ጋላን የመውጋት ውሳኔ የቀረበትን ምክንያት እዚህ ላይ እንገልጻለን፤

“አዜጌ በጉባኤ (ከተማ) በነበሩ ጊዜ፥ ረዳኢ ግብሬን ብዙ እህልና ማር እልካለሁ፥ ከብትና በጎችም እንዲሁ ያለዎትን ግብር መላክ አስቀረ። ከዚህ ሁሉ ምንም የለም፤ አንዳችም ነገር አልሰጠም” የሚል መልእክት (ከጉባኤ ከተማ) መጣ።

(ንጉሡ) ይሸንን ሰምቶ ልቡ እንደ እሳት ተቃጠለ፤ በዚያን ጊዜ ጋላን መውጋት ትቶ ፈላሾችን ሊወጋ ምክር ጀመረ። ወታደሩ ሁሉና የትግሬ ሹማምንት ከቀጠራቸው ቦታ ድረስ እንዲመጡ ላከባቸው። ከዚሁ አያይዞ እንዲህ ይል ነበረ፤ “ጋላን ለመውጋት ከምሄድ ይልቅ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ደመኞች ጋራ ብጣላ ይሻለኛል።” ይሸንን ውሳኔ በክረምት ወራት አጸና...።

በዚያች ዕለት ብዙ እግረኞችና ፈረሰኞች ወደ ሽዋዳ ወርደው ብዙ የእስላሞችንና ከክርስትና ወደ ይሁዲነት የተመለሱ ክርስቲያኖችን ከብት ማረኩ። ምክንያቱም ወደ ሐዜጌ “እነሆ ከከብቶቻችን፥ ከሴቶቻችን፥ ከልጆቻችን ጋራ ሆነን ወደጌታችን መጥተናል” ብለው ልከው ነበረ። ከዚያ አስቀድሞ ግን ኑሯቸው በረዳኢ የግዛት ምድር ውስጥ ነበር።

እነዚህ የተማረኩት ከተማረኩ በኋላ ገንዘባቸውን በመመለስ የጌታችን (የንጉሡ) ቸርነት ትታወቅ ዘንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ፥ የነሱ መምጣት ከነዚህ ኃይለኞች ዘመቻ ጋራ ገጠመ። በዚያን ዕለት የእህል ዓይነት ብዙ ተዘርፎ ነበረ፤ ግን ከስንዴና እንደ(ስንዴ) ጥሩ ከሆነ እህል በቀር ዳጉሳና እሱን የመሰለውን አልወሰዱም፤ ለተማረኩባቸው የተወሰደባቸውን ገንዘባቸውን ሁሉ በግዘት መለሰላቸው። “ክርስቶሳዊያን ሠራዊቴ የእስላሞችንና የፈላሾችን ገንዘብ ቢወስዱ ምን ችገረኝ” ብሎ አላመካኘም። አቤት ይቺ ደግነት፤ ፀሐይን በደጎችና በክፉዎች ላይ የሚያወጣ፥ ዝናምንም በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ የሚያዘንም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ደግነት የምትመስል!

በማግስቱ ዓርብ ዕለት እዚያ ዋልን። መንገድ እንዲጠርግና ጉድጓዶቹን ሁሉ እንዲሞላ አዛዥ ሐሊቦን በፊቱ ላከው። ምክንያቱም ፈላሾች በዚያን ጊዜ መንገዱን በቅሎና ፈረስ እንዳይሄድበት አፈራርሰው አውድመውት ነበረ። አዛዥ ሐሊቦ በዚያች ቀን የተበላሸውንና ወጣ ገባውን አሣምሮ የቀና ጥርጊያ አደረገው።

15. ኢሳይያስ 55፡ 8።

በማግስቱ፥ ቅዳሜ ዕለት መሆኑ ነው፥ (ንጉሡ) ከዚያ ተነሥቶ ጉዞውን ወደ ለርዊ አደረገና ጻሮጻ ላይ ሰፈረ። በዚያች ዕለት ከሰው እስከ እንሰሳ በመንገድ የተደናቀፈ ያዳለጠውም አልነበረም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቀኝ (እጅ) የዚህን ንጉሥ መንገድ ታካሂደው ነበረ። እሑድ ዕለት ቅዳሜ ዕለት በሰፈርንበት ዋልን።

የረዳኢ ወንድም ካሌፍ ደግሞ ቤቶቹን በውስጣቸው ካለው (ንብረት) ጋራ ሁሉ በእሳት ማቃጠል ጀመረ። በማሳ ላይ ያለውንም እህል (አዝመራውን) አቃጠለው፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ነጭ ሆኖ ለስብሰባ ደርሶ ነበረ[16]። ነዶውንም ከተከመረበት ያላንዳች ምሕረት አቃጠለው። ይኸን የሚያደርገው (ሠራዊቱ) የሚበላ ሲያጡ የሚመለሱ መስሎት ነው፤ እግዚአብሔር እንደፈረደበት አላወቀም።

እኛ ግን ሀገሪቷን ሁለንተዋ በዘር ልምላሜና በሰብል ፍሬ አጊጣ ስናያት በፍቅሯ ተነደፍን[17]። ጴጥሮስ በደብረ ታቦር ለጌታችን፥ "እዚህ ብንኖር ይሻለናል"[18] እንዳለው፥ በውስጧ መኖርም አማረን።

ረዳኢ ሐርቦ (ካሁን በፊት) የመጣበት ጊዜ የተናገረውን የትንቢት ቃል እዚህ ላይ (ሳናነሣው) አንተወው። እሱ ደጀን ሆኖ በጦርነት የሰለጠኑትን ሠራዊቱን የአፄዬ ሰዎች ወደዘረፉት ወደሸዋዳ ልኮ ነበረ። ያችን በማህል ያለችዋን ወንዝ ግን ሊሻገራት የደፈረ አልነበረም።

በዚያን ጊዜ (ከወንዝ ማዶ ሆኖ) እንዲህ ሲል የስድብ ቃል ወደ ሐርቦ ላከ፤ "ኃይለኛው አዝማች ሐርቦ ሆይ፥ ማርና ወተት የምታፈስ ምድረ ርስት[19] ከፊትህ እነሆትልህ፤ እንድትዋረሳትና አትክልቶቿን እንድትከፋፈል ፈጥነህ ና፥ አትዘግይ።"

ሐርቦ ግን ዝም አለ፤ አንዳችም ነገር አልመለሰም። ግን ለእውነት ፈራጁ ነግሯል። ሠራዊቱ ሲዋጉም በዚያች ዕለት ፈላሾች ጠነከሩባቸው፤ የሐርቦን ሠራዊት አባረሯቸው። እስከ ዓቀበቱ ማህል ድረስ አሳደዷቸው። ሆኖም ከታላላቆቹ ሰዎች ውስጥ ካንዱ በቀር ከማህላቸው ሰው አልተበላሸባቸውም። ይህ ሁሉ ሆኖ ሐርቦ ወደሀገሩ በደኅናና በሰላም ተመለሰ።

ከብዙ ዓመት በኋላ የዚች ስድብ ፍዳ ሆኖ (እነሆ) ኀይለኛው ንጉሥ መለክ ሰገድ (ሠርፀ ድንግል) ወደ ስሜን መጣ። ይኸ አመጣጡ ለረዳኢ "ወዳንተ እንዲመጣ ለሐርቦ ላክህበት፤ በሱ ፈንታ አትክልትህን ልካፈል እኔ መጣሁ። ያልፈለግኸኝን አገኘኸኝ፤ ያልጠራኸኝ መለስኩልህ"[20] የሚለው ይመስላል። የጌታችን ወደፈላሻ

16. ምንጭ ዮሐንስ 4፡ 35፡ "ዓይናችሁን አንሡ፤ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ።"
17. ምንጭ መኃልይ 2፡ 5 "በፍቅሩ ተነድፌያለሁ።"
18. ማቴዎስ 17፡ 4።
19. "ማርና ወተት የምታፈስ ምድረ ርስት" እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጣት አገር መጠሪያ ነው፤ ለምሳሌ ዘፀአት 13፡ 5ን ተመልከት።
20. ምንጭ መኃልይ 5፡ 6፡ "ፈለግሁት፥ አላገኘሁትም፤ ጠራሁት አልመለሰልኝም።"

መምጣት ይኸንን የሚል ይመስላል፤ ምክንያቱም በግርማው አገሪቷ በመላ ተሸበረች -- "ምድርን አድለቀለቅሃት፤ አሸበርካትም"[21] እንደተባለ።

ሰኞ ዕለት ከጻሮጻ ተነሥተን ማክሰኞ ዕለት በካሌፍ አምባ አጠገብ ሰፈርን። ጥቂት ሰዎች ሳያዟቸው ወደ ቄላ ወረዱ። በዚያን ጊዜ (ካሌፍ) ብዙ ጋሻና ጦር የያዙ ወታደሮች አሳያቸው። ግን ወደነሱ አልመጣም፤ እነሱም ወደሱ አልሄዱም፤ እርስ በእርሳቸው ተፈራርተዋል። እህል ዘርፈው (ብቻ) ሰፈራቸውን ፊት ለፊቱ አደረጉ። በዚያች ዕለት ከፈላሾቹ ወደእነሱ ቀርቦ ሊጐዳቸው የደፈረ አልነበረም። ምክንያቱም የዚህ ንጉሥ የግርማው ሞገስ ትከለክላቸው፥ መልአኩም በዙሪያቸው ሰፍሮ ነበረ[22]። ይህ ሁሉ የሆነው በጥቅምት 29 ቀን (1572 ዓ. ም.) ነው። የአፄ ስፍራም ደጋ ምድር ነበረ፤ ብርዱ ጠንካራ ነበረ።

አፄ በማግሥቱ ረቡዕ ዕለት ካሌፍን ለመውጋት ከላይ ወደ ታች ወረዱ። በሰፈሩ ዶባ ሥልጣን እና ሳዊሮስን[23] ከብዙ ፈረሰኛና ጠመንጃ (ያዥ)፥ ከብዙ ጋሻ (ተሸካሚ) ጋራ አስቀሯቸው። አፄውም ወርደው የትናንትናዎቹ ሰዎች ከሰፈሩበት ሰፈሩ። ይህ የሆነው በኅዳር (በጥቅምት?) 30 ነው።

የዚያች ዕለት ጉዞ በሶስት ክፍል ነበረ። በሶስተኛው መንገድ በሚሄዱት ላይ ፈላሾች ተነሡባቸው፤ ምክንያቱም ይህ አሸናፊ ንጉሥ እዚያ እንዳልነበረ፥ በሌላ መንገድ እንደሄደ፥ ዐውቀው ነበረ። በዚያች ጊዜ የአዛዥ ፋኑኤል ልጅ ፊቅጦር አየለባቸው። ከነሱም ብዙ (ሰው) ገደለባቸው። ለአፄ ሃያ የሚያክል ሽብሸቦ[24] አስረከበ። ይህ የጌታችን (በፈላሾች ላይ) የመጀመሪያ ድል ነው፤ የፈላሾችም የመሸነፍ መጀመሪያቸው ነው።

---

21. መዝሙር 59፡ 4።
22. ምንጭ መዝሙር 33፡ 7፡ "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል።"
23. ዶባ ሥልጣን የአፋር (የጥልጣል) ገዢ የሹመት ስም ነው። ግዕዙ የሹመቱን ስምና ሳዊሮስን በዋዌ (በመስተጻምር) ስላያያዛቸው ሁለት ሰዎች አስመሰላቸው እንጂ ሹመ ሳዊሮስ ሳይሆን አይቀርም።
24. ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ቃል "ቸብቸቦ" ነው። ተዋጊዎች የሰው ጭንቅላት "ግድያ ይጥላሉ"፤ ምናልባትም ይፎክሩበት ይሆናል። ከጥንት ጀምሮ ባህል ሆኖ ሁለቱም ተጋጪ ወገኖች ጠላት ሲገድሉ ጭንቅላት እየቁረጡ ያሳያሉ፤ ለምሳሌ ማቴዎስ 14፡ 8-10 ላይ ያለውን ስለመጥምቁ ዮሐንስ ራስ ተቁርጦ በሳህን መቅረብ የተጻፈውን ተመልከት። በኛ ዘንድ እስከ ቅርብ ጊዜ ቀጥሎ እንደነበረ የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ያሳያል። ጋሪድ የሚባል ያጎታቸው ልጅ ጦር አዘጋጅቶ ሥልጣናቸውን እንደተቀናቀነ ይታወሳል። ሲያሸንፉት አንድ ሺ አምስት መቶ ያህል ወታደር ማርከውበት ነበር፤ "(አፄ ቴዎድሮስ) ይኸን ሁሉ ሰው ሰብስቦ ደባርቅ ከሚባል ገበያ ላይ ወስዶ አንገት አንገቱን ቆርጦ እንደ ካብ ካበው"፤ *የጎጃም ታሪክ* ፥ EMML 5403, f.108b.

በዚች የሐሙስ ዕለት አጥቢያ ሌሊት ለዓይኖቹ መኝታ፥ ለሽፋሽፍቶቹም እንቅልፍ ሳይሰጥ[25] ካሌፍን እንዴት እንደሚወጋውና ከተሸሸገበት ተራራ ጫፍ እንዴት እንደሚያወርደው ሲያስብና ሲመክር አደረ። በዚች የሐሙስ ዕለት በግሥጋሜ (ሲሄድ) አነጋና ካሌፍን ለመውጋት ሄደ።

ከዚህ በኋላ ተዋጊዎቹን በሶስት መንገድ ላካቸው። አዛዥ ሐሊቦ ከባሕር አሥላ ጋራ በታችኛዋ መንገድ ሄደ። በፊቱ ጐጥም ነጋሽ ደጎረሳት ከውራን ጋራ ሆነ። በነሱ ጐን ከጦር ውርወራ፥ ከድንጋይ፥ ከነፍጥ፥ ከወስፈንጥር ምት ፊታቸውን የማይመልሱ የዚህ ንጉሥ ጎይለኞች (እነ) ቁጮርባን ሆኑ። እነዚህን ሁሉ በየነገዳቸውና በየሕዝባቸው ብዙ ጠመንጃ ጨምሮ ላካቸው። እሱ ደግሞ ካሌፍ ከሠራዊቱ ጋራ በሰፈረበት ፊት ለፊት ቆመ። ካሉበት የርቀቱ መጠን ሰባት ምዕራፍ ወይም በለጥ ይላል። በዚህ ላይ ደግሞ፥ ሊሻገሩት የማይቻል ትልቅ ገደል በማህላቸው አለ።

በዚያች ዕለት በዚህ ንጉሥ ሠራዊትና በፈላሾች ማህል ትልቅ ጦርነት ተካሄደ። የካሌፍ ሰዎች ጦርነት በድንጋይ ነበረ። በላያቸው ላይ እየናዱባቸው ከታች ወደላይ መውጣትን ይከለክሏቸው ነበረ። በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜ ቆየ፤ በስድስት ሰዓት ላይ ንጉሡ መድፎቹን እንዲተኩሱ አዘዘ። በአንድ መድፍ ተኮስ (ሰንደቅ) ዓላማ ተሸካሚውን ጣለው -- ከዛፍ ስር ተደብቃ የነበረችውን ሴት ጨምሮ። በዚያን ጊዜ ካሌፍና ሠራዊቱ ሁሉ ተሸበሩ። የጦር ሠራዊቱ በሞላ ተፈታ፤ ምክንያቱም ከሰማይ መብረቅ የወደቀባቸው መሰላቸው። ዶብዓ ሥልጣንም[23] ከላይ በኩል ወደነሱ ወረደ፤ ምክንያቱም በር ለመጠበቅ እላይኛው ሰፈር ቀርቶ ነበረ። የቀኙም የግራውም፥ የላዩም የታቹም እርስ በእርሳቸው ተረዳዱ።

ካሌፍ ደግሞ ልቡናውን አጣ፤ ምክንያቱም ልቡ ከፍርሃት ብዛት አምልጦት ነበረ። በሁሉም አቅጣጫ ሲጨነቅ ጊዜ ከጥቂት ሎሌዎቹ ጋራ ሆኖ ከትልቅ ገደል (አፋፍ) ወጣ። እዚህ ገደል ላይ ካሁን በፊት ማንም አልወጣም። ይሽንን ጎፍረተ ቢስ ግን ፍርሃት አወጣው።

በመድፉ ግርማና መጽሐፍ ፍጥነታቸውን በንስር ፍጥነት፥ ጥንካሬያቸውን በአንበሳ ጥንካሬ ያስመሰላቸውን የዳዊትን ኃይለኞች[26] ከሚመስሉት የዚህ ንጉሥ ኃይለኞች ጦር ፍርሃት የተለዩት የጦር ሠራዊቱ ደግሞ በዚያን ጊዜ ግማሻቸው በጦር ወደቁ፤ አብዛኞቹ ሲሸሹ ገደል ገቡ። ከእንስሳም እንደነ ላም፥ በሬ፥ በቅሎ፥ አህያ ያሉትን በሕይወት አልተዋቸውም፤ "የግብጾችን በኮሮጆቻቸውን ከሰው እስከ እንሰሳ ገደለ"[27] እንደተባለው አጠፏቸው እንጂ። ምክንያቱም

25. ምንጭ መዝሙር 131፡ 4፡ "ለዓይኖቼ መኝታ፥ ለሽፋሽፍቶቼም ዕንቅልፍ፥ ለጉንጮቼም ዕረፍትን አልሰጥም።"
26. ሳሙኤል ካልዕ 1፡ 23።
27. ዘፀአት 12፡ 29።

እንዳይምሩ፥ ወንድ፥ ሴት ሽማግሌ፥ ሕፃን፥ በእግሩ የሚሄደውን ሁሉ እንዳያስተርፉ አባ ንዋይ አውግዘው ነበረ።

በዚያች ዕለት የሚያስገርም ታሪክ ሆነ፤ አንዲት የተማረከች ሴት አንድ ሰው እጇን ከእጁ ጋራ አስሮ ሲያመጣት በመንገድ ሳለች አጠገቧ ትልቅ ገደል ስታይ፥ "አዶናይ እርዳኝ" ብላ ገደል ተወረወረች። እጇን ከእጁ ጋራ ያሰረውን ሰውም ያለፈቃዱ ይዛው ሄደች።

## (ለ) የኦሮሞዎች "ሰብአ ትካትነት"

በኦሮሞዎችና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ከመጀመሪያው ላይ የነበረው ግጭት ኦሮሞዎች እንደ ፈላሻዎቹ ግብር ስለከለከሉ አይደለም፤ ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው። በኋላ የመጡ የዛሬ ታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚተረጉሙትም ኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ መንግሥት በጎይል ሊከለክላቸው ስለሞከረም አይደለም። እስከ ቅርብ ታሪኳ ድረስ ኢትዮጵያ ማንም ሰው፥ ጎሳ፥ ወይም ነገድ፥ ማንም ሳይከለክለው ገብቶ ከባዶ ቦታ ሰፍሮ አገሩ ሊያደርጋት የሚችል አገር ነበረች። በአፄ ሱስንዮስ ዘመን የስናር ንጉሥ ከነሠራዊቱ ቢመጣ ሱስንዮስ ጭልጋን ጠቅልሎ እንደሰጠው አንብበናል፤ እዚህም ገጽ 131-135 ላይ ተመልከት። በሰላማዊ መጤዎችና በመንግሥት መካከል ግጭት ለመፈጠሩ የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ የለንም። የኦሮሞዎች ጊዜ ግን ጦርነት ነበረ፤ ያውም ቢሆን አባ ባሕርይ "ጋላ ዘድኅር" ("የኋለኞቹ ጋሎች") ከሚሏቸው ከዳዊ ጋራ ነበረ። ለምን?

የግጭቱ መንሥኤ የዚያን ጊዜ የኦሮሞዎች የኑሮ ዘይ ነው። ኦሮሞዎች ወደማህል አገር የገቡ ጊዜ አገሬው አርሶና አሳርሶ፥ ነግዶና አስነግዶ፥ ቀድሶና አስቀድሶ የሚኖር "ነባር" ወይም "ሰፋሪ" ሕዝብ ነበረ። ዘላኑም ቢሆን በዚያው በሚኖርበት (በሰፈረበት) አገር አካባቢ የግል ከብቶቹን እየነዳ "ይዘልን" ነበረ እንጂ፥ እንደ ሕዝብ፥ እንደ ነገድ፥ እንደ ጎሳ በአንድነት ካካባቢው እየወጣ አይመላለስም።

ኦሮሞዎች፥ በተለየም "ዳዌ" የሚባል ስም የወጣለት ነገድ፥ በ16ተኛው ምእት ዓመት ወደ ማህል ኢትዮጵያ ሲመጡ የኑሮ ዘይቸው ከነዚህ ኢትዮጵያውያን፥ ከነባሩም ሆነ ከዘላኑ፥ ኑሮ ፈጽሞ የተለየ ነበረ። የጎሳቸው አወቃቀር እንደሌሎች ኩሳዊ ነገዶች[28] ጎብረተ ሰባዊ፥ ወይም

28. "ለጋዳ ሥርዓት መስፋፋትም ቢሆን ጋሎችን ተጠያቂዎች ማድረግ አይቻልም። እንደእውነቱ፥ ይህ ልዩ የሆነ የጎብረተ ሰብ አወቃቀር በጠቅላላው ከምሥራቅ ኩሳዊ የቋንቋ ቤተ ሰብ ሕዝብ ጋራ የተያያዘ ነው፤ እርግጥ የጋሎቹን፥ የሲዳማ-ሐዲያዎቹን ወይም የኮንሶዎቹን ሥርዓቶች፥ የቅርብ ጊዜ የጋራ ግኝት ያላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ፥ የተለየ አድርጎ ማየት ይኖራል" ("Auch für die Verbreitung des

በዛሬው ቋንቋ አነጋገር፥ **በእኩልነት የተደራጀ ወታደራዊ ኮሚኒዝም ሆኖ ኤኮኖሚያቸው ዝለና** ነበረ። የሚዘልኑትም በባዶው ሀገር ላይ ሳይሆን በነባሩ ሕዝብ ኑሮ ላይ ነበረ። በሰብሉ ላይ ከብታቸውን ያሰማሩበታል፤ ከብቱን ይነጥቁታል፤ ንብረቱን ይዘርፉታል። ሰዉንም እየፈነገሉ አገልጋያቸው ያደርጉታል። የጸሎት ቦታዎች (አብያተ ክርስቲያንና መስጊዶች) ለነሱ ምንም ትርጉም የሌላቸው የሚፈርሱ የጠላት ንብረቶች ነበሩ። ኑሯቸው በከብት ርቢ ቢሆንም የዱር አውሬ እያደኑና የዱር ፍሬ እየሰበሰቡ የሚኖሩ **የሰብአ ትካትን** (ማለት፥ የጥንት ሰዎችን) ኑሮ ይመስላል፤ ብቻ የአደኑና የፍሬ ስብሰባው ልዩነት የሰብአ ትካቱ በዱር፥ የኦሮሞዎቹ በመንደር ሆነ እንጂ።

አባ ባሕርይ ***ሰላመ ቅዱሳን*** ደርሰው ሲጨርሱ ዘመኗን "**ይቅርታ ያጣች**" (የፈረደባት) እንዳሏት እናስታውሳለን (ገጽ 51)። መዝሙር 73ን የደረሱት ለዚያች "**ይቅርታ ያጣች**" ላሏት ዘመን ነው። መዝሙሩ ስሜታቸውን ስለሚገልጽና የዘመኑን ታሪክ ስለሚያንጸባርቅ እንዳለ እዚህ ቦታ ቢጠቀስ ተስማሚ ነው (ከቅጠል 70ለ-እስከ 71ለ)፤

*ለምንት ገደፍከነ እግዚኦ ለዝሉፉ፥*
*ዘታስተጋብእ ዝርዋነ ወተንሥሥ እለ ተገድፉ (ኪዳን)፥*
*ተዘከር ሕዝበከ ዘተግሣጸከ ተወክፉ፥*
*ወበመቅሰፍትከ ዘተቀስፉ፥*
*ወአልቦ አመ እምሁከት አዕረፉ።*
*ወበእንተዝ አሕዛብ ላዕሌነ ይጸርፉ።*
*መጠነሰ አኀሠመ ፀራዊ ዲበ ቅዱሳኒከ፥*
*ኮሉ ተአምር ወኢትፈቅድ ከመ ይንግሩከ።*
*እስመ ይትዔየር ዲበ እለ ይሰምዩከ አምላከ፥*
*ፈድፋደሰ በቤተ መቅደስከ።*
*ናሁ ከመ ዕፀ ገዳም አውዳየ መዓፅወ ሥጋታ።*
*ወከመ ልገተ አቅማሕ ነሰተ አረፍታ።*
*አስተሐቀረ ክብራ ወአርኰሳ።*
*ወረሰያ ለቤተ ቅዳሴ ምርአየ እንስሳ።*
*እፎ አዕበይከ ኪያሃ አመ መዋዕለ ንእሳ፥*
*ይእዜሰ ለምንት ተኃሥሮ ለክብራ፥ ወተአትቶ ለሞገሳ።*
*እመኒ ወሀከተከ በአበሳ፥*
*ቦኑ ሐቃላዊ ይኄይሳ።*
*ኦለልቡ ዘፈንሐሰ አንፈሳ (ዘጎልቍ)፥*

gada-Systems kann man die Galla nicht verantvortlich machen. Diese eigentümliche Sozialverfassung ist zwar ausschließchlich mit den Völkern der ostkuschitischen Sprachfamilie verbunden, doch sind die Systeme der Galla, Sidamo-Hadya oder Konso zu verschieden, als daß sie eine jüngere gemeinsame Herkunft haben könnten."), Eike Haberland, *Galla Süd-Äthiopiens*, p. 3.

*እስከ ማእዜኑ በመዓት ታረምማ ወትትዓገሣ::*
*መኑ እምይእዜ ለሕግከ የኀሥሣ፤*
*ወበምንትኑመ ለስምከ ንቄድሳ፤*
*እስመ መጻሕፍት ውዕያ ወተደምሰሳ (ዕዝራ)::*
*ተሠሃል ላዕሌነ አምሳለ እም ላዕለ ውሉደ ክርሣ::*
*መኑ እግዚእ ዘኢይቀስፍ ሶበ ተምዓ፤*
*ወአልቦ መምህር ዘኢይጌሥጽ ረድኡ::*
*ወኢረከብነ ዘኢይምሕር እምድኅረ ቍጥዓ::*
*እስመ በትረ ወመቅሰፍት ቅድመ ተሠርዓ፤*
*ለዘ ተህሰየ ቅኔሁ ወለዘ ትእዛዞ ረስዓ::*
*ወይምሕረዎ ለእመ ነስሐ ወገብአ::*
*ወአምሳለዝ በመጻሕፍት ተየድዓ፤*
*ክመ እምድኅረ ዓመታት ሰብዓ፥*
*ተሠሃልካ ለጽዮን ወመሐርከ ሰብኣ (ኤርምያስ)፤*
*ወዝርወታተ ደቂቀ ሕዝባ ተጋብአ::*
*አክርስቶስ ርእሰ አሕይዎ፥*
*መሐር ሕዝበከ ወለፀርሞሙ ሠርዎ፤*
*ወአስተጋብኦሙ እምተዘርዎ፤*
*እስመ ለአባሲ ይምሕርዎ፥ ወለሰአሊ ይሁብዎ::*
*ወኢ ትበለነ ከመ በዜና ነቢያት ትብል (ሕዝቅኤል)፥*
*እመ ቆሙ ቅድሜየ በስኢል፥*
*ጻድቃነ ዘመን ብሉይ ኖኅ ወኢዮብ ወዳንኤል፥*
*ዲበ ዝንቱ ሕዝብ ኢይሠሃል::*
*ወእመኒ መድሎተ ጌጋይነ ይኄይል፥*
*እምጽድቀ እሉ ዓበይተ ሕዝብ ክቡድ፥*
*ተዘከር ንጽሐ እምከ እምኮሉ ዘይፈደፍድ፤*
*ወሐሊ ቅንዋተ አእጋር ወእድ፤*
*ክመ ትምሐረነ ወትሠሃል ኪያነ፥ አወልደ አብ ዋሕድ::*

❖

**ጌታ ሆይ፥ ለምን ለሁል ጊዜ ተውከን፤**
**የተበተኑ የምትሰበስብ፥ የወደቁ የምትፈልግ (ሆይ)[29] (ኪዳን)፥**
**ተግሣጽሕን የተቀበሉ ሕዝብህን አስታውስ፤**
**በቅጣትህም የተቀጡትን::**
**ከብጥብጥ ያረፉበት ጊዜ የለም::**
**በዚህም ምክንያት አሕዛብ ይሳደባሉ::**
**ጠላት በቅዱሶችህ ላይ የቱን ያህል ክፋት እንደፈጸመ፥**

29. "ያስተጋብኦሙ ለዝርዋን" ("የተበተኑትን ይሰበስባቸው ዘንድ" -- በፈቃዱ ሞተ፥ ተቀበረ)፤ *መጽሐፈ ቅዳሴ በግዕዝና በአማርኛ፥* አዲስ አበባ ፲፱፻፷፩ ዓመተ ምሕረት፥ ገ. 95፡ 40::

ሁሉን ታውቃለህ፤ እንዲነግሩህ አትፈልግም።
አምላክ በሚሉህ ላይ ያላግጣልና፤
በይበልጥም በቤተ መቅደስህ ላይ።
እነሆ የበሯን መዝጊያ እንደዱር እንጨት አቃጠለው።
ግድግዳዋንም እንደ ሰብል ጎጆ[30] አፈረሰው።
ክብሯን አዋረደ፥ አረከሳትም።
የቅዳሴውን ቤት የከብት መዋያ (በረት) አደረገው።
በልጅነት ዘመኗ እንዴት ከፍ ከፍ አደረግሃት፤
አሁንስ ለምን ክብሯን ታዋርደዋለህ፥ ሞገሷንም
ትገፈዋለህ።
በጥፋት ብታበሳጭህስ፥
በውነት ዘላን ይሻላታልን።[31]
የፊንሐስን ልብ ያሳረፍክ ሆይ (*ዘኁልቊ*)[32]፥
እስከመቸ በቁጣህ ዝም ትላታለህ፤ ትታገሥባታለህም።
ካሁን በኋላ ሕግህን ማን ይፈልጋታል፤
ስምህንስ በምን እንቀድሰው፤
ምክንያቱም መጻሕፍቱ ተቃጠሉ፤ ተደመሰሱም (*ሰዝራ*)[33]።
ይቅርታ አድርግልን (እንጂ)፥ እንደ እናት በሆዷ ልጆች
ላይ።
ሲቆጣ የማይቀጣ ጌታ ማነው፤
ደቀ መዝሙር የማይገሥጽ መምህርም የለም።
ከቁጣ በኋላ የማይምርም አላገኘንም።
ዱላና ቅጣት ከጥንት ተሠርተዋል፥
በግዴታው ላይ ለሚለግምና ትእዛዘን ቸል ለሚል።
ሲጸጸትና ሲመለስ ደግሞ ይምሩታል።
የዚህ ምሳሌ በመጻሕፍት ታውቋል፤
ከሰባ ዓመት በኋላ፥
ጽዮንን ይቅር እንዳልካትና ሰዎቿን እንደማርክ (*ኤርምያስ*)[34]፥
የሕዝቧ ልጆች ብትንታኔ እንደ ተሰበሰበ።
የሕይወት መስጠት ራስ ክርስቶስ ሆይ፥

30. ሚክያስ 3፡ 12 ("ወትከውን ኢየሩሳሌም ከመ ልገተ ዓቃቤ ቀምሕ" ያለውን ሲጠቅስ ነው።)
31. "ዝኩ ... ሐቃላዊ" ("ይህ ዘላን ...")፤ የሠርፀ ድንግል/መለክ ሰገድ ታሪክ፥ Conti Rossini, *Historia Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)* p. 53.
32. ዘኁልቊ 25፡ 10–13።
33. ሱቱኤል 2፡ 23።
34. ተረፈ ኤርምያስ። መጽሐፉ በሞላ የሚተርከው የእስራኤልን ወደ ባቢሎን በግዞት (በዔዋዌ) መወሰድንና በእግዚአብሔር እርዳታ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስን ነው። መጽሐፉን ፕሮቴስታንቶች አይቀበሉትም፤ "ተረፈ ኤርምያስ" ማለት ከመጽሐፈ ኤርምያስ የተረፈ (ተቆርጦ የቀረ) ማለት ነው።

ሕዝብህን ማር፥ ጠላታቸውንም ንቀለው፤
ከመበተንም ሰብስባቸው፤
አጥፊን ይምሩታልና፥ ለለማኝም ይሰጡታል።
በዜና ነቢያት እንዳልከው አትበለን (*ሕዝቅኤል*)[35]፥
"በልመና ከፊቴ ቢቆሙም፥
የብሉይ ዘመን ጻድቃን -- ኖኅ፥ ኢዮብ፥ ዳንኤል --
ይኸንን ሕዝብ ይቅር አልለውም።"
የኃጢአታችን ሚዛን ቢከብድና፥
ከነዚህ የከባድ ሕዝብ ታላላቆች የጽድቅ (*ሥራ ሁሉ*)
ቢበልጥ እንኳን፥
ከሁሉ የሚበልጠውን የናትህን ንጽሕና አስታውስ፤
የእግርና የእጅ(ህ)ን የምስማር ቁስሎች አስብ፤
እንድትምረንና ይቅር እንድትለን፥ የአብ አንድ ልጅ ሆይ።

አድያም ሰገድ ኢያሱ በ1676 ዓ.ም. ውጫሌን ለመውጋት ወደ ወሎ ሲዘምት የጸለየው እንዲህ ብሎ ነበር[36]፤

*ኦእግዝእትየ ወልታየ በውስተ ፀብዕ ወምስዋርየ እምህከከ ሰብእ...ይእዜኒ አንቲ ሠርሒ ፍኖትየ ወጸግውኒ ኃይለ መዊእ ላዕለ ፀርየ ወጸላእትየ እለ ይቀትሉ ምዕመናነ ወካህናተ ወየውዕዩ አብያተ ክርስቲያናት ዘውስቴቶን ይጠባሕ ሥጋሁ ቅዱስ ወውስቴቶን ይትቀደሕ ደሙ ክቡር ለወልድኪ አምላከ ሰማይ ወምድር ... ኢትረስዪኒ ሰላቀ ለጸላእትየ እለ ያመልኩ ሰብሐ ...*

❖

እመቤቴ ሆይ፥ በጦርነት ጊዜ ጋሻዬ፥ ከሰው ንዝንዝ መደበቂያየ ነሽ፤
... አሁንም መንግዴን አንቺ አሣምሪው፤ ምእመናንና ካህናትን በሚገድሉ፥ የሰማይና የምድር አምላክ የሆነው የልጅሽ ቅዱስ ሥጋ በውስጣቸው የሚሠዋባቸውን፥ ክቡር ደሙ የሚቀዳባቸውን ቤተ ክርስቲያኖችን በሚያቃጥሉ ጠራና ጠላቶቼ ላይ የድል ኀይል ስጭኝ።...ስብ ለሚያመልኩ ጠላቶቼ መሳለቂያ አታድርጊኝ።

ግራኝ ከማመፁና ኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ በዳመጣ ከመስፋፋታቸው በፊት ከፖርቱጋል መልእክተኞች መጥተው አገሪቷንና መኳንንቱን (ንጉሡንም ጳጳሱንም) ጐብኝተው እንደሄዱ እናስታውሳለን። ሀገራቸው ሲመለሱ ለንጉሣቸውና ለሕዝባቸው ያቀረቡት ዘገባ እንደሚያመለክተው፥ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ከከፍተኛ ሥልጣኔ ደርሳ ነበረ። ለምሳሌ፥ መልእክተኞቹ ስለ አንዳንዶቹ የአብያተ ክርስቲያን

35. ሕዝቅኤል 14፡ 14።
36. I. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyāsu I et Bakāffā*, part II, p. 73.

ሕንፃዎች ሲጽፉ እንዲህ ያለ ሕንጻ ፖርቱጋል ውስጥም አላየን ብለዋል[37]። ግራኝ እንዲዋጉለት በወርቅ አባብሎ ያመጣቸው ቱርኮችና ዓረቦችም የመሰከሩት ይኸንኑ ነው[38]። ሱስንዮስ ያመጣቸው የካቶሊክ ጳጳስ (ሜንዴዝ) ተሰብስበው ለተቀበሏቸው የሀገሪቱ ባለሥልጣኖችና ሊቃውንት ያደረጉት ንግግር ለአካዴሚ ጉባኤ የተሰጠ ይመስል ነበረ[39]። ጳጳሱ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት እነማን እንደሆንን ለማወቅ ጥረት አድርገው እንደነበረ ግልጽ ነው።

በየገዳማቱ የተቋቋሙት በአካዴሚ ደረጃ የሚታዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበሩ ሊቃውንት በዚያን ጊዜ የተረጐሟቸውንና የደረሷቸውን መጻሕፍት እስካሁን መርምረን አልጨረስናቸውም። የግራኝ ወታደሮችና የኦሮሞ ቄንደላዎች በማቃጠል ባይቀንሷቸው ኖሮማ ጥናታቸው ገና ብዙ ዘመን ይፈጅ ነበር። እንግዴህ የዚያን ጊዜው ግጭት ባንድ በኩል እንደዚህ በተራቀቀ ሕዝብና በሌላ በኩል በሰብአ ትካትነት ሕይወት በሚኖሩ ነገዶች መካከል ነበረ። ግጭቱ ሀገሪቷን ዶጋ አመድ ነው ያደረጋት። ዛሬ እንኳን መጻሕፍቱን አንዳንዶቹ ገዳማት መኖራቸውን እንኳን የምናውቀው ስማቸውን ከታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ስናገኘው እንጂ ከዚያ ውጪ የት እንዳሉ አናውቅም። ኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ ገብተው የያዙት ሀገር ግራኝ ባዶ ያደረገውን ነው የሚሉትን የዛሬ የኦሮሞ ታሪክ ጸሐፊዎችን የአባ ባሕርይ ጥናት አይደግፈውም። ኦሮሞዎች ሀገር ሲወሩ ነባሩን ሕዝብ እያጠፉና ኦሮሞ እያደረጉ ነበረ።

## (8) የመንግሥት አቅምና ኦሮሞዎች

ዘበኛ የሌለው ወይም ራሱን ለመጠበቅ ያልተደራጀ ሰላማዊ ሕዝብ "ጋላ መጣ" ሲሉት የሚያመጡበትን አደጋ ስለሚያውቅ "ኡኡ" ይል ጀመረ። አውላላ ሜዳ ላይ ሆና የተራበ ነምር ያየች ሚዳቋ መሰሉ። አንዳች ኮሽታ

37. Lord Stanley of Alderley, *Narrative of the Portuguese Embassy to Abyssinia During the Years 1570-1527. By Father Francisco Alvarez*, New York 1881, pp. 75 and 122. "They also were surprised at our coming into the church with our shoes on, and still more at our spitting in it," p. 30. ("ደግሞ ጫማችንን እንዳደረግን ከቤተ ክርስቲያን በመግባታችን፥ ይልቁንም ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመትፋታችን፥ ተገረሙ")።

38. M. René Basset, *Histoire de la conquête de l'Abyssinie (XVIe siècle) par Chihab Eddin Ahmed Ben 'Abd el Qâder surnommé Arab-Faqih*, Paris Vol. I (1897), pp. 213-4.

39. Philip Caraman, *The Lost Empire The Story of the Jesuits in Ethiopia 1555-1634*, Notre Dame (Indiana), 1985, p. 142: "The speech was spattered with quotations from Aristotle, Tertullian, Eusebius and Jerome, and would have been an impressive display of erudition in any European university" ("ንግግሩ ከአርስጣጣሊስ፥ ከተርቱሊያኖስ፥ ከአውሳብዮስ፥ ከኢየሮም የተወሰዱ ጥቅሶች

ሲሰማ መበርገግ ሆነ። ታሪክ ጸሐፊው እንደመዘገበው፥ አንድ ጊዜ አንዲት ሴት አሻሮ ስትቁላ ማገዶ ልታገባ እዳሪ ወጥታ ሳለ ጎረቤቷ እሳት ልትጭር ወደቤቷ ብትገባ አሻሮዋ ሲያር አገኘችው። ባለቤቷን ለማስጠንቀቅ "አሻሮው አረረ፥ አሻሮው አረረ" ብላ ብትጣራ "ባላስተናበረ ጀሮ ጋላ ወረረ፥ ጋላ ወረረ" ያለች መስሏት አማራ ተሸበረ። ጓዙን እየነዳ ሸሸ ይባላል[40]።

ካህናቱ ለደረሰው መቅሠፍት ምክንያት ሲፈልጉ የአፄ ልብነ ድንግል ጥጋብ ያመጣው ቅጣት አድርገው ይናገራሉ። ለዚህም ማስረጃ ሲሰጡ ጦር አምጣ ብሎ እግዚአብሔርን ለምኗል፤ ገዳማቱም ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልዩለት ዕጣን አስጭኖላቸዋል ብለው ጽፈዋል። ታሪኩን በመቀጠል፥ ንጉሡ በጸሎት ያገኘው መቅሠፍት ስለጸናበት ተጸጽቶ ቅድስት ማርያምን ቢማፀን የኦሮሞዎች ዘመን መቼ እንሚፈጸም በራእይ ነግራዋለች ይላሉ። ሕዝቡ የሚያደርገውን ከማጣት የተነሣ ደብተራዎቹን ይጠይቃል። ደብተራዎቹም "ጋላ የሚመጣበትንና የማይመጣበትን፥ ቢመጣም የሚሸነፍበትንና የማይሸነፍነትን ቀን" መጽሐፍ ገልጠው (ኮከብ ቈጥረው) ለማግኘት ***ሐሳበ ጋላ*** እስከ መድረስ በቅተዋል[41] ። የጻድቃኑ ገድል ጸሐፊዎችም ጻድቆቻው ከኦሮሞ ወራሪ እንዳዳኗቸው የሚያሳይ ተአምር ደርሰውላቸዋል። አንዱ በአፄ ሱስንዮስ ዘመን የኖሩ የአባ ሐራ ድንግል ገድል ነው። ታሪኩን ከሌላ ቦታ ስላላየሁት አዲስ ሊሆን ይችላልና እንጥቀሰው[42]፤

> *እንዘ ይገብር ምግባራተ ንጹሐተ ውስተ ገዳሙ ቅድስት ተሐውክት አሜሃ ኦሮሳ ሀገር በጸቢዓ አረሚ ዘይብልዎ ወርዳያ። ብዙኃን ሰብአ ቀተለ በእዴሁ፤ ወብዙኃን ሰብአ ጼወወ። ወማህረከ አልህምተ ወአባግዓ ወእንስሳተ ብዙኃተ ዘህለዋ ኦሎን አህጉራተ እንበለ ያትርፍ ፅሂ እምኦሉ ሀገር።*
>
> *ወበውእቱ ጊዜ መጽአ ጸባኢት ብዙኃን ኀበ ዝንቱ ብሔር። ወቆመ መንፈቆሙ በክሐ ወመንፈቆሙ በለፈ፤ ወኢበጽሑ ኀበ ገዳሙ ለአቡነ እንተ ሀለወት ማዕከሌሆሙ እንዘ ይሬእይዋ ወይጐዩኡ ለበጺሖታ እስመ ከልኦሙ መልአከ እግዚአብሔር፤ ወአፍርህሙ ከመ ይርኃቁ እምአድያሚሃ ወእምጽናፈሃ ለገዳሙ። ወተመይጡ እሙንቱኒ ነገደ አረሚ እምሀገረ አቡነ ኀበ ካልእ ሀገር ዘይጸብእዎ።*

❖

(አባ ሐራ ድንግል) በቅድስት ገዳሙ ውስጥ ንጹሕ ሥራዎች ሲሠራ ወርዳያ በሚሉት አረሚ ጦር ምክንያት ሀገሪቷ በሞላ ተሸበረች።

---

ተዘርተውበት ነበር፤ በየትኛውም የአውሮፓ ዩኒቨርስቲ (ቢደረግ) የሚደነቅ የሊቅነት ትርኢት ይሆን ነበር")።

40. የጎጃም ታሪክ፥ EMML 5403, f. 62b.

በእጃቸው ብዙ ሰው አጠፉ፤ ብዙ ሰውም አጋዙ። ከብትም፥ በጎችም በየአገሩ ያሉትን እንሰሶች አንዳችም አገር ሳያስተርፍ ዘረፈ።

በዚያን ጊዜ ብዙ ጦረኞች ወደዚህ ሀገር መጡና ግማሾቹ በዚህ ግማሾቹ በዚያ ቆሙ። እያዩዋትና ሊደርሱባት ቢጣደፉም በማህላቸው ወዳለችው ወደ አቡነ (ሐራ ድንግል) ገዳም አልደረሱም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መልአክ ከልክሏቸዋል፤ ከገዳሙ ሀገሮችና ከድምበሯም እንዲርቁ ፍርሃት ጣለባቸው። እነዚያ የአረሚ ነገድ የአቡነ (ሐራ ድንግልን) ሀገር (ትተው) ወደሚወጉት ወደሌላ አገር ፊታቸውን አዞሩ።

ሕዝቡ የመንግሥት እርዳታ ለመጠየቅ ቢሞክርም፥ መንግሥትና ወታደሩ ያሉት ሩቅ በመሆኑ መልክቱ ሳይደርስ የኦሮሞዎች አደጋ ይቀድማል። አባ ባሕርይ ስለ ዳሞት ጥፋት ሲጽፉ "አገሪቷን የሚያድንና የሚያስጥል የሌለ ሆኖ ሲያገኛት ሰውና ከብት አጋዘ" ያሉት ለማንኛውም አውራጃ የሚጸና አነጋገር ነበር (ክፍል ፲፬ን ተመልከት)።

በዚያ ላይ የክርስቲያኑ መንግሥት ከእስላም ኃይል ጋራ የጀመረው መጨረሻ አልባ ትግል በግራኝ መሪነት የክርስቲያኑን ሕዝብ ጉልበት ሰብሮት፥ ቅርሱንም እንዳያንሰራራ አድርጎ መትቶት ነበረ። ይህ በመቶ በሚቈጠሩ ዓመታት ከግራኝ በፊት የጀመረ ጦርነት በግራኝ ሞት አላከተመም፤ በመቶ ለሚቈጠሩ ዓመታት ቀጥሏል። በምሥራቅ ከአዳሎች ጋራ፥ በሰሜን ከቱርኮች ጋራ ይዋጉ ነበረ። ለምሳሌ አፄ ሠርፀ ድንግል ከደምቢያ እየተነሣ ዳሞት፥ ጉራጌ፥ እናርያ ብዙ ጊዜ፥ ዋቢ ሸበሊ ወንዝ አንድ ጊዜ፥ ደኸኖ (ምዕዋ) ሁለት ጊዜ ዘምቷል። ኢትዮጵያን የሚያውቃትና ያንን ሁሉ ወጣ ገባ መንገድ በእግርና በከብት ለመጓዝ ያለበትን ድካምና የሚፈጀውን ጊዜ የሚገምት ሰው አገሪቷ ለወራሪ ክፍት እንደነበረችም መገመት አያዳግተውም።

ሁለተኛም፥ የመንግሥቱ ሠራዊት የኦሮሞዎቹን ያህል የጦር ስልትና ጨክኖ እየተዋደቁ የማሸነፍ ፍላጎት ያላቸው አይመስሉም።

41. ለምሳሌ፥ EMML 5298, f. 153b. ኮከብ የሚቈጠረው በተፈራው ጎሳ ስም (ወርድያ፥ አበጢ፥ ወዘተ)፥ በሀገሩ ስም (ደምቢያ፥ ወለቃ፥ ወዘተ)፥ በወሩ (ታኅሣሥ፥ የካቲት፥ ወዘተ)፥ በወንጌላዊው (ማቴዎስ፥ ሉቃስ፥ ወዘተ) ሆኖ በ6 ይገደፋል። ውጤቱ 1 ከሆነ ወሬ ብቻ ነው፤ 2 ከሆነ አይመጣም፤ 3 ከሆነ (ይመጣል) ሰውም ከብትም ያገኛል፤ 4 ጥሩ ነው (ጋላ) አይመጣም። 5 ይመጣል፥ ሰው ያጠፋል።

42. *ገድለ አባ ሐራ ድንግል*፥ EMML 69, f. 41ab, Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. I, p. 71. ታሪኩ አባ ባሕርይ በዜናሁ ለጋላ ክፍል ፲፯ ውስጥ የነገሩን ሳይሆን አይቀርም። ጎጃም ውስጥ የዲማ ጊዮርጊስም ተአምር ሠርቷል። በቀዳማዊ ኢያሱ ዘመን (ደጃዝማች) ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያሠራ አራት ቤት ቱለማዎች ወረው ነበረ። በሰማዕቱ እርዳታ ተሸነፉ (EMML 5747, ff. 141b-142b)።

የሠራዊቱ ዓላማ ዝርፊያ ስለነበረ ባካባቢያቸው የሚዘረፍ ካገኙ የሩቁን ሕዝብ ለማዳን ሲጠሩ ያጉረመርማሉ[43]::

ሶስተኛ፥ ንጉሥ ሲሞት አዲስ ንጉሥ የበላይነቱን የሚይዘው ጥቅመኞች መኳንንት የራሳቸውን ሰው ለማንገሥ "እስራኤላውያኑን" ከወህኒ እያወረዱ ረጅም ጊዜ የሚፈጅ፥ ብዙ ሕዝብ የሚጨርስ፥ ብዙ ንብረት የሚያወድም ትግል ካካሄደ በኋላ ነው:: አንዳንዶቹማ ክርስቲያኖች ነን እያሉ የአዳሉ አሚር በላያቸው እንዲነግሥ እስከመላላክ ደርሰዋል[44]::

አራተኛ፥ የሃይማኖት ጭቅጭቅ ያስከተለው ኋላ ቀርነት በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: "ባሕታዊያን" ከንጉሡ ዘንድ በጓሮ ገብተው "ይህንን ሃይማኖት (ቅብዓት ወይም ጸጋ) ካልያዝክ የግዛት ዘመንህ ባጭር ይቀጠፋል" ይሉታል:: ይሄ እንዲደርስበት የማይፈልግ ንጉሥ ሃይማኖቱን ሲለውጥ፥ አንዱ ሃይማኖት በነገሠበት ጊዜ የተሰደዱት (ስዱዳን) ይመለሳሉ፤ በሥልጣን ላይ ያሉት ተራቸውን ስዱዳን ይሆናሉ፤ እርስ በእርስ መጨራረስ ይጀምራል:: አፄ ሱስንዮስ ሃይማኖቱን የለወጠውና በዚህም ምክንያት ረጅም ጊዜ የፈጀና በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ያለቀበት የእርስ በርስ ጦርነት የተካሄደው አሮሞዎች ለዝርፊያ በጐለበቱበት ዘመን ነው::

ሌሎቹን የድክመት ምክንያቶች አባ ባሕርይ በቅርብ ሆነው ታዝበው በዜናሁ ለጋላ ውስጥ አንድ ሙሉ ክፍል ሰጥተው ዘርዝረዋቸዋል (ክፍል ፲፱ን ተመልከት)::

ከትንተናቸው የምንገነዘበው ግራኝ በወታደር ብቻ ያሸነፈውን መንግሥት ሞላው የአሮሞ የሉባ ትውልድ የጦር ሠራዊት ሆኖ ሲዘምትበት ቢያሸንፈው የማይገርም መሆኑን ነው:: የአሮሞዎች ዋና ዋናዎቹ የጎይል ምንጮች ሶስት ናቸው፤

<u>አንደኛ</u>፥ በየስምንት ዓመት አዲስ ትውልድ ሲተካ አዲሱ የግዝረት ትውልድ ዘመናቸውን የሚጀምሩት በጎብረት ተገዝረው አዲስ ሹም ተክተው፥ ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ሁሉም አብሮ በመዝመት አዲስ ሀገር

43. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 108: "ከጥቂት ጊዜ በኋላ (ሱስንዮስ) በወለቃ ያለውን ጋላ ሊወጋ መሄድ ፈለገ:: የንጉሡ ሠራዊት ሲሰሙ እንዲህ ሲሉ አጉረመረሙ፥ "በአንድ በጋ ጋላን አራት ጊዜ ድል አደረግን፤ ደግሞ አሁን እንዴት ወደጋላ ዘመቻ ይወስደናል?" ንጉሡ እንደ ተሳነፉበት ሲሰማ ይህንን ጉዳይ ተወው::"

44. የአፄ ዮሐንስ/አእላፍ ሰገድን ታሪክ ገጽ 28 ላይ ብንመለከት እንዲህ የሚል እናገኝበታለን፤ በዚህ ወር ውስጥ ፋሬስና ዘማርያም የጌታችንን የንጉሠ ነገሥት አዕላፍ ሰገድን መንግሥት ለማፍለስ ፈልገው ለአደሉ ሹም እንዲህ ሲሉ ላኩበት፤ "እነሆ ፈረስና ፫ በቅሎዎች ከብዙ ንብረትና ገረዶች ከሚሆኑህ ከተማረኩ ሴቶች ጋራ ልከንልሃል:: እኛም አምነንብሃል፥ እንገዛልሃለንም፤ ብቻ በኛ ላይ እንድትነግሥ አመጣጥህን አፋጥን::"

በጎብረት በመምታት መራቸውን (ግዴታቸውን) በማውጣት ነው። አውሬ ወይም "ሲዳማ" (ነገዱ ኦሮሞ ያልሆነ ማለት ነው) ያልገደለ ቅማል ቢፈጀውም እንኳን ጠጉሩን አይላጭም፤ ሕጋቸው ነው። ራስ ላይ ከቁንጮ የበለጠ ጠጉር መታየት የሀፍረት ምልክት ነው። ካገባም ሚስቱ "የጠጉራም ሚስት" እንዳትባል፥ ክብሩንና ክብሯን ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ያደርጋል። ቀናው መፍትሔ "ሲዳማ" መግደል ነው። ካልገደለ "የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት" እድሜ ልኩን ሐዘንተኛ ሆኖ ይሞታል።

ሁለተኛ፥ ድንገት ካልተደረሰባቸው በቀር ምንም ቢሆን ከጠላት ጦር ጋራ ፊት ለፊት ውጊያ አይገጥሙም። የጦር ጎይል መምጣቱን ሲሰሙ በተገኘው አቅጣጫ ሁሉ ይሸሻሉ፤ ሲሸሹ ገደል አይመልሳቸውም። የሚወሩት ሰላማዊውን መንደር ሲሆን ምሕረት የሚባል ባህል የላቸውም። አባ ባሕርይ ክፍል ፲፬ ላይ፥ "ዳሞትን ... የሚያድንና የሚያስጥል የሌለ ሆኖ ሲያገኛት ጊዜ ሰውና ከብት አጋዘ" ያሉትን ማስታወስ ይበቃል። በሕዝቡ ሰላማዊነት ያላግጡበታል፤ "ከብት" ይሉታል። ሰዎች የክርስትና ጥምቀት ሲጠመቁ አይተው፥ እያሳደዱ ከውሐ ይደፍቁና፥ "ባሕር የሚለብሱትን ሲዳማዎች ከባሕር ገፈተርኳቸው" እያሉ ይፎክራሉ (*የዘናሁ ለጋላን* ክፍል ፲፭ ተመልከት)።

ፋሲልን የሚያህል የዘመኑን ትልቅ ባለሥልጣን እንደገደሉ አባ ባሕርይ ነግረውናል (ገጽ 79)። ቢዘመትባቸው ምን እንዳደረጉ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ታሪክ ውስጥ የተመዘገበውን እንመልከት[45]፤

> *እምድኅረ ዝንቱሰ ንትመየጥ ኀበ ዜና ፍኖቱ ለንጉሥ መለክ ሰገድ ዳግማዊ ቈስጠንጢኖስ ዘአጸወ አብያተ ጣዖታት ወአርኃወ አብያተ ክርስቲያናት። ወበራብዓዊ ዕለት እምዕለተ ክርስትና አመ ሠላሳሁ ለወርኃ መጋቢት ተንሥአ እምውእቱ ስፍራ ወአርትዓ ፍኖቶ መንገለ ወጅ ለጸቢአ ጋላ። ዝንቱሰ ሑረቶሙ ኮነ በወርኃ ዐቢይ ጾም። ወበመኃትው ፋሲካ በጽሑ ሴፍ በር።*
>
> *ጋላሰ ሶበ ሰምዑ ዜና ምጽአቱ እንዘ ሀለዉ በጉራጌ ፍርሃት ወረዓድ አኀዘሙ ወጐዩ ምስለ አንስቲሆሙ ወደቂቆሙ ወአልህምቲሆሙ ወተዘርዉ ውስተ ኦሶ ፍናዋት ከመ ተዘርዎተ ጢስ እምገጸ ነፋስ። ወእምዝ መከረ ከመ ይጽብኦ ለጋላ ዘሀሎ በበጥራሞራ ዘይትበሀል ዳዌ ዘአጎዬሎ ለፋሲሎ ምስለ ሰራዊቱ።*
>
> *ውእቱኒ ሶበ ሰምዐ ዜና ምጽአቱ ለዝንቱ ንጉሥ ግራም ዘይጌርም እምነገሥተ ምድር ጐየ ርሑቀ እስከ ተጎጥአ አሰረ ህላዌሁ። ወሶቤሃ መከሩ ዓበይተ መንግሥት እንዘ ይብሉ ምንተ ነገሥሥ እምድኅረዝ። ናሁ ተጎጥአ አሰረ ጋላ ወኢተአውቀ ኀበ ሖረ። እክልኒ ለዘረፉ ወለመሸመቻ ተጎጥአ፤ ናሁ ጸንአ ረሀብ በከተማነ። እምድኅረ ዝንቱሰ*

45. Conti Rossini, *Historia, Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp. 127-8.

*ንትመየጥ ውስተ ከተማነ ዘይእቲ አሐቲ ጉባኤ እንተ ሐዋርያት አኮኑ ተብህለ ይኄይስ መዊት በከሩናት እመዊት በረኃብ። ውእቱኒ ተሰጥዎሙ እንዘ ይብል፥ አሆ ይኩን በስመ ትቤሉ። ወዘንተ ብሂሎ ሜጠ ገጸ ወረሰየ ፍኖት እንተ ፍኖተ ጉራጌ ወሐረቱኒ ኮነ ጕጕአ።*

*ወእንዘ ሀለዉ በጉራጌ ነሥአ ቦኻ ሹም ጥምቀተ ክርስትና አመ ፫ወ፫ ለወርኃ ሚያዝያ በዕለተ ዕረፍቱ ለቅዱስ ጊዮርጊስ። ወኮነ ሎቱ ተሐባቤ ዝንቱ ንጉሥ መሲሐዊ ርቱዓ ሃይማኖት፥ ወወህበ ሥርጋዌ ዘይዔድም ለዓይን ወሰመየ ስሞ ጊዮርጊስ። ወወህበ መምህረ መንፈሳዌ ከመ ይምሐሮ ሃይማኖተ ወከመ ያጥምቅ ኦሎ ሰብአ ሀገሩ። ወበዘ ከመዝ ግብር አስተፋነዎ ወሖረ ብሔሮ በሰላም።*

*ወእምድኅረዝ አርትዓ ፍኖተ በቀዳማዊ ፍኖት ዘመጽአ ባቲ። ሰብአ ሐዌጌሰ ኮነ ይጽሕቁ በጺሐ በፍጡን ለለ አብያቲሆሙ ወለለ ሥርዓቶሙ። ወብጽሐቶሙኒ ኮነ ኀበ ጉባኤ አመ ረቡዑ ለወርኀ ሐምሌ ዘበሳኒታሁ ተዝካረ ዕረፍቶሙ ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ብርሃናተ ዓለም።*

*ዝንቱሰ ኦሎ ኮነ በ፳ወ፯ዓመተ መንግሥቱ ለንጉሥ መለክ ሰገድ። ይእቲ ክረምት ኮነት ከረምተ ሣህል መምሕረት፥ ክረምተ ትፍሥሕት ወኃሤት።*

❖

ከዚህ በኋላ አብያተ የጣያትን ዘግቶ አብያተ ክርስቲያንን ወደከፈተ ወደ ዳግማዊ ቈስጠንጢኖስ ወደ ንጉሥ መለክ ሰገድ (ሠርፀ ድንግል) ጉዞ እንመለስ። ከክርስትና ዕለት (ከስቅለት) በአራተኛይቱ ቀን፥ በመጋቢት ሰላሳ፥ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ጋላን ሊወጋ መንገዱን ወደ ወጅ አቀና። ይኸ ጉዟቸው በዐቢይ ጾም (በሑዳዴ) ነበረ። በፋሲካ ዋዜማ ሴፍ በር ደረሱ። ጋሎች ግን መምጣታቸውን ሲሰሙ በጉራጌ እንዳሉ ፍርሃትና ድንጋጤ ያዛቸው። ሴቶቻቸውን፥ ልጆቻቸውን ከብቶቻቸውን ይዘው ሸሹ፥ ጢስ ከነፋስ ፊት እንደሚተን በየአቅጣቸጫው ተነኑ።

ከዚያ በበጥራሞራ ያሉትን ፋሲሎን ከነሠራዊቱ ያበላሹትን ዳዌ የተባሉትን ጋሎች ሊወጋ ወሰነ። እነሱም የዚህን ከምድር ንጉሦች ሁሉ የሚያስገርም ባለግርማ ንጉሥ የመምጣት ወሬ ሲሰሙ ያሉበት ፈለጉ እስኪጠፋ ድረስ ርቀው ሸሹ።

በዚህ ጊዜ የመንግሥቱ ታላላቅ ሰዎች "ከዚህ በኋላ ምን እንፈልጋለን? እነሆ የጋላ ፈለጉ አልተገኘም፥ ወዴት እንደሄደ አልታወቀም። እህልም ለዘረፋም ሆነ ለሽመታ የለም። እነሆ በሰፈራችን ረኀብ ጠና። እንግዴህስ የሐዋርያት ጉባኤ ወደሆነችው ወደመዲናችን እንመለስ። በረኀብ ከመሞት በጦር መሞት ይሻላል አልተባለምን?"[46] ሲሉ ምክር አቀረቡ። እሱም "እሺ፥ እንዳላችሁ

46. ሰቆቃወ ኤርምያስ 4፡ 9።

ይሁን" ሲል መለሰላቸው። ይኸንን ተናግሮ ፊቱን አዙሮ መንገዱን ወደ ጉራጌ አደረገ። ሂደቱም በጥድፊያ ነበረ።

በጉራጌ ባሉበት ጊዜ፥ ሚያዝያ 23 ቀን፥ የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕረፍት ዕለት፥ ቦሻ ሹም ክርስትና ተነሣ። ይህ ኦርቶዶክሳዊው መሲሐዊ ንጉሥ ዋስ (የክርስትና አባት) ሆነው። ለዓይን የሚያስገርም ጌጥ ሰጠው። ስሙንም "ጊዮርጊስ" አለው። ሃይማኖት እንዲያስተምረውና የሀገሩን ሰዎች ሁሉ እንዲያጠምቅ መንፈሳዊ መምህር ሰጠው። (ጊዮርጊስን) በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ሸኝቶት ወደሀገሩ በሰላም ተመለሰ።

ከዚህ በኋላ በመጣባት በፊተኛዋ መንገድ ጉዞውን አቀና። የሐዌጌ ሰዎችም ቶሎ በየቤታቸውና በየትዳራቸው እንዲደርሱ ይጓጉ ነበረ። ከጉባኤ (ከከተማቸው) የደረሱትም፥ በማግስቱ የዓለም ብርሃናት ጴጥሮስና ጳውሎስ ዕረፍታቸው በሚሆንበት በሐምሌ አራት ቀን ነበረ።

ይህ ሁሉ የሆነው በንጉሥ መለክ ሰገድ 27ኛ ዓመተ መንግሥት ነው። ያቺ ክረምት የይቅርታና የምሕረት ክረምት፥ የደስታና የመደሰቻ ክረምት ሆነች።

<u>ሰስተኛ</u>፥ ኦሮሞዎች መዋጋት ካለባቸው፥ ጭፍራ የሚሉት የጦር ስልት አላቸው፤ ሁሉም ባንድነት ሄደው ከጠላት ላይ ይረባረቡበታል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆን አፄ ሱስንዮስን እንዴት እንደመቱት ገጽ 146-150 ላይ እናያለን፤ አሁን የኦሮሞዎች ሰብአ ትካታዊ ወረራ ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች የተጠቀሱት ዘገባዎች እንጨምር።

**ከአፄ ሠርፀ ድንግል** (1555-1589 ዓ. ም.) **ታሪክ**[47]፤

*ወእምድኅረ በዓለ ፋሲካ ተንሥአ እምደምብያ ከመ ይሖር ሸዋ፤ እስመ ጎኅኦ ውእቱ ለዓቂበ ሀገር እምነ ጋላ። እስመ ሸዋ ሀገረ መንግሥት ይእቲ። ወአሜሃ ወህበ ሐርቦ አምኃ ለአስተፋንዎቱ አፍራስ ጎፍያነ ዘኢየኃፅፁ እምዘ ወህበ ይስሐቅ፤ በውእቱኒ ጊዜ ዳግመ ነሥአ ቡራኬ። ዝኮሉ ሀብተ ሐርቦ ኮነ በምክረ ሠርፀ ክርስቶስ ማእምር ወለባዊ ላዕሌሁ ሰላም፤ ይምሐሮ ወይሠህሎ እግዚአብሔር።*

*ወእምዝ አርትዐ ፍናዶ መንገለ ግንድ በረት። ወከረመ በህየ። ወኃሊፎ ወርኃ ክረምት ሰምዓ ከመ መለክዋ ጋላ ለምድረ ወጅ። ወሶቤሃ ለአከ ውስተ ኮሎ አህጉረ መንግሥቱ ከመ ይትጋብኡ ጨዋ እምለፌ ወእምለፌ። ወለአከ ጉዣም ጎበ ዘርአ ዮሐንስ፥ ወጎበ ተክለ ጊዮርጊስ ዳሞት ጸሐፈ ላም፥ ወጎበ ዳጎረጎት ወጅ ቃጽ ከመ ይምጽኡ ኮሎሙ ምስለ ኮሎ ሠራዊተ ፀብኦሙ።*

*ወሶቤሃ ተንሥአ እምግንድ በረት ወተራከበ በወረብ ምስለ እሉ ዘዘከርናሃሙ። ወሶበ በጽሐ ወጅ ረከቦሙ ለጋላ በሚያ ወበወጅ*

47. Conti Rossini, *Historia, Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp. 44-5.

*መሊኦሙ ኮላ ምድረ ምስለ ኣልህምቲሆሙ ወደቂቆሙ ወእንስቲያሆሙ። ውንጥኡ ፍኖተ ኀበ የሐውሩ እስመ መልእ ኣልህምቲሆሙ ውስተ ኵሉ መካን። ወእምብዝኖሙ ለኣልህምት ኢይትረአይ ፅምስለ ካልኡ። ወእምዕፁብ ግብር የሐውሩ እንዘ ይነድኡ ኣልህምተ ለፈ ወለፈ ከመ ይርከቡ ፍኖተ። ጋላኒ ኢያእመረ ምጽኣቶሙ ለዘመጠነዝ ሠራዊት ዘይከድንዋ ለምድር እንዘ የሐውሩ።*

*ወሠርዐተ ፀብኦሙሰ ኮነ በሠለስቱ ጸታ። ቀዳማዊ ጸታ ረከብዎ ለጋላ ኀበ ተዐይነ። ወሶበ ርእዮሙ ግብተ ተንሥኡ ወተፃብኦሙ። ወእምዝ ተታለዉ ክልኤቱ ጸታ ኣሐዱ ድኅረ ኣሐዱ፣ ወተፃብእዎ፣ ወቀተሉ እምኔሁ ብዙኃ ዘኣልቦ ኖልቈ እስከ ኣንስቲሆሙ ወደቂቆሙ። ኣልህምተሰ ኢማህረኩ ኣላ ዴገንዎ ለዘኣምሠጠ ወጐየ እምኔሆሙ እስከ ፈጠጋር ወደዋሮ። ወኢያትረፉ እንበለ ጎዳጣን። ወእንዘ ይትመየጡ እምሰዳዳ ማህረኩ ኣልህምተ ዘኃደግዎሙ ቀዳሚ። ወኣኃዙ በበዐሠርቱ ምእት ወበበ ኃምስቱ ምእት። ኮሉ ማኅረከ ኣምጣነ ክሂሎቱ። ሰብኣ ሀገርኒ ነሥኡ ዘየኣክሎሙ ወኃደጉ ዘተሥእኖሙ። ወእምኣመ ወፅኡ ጋላ ኣልቦ ዘገብረ መኑሂ ዘከመዝ ኃይለ ዐቢየ በሠርዎተ ጋላ ኢእምእስላም ወኢእምክርስቲያን። ሰብሐት ለእግዚኣብሔር ክቡር ወልዑል ገባሬ ኃይል በእደ መሲሑ ሠርፀ ድንግል።*

❖

ከፋሲካ በዓል በኋላ (ሠርፀ ድንግል) ወደሸዋ ለመሄድ ከደምቢያ ተነሣ፣ ምክንያቱም ሀገሪቱን ከጋላ ለመጠበቅ ችኩል ነበረ። ሸዋ የመንግሥት ሀገር ነችና። በዚያን ጊዜ ሐርቦ ለመሸኘ የሚሆኑ (ባሕር ነጋሽ) ይሥሐቅ ከሰጠው የማያንሱ ምርጥ ፈረሶች ገጸ በረከት ሰጠ። በዚህም ጊዜ ድጋሚ ቡራኬ (ምስጋና) አገኘ። ይህ ሁሉ የሐርቦ ሀብት የተገኘው በዐዋቂውና በአስተዋዩ (በአፄ ሠርፀ ድንግል መምህር) በሠርፀ ክርስቶስ ምክር ነው፣ ሰላም ይረፍበት፣ እግዚአብሔር ይማረው፣ ይቅር ይበለው።

ከዚህ በኋላ መንገዱን ወደግንደበረት አቀና። ክረምቱንም እዚያ አሳለፈ። የክረምት ወራት ሲያልፍ ጋሎች ምድረ ወጅን እንደተቈጣጠሯት ሰማ። በዚህ ጊዜ ትክለኛ የጦር ሠራዊት (ጨዋ) ከዚህም ከዚያም እንዲሰበሰቡ በመንግሥቱ አውራጃዎች ሁሉ መልእክት አስተላለፈ። ሁሉም ከመላ ጦር ሠራዊታቸው ጋራ እንዲመጡ ጐጐም ወደ (ጐጐም ነጋሽ) ዘርአ ዮሐንስ፣ ወደ ዳሞት ጸሐፈ ላም ተክለ ጊዮርጊስ፣ ወደ ወጅ ቃጽ ዳጎረሳት ላከባቸው።[48]

በዚያን ጊዜ ከግንደበረት ተነሥቶ ወረብ ላይ ከነዚህ ከአነሣናቸው ጋራ ተገናኘ። ወጅ ሲደርስ ጋሎችን ከከብቶቻቸው፣

48. "ጐጐም ነጋሽ"፣ "ዳሞት ጸሐፈ/ፌ ላም"፣ "ወጅ ቃጽ" የሀገረ ገዢዎች የማዕርግ ስሞች ናቸው።

ከልጆቻቸው፥ ከሴቶቻቸው ጋራ በማያ እና በወጅ በሞላ መሬቷ ጢም ብለውባት አገኛቸው። (ሠራዊቱ) ማለፊያ መንገድ አጡ፥ ምክንያቱም ከብቶቻቸው በቦታው ሁሉ ሞልተውበት ነበረ። ከከብቶቹ ብዛት የተነሣ (ሰው) አንዱ ከሌላው አይተያይም ነበረ። መንገድ ለማግኘት ከብቶቹን ወዲያና ወዲህ ሃይ እያሉ በጭንቅ ሁኔታ ይሄዱ ነበረ። ጋሎች ደግሞ ሲጓዝ መሬቷን የሚሸፍናት ይኸን የሚያህል ሠራዊት መምጣቱን አላወቁም።

(የንጉሡ ሠራዊት) የውጊያ ሰልፋቸው በሶስት ክፍል ነበረ። ቀዳሚው ክፍል ጋሎችን እሰፈሩበት አገኛቸው። ድንገት ሲያይዋቸው ተነሥተው ተዋጓቸው። ከዚያ ሁለቱ ክፍሎች አንዱ ሌላውን እየተከተለ ወጓቸው። እስከ ሴቶቻቸውና ልጆቻቸው ድረስ ቍጥር የሌው ብዙ (ሰው) ፈጁ። ከነሱ ያመለጠውንና እስከ ፈጠጋርና እስከ ደዋሮ የሸሸውን አሳደዱ እንጂ (መጀመሪያስ) ከብት አልማረኩም። ከጥቂቶች በቀር ምንም አላስተረፉም።

ከማሳደድ ሲመለሱ በፊት የተዋቸውን ከብቶች ማረኩ። በየአንድ ሺው በየአምስት መቶው ወሰዱ፥ ሁሉም እንደችሎታው ማረከ። የሀገሩ ሰውም የሚበቃቸውን ያህል ወሰዱ፥ ያልቻሉትን (የትም) ተውት። ጋላ ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ፥ ጋሎችን በመንቀል ከእስላምም ከክርስቲያንም እንደዚህ ከፍ ያለ ኀይል የፈጸመ የለም። በመሲሑ በሠርፀ ድንግል እጅ ኀይል ለሠራ ክቡርና ልዑል ለሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።

## ከአፄ ሱስንዮስ/ሥልጣን ሰገድ (1600-1625) ታሪክ[49]፥

*ወእንዘ ሀሎ በምድረ በድ መጽአ አሊ ወልደ አጅብ ምስለ አብድልቃድር ንጉሠ ስናር በምክንያተ ህክክ ዘተንሥአ በውስተ ሀገሩ እንዘ ምስሌሁ ብዙኃን መስተፅዕናን አፍራስ ወሰብአ እግር። ውእደረ ሎቱ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ፥ ወኮኖ ንጉሠ ስናር ወዓሌ ወተአዘዘ ሎቱ ከመ ገብር። ወንጉሥኒ አሠነየ ሎቱ ኮሎ መፍቅዳተ ሥጋ፤ ወአሠርገዎ በአልባሰ ሐሪር ወበወርቅ አምባር ወኢያንጥአ ምንተኒ እምዝ ፈቀደ። ምድረኒ ወህበ ጭልጋሃ። ወዘንተ ኮሎ እምድኅረ ገብረ ወዐለ በህየ በዐለ ልደት ዘለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት።*

*ወእምዝ ሶበ ሰምዓ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከመ ተጐናደዩ አውፅአ ጸባሕት ሰብአ ወንድጌ ወለግ ተምዕዓ ወአዘዘ ይምህርክዎሙ፥ ወማህረኩ ብዙኃ አልህምተ። ወአጥፍኡ እክለ ወአውዐዩ አብያተ። ወኮሎሰ ዘተማህረከ አልህምተ እምነ ለግ ወህበ ለንጉሠ ስናር ወለአሊ ወልደ አጅብ።*

*ወእምዝ ተንሥአ እምውእቱ መካን ወሖረ መንገለ ሳርካ፤ ወበጽሐ ኀበ መካን ዘህለወ ቦቱ ንስቲት ባሕር ዘትሰመይ ገደማ። ወወዓለ በህየ*

49. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 103-7.

በዓለ ጥምቀቱ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። ወእምዝ ተንሥአ እምህየ ወሖረ እንተ ፍኖተ ጸላሎ፥ ወዓደወ ፈለገ አብያ ወበጽሐ ምድረ ቡዳ፥ ወአሰንበተ በህየ።

ወእምዝ ተንሥአ እምውእቱ መካን ዘአሰንበተ ቦቱ ወወረደ መንገለ ዣራ እንተ ፍኖተ ወንዳላ። ወበጽሐ ኀበ አሐቲ ሀገር ዘህለወት በጽንፈ ፈለገ ሱኋ፥ ወአሰንበተ በህየ ወወዓለ በዓለ ቀበላ ጸም። ወእምድኅረ በዓተ ጸም ተንሥአ እምውእቱ መካን ወሖረ ኀበ አሐቲ ሀገር ዘስማ ሻሼ እንተ ስፋሕ መርሕባ፥ ወበህየ ረሰየ ከተማሁ።

ወእንዘ ህሉ በውእቱ መካን ተሰምዓ ዜና ምጽአተ ጋላ እመንገለ በረንታ። ወሶበ ሰምዓ ተንሥአ በጊዜሃ፥ ወሖረ በጉሮአ፥ እስመ ጉሮአ ውእቱ ለፀብእ ከመ ይጌገኤ ብእሲ ርኁብ ለመብልዕ፥ ወብእሲ ጽሙእ ለሰትይ። ወእምቅድመ ሑረቱ ፈነዎሙ ለራስ የማነ ክርስቶስ ወለራስ ሥዕለ ክርስቶስ አኃዊሁ እንተ ካልኤ ፍኖት። ወንጉሥኒ ሖረ ምስለ እሊአሁ እንተ ካልኤ ፍኖት። ወአቅዲሞ ፈነዎ ለአቤተኑን ወልደ ክርስቶስ ዘከነ ብላቴናዎች ጌታ በውእቱ ዘመን ምስለ ጎዳጣን ሠራዊተ ፀብእ ጊዜ ፍና ሰርክ።

ወበጽባሕ ተለወ ንጉሥ አሰሮ ወረከቦ ለጋላ ዘውእቱ ወረንሻ በምልኡ ወካልእኒ ጋላ ዘእምነገደ በርቱማ ምስሌሁ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት አመ ፲ወ፪ ለየካቲት በምድረ ለምጨን። ወተቃተሉ ጋላ ወሠራዊተ ንጉሥ ዓቢየ ቀትለ። ወኮነ መዊእ ለንጉሥ። ወተቀትሉ አሜሃ ብዙኃን ጋላ። ወእንዘ ይጐይይ ቦዘወድቀ ውስተ ጸድፍ ወውስተ ማይ ዘህሉ ማእከለ ጸድፍ፥ እስከ ኮነ ውእቱ ማይ ደመ እምብዙኀ ተቀትሎቱ ለጋላ።

ወአኀዊሁሰ ኢረከቡ ጋላ እስመ ተህከዩ ቦሙ ሰብእ፥ ወኢያንሑ መንገደ ወኢበጽሑ እስከ አባዊ።

ወእምድኅረ ዝንቱ መዊእ ፈቀደ ንጉሥ ከመ ይሖር መንገለ ወለቃ ከመ ይፅብኦ ለጋላ ዘህሉ በህየ። ወአንጕርጕሩ አቁትዝር፥ ወአቀ ሐዊሮ ተመይጠ እንበይነ ዘአንጕርጕሩ ቦቱ ሰብአ ከተማ። ወእምድኅረ ተመይጠ ረሰየ ከተማሁ ኀበ ጽንፈ ፈለገ ሱኋ።

ወእንዘ ህሉ በህየ ሰምዓ ምጽአተ ጋላ እመንገለ ወሰን አምባ። ወተንሥአ ንጉሥ በከመ ልማዱ እንዘ ይጌገኤ። ወሖረ ወበጽሐ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ዣን በድል። ወበህየ ረከቦ ለሊበን ጋላ፥ ዓቢይ ነገድ ዘየዓቢ እምኵሉሙ ነገደ ጋላ፥ በምድረ ዣን በድል በጽንፈ ፈለገ ብር። ወውእቱሰ ሊበን ብዙኀ ጥቀ ከመ አንበጣ ወማእምረ ፀብእ፥ ወኃያል ውእቱ እምኵሉሙ ነገደ ጋላ። ማህረክ ወአስተጋቢኦ ኵሉ አልህምተ ጋፋት፥ ወአልህምተ ጮሜ፥ አልህምተ አገው፥ ወአልህምተ ዳሞት፥ እስከ ሳከላ ወገበርማ አጥፊኦ ሀገረ፥ ወቀተሉ ብዙኃን ሰብአ፥ ወፈዊዎ ደቀ ወአንስተ። እኒሆ ምህርካሁ እንዘ ይትመየጥ ሀገሮ ረከቦ ንጉሥ በምድረ ዣን በድል በዕለተ ሐሙስ አመ ፳ወ፬ ለየካቲት።

ወርእዮ ጋላ ከመ መጽአ ቦቱ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ምስለ ብዙኃን ሠራዊት ይቤ፡ ምንትኑ ዝነገር፤ አእዋምኒ ወኮሉ ዕፀው አድባርኒ ወኮሉ አውግር ያንሰስዉ ከመ ሰብእ። ወነበረ አሜሃ ጋላ ከዊኖ ለኀበ ፫ ወ፬ ጭፍራ፤ ሉባ በባሕቲቱ፡ ቁሮ በባሕቲቱ፡ ቄንደላ በባሕቲቱ።

ወበጽሐ ንጉሥ ምስለ ኮሎሙ ሠራዊቱ መስተዕዶናን አፍራስ በዓቢይ ጉጉአ። ለሰብአ እግርሰ ኀደኀሙ ይትልውዎ በድኅሬሁ። ወተፃብኡ ንጉሥ ወሊበን፤ ወኮነ መዊእ ለንጉሥ በጊዜ ዘይፈጥን እምቅጽበተ ዓይን። ወተቀትለ ጋላ ዘአልቦ ኁልቈ። አሜሃ አልቦ ብእሲ መስተዕዶን ፈረስ እምኃያላኒሁ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ዘኢቀተለ ጋላ ወዘኢያምጽአ ችብችቦ፤ ወወገሩ አምሳለ እብን አርአስቲሆሙ ለጋላ ውስተ ኮሉ ገጸ ምድር ኀበ ቆመ ንጉሥ። ወዝንቱ መዊእ ኮነ በትእዛዘ እግዚአብሔር ክቡር ወልዑል፡ ይዕበይ ስሙ።

ዳዲ በሳኒታሁ ለውእቱ ዕለት ዕለተ ዓርብ አመ ፭ ወሮ ለዝወርኀ ሰምዓ ንጉሥ ከመ መጽአ ጋላ ማህሪኮ አልህምተ ብዙኃ ደቀ ወአንስተ እምነ ጋፋት ወአገው። ወሖረ ቦቱ ንጉሥ ምስለ ኮሉ ሠራዊቱ። ወሶበ ርእየ ጋላ ከመ መጽአ ንጉሥ ለዐቢአቱ ኢቆመ ለምዕራ፡ ዳእሙ ጐየ ወገብአ ውስተ ጸድፍ ዘፈለገ ብር። ወንጉሥኒ ተዓየነ በመልዕልቴሁ ወወረደ እንተ ካልእ ፍኖት ምስለ ኮሎሙ እኁዛነ ነፍጥ ወቀስት፡ ወዓርገ ኀበ ሀለወ ጋላ። ወአኀዘ ይቅትሎሙ እምጊዜ ፫ ሰዓት እስከ ፍና ሰርክ፡ እስከ ኮነ ፈለገ ብር ኮለንታሁ ደመ።

ወእምድኅረ ምሴት ወዕአ ኀበ ትዕይንቱ ዘተዓየነ መልዕልተ ጸድፍ ከመ ይክልኦ ሙፃአ ለጋላ። ወጋላሰ ሀሎ አሜሃ ስቁለ ማእከለ ጸድፍ አምሳለ ሆባይ ወጦጣ፤ ኢይወርድሂ ወኢይወዕእ። ወባሕቱ በይእቲ ዕለት ዘአምሰጠ እምቀትል ወሪዶ ሌሊተ እምጸድፍ በበ ንስቲት ንስቲት ሖረ መንገለ ሀገሩ።

ወእምዝ በሣልስት ዕለት ሰምዓ ንጉሥ ከመቦ ጋላ በቈላቲሃ ለኮንድል ዘትሰመይ ዘረገም። ወሖረ ንጉሥ ምስለ ኮሉ ሠራዊቱ። ወበጺሖ ረከቦ ለጋላ ዘስመ ነገዱ ዲገሉ በውስተ ውእቱ ምድር፤ እስመ ቦቱ ብዙኃ ምህርካ እንሰሳ ወሰብእ። ወውእቱኒ ጋላ ብዙኀ ጥቀ ፈረስኒ ወእግር። ወተፃብኡ ንጉሥ ወጋላ ዓቢየ ፀብአ። ወኮነ መዊእ ለንጉሥ ወተመውአ ለጋላ። ወተቀትለ ጋላ ዘኢኮነ ብዙኃ ወኢጎዳጠ፤ ውኔደገ ኮሎ ምህርካ አልህምት ዘኢይትኄለቍ። ወንጉሥኒ ቀቲሎ አምጣነ ተቀትለ ወአኀዲኅ ኮሎ ምህርካሁ ተዓየነ ኀበ ምድር ዘትሜኒ ለትዕይንት።

ወዝንቱ መዊእ ኮነ በዕለተ ሰኑይ አመ ፭ወ፪ ለየካቲት። ስብሐት ለእግዚአብሔር ወሀቤ መዊእ ለዘ ይትዌከል ቦቱ ወለዘያሰምክ በረድኤቱ።

❖

(ሱስንዮስ) በምድረ በድ ሳለ አሊ ወልደ (ኢብን) አጅብ ከስናር ንጉሥ ከአብድልቃድር ጋራ ሆኖ በሀገሩ በተነሣው ብጥብጥ ምክንያት ከብዙ ፈረሰኞችና እግረኞች ጋራ መጣና ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ አደረለት። የስናሩ ንጉሥ አሽከር ሆነለት፣ እንደአገልጋይም ታዘዘለት። ንጉሡም ለሕይወት የሚያስፈልገውን ሁሉ አሣመረለት። በሐር ልብስና በወርቅ አምባርም አስጌጠው። ከሚፈልገው ምንም አላሳጣውም። ምድርም ጭልጋን ሰጠው። ይሽንን ሁሉ ካደረገ በኋላ ክብር የሚገባውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል እዚያ አከበረ።

ከዚህ በኋላ የወንድጌ እና የለግ ሰዎች ግብር ከማግባት እንደለገሙ በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ (ሠራዊቱ) እንዲዘርፏቸው አዘዘ፣ ብዙ ከብቶች ማረኩ። እህል አጠፉ፣ ቤቶችም አቃጠሉ። ከለግ የተማረከውን ከብት ደግሞ ለስናሩ ንጉሥና ለአሊ ወልደ አጅብ ሰጣቸው።

ከዚህ በኋላ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ወደ ሳርካ ሄደ። ገደማ የምትባል ትንሽ ኩሬ ካለችበት ቦታ ደረሰ። ክብር የሚገባውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት እዚያ አከበረ። ከዚያ ተነሥቶ በጽላሎ መንገድ ሄዶ የአብያ ወንዝን ተሻገረ፣ ከምድረ ቡዳ ደረሰ። እሑድን እዚያ አሳለፈ።

ከዚያም እሑድን ካሳለፈበት ቦታ ተነሥቶ በወንዳሳ መንገድ ወደጥራ ወረደ። ከሱኋ ወንዝ ዳርቻ ወዳለች አንድ አገር ደረሰ። እሑድን እዚያ አሳልፎ የጸም ቅበላ አደረገ። ጸም ከገባ በኋላ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ መስኳ ሰፊ ወደሆነው ስሟ ሻሼ ወደሚባል አንዲት አገር ሄደ። ሰፈራውን እዚያ አደረገ።

እዚያ ቦታ እንዳለ በበረንታ በኩል የጋላ መምጣት ተሰማ። (ንጉሡ ዜናውን) ሲሰማ ወዲያው ብድግ ብሎ በፍጥነት ሄደ፣ የተራበ ለምግብ፣ የተጠማ ለመጠጥ እንደሚቸኩል ለጦርነት ችኩል ነውና። ከመሄዱ በፊት ወንድሞቹን ራስ የማነ ክርስቶስንና ራስ ሥዕለ ክርስቶስን በሌላ መንገድ ላካቸው። ንጉሡ ደግሞ ከራሱ (ሰዎች) ጋራ በሌላ መንገድ ሄደ። ሲመሻሽ፣ በዚያን ዘመን የብላቴኖች ጌታ የሆነውን አቤተጉን ወልደ ክርስቶስን ከጥቂት የጦር ሠራዊት ጋራ አስቀድሞ ላከው።

ጠዋት ንጉሡ ፈለጉን ይዞ ተከተለው። ጋሎችን፣ ማለት መላ ወረንሻንና ከነገደ በርቱማ ሌሎችንም ጋሎች፣ አብረው ሆነው ቅዳሜ ዕለት የካቲት 12 ቀን በምድረ ለምጨን አገኛቸው። ጋሎችና የንጉሡ ሠራዊት ታላቅ ግድያ ተጋደሉ። ድል ለንጉሡ ሆነ። በዚያን ጊዜ ብዙ ጋሎች አለቁ፣ ሲሸሹ ከገደልና እገደሉ ታች ካለው ውሐ የገባም ነበረ፣ ከጋሎቹ መገደል ብዛት ውሐው ደም ከመምሰል እስኪደርስ ድረስ።

ወንድሞቹ ግን ጋላ አላገኙም፣ ሰዎቻቸው ተጓተቱባቸው፣ መንገድ አላረዘሙም፣ እስከ አባይ ድረስ (እንኳን) አልደረሱም።

ንጉሡ ከዚህ ድል በኋላ ወለቃ ያለውን ጋላ ለመውጋት ወደዚያ ለመሄድ ፈለገ። ግን አቄትገር (ሠራዊቱ) አጉረመረሙ፤ ትንሽ ሄዶ የሰፈሩ ሰዎች ስላጉረመረሙ ተመለሰ። ከተመለሰ በኋላ ሰፈሩን ከሱኋ ወንዝ ዳርቻ አደረገ።

እዚያ ሳለ በወሰን አምባ በኩል የጋላን መምጣት ሰማ። ንጉሡ እንደልማዱ በጥድፊያ ተነሣ። ሄዶም ጣን በድል ከምትባል ምድር ደረሰ። እዚያ በብር ወንዝ ዳርቻ፥ ጣን በድል ምድር ላይ፥ ትልቁን ነገድ፥ ከነገደ ጋላ ሁሉ የሚበልጠውን፥ ሊበንን አገኘው። ይህ ሊበን እንዳንበጣ በጣም ብዙ፥ ጦር ዐዋቂ፥ ከጎይለኞቹ ጋሎች ሁሉ የበለጠ ጎይለኛ ነው። የጋፋትን ከብቶች፥ የጮሜን ከብቶች፥ የአገውን ከብቶች፥ የዳሞትን ከብቶች ሁሉ ማርኮና ሰብስቦ፥ እስከ ሳከላና እስከ ገበርማ ድረስ አገር አጥፍቶ፥ ብዙ ሰው ገድሎ፥ ሕፃናትንና ሴቶችን አግዞ ምርኮውን ይዞ ወደሀገሩ ሲመለስ ንጉሡ ጣን በድል ምድር ላይ ሐሙስ ዕለት የካቲት 24 ቀን አገኘው።

ጋሎቹ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድን ከብዙ ሠራዊት ጋራ ሲያዩ፥ "ይህ ነገር ምንድነው? ዛፎቹም እንጨቶቹም ሁሉ፥ ተራሮቹም ጋራዎቹም ሁሉ እንደሰው ይንቀሳቀሳሉ" አሉ። በዚያን ጊዜ ጋሎቹ በሶስትና በአራት ሰልፍ ተደራጅተው ነበረ -- ሉባው ለብቻው፥ ቄሮው ለብቻው፥ ቄንደላው ለብቻው[50]።

ንጉሡ ከፈረሰኛ ሠራዊቱ ሁሉ ጋራ በታላቅ ጥድፊያ መጣ። እግረኞቹን ከኋላው እንዲከተሉት ተዋቸው። ንጉሡና ሊበን ተዋጉ፤ ከዓይን ቅጽበት በሚፈጥን ጊዜ ውስጥ ድል ለንጉሥ ሆነ። ቁጥር የሌላቸው ጋሎች አለቁ። በዚያን ጊዜ ከንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ጎይለኞች ፈረሰኞች ውስጥ ጋላ ያልገደለና ቸብቸቦ[51] ያላመጣ (ሰው) አልነበረም። የጋሎቹን ጭንቅላት ንጉሡ በቆመበት ምድር ዙሪያውን እንደድንጋይ ከመሩት። ይህ ድል የሆነው ክቡርና ልዑል በሆነው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው፤ ስሙ ከፍ ከፍ ይበል።

ደግሞ በዚያ ዕለት ማግስት ዓርብ ዕለት ሚያዝያ 25 ቀን ጋሎች ከጋፋትና ከአገው ብዙ ከብት፥ ሕፃናትና ሴቶች ማርከው እንደመጡ ሰማ። ንጉሡ ከሠራዊቱ ጋራ ሁኖ መጣባቸው። ጋሎቹ ንጉሡ ሊወጋቸው እንደመጣ ሲያዩ ለአንዳፍታም አልቆሙም፤ ሸሽተው በብር ወንዝ ገደል ገቡ። ንጉሡም ከበላዩ ሰፈረ፤ ነፍጥና ቀስት ከያዙት (ሠራዊቱ) ሁሉ ጋራ ሆኖም በሌላ መንገድ ወረደ፤ ጋሎች ወደአሉበትም ወጣ። ከሶስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ ይገድላቸው ጀመረ-- የብር ወንዝ ሁለንተናው ደም እስኪሆን ድረስ።

ከምሽት በኋላ ከገደሉ አፋፍ ሰፈር ወደአደረገበት ሰፈሩ ጋላውን መውጫ ለመከልከል ወጣ። ጋላ ደግሞ በዚያን ጊዜ በገደል ማህል እንደዝንጀሮና እንደጦጣ ተንጠልጥሎ ነበረ፤ አይወጣ አይወርድ።

50. እነዚህ ምን እንደሆኑ የዜናሁ ለጋሳን ክፍል ፰ ተመልከት፤ ጸሐፊው እንዲህ ሲደረድራቸው ኦሮሞዎችን እንደሚያውቃቸው ያመለክታል።

51. ስለ ቃሉና ስለ አንገት ቁረጣ ባህል፥ ገጽ 116፥ ጎዳግ ቁ. 24ን ተመልከት።

ግን በዚያች ዕለት ከግድያ ያመለጠ በሌሊት ከገደል ወርዶ ጥቂት በጥቂት እየሆነ አገሩ ሄደ።

ከዚህ በኋላ በሰባተኛው ቀን ንጉሡ ዘረገም በምትባል የኮንድል ቄላ ጋላ እንዳለ ሰማ። ንጉሡ ከሠራዊቱ ሁሉ ጋራ ሆኖ (ወደዚያ) ሄደ። ሲደርስ የነገዱ ስም ዲገሉ የሆነ ጋላ በዚያ ምድር አገኘ፥ (አገሩ) ብዙ የእንስሳና የሰው ምርኮ ነበረበትና። ጋላውም በጣም ብዙ ነበረ፥ ፈረሰኞችና እግረኞች (ጭምር)። ንጉሡና ጋሎቹ ትልቅ ውጊያ ተዋጉ። ድል ለንጉሡ፥ ሽንፈት ለጋላ ሆነ። ብዙ ወይም ትንሽ ባይባልም ጋላ ተገደለ። ቍጥር የሌለውን የከብት ምርኮውን በሞላ ለቀቀ። ንጉሡም የተገደለውን ያህል ገድሎ፥ ምርኮውን ሁሉ አስጥሎ ለሰፈራ ከምትመች ምድር ሰፈረ።

ይህ ድል የሆነው ሰኞ ዕለት የካቲት 22 ቀን ነው። ለሚታመንበትና ረድኤቱን ድጋፍ ለሚያደርግ ድል ለሚሰጥ እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።

**ገለልተኛው ዜና መዋዕል በአፄ ፋሲል ዘመን** (1625–1660) **ከመዘገበው**[52]**፥**

*መስከረም፥ ዕለቱ ቀዳሚት ሰንበት፥ ወንጌላዊ ማቴዎስ፥*

*ሐረ ጎጦም። ወበውእቱ ዘመን መጽአ ጋላ ብሔረ ትግሬ ዘስሙ ለበቻ መጠነ ፴ሺህ ጋላ፥ ወአጥፍአ ሰራዌ። ወበተመይጦቱ አገትዎ ስዩማነ ዕራዶ ወተምቤን ወአሕለቅዎ እንበለ አትርፎ በምድረ አላ። ወነበረ ንጉሥ በዶቢት። ወሞተ ወልዱ ዘበኵሩ አቤቶ ቈስጠንጢኖስ።*

*ተፈጸመ ፱ ዓመት።*

❖

መስከረም፥ (የ1633 ዓ. ም. መጀመሪያ) ዕለቱ ቅዳሜ፥ (ዘመኑ) ማቴዎስ፥

(ንጉሡ) ጎጃም ሄደ። በዚህ ዓመት ስሙ ለበቻ መጠኑ አርባ ሺህ የሆነ ጋላ ወደትግሬ መጣ፤ ሰራዌንም አወደማት። ሲመለስ የዕራዶና የተምቤን ሹማምንት በምድረ አላ ላይ ከበው ምንም ሳያስተርፉ ፈጁት። ንጉሡ በዶቢት ተቀመጠ። የበኽር ልጁ አቤቶ ቈስጠንጢኖስ ሞተ።

(የግዛቱ) ፱ኛ ዓመት ተፈጸመ።

**ቀዳማዊ ዮሐንስ/አእላፍ ሰገድ** (1660–1674) **በነገሠ በዓመቱ**[53]**፥**

*አመ ፲ወ፪ ለታኅሣሥ ፀብያሙ ራስ መልክዓ ክርስቶስ ለ፲ወ፪ ቤተ ጋላ ዘውእቱ ውጫላ፥ ወረጣየ፥ ወረሚኑ፥ ወሬጌ፥ አበጢ፥ አና፥ ጉራ፥ ሱባ፥ ወሬብኮ፥ ወሬጁ፥ አርሱ፥ ኡሩካላ ዘወዕአ በአሸንጓ ወበጽሐ*

52. ዜና መዋዕል፤ EMML 7109, f. 65b. አፄ ፋሲል ከሰላሳ ዓመታት በላይ ገዝቶ ታሪኩን የጻፈለት የለም፤ ተጽፎለትም እንደሆነ እስካሁን አልተገኘም።

53. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyāsu I et Bakāffā*, part I, p. 9.

*ወራሪሁ በምልዓ ቤገምድር:: ወወሀቦ እግዚአብሔር ኀይለ ወመዊዓ በረድኤቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወበጸሎቱ ለአቡነ ሳሙኤል መምህረ ትሩፋት እስከ ቀተለ ብዙኃነ በይእቲ ዕለት::*

❖

**ታኅሣሥ 12 ቀን ራስ መልክዓ ክርስቶስ 12ቱን ቤተ ጋላ፥ ማለትም በአሽንጓ የመጣውንና ወራሪው በሞላ ቤገምድር የደረሰውን ውጫላን፥ ወረጣየን፥ ወረሚኑን፥ ወሬጉን፥ አበጢን፥ አናን፥ ጉራን፥ ሱባን፥ ወሬብኮን፥ ወሬጁን፥ አርሱን፥ ኡሩካላን፥ ወጋቸው:: እግዚአብሔርም በሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ረድኤትና በመምህረ ትሩፋት በአቡነ ሳሙኤል ጸሎት ኀይልና ድልን ሰጠው -- በዚያች ዕለት ብዙዎች እስኪገድል ድረስ::**

(ታኅሣሥ 12 ቀን ቅዱስ ሚካኤልና አቡነ ሳሙኤል የሚታሰቡበት ቀን ነው::)

**በነዚህ ሁሉ ውጊያዎች ኦሮሞዎች የተመቱት የጠላታቸው ጦር ድንገት ስለመጣባቸው ነው:: እነሱ ዘመቻ ሲወጡ ግን የሚደነቅ የጦር ዘዴ እንዳላቸውና ሱስንዮስ ሥልጣን ለመያዝ ሲያምፅ እንደተጠቀመበት እነዚህ ከአፄ ሱስንዮስ ታሪክ የቀዳኋቸው ጥቅሶች ያሳያሉ፤**

**(1)** *ወመከረ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከመ ይፅብኦ ለዘሥላሴ እንዘ ሀሎ በባሕቲቱ:: ኣጥብዓ ልቦ ወሖረ ምስለ እሊኣሁ ጎዳጣን ሰብእ መስተዕዕናን ኣፍራስ ወሰብእ እግር:: ወጸንሖ ተነቢኦ ውስተ ትሕት ምድር ዘወግዳ ዘትሰመይ መንታ ደፈር::*

*ወበጽሐ ዘሥላሴ በዓቢይ ትዕቢት ወበተነፍሖ ልብ እንዘ ይብል፥ መኑ ይቀውም ቅድሜየ ወመኑ ይደፍረኒ:: ወንጉሥኒ ሥልጣን ሰገድ ተንሥኣ እምዘነበረ ወኣሠነየ ጭፍራሁ ኣምሳለ ጋላ:: ወሠራዊተ ዘሥላሴሰ ወኮሎ ኣምኃራ ኣሜሃ ኢየኣምሩ ጭፍራ፤ መኑ ሕውሳነ ከመ ሰብእ ምስየጥ::*

❖

**(1) ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ዘሥላሴን ብቻውን ባለበት ሊወጋው ወሰነ:: ልቡን አጠንክሮ ከጥቂት (ሰዎቹ)፥ ፈረሰኞችና እግረኞች፥ ጋራ ሆኖ ሄደ:: መንታ ደፈር ከምትባል ረባዳ ከሆነች የወግዳ መሬት ተደብቆ ቆየው::**

**ዘሥላሴ በታላቅ ትዕቢትና በተነፋ ልብ፥ "ማነው በፊቴ የሚቆም፤ ማንስ ይደፍረኛል" እያለ መጣ:: ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ደግሞ ከነበረበት ተነሥቶ ጭፍራውን (የርብርቦሽ ሰልፉን) እንደ ጋላ (አሰላለፍ) አሣመረ:: የዘሥላሴና የአምኃራ ሠራዊት ደግሞ በዚያን ጊዜ ጭፍራ (የርብርቦሽ) አሰላለፍ አያውቁም፤ እንደ ገበያተኛ እርምስምሶች ነበሩ[54]::**

54. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 79.

(2) *ወተባህሉ ኵሉሙ ቍርባን፥ እስከ ማእዜ ንነብር እንዘ ንደክም በገቢረ ዘለሳ ወበስዒረ ሰንበት። ለእመ ተቃተልነ ንሕነ ሠራዊተ ንጉሥ ያዕቆብ ይበጽሐነኑ ለዊ ዕደው ፩ ብእሲ እምኃያላኒሁ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ።*

*ወእምድኅረ አኀለቁ ቍርባን ምክረ ትዕቢት ወነገረ ትዝኅርት አጥብዐ ልቦ ንጉሥ ያዕቆብ ወዓርገ ለተቃትሎ ኀበ ሀሎ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ፤ እስመ ኮነ በውእቱ ጊዜ መልዕልተ ዓቀብ ውእቱኒ በመትሕቲሁ።*

*ወበጺሖ ንጉሥ ያዕቆብ ሠርዐ ሰልፈ ከመ ሥርዐተ አምኃራ ዘወትር፤ ወአንበሮሙ ለለ ፩፩ ብእሲ በጠወታ ዘውእቱ በተርታ። ወንጉሥኒ ሥልጣን ሰገድ ወረደ ንስቲተ እምዓቀብ በጭፍራ አምሳለ ጋላ። ወአኀዙ ይትቃተሉ፤ ወወገሩ ትርኮ ወናር ብዙኃ እርሳሰ ውዑየ አምአፈ ነፍጥ። ወአልቦ ዘቀተሎ እንበለ ፩ ብእሲ። ወኮነ መዊእ በጊዜ ፍጡን ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ እንበለ ያንሥኡ እደ ሠራዊተ ንጉሥ ያዕቆብ።*

❖

(2) ቍርባን (የሚባሉት ሠራዊት) ሁሉም፥ "እስከ መቸ ድረስ ዘለሳ በመሥራትና ሰንበት በመሻር ስንደክም እንኖራለን? እኛ የንጉሥ ያዕቆብ ሠራዊት ብንዋጋ ከንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ጎይለኞች አንድ ሰው ለሰላሳ ሰዎች ይደርሰናልን?" ተባባሉ።

ቍርባን የትዕቢት ምክርና የትጅርት ነገር ሲጨርሱ ንጉሥ ያዕቆብ ልቡን አጠንክሮ ለጦርነት ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ወዳለበት ወጣ፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ እሱ (ሥልጣን ሰገድ) አቀበቱ ላይ፥ እሱ (ንጉሥ ያዕቆብ) ደግሞ ከበታቹ ነበረ።

ንጉሥ ያዕቆብ እንደደረሰ በወትሮው የአምኃራ ሥርዐተ ሰልፍ አሰለፈ፤ እያንዳንዱን ሰው በጠወታ፥ ማለት በተርታ፥ አቆመው። ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ደግሞ ከአቀበቱ እንደ ጋላ በጭፍራ ሆኖ ትንሽ ወረድ አለ። ይዋጉ ጀመር፤ ትርኮና ናር ከጠመንጃ አፈ ሙዝ የሚነድ ብዙ እርሳስ ተኮሱ፤ ከአንድ ሰው በቀር አልገደለም። ድል በአጭር ጊዜ ውስጥ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ሆነ -- የንጉሥ ያዕቆብ ሠራዊት ግና እጃቸውን ሳያነሡ[55]።

## (9) ኦሮሞዎችን የማስፈር ፖሊሲ

ነገሥታቱ የችግሩ ምንጭ ኦሮሞዎች እንደ ሌላው ሕዝብ ነባር (ሰፋሪ) አለመሆናቸውን ሲረዱ ያሰፍሯቸው ጀመር። አቶ ዐፅሜ የሚሉትን እንስማ[56]፤

55. እዚያው ገ. 91።.

56. Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis and His Work*, p. 163.

አጼም (ሠርፀ ድንግል) ከብልሃትና ከማስተዋል ጋራ ጐበዝ ነበሩ፤ ... ጋላውን በእርቅ እየሳቡ በጎጥምና በደምቢያ መሬት ያልታረሰውን ውድማ እያዩ መሩት፤ ከክርስቲያን ጋራ ቀላቀሉት።

ቦረኖች (*"ጋላ ዘሰሙ ቦረን"*) አፄ ሱስንዮስን በልጅነቱ አባቱን ገድለው እሱንና እናቱን ማርከው ወስደው "እንደ ልጃቸው ደግ ስለሠሩለት" ለሱ ፍቅር ነበራቸው። ስለዚህ ዕርቅና ሰላም ለመደራደር እሱም ጥሩ ዕድል ነበረው። ቋንቋቸውን ይናገራል፤ ያምኑታልም። ከዚህ በታች ያሉትን ከንጉሡ ታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ የተቀዱትን ጥቅሶች እንመልከት፤ ፍቅራቸውንና ለማስፈር ያደረገውን ሙከራ ያሳያሉ።

> (1) *ወእንዘ ሀሎ በዘከመዝ ግብረ መከራ መጽአ ጋላ ለፀቢአ ወለቃ። ወሶበ በጽሐ ኀበ ሐምቦ ዘትሰመይ ጽኆ በር ቅርብተ አባዊ ርእይዎ ለጋላ። ወጋላኒ ርእዩ ከመ ሀለዉ ሰብእ፤ ወጸውዓ በዓቢይ ቃል ወይቤ መኑ ውእቱ ዝንቱ። ወአጠየቅዎ እሊአሁ ወይቤልዎ አቤቶኑን ሱስንዮስ ውእቱ ወልደ አቤቶሁን ፋሲለደስ ዘአንተ ተአምሮ።*
>
> *ወሶበ አእመረ ጋላ ሮጸ ወበጽሐ ኀበ ሀሎ ወልደ ንጉሥ ውስተ ፈለግ ዘትሰመይ ሰደይ፤ ወወድቀ ታሕተ እገረሁ ወአንገርገረ በነገርጋረ ፍቅር እንዘ ይጠቡ አፃብዓ እግሩ። ወተጋነየ ሎቱ ብዙኃ ተጋንዮ ወሰሙ ለውእቱ ጋላ ቡኮ ዘእምነገደ ኮኖ።*
>
> *ወእንዘ ሀሎ ምስለ ውእቱ ጋላ ሰምዓ ዜና ከመ ጥቀ የኀሥሥዎ ሠራዊተ ፀብእ የአኀዝዎ ወይሞቅሕዎ። ውእቱኒ ሖረ ምስለ ዝኩ ጋላ ኀበ ደብር ዘትሰመይ ቋዓት። ወነበረ ህየ ኀዳጠ መዋዕለ።*

❖

(1) (ሱስንዮስ ለመንገሥ ባመፀበት ጊዜ) በእንደዚህ ያለ የመከራ ሁኔታ ላይ እንዳለ፤ ጋሎች ወለቃን ለመውጋት መጡ። አባይ አጠገብ ጽኆ በር ከምትባል አምቦ (ሐራ) ሲደርሱ ጋሎቹን አዩዋቸው። ጋሎቹም ሰው እንዳለ ሲያዩ "ይሄ ማነው?" ብሎ (መሪያቸው) ከፍ ባለ ቃል ተጣራ። የራሱ ሰዎች፥ "የአቤቶኑን ፋሲለደስ ልጅ አንተ የምታውቀው አቤቶኑን ሱስንዮስ ነው" አሉት።

ጋላው (ይኸንን) ሲያውቅ እየሮጠ የንጉሡ ልጅ ወዳለበት ሰደይ ወደምትባል ወንዝ ደረሰና እግሮቹ ላይ ወደቀ። የእግሩን ጣቶች እየጠባ በፍቅር እንጉርጉሮ አንጎራጎረ። እጅግ ወደቀለት። የዚህ ጋላ ስም ቡኮ ነው -- ከኮኖ ነገድ።

(ሱስንዮስ) ከነዚህ ጋሎች ጋራ ሳለ (የመንግሥቱ) ጦር ሠራዊት ይዘው ለማሰር አጥብቀው እንደሚፈልጉት ወሬ ሰማ። እሱም ከነዚያ ጋሎች ጋራ ቋዓት ወደምትባል ተራራ ሄዶ እዚያ ጥቂት ጊዜ ተቀመጠ[57]።

57. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 11-12.

(2) *ወእምዝ እምድኅረ በዓለ ፋሲካ ተንሥአ እምቤተ ጋላ ወሖረ መንገለ ሸዋ ሶበ ጸንዓ ቦቱ ረኀብ። ወእንዘ የሐውር በጽሐ ኀበ ሀገር ዘትሰመይ ደብረ ድኑኃን እንተ ይእቲ መካነ ዝሀሩ ወጸዋሪተ ዓፅሙ ለአብ ክቡር አባ ታዴዎስ ወልደ አበ አበው አባ ተክለ ሃይማኖት በረከተ ክልኤሆሙ ትብጽሐነ።*

*ወበህየ ረከቦ ለጋላ ዘይሰመይ ኮኖ ወተ፡ነዘበ ወሬዛ ማእምር ወጠቢብ ወመሰሎ ዘይፀብአ። ወጋላኒ መጽአ ፡ነቤሁ አእሚሮ ሶበ ጠየቀ ከመ ውእቱ ወልደ ንጉሥ፣ እስመ ኮነ ውእቱ ፍቁሩ እምትካት። ወገነየ ሎቱ በከመ ይገኒ ገብር ለእግዚኡ።*

*ወእምድኅረ ኩነተዝ ነገር ሖረ ወበጽሐ ኀበ ሀገር ዘትሰመይ ብልዕት። ወአመ ዕለተ ብጽሐቱ በጽሑ ህየ ብዙኃን ነጋድያን እምዝዋይ እኒዞሙ ብዙኃ ንዋየ። ወርእዮሙ ሰብአ ሀገር እሎንተ ነጋደ መሰሎሙ ከመ መጽአ ጋላ ለፀቢኦ ሀገር። ነገርዎ ለወልደ ንጉሥ እንዘ ይብሉ መጽአ ጋላ ብዙኅ።*

*ወውእቱኒ ሶበ ሰምዓ ዘንተ ተፅዕነ ላዕለ ፈረስ ወሖረ ምስለ እሊአሁ። ወበጺሖ ፡ነቤሆሙ አእመረ ከመ ነጋድያን እሙንቱ ወኢኮኑ ሠራዊተ ፀብእ። ወበእንተዝ ኢያሕሰመ ላዕሌሆሙ በሞት፣ ዳእሙ ነሥአ ኆሎ ዘበሙ ወኢ፡ነደገ ምንተኒ ወገብረ ለዘፈቀደ።*

*ወእምዝ ዓለውዎ ሰብአ መገዝ፣ ውእቱኒ አምጽአ ቦሙ ብዙኃነ ጋላ ዘይሰመዩ ቱላማ ከመ ይፅብአሙ። ወእሙንቲኒ ሰብአ መገዝ ርእዮሙ ብዝኃ ፀባኢት ፈርሁ ጥቀ፣ አምኑ ወተጋነዩ ሎቱ።*

*ለጋላኒ ዘመጽአ ለረዲኦቱ አስተፋነዎ ይሑር መንገለ ቤቱ። ወተመይጠ ጋላ እንዘ ያንኰረገ፡ር እስመ ኢ ማህረከ ወኢቀተለ በከመ ሐለየ ልቡ።*

*ወውእቱኒ ወልደ ንጉሥ ተርፈ ምስለ ሰብአ ሸዋ። ወእምድኅረዝ ሖረ መንገለ ደብረ ሊባኖስ ወነበረ ኀበ አሐቲ ምድር ዘትሰመይ ዓጽቃ።*

*ወአሜሃ ኮነ ቦቱ ዓቢይ ረኀብ ወአልቦቱ ዘይሴሰይ ምንትኒ ዘእንበለ አሐቲ ጸገት። ወኮነ ይሰትዩ ሐሊበ ዚአሃ ጽባሕ ለሊሁ ወልደ ንጉሥ ወምሴተ ቃሶ።*

❖

(2) ከዚህ በኋላ ረኀብ ቢጠናበት፥ ከፋሲካ በዓል በኋላ ከቤተ ጋላ ተነሥቶ ወደ ሸዋ ሄደ። ሲሄድ ደብረ ድኑኃን ደረሰ፣ ይች (ደብር) የክቡሩ አባት፥ የአባቶች አባት፥ የአባ ተክለ ሃይማኖት (የመንፈስ) ልጅ የሆነው የአባ ታዴዎስ የመቃብሩ ቦታና የዓፅሙ ተሸካሚ ናት[58]፣ የሁለቱም በረከት ትድረሰን።

እዚያ፥ ኮኖ የሚባሉትን ጋሎች አገኛቸው፣ ዓዋቂውና ጥበበኛው ጌልማሳ (ሱስንዮስ) ተጠራጠረ፣ የሚወጋው መስሎታል። ጋሎቹ

58. ገድላቸውን ቬሮኒካ ሲክስ አጥንታ ከጀርመንኛ ትርጉሟ ጋራ አሳትማዋለች፣ Six, *Die Vita des Abuna Tādēwos von Dabra Māryām.*

ደግሞ ወልደ ንጉሥ (ሱስንዮስ) መሆኑን ተረድተው ወደሱ መጡ፤ ምክንያቱም ከጥንት ጀምሮ ወዳጆቹ ናቸው። አገልጋይ ለጌታው እንደሚገዛለት ተገዙለት።

ይህ ነገር ከሆነ በኋላ ሄዶ ብልዕት ከምትባል ሀገር ደረሰ። የደረሰ ዕለት ብዙ ነጋዴዎች ብዙ ገንዘብ (የንግድ ሸቀጥና ከብት) ይዘው ከዝዋይ እዚያ ደረሱ። የሀገሩ ሰዎች እነዚያን ነጋዴዎች ሲያዩ ጋሎች ሀገር ለመውጋት የመጡ መስሏቸው፥ "ብዙ ጋሎች መጡ" ሲሉ ለወልደ ንጉሥ (ለሱስንዮስ) ነገሩት።

እሱም ይህንን ሲሰማ በፈረስ ሆኖ ከሰዎቹ ጋራ (ወደዚያ) ሄደ። እነሱ ዘንድ ሲደርስ ነጋዴዎች እንጂ የጦር ሠራዊት እንዳይደሉ ዐወቀ። ስለዚህ በሞት አልጐዳቸውም፤ ግን ያላቸውን ሁሉ ምንም ሳያስቀር ወሰደባቸውና ለፈለገው አዋለው።

ከዚህ በኋላ የመገዝ ሰዎች ከዱት፤ እሱ ደግሞ እንዲወጓቸው ቱላማ የሚባሉ ብዙ ጋሎች አመጣባቸው። እነዚህ የመገዝ ሰዎች የጦሩን ብዛት ሲያዩ እጅግ ፈሩና አመኑ፤ ተገዙለትም።

ሊረዱት የመጡትን ጋሎች ወደቤታቸው እንዲሄዱ ሸኛቸው። ጋሎቹም በልባቸው እንዳሰቡት ስላልማረኩና ስላልገደሉ እያጒረመረሙ ተመለሱ።

ወልደ ንጉሥም ከሸዋ ሰዎች ጋራ ቈየ። ከዚያ በኋላ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄዶ በአንዲት ዓጽቃ በምትባል ሀገር ተቀመጠ። በዚያን ጊዜ ትልቅ ረኀብ ደረሰበት። ከአንዲት ጥገት በቀር ምንም አልነበረውም፤ ወተኒን (ተራ በተራ) ጠዋት ወልደ ንጉሥ፥ ማታ ቃሶ ይጠጡ ነበረ[59]።

(3) *ወእንዘ የሐውር ኀቢሆን ምስለ እሊአሁ ኮነ ፍናቱ ፍኖተ ዓቀብ። ወበህየ ተዳደቆሙ ጊሜ ጽፉቅ ምስለ ፋፃ እስከ ኢይክሉ ይትረአዩ በበይናቲሆሙ። ወእምድኅረዝ ተዓየኑ በወፈማ ወነበረ ህየ ኀዳጠ መዋዕለ።*

*ወእንዘ ህሎ በህየ ቦኡ ሎቱ ጋላ ብዙኀ ዘኢይትኄለቍ ዘእምነገደ ከረዩ ዘውእቶሙ በላዕ ወጅሌ። ወውእቱኒ ተቀበሎሙ ምስለ እሊአሁ እንዘ ይትሬሰይ ንዋያተ ፀብእ እመንገለ ትሕዝብት፤ እስመ ብእሲ ኃያል ኮነ ይትኄዘብ ሎሌ ጊዜ ወይከውን ከመ ድብ ሐራስ ወከመ አንበሳ ዘይጥህር ጊዜ የኃሥሥ መብልዐ። ከማሁ ዝንቱኒ ንጉሥ ሥልጣን ሰገደ ኮነ ይትኄዘብ በሎሌ ጊዜ ወኢይትየዋህ እስከ ይገብር እግዚአብሔር ክቡር ወልዑል ዘፈቀደ።*

*ወእምዝ ተንሥአ እምወፈማ ወሖረ ኀበ ዱድ ወተዓየኑ በህየ። ወእንዘ ህሎ ህየ ዓዲ ቦአ ሎቱ ጋላ ዘእምነገደ ወሎ።*

❖

59. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 37-39.

(3) ከሰዎቹ ጋራ ሆኖ ወደነሱ (ወደ መንደሮቹ) ሲሄድ መንገዱ የዓቀበት መንገድ ሆነበት። በዚያም እርስ በርሳቸው መተያየት እስኪሳናቸው ድረስ ጥቅጥቅ ያለ ጉም (ከወጨፎ?) ፉጨት ጋራ ቀደማቸው። ከዚያ ወፈማ ላይ ሰፍሮ እዚያ ጥቂት ቀናት ተቀመጠ።

እዚያ ሳለ ቍጥር የሌላቸው ብዙ ጋሎች ከከረዩ ነገድ በላዕና ጅሌ ገቡለት። እሱም ከሰዎቹ ጋራ ሆኖ ለጥርጣሬ የጦር ትጥቅ ታጥቆ ተቀበላቸው፤ ምክንያቱም ኃይለኛ የሆነ ሰው እንደ አራስ ድብና ምግብ ሲፈልግ እንደሚያገሳ አንበሳ ሁል ጊዜ ይጠራጠራል። ይህ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድም እግዚአብሔር የፈቀደውን እስኪፈጽም ድረስ ሁልጊዜ ይጠራጠር ነበር።

ከዚህ በኋላ ከወፈማ ተነሣና ወደ ዱድ ሄዶ እዚያ ሰፈረ። እዚያ እያለ ደግሞ ከነገደ ወሎ የሆኑ ጋሎች ገቡለት[60]።

(4) *ወእምድኅረ ዝንቱ ተመይጠ ወአደወ ፈለገ አብያ ወበጽሐ ምድረ ኰሊሳ፤ ወተዓየነ በህየ ወነበረ ሰሙነ መዋዕለ። ወእንዘ ሀሎ በህየ ገብአ ሎቱ ጋላ ዘየአክል መጠነ ሠላሳ።*

❖

(4) ከዚህ በኋላ ተመለሰና የአብያን ወንዝ ተሻግሮ ምድረ ኰሊሳ ደረሰ። እዚያ ሰፍሮ አንድ ሳምንት ተቀመጠ። እዚያ እንዳለ ሰላሳ የሚያህሉ ጋሎች ገቡለት[61]።

(5) *ወእምድኅረ ኀለፈ ክረምት ወኮነ ሀጋይ ሰምዓ ንጉሥ ከመ ከድአ ጋላ ዘውእቱ ወረንሻ፤ ወቀተሎሙ ለሰብአ ወለቃ ወሰበረ ብዙኃነ አምባ።*

*ዝንቱ ጋላ እኩይ ውእቱ ወገኒአላዊ እምጥንቱ አምሳለ ሰይጣን፤ ኀፁፅ ውእቱ ወምኑነ ዘመድ እምኮሎሙ። ነገደ ጋላ እለ ይነብሩ ውስተ ብሔረ በድው። ቅድመ ነበረ ምስለ ወርዳያ። ወከድአ ለወርዳያ፤ ወቀተለ ብዙኃ እምኔሁ ወኮነ ምስለ አኽቸ።*

*ለአኽቸኒ ከድአ ወገብረ ላዕሌሁ አምሳለ ወርዳያ ወሖረ ኀበ ሊበን፤ ወነበረ ምስሌሁ።*

*ለሊበንኒ ከድአ ወቀተለ እምኔሁ ብዙኃ ወበአ ኀበ ወሎ ወነበረ ምስለ ወሎ።*

*ዓዲ ለወሎኒ ከድአ ወገብረ ዕርቀ ምስለ ሊበን።*

*ለሊበንኒ ከድአ ዳግመ ወነደረ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ፤ ወንጉሥኒ ወህበ ምድረ ዝማ ወአሞናት።*

*ወእንዘ ሀሎ በህየ ከድአ ለንጉሥ ወቀተሎሙ ለሰብአ ወለቃ፤ ወአምጽአ ለኢቱ ልኢኮ እምነ አደል ከመ ያጥፍእ ሀገረ ወለቃ ወጌዣም።*

60. እዚያው ገ. 76-7።
61. እዚያው ገ. 85።

ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ከመ ገብረ ዘንተ ወረንሻ አዘዘ ክትቻ፤ ወተንሥአ እምድኅና ወሖረ እንተ ፍኖተ በጌምድር:: ወወዐለ በህየ በዓለ ልደት ወጥምቀት::

ወተንሢአ እምህየ ዓደወ ፈለገ በሸሎ ወወዕአ መንገለ አምኃራ እንተ ፍኖተ እምቢስማን:: ወእምአምኃራኒ ዓደወ መንገለ ወለቃ፤ ወእምወለቃኒ ወዕአ መንገለ ደራ ወቤተ ማርያም::

ወበይእቲ ዕለት እምቅድመ ይብጽሑ ኀበ እሉ መካናት ደንገፁ ሠራዊተ ንጉሥ ወጐዩ በከንቱ እንዘ አልቦ ዘያደነግፆሙ:: ወቆመ ንጉሥ ባሕቲቱ ወተነጥአ ሰብእ በቅድሜሁ ወበድኅሬሁ በየማኑ ወበፀጋሙ:: ወሶበ ኀጥኡ ሠራዊተ ንጉሥ ዘይዴግኖሙ ተጋብኡ ሎቱ ወተመይጡ እምኔይይ::

ወኀሊፎ ንጉሥ እምአንቀጸ ጨረን ነበረ እስከ ይጸብሕ ሎቱ:: ወጸቢሖ ወዕአ ንጉሥ መንገለ ደራ ወሖረ ኀበ አሞናት:: ወበህየ ረከቦ ለወረንሻ ምስለ ኮሉ ኀእዙ ወአልህምቲሁ:: ወተቀትለ ጋላ ብዙኀ በእደዊሆሙ ለሠራዊተ ንጉሥ:: ወተማህረኩ ደቅ ወአንስት ወአልህምት ዘኢይትኰለቁ::

ወበሳኒታ ይእቲ ዕለት ገብረ ንጉሥ ከማሁ፤ ወእምዝ ተመይጠ::

ወእንዘ ይትመየጥ ፈነዎ ንጉሥ ለአሐቲ አረጋይት ዘተዜወወት እምወረንሻ እንተ ይእቲ እሙ ለከረዩ ፁጠ ምስለ ንኡስ ወልዳ፤ ወለአካ ኀበ ወረንሻ እንዘ ይብል ሶበ አንትሙ ከዳእክሙ ወፀባእክሙ ሀገረ ወለቃ ወሰበርክሙ አምባ:: አነኒ በእንተዝ መጻእኩ ለፀቢአትክሙ:: ባሕቱ ሰረይኩ ለክሙ ዕዳክሙ:: ንዑ ግበሩ ዕርቀ ምስሌየ::

ወሰሚያሙ ወረንሻ መልእክተ ንጉሥ እምአፈ ይእቲ አረጊት መጽኡ መጠነ ፴ ጋላ ወገብሩ ዕርቀ ምስለ ንጉሥ::

ወተመይጠ ንጉሥ መንገለ አምኃራ፤ ወወዐለ በዓለ ቀበላ ጸም በቤተ አምኃራ:: ወበህየ ሤሞ ሚመተ ትግሬ መኰንን ወባሕር ነጋሽ ለዮልዮስ:: ወለራስ ሥዕለ ክርስቶስኒ ወህቦ ጐዣምሃ በምልኡ ከመ ራስ አትናቴዎስ::

ወተንሢአ ንጉሥ እምቤተ አምኃራ ወረደ በፍኖተ ደንቆሮ፤ ወበጽሐ ኀበ አኻዮ:: ወእምዝኒ ዓደወ ፈለገ በሸሎ፤ ወእምዝ ወዕአ መንገለ ስማዳ:: ወእንዘ የሐውር በጽሐ ኀበ ምድረ ቅርኛ፤ በህየ አስተፋነዎ ለዮልዮስ ከመ ይረድ መንገለ ትግሬ:: ወንጉሥኒ አተወ ጉርኃራ ወነበረ በህየ እስከ ወርኃ ሰኔ::

ወወረንሻኒ ከድኦ ለኢቱ ወቀተለ ሰብአ ዚአሁ ወነሥአ አልህምቲሁ:: ወሶበኒ መጽአ ለገቢረ ዕርቅ አሰሮ ለአዛገ ሀካኮ ዓቢይ ጋላ ወማእምረ ኮሉ ነገር:: ወአልቦ ዘከማሁ በውስተ ኮሉ ጋላ::

ወወህበ ለፊት አውራሪ ወልዶ ዘከነ በውእቱ መዋዕል ሥዩመ ወለቃ::

ወእምድኅረዝ ለአከ ወረንሻ ኀበ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ እንዘ ይብል ተቀበለኒ:: ወዓደወ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ መንገለ ወለቃ ወተቀበሎ ወአዕደዎ ኀበ ምድረ ጐዣም ወከረመ በህየ::

*ወእምድኅረ ከረመ ወረንሻ በምድረ ጐግም ወሀበ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ምድረ ገንገር። ወሀሎ በህየ እስከ ተጽሕፎተ ዝንቱ ታሪክ።*

❖

(5) ክረምት አልፎ በጋ ሲሆን ወረንሻ ጋላ እንደከዳና የወለቃን ሰዎች እንደፈጃቸው፥ ብዙ አምባ እንደሰበረም ንጉሡ (ሱስንዮስ) ሰማ።

ይህ ጋላ ከጥንቱ ጀምሮ እንደሰይጣን እኩይና ብልሹ ነው። በምድረ በዳ ከሚኖሩ ከነገደ ጋላ ሁሉ ጐደሎና ወገኑ የተጠላ ነው። መጀመሪያ ከወርዳያ (ጎሳ) ጋራ ነበረ፤ ወርዳያን ከዳው፤ ከእሱም ብዙዎች ፈጀበትና ከአኽቹ ጋራ ሆነ።

አኽቹንም ከድቶ በወርዳያ ላይ እንዳደረገው አደረገበትና ወደሊበን ሄዶ ከሱ ጋራ ኖረ።

ሊበንንም ከድቶት ከሱ ብዙ ሰው ፈጅቶበት ለወሎ ገብቶ ከወሎ ጋራ ተቀመጠ።

ደግሞ ወሎን ከድቶት ከሊበን ጋራ ታረቀ።

ሊበንን እንደገና ከድቶት ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ አደረ። ንጉሡም ምድረ ገርማን እና አሞናትን ሰጠው።

እዚያው ሆኖ (እነሆ) ንጉሡን ከድቶ የወለቃን ሰዎች ፈጃቸው። (በዚያ ላይ) ወለቃንና ጐጃምን እንዲያጠፋቸው ኢቱን ተላልኮ ከአደል (ከአዳል) አመጣው።

ንጉሡ ወረንሻ ይኽንን እንዳደረገ ሲሰማ ክትቻ ዐወጀና ከድኻና ተነሥቶ በቤገምድር በኩል ሄደ። እዚያ የልደትን በዓልና ጥምቀትን አሳለፈ።

ከዚያ ተነሥቶ የበሸሎን ወንዝ ተሻገረና በእምቢስማን በኩል ወደ አምኃራ ወጣ። አምኃራንም ወደ ወለቃ ተሻገረው። ከወለቃ ደግሞ ወደ ደራና ወደ ቤተ ማርያም (ወደ ሀገረ ማርያም) ወጣ።

የንጉሡ ሠራዊት በዚያች ዕለት እነዚህ ቦታዎች ገና ሳይደርሱ ምንም የሚያስበረግጋቸው ሳይኖር በርግገው በከንቱ ሸሹ። ንጉሡ ብቻውን ሆነ፤ በፊቱም በኋላውም፥ በቀኙም በግራውም ሰው ጠፋ። የንጉሡ ሠራዊት የሚከታተላቸው ሲያጡ ተሰባስበውለት ከሸሸት ተመለሱ።

ንጉሡ ከጨረን በር አልፎ እስኪነጋለት ድረስ ቆየ። ሲነጋ ንጉሡ ወደ ደራ ወጥቶ ወደ አሞናት ሄደ። እዚያ ወረንሻን ከጓዙና ከከብቱ ሁሉ ጋራ አገኘው። ብዙ ጋላ በንጉሡ ሠራዊት እጅ አለቀ፤ ቍጥር የሌላቸው ሕፃናት፥ ሴቶች፥ ከብቶች ተማረኩ።

ንጉሡ በዚያች ዕለት ማግስትም እንደዚሁ አደረገ። ከዚያ በኋላ ተመለሰ።

ሲመለስ የከረዩ ፉጦ እናት የሆነችውን ከወረንሻ የተማረከችውን አንዲት አረጋዊት ከትንሽ ልጇ ጋራ ላካት። እንዲህ ሲል ወደወረንሻ

ላካት፥ "እናንተ ብትከዱኝና ወለቃን ብትወጉ፥ አምባም ብትሰብሩ እኔ ደግሞ በዚህ ምክንያት ልወጋችሁ መጣሁ። ግን እዳችሁን ይቅር ብየላችኋለሁ። ኑ፥ ከኔ ጋራ ታረቁ።"

ወረንሻ የንጉሡን መልክት ከዚች አረጋዊት ሲሰሙ አርባ የሚሆኑ ጋሎች መጥተው ከንጉሡ ጋራ ታረቁ።

ንጉሡም በአምኃራ በኩል ተመለሰ። የ(ዐቢይ) ጾም ቅበላን በቤተ አምኃራ አሳለፈ። እዚያ ሆኖ ዮልዮስን የትግሬ መኰንንና የባሕር ነጋሽ ሹመት ሾመው። ለራስ ሥዕለ ክርስቶስ ደግሞ ድፍን ጐጃምን ሰጠው -- እንደ ራስ አትናቴዎስ።

ንጉሡ ከቤተ አምኃራ ተነሥቶ በደንቆሮ መንገድ ሄዶ አኻዮ ደረሰ። ከዚያም የበሽሎን ወንዝ ተሻገረ። ከዚያም ወደስግዳ ወጣ። ሲሄድ (በዚያው) ምድረ ቅርኝ ደረሰ። ከዚያ ዮልዮስን ወደትግሬ እንዲወርድ ሸኘው። ንጉሡም ጎርጎራ ገባ። እዚያ እስከሰኔ ወር ድረስ ተቀመጠ።

ወረንሻም (ጎትቶ ያመጣውን) ኢቱን ከድቶት ሰዎቹን ገደለበት፥ ከብቶቹንም ወሰደበት። አዛዥ ሀካኮን ዕርቅ ለማድረግ ሲመጣ አሰረው። (ሀካኮ) ሁሉን ነገር ዐዋቂ ትልቅ ጋላ ነው። እንደሱ ያለ በጋላ ውስጥ የለም። (አስሮ) በዚያን ጊዜ የወለቃ ሹም ለነበረው ለፊታውራሪ ወልዶ ሰጠው።

ከዚህ በኋላ ወረንሻ "ተቀበለኝ" ብሎ ወደራስ ሥዕለ ክርስቶስ ላከ። ራስ ሥዕለ ክርስቶስ ወደወለቃ ተሻግሮ ተቀበለው። ወደምድረ ጎጃምም አሻገረውና ክረምቱን እዚያ አሳለፈ።

ወረንሻ በምድረ ጎጃም ከከረመ በኋላ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ምድረ ገንገቦን ሰጠው። ይህ ታሪክ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ እዚያ አለ[62]።

ይህንን ሁሉ የጻፉልን አዛዥ ተክለ ሥላሴ ጢኖም እንደ አዛዥ ሀካኮ ኦሮሞ ሳይሆኑ አይቀሩም። ኦሮሞዎችን የሳቸውን ያህል የሚያውቅ የለም።

አፄ ሱስንዮስ በአልጋው ሲደላደል በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኑን ቅፈፍ (መሬት) እየወሰደ ብዙዎቹን አስፍሯቸው ነበር[63]። በዚያ ላይ ኦሮሞዎቹ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከመንግሥት ጋራ እንደዚያ እየተጣሉ በኢትዮጵያዊነት የመንግሥት የጦር ሠራዊት ውስጥ ተመልምለው የዝርፊያ ጥቅማቸውን በዚያ በኩልም ያገኙት ነበረ። ይኸንን የምናውቀው ታሪክ ጸሐፊዎች አንዳንዶቹን ኦሮሞዎች በስማቸውና የነገዳቸውን ስም ጠርተው ሲያስተዋውቁን ነው። በክርስትና

62. እዚያው ገ. 141-3።

63. *ዮሳጀም ታሪክ*፥ EMML 5403, f. 65ab: "አጼ ሱስንዮስም መንግሥቱ በጸና ጊዜ አብረው የመጡትን ጋሎች በጎጃምና በዳሞት በመተከልና በባንጃ ሠራቸው (አሰፈራቸው)። የተረፉትን ጋሎች ደግሞ የሚሠራበት (የሚያሰፍርበት) ቢአጣ ለየአድባራቱ የገባውን ቅፈፍ (መሬት) ኢየነቀለ ጋላ ሠራበት (አሰፈረበት)።"

ስማቸው የሚጠሯቸውማ "የሰሜንና የማህል ኢትዮጵያ ሰዎች" ወይም እንደ ዶክተር መሐመድ ሐሰን አጠራር "አቢሲኒያውያን" እንጂ ኦሮሞዎች አይደሉም::

ግን ምንጮቹ እንደሚያሳዩት፥ ኦሮሞዎች በጎሳነት አንድ አካባቢ ከያዙ በኋላም ከሰብአ ትካታዊ ዘላንነት ወጥተው በያዙት አካባቢ በግብርናም ሆነ በከብት ርቢ "በግምባር ላብ" ለመኖር ጊዜ ፈጅቶባቸዋል:: ባህላቸው ያልዘሩትን ማጨድ የማይከለክል፥ እንዲያውም የሚያበረታታ ይመስላል፤ መንፈሳዊ መሪያቸውን ከሩቅ አገር ድረስ እየመጡ ቡራኬ ሲጠይቁት የሚሰጣቸው ቡራኬ፥ "ውለዱ ክበዱ፤ የሥራችሁን ፍሬ ዋቃ ይባርክላችሁ" የሚል ሳይሆን ለድል አደራጊነትና ለዘረፋ የሚሆን ምረቃና መድኃኒት ነው:: አንድ ጊዜማ ማህል ለማህል እየገፉ መጥተው የራሱን የወዳጃቸውን የአፄ ሱስንዮስን ከተማ ዘርፈው ቤቶቹን በእሳት አጋይዋቸው[64]፤

> *ወእንዘ ሀሎ በአይባ ፈነወ ደጅ አዝማች ሀፈ ክርስቶስ መጽሐፈ መልእክት እንዘ ይብል:: ናሁ መጽኡ ፫ ቤት ጋላ ዘውእቶሙ አና ዑሩ ወአበጢ ዘበተጋብኦቶሙ ይሰመዩ በስመ ፩ ነገድ ዘውእቱ መረዋ:: ወምጽኡተ ጋላሰ ኮነ ለአጥፍኦ በጌምድር::*
>
> *ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ዘንተ ነገረ ተንሥአ እምአይባ ከመ ይሖር ለተፃብኦተ ጋላ መንገለ በጌምድር፥ ወተዓየነ በወይና ደማዓ:: ወበህየ ኖለቁ ንጉሥ አፍራሰ ሠራዊቱ ወኮኑ መጠነ ፱ወ፻:: ወኢሀሎ መኑሂ ዘእንበለ ጸናሕያነ ዴዴ:: ወራሰ የማነ ክርስቶስኒ አሜሃ ሀለወ ምስሌሁ መጺኦ እምነ አምኃራ:: ወእምወይና ደግዐኒ ወረደ እንተ ፍኖተ ደሪጻ፥ ወዓደወ ፈለገ ርብ ውነለፈ ካዕበ እንተ ፍኖተ ዘንግ ወተዓየነ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ቁጠማ:: ወእምህየኒ በጽሐ ምድረ ጸምኦ አመ ፲ወ፫ ለወርኃ ታኅሣሥ በዕለተ ረቡዕ::*
>
> *እምድኅረ ተዓየነ በውስተ ውእቱ ምድር ለነዲር ጊዜ ፱ ሰዓት መጽኡ ሰብአ ዓይን ወነገርዎ ለንጉሥ ከመ ሀሎ ጋላ በቅሩብ:: ወንጉሥኒ አዘዘ ከመ ያጥፍኡ እሳተ ለእመ ርእየ ጋላ ከመ ኢይገዋይ እንበለ ይግበር ፀብአ:: ወተአዘዙ ኵሉ ሠራዊቱ ወአጥፍኡ እሳተ፥ ውነደሩ በትዕቢት ወበተመክሖ::*
>
> *ወበጽባሕ ተንሥአ ንጉሥ ወሖረ ኀበ ሀሎ ጋላ ወጊዜ ፫ ሰዐት በጽሐ ኀበ አምባ ዘሠርዖ ወልደ ሐይቶኒ:: ወአምጽአ ሠርዖ መጠነ ፲ወ፭ ቸብቸቦ ዘጋላ:: ውነሊፎ ንስቲተ እምነ ውእቱ አምባ ተመይጡ ሰብአ ዓይን ዘፈነዎሙ ንጉሥ ከመ ይርአዩ ኀበ ሀሎ ጋላ ወነገርዎ ወይቤልዎ ሀሎ ጋላ በቅሩብ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ውቅሮ:: ወባሕቱ ይፈቅድ ሐዊረ ወገቢረ ገኃዞ::*
>
> *ወንጉሥኒ እምቅድመ ይርአይ ሀልዎተ ጋላ አዘዘ ለኵሉ ሠራዊቱ ከመ ኢይቁሙ ምስሌሁ አላ ይሑሩ ወኢይስድድዎ ለጋላ:: ወሶቤሃ*

64. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 116-19.

ፈትሑ ወራሪ ኮኑ ሠራዊተ ንጉሥ ከመ ዘይፈትሑ ወትረ ላዕለ ጎንጋ ወሻንቅላ:: ወሶበ በጽሑ ተርእየ ጋላ፣ ወሀሎ ሠሪያ ጭፍራሁ ወተደሊዎ ለፀብእ::

ወሀሎ ማእከለ ጋላ ወማእከለ ሠራዊተ ንጉሥ ቍልቍለት ዘኢኮነ ነዊኃ ወኢሐጺረ:: በፍጻሜ ቍልቍለትኒ ሀሎ መርጎብ ሠናይ ዘይበቍዕ ለተፃብኦ ወለምርዋጻ አፍራስ:: ውኂፎ ጋላ ዛተ መርጎበ ሀሎ ንቡረ በጭፍራ ኀበ ምድር ዘትልዕል፣ ወትመጥቅ እምነ ይእቲ መርጎብ::

ወሠራዊተ ንጉሥሰ እለ ይበዝኑ ኢቀርቡ ለተፃብኦ ጋላ፣ አላ ቆሙ እምርሑቅ፣ መንፈቆሙ በፍርሀት ወመንፈቆሙ በትምይንት:: ወእለሰ ጠብዐት ልቦሙ ወእለ ፈርሁ ኀፍረተ ወረዱ ምስለ ራስ የማነ ክርስቶስ ወአቤተኑን ወልደ ክርስቶስ:: ወንጉሥኒ ወረደ እምነ ዓቀብ መንገለ መትሕት ወአትከለ ደበና::

ድብ አንበሳኒ ተዘብጠ ለትእምርተ ወጢነ ፀብእ፣ ወንስርቃና ተነፍሐ:: ወጋላሰ ሀሎ ፈረስ ዘጭፍራ በባሕቲቱ ምስለ ጎዳጣን እግር፣ ወጭፍራ ዘእግር በባሕቲቱ ዘአልቦ ኑልቄ:: ወአንዙ ይትቃተሉ ዓቢየ ቀትለ:: ወኮኑ ያጐይይዎ ምዕረ ጊዜ ሠራዊተ ንጉሥ ለጭፍራ ዘፈረስ:: ወምዕረ ጊዜ ያጐይዮሙ ጋላ:: በዘከመዝ ግብረ ተፃብኦ ወዐሉ ሰዓተ እሙረ::

ወሶበ ርእየ ጋላ ዘሀሎ ንቡረ በጭፍራ ከመ ብዙኃን ፈራሃን እለ ቆሙ መልዕልተ ዓቀብ ያንጎግው ድኅረተ ወይትሐወሱ ከመ ብርዕ ይትሐወስ በኀይለ ነፋስ:: ተንሥአ ጋላ በምልኡ ወኢክህሉ ሠራዊተ ንጉሥ ተቃውሞቶ:: ወቀደሙ ጐይየ እለ ቆሙ በርኑቅ:: ወኮነ አሜሃ መዊእ ለጋላ ወተመውኦ ለንጉሥ::

ወተቀትሉ ብዙኃን መኳንንት በእደ ዝኩ ጋላ ዘውእቶሙ አቤተኑን ወልደ ክርስቶስ፣ ወአስጓ ልሳነ ክርስቶስ፣ ወልሳነ ክርስቶስ ወልደ አቤተኑን ሣህሉ፣ እስክንድር ወልደ ተክለ ሥሉስ ዘሲሬ፣ ለባሲ ሥዮም (ሥዩም?) ዘዝፋን ቤት፣ ወንኡስ የማኖ ዘልህቀ ታሕተ እግረ ንጉሥ፣ ሼቶ እምነ አርባብ:: ወመለክ ሐራ ዕንቆ፣ ወካልኦን ብዙኃን እምነ ቍርባን:: ወእምነ ሰራዊተ ንጉሥ መስተፅዕናነ አፍራስ ወሰብአ እግር እለ ሞቱ በውእቱ ዕለት አልቦሙ ኑልቄ:: ወዝንቱ ተመውኦ ኮነ አመ ፲ወ፱ ለታኅሣሥ በዕለተ በዐሉ ለቅዱስ ገብርኤል:: አልቦ ቤት ውስተ ከተማ ንጉሥ ዘኢሀሎ አሜሃ ሰቆቃው ወላህ በእንተ ብዝኀነ ሞቶሙ ለሰብእ::

ንጉሥሰ እምድኅረ ኮነ መዊእ ለጋላ ወዕዐ እንተ ፍኖተ ዳባት:: ወበሳኒታሁ ኃለፈ እምዳባት ወተዓየነ መልዕልተ አሐቲ ወግር ዘትሰመይ ድባና:: ወእምዝኒ ኀለፈ መንገለ ማኀደረ ማርያም ወአሰንበተ ባቲ::

ወበህየ መጽአ ጐዣም ኑጋሽ ክፍሉ ምስለ ጨዋ ዘይሰመዩ ኀይላት ወምስለ ብዙኃን ሰብአ አፍራስ ወእግር:: ዓዲ እንዘ ሀሎ ውስተ ይእቲ

*ማኅደረ ማርያም ፈነወ ንጉሥ ኀበ ዮልዮስ መጽሐፈ መልእክት እንዘ ውእቱ ሀሎ አሜሃ በምድረ ጉማን። ወነገረ መልእክቱሰ ለንጉሥ ይነግር ኩነተ መዊእ ወተመውአ ወይኤዝዝ ከመ ይብጻሕ ፍጡነ ለረዲኦቱ።*

*ወእምድኅረ ፈነወ ዘንተ መልእክተ ተንሥአ ንጉሥ እማኅደረ ማርያም ወሖረ ገዳሠ ወነደረ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ኾድ ገበየ። ወእምዝኒ ኀለፈ መንገለ ቃሮዳ። ወእምቃሮዳኒ ተንሢኦ ተጓየነ ማእከለ ቆጋ ወአምጣ ማርያም ኀበ ምድር ዘትሰመይ ማሸሉት። ወበህየ ወዐለ በዐለ ልደት ዘለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘክሮቱ ሰጊድ።*

*እምድኅረ በዐለ ልደት ወፅአ ንጉሥ በፍናተ ወይና ደግዓ መንገለ ደንቀዝ። ወኮነ ይጸንሕ በህየ ተጋብኦተ ሰብእ እምዝርወት ወምጽአተ ሠራዊት እምርኁቅ ወቅሩብ ከመ ይፃባእ ዳግመ ምስለ ጋላ። ወጋላሰ ወረደ አሜሃ እምውቅሮ መንገለ ሐሙስ ወንዝ። ወእምዝኒ መጺኦ በጭፍራ ኣጥፍአ ወአማሰነ ኮሎ አህጉራተ እንፍራዝ ወማህረከ እስከ ጎረባ ወእስከ ጭኽራ። ወአውዳየ መዲና ንጉሥ ዘቆጋ ወተመይጠ መንገለ ሐሙስ ወንዝ።*

❖

(ሱስንዮስ) በአይባ በነበረበት ጊዜ ደጅ አዝማች ሀፈ ክርስቶስ (ወደ ንጉሡ) እንዲህ ሲል የመልእክት ደብዳቤ ላከ፤ "እነሆ ሶስቱ ቤተ ጋላ፥ እነሱም ሲሰባሰቡ መረዋ በሚል አንድ ነገድ የሚጠሩ፥ እነ አና፥ ዑሩ፥ አበጢ መጡ። የጋሎች አመጣጥ በጌምድርን ለማጥፋት ነው።"

ንጉሡ ይኸንን ነገር ሲሰማ ጋሎችን ለመዋጋት ወደ በጌምድር ሊሄድ ከአይባ ተነሣና ወይና ደግዓ ላይ ሰፈረ። ንጉሡ እዚያ የሠራዊቱን ፈረሶች ቁጠረ፤ አንድ መቶ አርባ ነበሩ። ከግቢው ጠባቆች በቀር (የቀረ) ሌላ ማንም አልነበረም። ራስ የማነ ክርስቶስም ያን ጊዜ ከአምኃራ መጥቶ አብሮት ነበረ። ከወይና ደግዐ ወደ ደሪጻ መንገድ ወረደ። የርብ ወንዝን ተሻግሮ ደግሞ በዘንግ መንገድ አልፎ ቁጠማ ከምትባል ቦታ ሰፈረ። ከዚያ በታኅሣሥ ፲፰ቀን ረቡዕ ዕለት ጸምአ ደረሰ።

ለማደር እዚያ በዘጠኝ ሰዓት እንደሰፈረ ሰላዮች መጥተው ጋሎች በቅርብ እንዳሉ ለንጉሡ ነገሩት። ንጉሡም ጋላ እሳት ሲያይ ሳይዋጓ እንዳይሸሽ እሳት እንዲያጠፉ አዘዘ። ሠራዊቱ ሁሉ ታዘው እሳት አጠፉና በትዕቢትና በትምክሕት አደሩ።

ጠዋት ንጉሡ ተነሥቶ ጋሎች ወዳሉበት ሄደ። በሶስት ሰዓት ከሐይቶኝ ልጅ ከሠርያ አምባ ደረሰ። ሠርያ ዓሥራ አንድ ያህል የጋላ ቸብቸቦ አመጣ። ከዚህ አምባ ጥቂት አለፍ እንዳለ ንጉሡ ጋላ ያለበትን እንዲያዩ የላካቸው ሰላዮች ተመልሰው መጡ። "ጋሎች በቅርብ ውቅሮ በምትባል ቦታ አሉ፥ ግን ጓዝ አንሥተው ለመሄድ ይፈልጋሉ" ብለው ነገሩት።

ንጉሡም የጋሎችን ሁኔታ ሳያይ ሠራዊቱን እንዳይለቁቸው (ወደነሱ) እንዲሄዱ፥ አብረውት እንዳይቆሙ አዘዛቸው። በዚያን ጊዜ የንጉሡ ሠራዊት በሞላ ዘወትር በጎንጋ እና በሻንቅላ ላይ ወራሪ እንደሚፈቱ ፈቱ፤ ሲደርሱ ጋሎቹ ታዩ። በጭፍራ ሰልፋቸው ሆነው ለጦርነት ተዘጋጅተዋል። በጋሎችና በንጉሡ ሠራዊት መካከል ረጅም ወይም አጭር የማይባል ቀላቀለት አለ። ከቀላቁለቱ ማለቂያ ላይ ለጦርነትና ለፈረስ ሩጫ የሚስማማ ጥሩ ሜዳ አለ።

ጋሎቹ ያችን ሜዳ አልፈው፥ ከሜዳዋ ከፍ ከምትልና ወደላይ ከምትሆን መሬት በጭፍራ (ሰልፍ) አሉ። የንጉሡ ሠራዊት ደግሞ ግማሾቹ በፍርሃት ግማሾቹም በንቀት አብዛኞቹ በሩቁ ቆሙ እንጂ ጋሎቹን ለመውጋት አልቀረቡም። ልባቸው የጨከነና እፍረትን የፈሩ (ሊዋጉ) ከራስ የማነ ክርስቶስና ከአቤተጉን ወልደ ክርስቶስ ጋራ ወረዱ።

ንጉሡም ከአቀበቱ ወደታች ወርዶ ድንኳን አስተከለ። ጦርነት ለመጀመር ድብ አንበሳ (ከበሮ) ተመታ፤ ንስር ቃናም (እምቢልታ) ተነፋ።

ጋሎች ደግሞ የጭፍራ ፈረሰኛ ከጥቂት እግረኞች ጋራ ለብቻው፥ ቍጥር የሌለው የእግር ጭፍራ ለብቻው ሆኖ ትልቅ ተጋድሎ ተጋደሉ። አንድ ጊዜ ፈረሰኛውን ጭፍራ የንጉሡ ሠራዊት ያባርሯቸዋል፤ አንድ ጊዜ ጋሎቹ ያባርሯቸዋል። በዚህ ዓይነት ጦርነት ለታወቀ ሰዓት (ለተወሰነ ጊዜ) ዋሉ።

በጭፍራ ያሉት ጋሎች ከአቀበቱ ላይ ያሉትን ብዙዎቹን ፈረሶች ወደኋላ ሲያፈገፍጉና በነፋስ ኃይል እንደሚወዛወዝ መቃ ሲርመሰመሱ ሲያዩዋቸው ጋሎቹ በሞላ ተነሡ። የንጉሡ ሠራዊት ሊቋቋማቸው አልቻለም፤ ከሩቅ የቆሙት ቀድመው ሸሹ። በዚያን ጊዜ ድል የጋሎች፥ ሽንፈት የንጉሡ ሆነ።

በእነዚህ ጋሎች እጅ ብዙ መኳንንት ተገደሉ። እነሱም እኒህ ናቸው፤ አቤተጉን ወልደ ክርስቶስ፥ አስጓ (የሹመት ስም ነው) ልሳነ ክርስቶስ፥ የአቤተጉን ሣህሉ ልጅ ልሳነ ክርስቶስ፥ የሺፈው ተክለ ሥሉስ ልጅ እስክንድር፥ አምባራስ (ባላምባራስ) ፍቅሮ፥ የወገራ ሹም ዘኢየሱስ፥ የዝፋን ቤቱ ሹም ለባሲ፥ በንጉሡ እግር ስር ያደገው ትንሹ የማኖ፥ ከአርባብ (የሠራዊት ስም ነው) ሼቶ፥ መለክ ሐራ (ሹመት ነው) ዕንቆ፥ ከቀሩባንም ሌሎችም ብዙዎች። ከንጉሡ ሠራዊት ፈረሰኞችና እግረኞች በዚህ ዕለት የሞቱ ቍጥር የላቸውም።

ይህ ሽንፈት የሆነው በታኅሣሥ 19 ቀን በቅዱስ ገብርኤል ዕለተ በዐል ነው። በዚያን ጊዜ ከሞተው ሰው ብዛት የተነሣ በንጉሡ ሰፈር ሐዘን የሌለበት ቤት አልነበረም።

ንጉሡም ድል የጋሎች ከሆነ በኋላ ወደ ዳባት መንገድ ሄደ። በማግስቱ ከዳባት አልፎ ድባና ከምትባል ኮረብታ ላይ ሰፈረ። ከዚያም ወደ ማኅደረ ማርያም አለፈና ሰንበትን በዚያ ዋለ።

ጐጥም ነጋሽ ክፍሌ ኃይላት ከሚባሉት ወታደሮች፥ ከብዙ ፈረሰኞች እና እግረኞች ጋራ ሆኖ እዚያ መጣ። ንጉሡ ደግሞ እዚች ማኅደረ ማርያም እያለ ለዩልዮስ -- በዚያን ጊዜ በምድረ ጉማን ሳለ -- የመልእክት ደብዳቤ ላከ። የንጉሡ የመልክቱ ይዞታ የማሸነፍንና የመሸነፍን ሁኔታ ይናገርና እንዲረዳው ቶሌ እንዲደርስ ያዛል።

ንጉሡ ይኸንን መልእክት ከላከ በኋላ ከማኅደረ ማርያም ተነሥቶ የጉዞ መንገድ ሄደና ኾድ ገበያ ከምትባል ምድር አደረ። ከዚያም ወደቃሮዳ አለፈ። ከቃሮዳ ተነሥቶ በቆጋ እና በአምባ ማርያም ማህል ማሽሉት ከምትባል ምድር ሰፈረ። እዚያ (ስሙን) ሲያነሡት ስግደት የሚገባውን የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል አከበረ።

ንጉሡ ከልደት በዐል በኋላ በወይና ደግዓ መንገድ ወደ ደንቀዝ ወጣ። ከጋሎች ጋራ እንደገና ለመዋጋት (አስቦ) የሰዎቹን ከተበተኑበት መሰባሰብና የሠራዊቱን ከሩቅና ከቅርብ መምጣት ይጠብቅ ነበረ።

ጋሎች ደግሞ በዚያን ጊዜ ከዚያ ከውቅሮ ወደ ሐሙስ ወንዝ ወረዱ። ከዚያ በጭፍራ መጥተው የእንፍራዝን አገሮች ሁሉንም አጠፏቸው፥ አበላሿቸው። እስከ ጎረባ እና እስከ ጭኽራ ድረስ ማረኩ። የንጉሡንም የቆጋውን መዲና አቃጠሉትና ወደ ሐሙስ ወንዝ ተመለሱ።

ጸሐፊው አልነገረንም እንጂ የነዚህ መኳንንትና የብዙው ሕዝብ ችብቸቦ በኦሮሞዎቹ ሰፈር ቦታ ጠቦት ይሆናል።

አፄ ሱስንዮስ አፄ ሠርፀ ድንግል ለእናርያ ሰዎች እንዳደረገው፥ ኦሮሞዎችን ክርስትና አስነሥቶ ከክርስቲያኑ ሕዝብ ጋራ አንድ ሊያደርጋቸው ሞክሯል። በሱ ምክርና ትእዛዝ ወረኃዎች በሞላ "የአባቶቻቸውን የጋላ ልማድ" ትተው እንደ ተጠመቁ አዛዥ ጢኖ እንዲህ ሲሉ ከሌላ ቦታ ነግረውናል[65]፤

*ወበውእቱ ወርኃ ክረምት አዘዘሙ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከመ እግዚእ አዛዚ ወሐዋርያ ሰባኪ ወተናገሮሙ ለጋላ ዘውእቶሙ ወረኃኅ በአሰናዎ ሀብት ሰማያዊ ወምድራዊ። ወይቤሎሙ እመኑ በክርስቶስ ወተጠመቁ በስሙ ከመ ትኩኑ ዕሩያነ ምስሌነ በክብር አመ ትንሣኤ ሙታን ወኅድጉ ልማደ አበዊክሙ ጋላ*

65. እዚያው ገ. 214-5። ጥቅሱ እንደሚያመለክተው ያልተገዘረ አባት የሚወልደው ልጅ እንደ ጉድ ይታይ ነበር። ባህሉ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ይከበር እንደነበረ ብዙዎች የኦሮሞ ባህል ተመራማሪዎች መዝግበውታል። ናይጄሪያ ውስጥ መንታዎች ሲወለዱ ይጥሏቸው እንደነበረ ማለት ነው። ኦሮሞዎች የሚገዘሩት በእድሜ ከገፉ በኋላ ስለሆነ ጎልማሶቹን ገሳጭ "ጎርሳዎች" ባይኖርባቸው እስኪገዘሩ ድረስ የማይፈለግ ብዙ ልጅ ይወለድ ነበር።

*ዘኢይሰነአው ምስለ ኣሚን በክርስቶስ እግዚኦ ሕያዋን ወሙታን:: ወይቤሉ ወረነሻ ኦሆ ለይኩን በስመ ኣዘዝከነ እግዚእነ ንጉሥ::*

*እስመ ልማዶሙ ለጋላ ኮኑ ይሰምይዎ ለሰማይ እግዚኣብሔርሃ ኣምላኮሙ ወውእቱ ፈጣሪሆሙ ዘፈቀደ ይቀትል ወዘፈቀደ የሐዩ:: ወኮሉ ሥልጣናተ ወዕዘዘ ይሁብዎ ሎቱ::*

*ዓዲ ይትኣመንዎ ለፀ ብእሲ እምኔሆሙ ዘስሙ ኣባ ሙዳ በስመ ይትኣምንዎ ኣይሁድ ለሙሴ ወተንበላት ለመሐመድ ወየሐውሩ ኀቤሁ እምርሑቅ ሀገር ወይትባረኩ እምኔሁ በበረከተ መዊእ ወበበረከተ ሰለባ:: ወይተፍእ ሎሙ ምራቆ በክርቤ:: እሙንቲኒ ቄጺሮሙ ይጸውርዎ በክርቤ ክመ ይኩኖሙ ተሰፋ ለዕለተ ፀብእ ምስለ ኮሉ ዘይፃብእዎ::*

*ዓዲ ኮሉ ጋላ በበ ነገዶሙ ፮ ኣንጋድ እሙንቱ፤ ወይሠየሙ በበ ዕብሬቶሙ በበ ፮ ዓመት:: ወእለ ተሠይሙ ወእለ ኮነት ዕብሬቶሙ ይሰመዩ ሉባ:: እስከ ይበጽሖሙ ዝንቱ ሚመት ዘውእቱ ሉብነት ኢይትገዘሩ ነፍሰቶሙ:: ወለእመኒ ወለዱ ተባዕተ ኣው ኣንስተ ኢያልህቅዎሙ ክመ ሥርዓተ ወላድያን ኣላ ይገድፍዎሙ ኣፍኣ ...::*

*ዓዲ ለእመ ኢቀተሉ ሰብኣ በመዋዕለ ሚመቶሙ ኢይትላጸዩ ሥዕርተ ርእሶሙ፤ ወኢያወፅኡ ጉቱ ለትእምርተ ቀቲሎቶሙ ሰብኣ ኣላ ይነብሩ ትኩዛኒሆሙ እንዘ ይበክዩ ወትረ ክመ ዘተፈትሐ ቦቱ ፍትሐ ሞቱ::*

*ወዘንተ ኮሉ ልማዳተ ጋላ ... ኣኀደጎሙ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ:: ወኣዘዘ ያጥምቅዎሙ በስመ ኣብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ወተጠምቁ ኮሉ ወረነሻ ወተመጠዉ ምሥጢረ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ:: ወኮኑ ኣሐደ መርዔተ ለኣሐዱ ኖላዊ ምስለ ኮሎሙ ክርስቲያን:: ወረነሻሰ ፩ ነገድ እሙንቱ እምነ ፯ ኣንጋደ በርቱማ::*

❖

በነዚያ የክረምት ወራት ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ወረነሻ የሚባሉትን ጋሎች እንደ ገዢ ጌታና እንደ ሰባኪ ሐዋርያ አዘዛቸው:: ሰማያዊና ምድራዊ ሀብት በሚሰጥ ተስፋ አነጋገራቸው:: (እንዲህም) አላቸው፤ "ሙታን በሚነሡበት ጊዜ በክብር ከኛ ጋራ እኩል እንድትሆኑ በክርስቶስ እመኑና በስሙ ተጠመቁ:: የሕያዋንና የሙታን ጌታ ከሆነው ከክርስቶስ እምነት ጋራ የማይስማማውን የአባቶቻችሁን የጋላ ልማድ ተዉ::" ወረነሻዎች "እሺ፥ ንጉሥ ጌታችን እንዳዘዘከን ይሁን" አሉ::

(ይህ የሆነበት) ምክንያት፥ ጋሎች ሰማይን አምላካቸውና ፈጣሪያቸው፥ የፈለገውን የሚገድል፥ የፈለገውን የሚያኖር እግዚአብሔር ይሉታል፤ ሥልጣኖችንና ገዥነትን ይሰጡታል።

ደግሞ፥ ከማህላቸው አባ ሙዳ የሚሉትን አንዱን ወንድ አይሁድ ሙሴን፥ እስላሞች መሐመድን እንደሚተማመኑበት ይተማመኑበታል። ከሩቅ አገር ድረስ ወደእሱ እየሄዱ በእሱ የማሸነፊያ ቡራኬና የመዝረፊያ ቡራኬ ይባረካሉ። ምራቁን በድኝ ላይ ይተፋላቸዋል፤ እነሱም ከሚወጉት ዘንድ ሁሉ የውጊያ ዕለት ተስፋ እንዲሆናቸው (ምራቁን) በድኝ ቋጥረው ይይዙታል።

ደግሞ ጋሎች ሁሉ በየነገዳቸው ሁነው አምስት መደቦች ናቸው። (አምስቱ መደቦች) በየተራቸው በየስምንት ዓመት ይሾማሉ። የተሾሙት ባለተራዎቹ ሉባ ይባላሉ። ይኸ ሹመት፥ ማለት ሉብነት፥ እስኪደርሳቸው ድረስ እስኪታቸውን አይገዘሩም፤ ወንድም ሆነ ሴት (ልጅ) ሲወልዱ (ልጆቹን) ... እደጅ ይጥሏቸዋል እንጂ እንደወላጆች ሥርዓት አያሳድጓቸውም።

ደግሞ በሹመታቸው ዘመን ሰው ካልገደሉ፥ የራሳቸውን ጠጉር አይላጩም። የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት (ሰው) ዘወትር እያለቀሱ በሐዘን ላይ ይኖራሉ እንጂ፥ ሰው ለመግደላቸውም ምልክት (የሚሆነውን) ቁንጮ አያወጡም።

... እነዚህን የጋላ ልማዶች ሁሉ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ አስተዋቸው። በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቋቸው አዘዘ። ወረነሻዎች ሁሉም ተጠመቁ። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የሥጋውንና የደሙን ምስጢር ተቀበሉ (ቈረቡ)። ከክርስቲያኖቹ ሁሉ ጋራ ያንድ እረኛ አንድ መንጋ ሆኑ። ወረነሻዎች ከሰባቱ የበርቱማ ነገዶች አንዱ ነገድ ናቸው።

ከ1713 እስከ 1723 ዓ. ም. ከገዛው ከአፄ በካፋ ታሪክ የተወሰደውን ስለማስፈር የሚናገረውን እንመልከት፤[66]

*ወአመ ሖረ አቡሁ ኢያሱ ምድረ ጊቤ ወእናርያ አትለም ድኅሬሁ እንዘ ያለብሶ ግስላ ወያጸውሮ ረምኃ። ወኢሐወጸ ፍርሃት እንዘ ወልደ ፲ዓመት...።*

*ስምዑኬ አዓቃብያነ መንግሥት ዘእነግረክሙ አነ ጸሐፌ ዝንቱ ታሪክ፤ እስመ ኮንኩ እተልም ለንጉሥ አቡሁ በምድረ ጊቤ። ወአመ ግዕዘ ንጉሥ እምነ ብሔር እንተ ትሰመይ ቱሉ ቁባ ሉባ ረከበኒ ፅጋላ ወተዛውዓኒ ብዙኃ ነገረ፤ ወይቤለኒ አርእየኒ እስኩ*

66. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyāsu I et Bakāffā,* part II, p. 272-3.

*ወልደ ንጉሥ ዘይሰመይ በካፋ:: ወኢርአይክም:: ወካዕበ በሣልስት ዕለት ረከበኒ ዝኩ ጋላ ወይቤለኒ፥ አእምር አንተ ብእሲ ናሁ ዝንቱ ሕፃን ዘሰመ በካፋ ይነግሥ ፅኑዓ መንግሥቱ፤ ወይቀንዮሙ ለሜጫ ወለቱለማ ኀቡረ:: ወእቤሎ በምንት ተአምር እንዘ አረማዊ አንተ:: ወይቤለኒ በትእምርተ አቡየ አአምር::*

❖

**አባቱ ኢያሱ (1674-98) ወደ ጊቤ እና ወደ እናርያ የሄደ ጊዜ (በካፋን) የግስላ (ለምድ) አልብሶት ጦር አሲዞት ከኋላው አስከትሎት ነበረ:: የዓሥር ዓመት ልጅ ሆኖ ሳለ ፍርሃት አልጐበኘውም...::**

**የመንግሥት ጠባቂዎች (ባለሥልጣኖች) ሆይ፥ እኔ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ (ሲኖዳ) የምነግራችሁን ስሙ፤ ምክንያቱም አባቱን ንጉሡን በምድረ ጊቤ ተከትየው ነበር:: ንጉሡ ቱሉ ቁባ ሉባ በምትባል ሀገር ሲጓዝ አንድ ጋላ አግኝቶኝ ብዙ ነገር አጫወተኝ:: "እስቲ በካፋ የሚባለውን የንጉሡን ልጅ አሳየኝ" አለኝ፤ አሳየሁት:: ይኸው ጋላ እንደገና በሶስተኛው ቀን አገኘኝና፥ "አንተ ሰው፥ ዕወቅ፤ እነሆ ይኸ ስሙ በካፋ የሆነ ሕፃን በተደላደለ መንግሥት ላይ ይነግሣል፤ ሜጫንና ቱለማንም አስተባብሮ ይገዛቸዋል" አለኝ:: "አንተ አረመኔ ሆነህ ሳለ እንዴት ታውቃለህ?" አልኩት:: "ካባቴ (በተማርኩት) ምልክት አውቃለሁ" አለኝ::**

**አባቱ ቀዳማዊ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) ከጎንደር ተነሥቶ ጊቤ ድረስ የሄደው ኦሮሞዎቹን ለማስፈርና ሰላም ለመፍጠር ነበረ፤ ግን የሆነውን አሁንም ከዚሁ ንጉሥ ከአፄ በካፋ (1713-1723) ታሪክ ወስደን እንመልከት፤**

**(1)** *እምይእዜሰ እነግረክሙ ብዝኃ መዓቱ ለዝንቱ ንጉሥ በካፋ፥ መፍርህ ወመደንግጽ፥ ወብዝኃ ምሕረቱ ዘኮነ ላዕለ ጀዊ እስመ በጥቃ መዓቱ ሀሎ ብዝኃ ምሕረቱ::*

*ወአመ ኮነ ዓመተ መንግሥቱ ፭ዓመተ ወ፰ዓውራኁ መጽአ ቦቱ ዜና ለንጉሥ ከመ አጽረረ ጠለታ ጃዊ ዘአምጽአ አቡሁ እምድረ ጊቤ ወአንበሮ በጽንፈ ዓባዊ::*

*አሜሃ አዘዞ ለቢትወደድ ኤራቅሊስ ከመ ይዕቀብ ትዕይንተ እስመ ህየ ሀሎ አክሊለ መንግሥቱ፤ ወለበጅሮንድ ማሞ አማዕቀቦ ኮሎ ንዋየ ቤቱ እስመ ምዕመን ውእቱ ወተወክፈ ስደተ በእንቲአሁ ...::*

*ወፈነወ ሎቱ ለደጃዝማች ማሞ ዘዳሞት መጠነ ፫ንፍጥ፤ ወአዘዘ ንጉሥ በቃለ ዓዋዲ ከመ ይትልዎ ኮሉ ሠራዊት እመኒ ዘመድ ወዘመደ ዘመድ።*

*ወአመ ፲ወ፭ለጥር በዕለተ ሐሙስ በዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ ተንሥአ ንጉሥ በካፋ እምነ ጐንደር ወኀደረ በወይና ዓረብ ...።*

*ወነበረ ንጉሥ በአሪንጎ ፲ወ፮ዕለተ። ወፈነወ ላእከ ኀቤሁ ደጅ አዝማች ማሞ ዘዳሞት ከመ ፀብዖ ወአሕለቆ ለጠለታ ጃዊ ...።*

❖

(1) አሁን ግን በዚህ በጃዊ ላይ የተፈጸመውን የዚህን አስፈሪና አስደንጋጭ ንጉሥ የበካፋን የቁጣውን ብዛት እነግራችኋለሁ፤ ምክንያቱም በቁጣው አጠገብ የምሕረቱ ብዛት አለና።

አባቱ ከምድረ ጊቤ አምጥቶ በዓባይ ዳር ያሰፈረው ጃዊ ጠለታ በጠላትነት እንደተነሣ በመንግሥቱ ዘመን በ፩ ዓመት ከ፰ ወር ዜና ደረሰው።

በዚያን ጊዜ ቢትወደድ ኤራቅሊስን ከተማ እንዲጠብቅ አዘዘው፤ ምክንያቱም የመንግሥቱ ዘውድ እዚያ ነው። በጅሮንድ ማሞን የቤቱን ንብረት በሞላ አስጠበቀው። ምክንያቱም (በጅሮንድ ማሞ) ታማኝ ነው፤ ለሱ ሲልም ስደት ደርሶበታል።

ለዳሞቱ ደጃዝማች ማሞ አምሳ ያህል ነፍጥ ላከለት። ሠራዊቱ ሁሉ ዘመድም ሆነ የዘመድ ዘመድም እንዲከተለው ንጉሡ በዐዋጅ ትእዛዝ ሰጠ።

ጥር 15 ቀን ሐሙስ ዕለት በወንጌላዊው ሉቃስ ዘመን ንጉሥ በካፋ (ለዘመቻ) ጐንደርን ለቅቆ ወይና ዓረብ አደረ።

ንጉሡ አሪንጎ ላይ ዓሥራ ስድስት ቀን ተቀመጠ። (እዚያ ሳለ) የዳሞቱ ደጃዝማች ማሞ ጃዊ ጠለታን እንደወጋውና እንደፈጀው ወደሱ መላክተኛ ላከ[67]።

(2) *ወበቀዳሚት ሰንበት በጽሐ ዋንካ። ወሀየ መጽኡ ጎዳጣን እምነ ጃዊ እለ ይብልዎሙ ቍዕር፤ ወይቤልዎ ለንጉሥ በቃለ ጃዊ፦ መሐረነ ኦንጉሥ እስመ ንሕነ አግብርቲከ ወአግብርተ አቡከ። እመኒ አበስነ እግዚኦ እስመ ለነ አበሳ ወለከ ምሕረት።*

*ወይቤሎሙ ንጉሥ ሑሩኬ መሐርኩክሙ። ባሕቱ አምጽእዎሙ ለሮጌ ወለነፍጫ እምዬ። እመሰ ኢ፲ምጻእክሙ ትበልዑ ኮሰሐክሙ ወትሰትዩ ስንተክሙ። ወኢ፲መስጠኒ ፩እስከ*

67. እዚያው ገ. 275-6።

*ዘያስተዓዝብ ዲበ ኦረፍት፣ ወእሁብ ሥጋክሙ ለአዕዋፈ ሰማይ ለእመ ኢመጻእክሙ እስከ ዕለተ ረቡዕ ሀበ ሀሎኩ አነ።*

❖

(2) ቅዳሜ ዋንካ ደረሰ። እዚያ (እያለ) ከጃዊ ውስጥ ቀኦር የሚሏቸው ጥቂቶች መጡና ለንጉሡ በጃዊ ቋንቋ (በጃዊኛ እንዲህ) አሉት፥ "ንጉሥ ሆይ፥ ማረን፣ ምክንያቱም እኛ አሽከሮችህ የአባትህም አሽከሮች ነን። ጌታ ሆይ፥ ብናጠፋ ጥፋት የኛ፥ ምሕረት ያንተ ነው።"

ንጉሡ (እንዲህ) አላቸው፥ "በሉ ሂዱ ምሬያችኋለሁ። ግን ሮጌን እና ነጮን ከእምዬ አምጧቸው። ካላመጣችሁ ኩሳችሁን ትበላላችሁ፥ ሽንታችሁን ትጠጣላችሁ። እዚህ አለሁበት ድረስ እስከ ረቡዕ ዕለት ድረስ ያልመጣችሁ እንደሆነ ግድግዳ ተጠግቶ የሚሸና (ወንድ) ሁሉ አያመልጠኝም። ሥጋውን ለሰማይ ወፎች እሰጠዋለሁ[68]።

## (10) በአንድ ሀገር ሶስት መንግሥት

ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ታሪክ እስኪታወቁ ድረስ በኢትዮጵያ ላይ ሁለት መንግሥት ተቋቁሞ ነበረ--አንዱ የሐፄ ሌላው የእጨጌ። ይኸ ታሪክ በይፋ የተቋቋመው ይኩኖ አምላክና ካህናቱ ተባብረው የዛጌዎችን መንግሥት በገለበጡ ጊዜ በ1263 ዓ. ም. ነው ቢባልም፥ ክርስትና ኢትዮጵያ ውስጥ ስር ከሰደደበት ጊዜ ጀምሮ የሐፄው ቤተ መንግሥትና የእጨጌው የሆነው ቤተ ክህነት እንደ ሥጋና እንደ ነፍስ አንድ አካል አንድ አምሳል ሁነው ይገዙ ነበር። በሁለቱ መንግሥታት መካከል ጎብረት እንጂ አልፎ አልፎ ካልሆነ የጎላ ግጭት አለመኖሩ ለሕዝቡ ትልቅ እፎይታ ነበር።

ኦሮሞዎች ሲመጡ ባሉት ሁለቱ (የተባበሩት) መንግሥቶች ላይ "ሕዝባዊ የሉባጌ" መንግሥት አቋቋሙ።

እንደሚመስለው፥ ኦሮሞዎች ያሰቡት እንደጳጳሱ ከሥነ ልቡናዊ የማያልፍ ሥልጣን ባለው አባ ሙዳ እና በሉባ ትውልድ አዝማች ስር ሆነው እያንዳንዱ ጎሳ በያዘው መሬት ላይ በዘላንነት (ወደኋላ ላይ በግብርናም) በራሱ ንዑስ መሪ የራሱን አስተዳደር ዘርግቶ ለመኖር ነበረ። ታሪክ ጸሐፊዎቹም ይኸንን ዐውቀውና ተቀብለው፥ የታሪክ ድርጊቶችን ዘመን ሲያመለክቱ በዚያን ጊዜ በሚገዛው አዜ ዘመን እንደሚቈጥሩ

68. እዚያው ገ. 278-9።

በኦሮሞዎቹ ሉባ ዘመንም ይቈጥሩ ነበረ። ለምሳሌ ከጸሐፊዎቹ አንዱ ስለ ግራኝ ዐመፅ አጀማመር መጻፍ ሲጀምር እንዲህ ይላል[69]፤

> እምአመ ሚመቱ ላሜልባሕ በ፱ ዓመት ተዋብኡ ሐዌ ወናግ ሰገድ ምስለ ግራኝ በሽምብራ ኩሬ።

❖

> በሜልባሕ በ9ነኛው የሹመት (ዘመን) አፄ ወናግ ሰገድ ከግራኝ ጋራ ሽምብራ ኩሬ ላይ ተዋጉ።

ስለአፄ ሠርፀ ድንግል የተጻፈ አንድ የዜና መዋዕል ቅጂ እንዲህ ይላል[70]፤

> ወበ፴ወ፪ አመት ወረደ እናርያ። ወሞተ ኬስትሮ። ወረሰዮሙ ንጉሥ ለሰብአ እናርያ ክርስቲያን።
>
> ወበ፴ወ፫ አመት ወጽአ ቤገምድር ለተዋብዖተ ጋላ በዘመነ ሚመቱ ለፈዳታ ዘሰመይዎ ቡራቃ።

❖

> (ሠርፀ ድንግል በነገሠ) በ፴ወ፪ ዓመት ወደ እናርያ ወረደ። ኬስትሮ ሞተ። ንጉሡ የእናርያን ሰዎች ክርስቲያን አደረጋቸው።
>
> በ፴ወ፫ ዓመት፥ ቡራቃ በሚሉት በፈዳታ የሹመት ዘመን፥ ጋላን ለመውጋት ወደ ቤገምድር ወጣ።

ብዙ ርቀን ሳንሄድ ራሱን ዜናሁ ለጋሳን በጥሞና ብንመለከተው ደራሲው ዘመኑን በሉባዎቹ የግዛት ዘመን እንደሚቈጥሩ በቂ ምልክት እናገኝበታለን። ለምሳሌ፥ እነዚህን እንመልከት፦

> ከወንድሞቻቸው ተለዩና ቦረን "አምቢሳ" በሚለው -- በርቱማ "ሮባሌ" በሚለው -- ሉባ ዘመን ኅብረት ፈጥረው "አፍሬ" ተባሉ (ክፍል ፩)።
>
> ቢርመጂ በሚባለው ሉባ ዘመን ኅብረት ፈጥረው "ሰደቻ" ተባሉ (ክፍል ፩)።

---

69. ዜና መዋዕል፥ EMML 7109, f. 58a. እርግጥ በኋላ የመጣ ቀጂ አሳስቷል፥ "ለ" መስተዋድድ መሆኗን ልብ ባለማለቱ ሹሙ "ላሜልባሕ" መስሎት "ለሜልባሕ" ("የሜልባሕ") ሊል የሚገባውን "ላሜልባሕ" ብሎ አበላሽቶታል። ሁለተኛም፥ አንድ ሉባ ከስምንት ዓመት በላይ አያስተዳድርም። ስለዚህ ደራሲው ያለው እንዲህ ይመስለኛል፥ "አፄ ወናግ ሰገድ በነገሠ በ19ነኛው ዓመቱ፥ በሜልባሕ የሹመት ዘመን፥ ከግራኝ ጋራ ሽምብራ ኩሬ ላይ ተዋጋ።"

70. Ignazio Guidi, "Di due frammenti relativi alla storia di Abissinia", pp. 590-1.

ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ የቢፎሌ ልጅ የሙልአታ ሹመት ሰባት ዓመት ሆኖታል (ክፍል ፲፰)።

ቤኪንግሃምና ሃንቲንግፎርድ የሚባሉ ሁለት እንግሊዛውያን ምንጮቹን መርምረው የሉባዎቹን የግዛት ዘመን በዓመተ እግዚእ እንደሚቀጥለው ገምተውታል[71]፤

1522-1530: ሜልባሕ፥ ገላን ወንዝን ተሻገረ። (ግራኝ በዚህ ዘመን ወረረ።)
1530-1538: ሙደና፥ ዋቢ ሸበሊን ተሻግሮ ባሌ ገባ። (የግራኝ ወረራ ቀጠለ።)
1538-1546: ኪሎሌ፥ የደዋሮን ቆላዎች ወረረ። (የግራኝ ወረራ አከተመ።)
1546-1554: ቢፎሌ፥ ደዋሮን አጠፋ።
1554-1562: ምስሌ፥ ጊቤን መቄጣጠር ጀመረ።
1562-1570: ሐርሙፋ፥ በጥረ አሞራን አጠፋ።
1570-1578: ሮባሌ፥ ሸዋን አጠፋ።
1578-1586: ቢርመጂ፥ ከጣና ባሕር እስከ ዳሞት መጣ።
1586-1594: ሙልአታ፥ ጎጃምን ወረረ።

የዘመኑ ነገሥታት ያልወደዱት ኦሮሞዎች ለራሳቸው በሚሾሙት የሉባ ትውልድና አባ ሙዳ የመንፈሳዊ በላይነት መተዳደራቸውን አይደለም፤ ኢትዮጵያ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ነገዶችና የእስላም ግዛቶችም አገር ነበረች። ከነገሥታቱ ጋራ ግጭት የሚፈጠረው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ሌሎች ነገዶች ሲያመጯቸው አንገብርም እንደሚሉት አንገብርም ሲሉ፥ ሁለተኛም መንግሥት የራሱ አድርጎ የሚጠብቀውን "ሀገረ መንግሥት" የሚባለውን ክፍለ ኢትዮጵያና ሌላውን (መንግሥት የሚዘርፈውን) ሁለቱንም እኛ እንዝረፍ ሲሉ ነበረ።

በዚያ ላይ አንድ የከፋው ባለሥልጣን ከመንግሥት ሲጣላ ኦሮሞዎችን "የከፋው ዋሻ፥ ያመፀኛ መሸሻ" ያደርጋቸዋል። ከብዙ ማስረጃዎች ውስጥ ይህንን ከአድያም ሰገድ ኢያሱ (1674-1698) ታሪክ የምጠቅሰውን እንመልከት[72]፤

*ወእምድኅረ በዓለ ፋሲካ ዓመፀ ወሌ ዘእምነገደ መጫ፥ ወበአ ውስተ ብሔረ ጋላ ኃይጎ ስመ ክርስትናሁ ጊዜ ርስእናሁ እስመ ክረዮ ጽጋብ እመንገለ ብዙኃ ጉልት። ወኮነ ዕፁብ ዝንቱ ነገር ውስተ ኵሉ ዓለም።*

71. Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, pp. lxxiv-lxxv and 205-212.
72. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyāsu I et Bakāffā*, II p. 96.

*ወዓዲ ዘየዓቢ እምዝ ዕፁብሰ ዕፁብ ውእቱ ወመንክር በዊኦቶሙ ውስተ ሀገረ ጋላ ለመምህረ ጐንጅ ወመምህረ እነጭላላ እንዘ ቆሞሳት ውእቶሙ ወመምህራነ ቤተ ክርስቲያን ወእንዘ አልቦሙ ምክንያተ ነገር ለበዊእ ውስተ ጋላ::*

❖

ከፋሲካ በዓል በኋላ ከመጫ ነገድ የሆነው ወሌ አመፀና ጋላ ሀገር ገባ -- ከጉልቱ ብዛት የተነሣ ጥጋብ ነፍቶታልና በእርጅናው ዘመን የክርስትና ስሙን ትቶ:: ይኸ ነገር በዓለም ውስጥ ሁሉ ጉድ ሆነ::

ደግሞ ከዚህ ጉድስ የሚበልጥ ጉድና አስገራሚ ነገር፥ የጐንጅ መምህርና የእነጭላላ መምህር እጋላ አገር መግባት ነው -- ቆሞሶችና የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሆነው ሳለና እጋላ አገር ለመግባት ምክንያት ሳይኖራቸው::

ይኸም ሁሉ ሆኖ፥ እንዳየነው እነዚህ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጎሳዎች ዛሬ ለኛ እንደሚመስለን አንድነት ኖሯቸው እንደሆነ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ይሆናል እንጂ ከገቡ በኋላስ አንድነት አይታይባቸውም:: ሌሎቹን ኦሮሞ ያልሆኑትን ጎሳዎች እንደሚዘርፏቸው አንዱ የኦሮሞ ጎሳ ሌላውን ይዘርፈዋል:: "ሁላችሁም ያው ጋላ ናችሁ" የሚሏቸው ሌሎች ናቸው እንጂ እነሱ ራሳቸውን እንዳንድ ሕዝብ አያዩም ነበር:: እርግጥ አንዳንድ ጊዜ የመንግሥቱን ግዛትም ሆነ ሌላውን የኦሮሞ/ጋላ ጎሳ ለመውጋት ሲፈልጉ ይረዳዳሉ፤ ግን ዘላቂ አንድነት አይፈጥሩም፤ አንድነቱን የሚፈልጉትም አይመስልም::

"ሉባጌው" የኦሮሞውንም ሆነ የሌሎቹን ነገዶች እንደተለያዩ የኦሮሞ ጎሳዎች እየቈጠረ ኢትዮጵያን በእኩልነት ባህላቸው ቢያስተዳደር ኖሮ ሀገሪቱ ከብዙ ውዝግብ ከመዳን አልፋ ሕዝቡ በውስጥ ነፃነት ብዙ ይራመድ፥ ዴሞክራሲውም ኢትዮጵያዊ ይሆን ነበር:: ግን ይህ በሰብአ ትካትነት የሚኖር ሕዝብ ሥልጣኔዋ ከፍተኛ ደረጃ ለደረሰ ሀገር "ይኸንን ባደረገላት" ብሎ መቆጨት አይታሰብም:: እንኳን ይህን ሊያደርጉ ራሳቸው ተበታትነው የሀገሪቷን መንግሥት ብትንትኑን አወጡት:: ያ እንኳ ባይሆን፥ ዛሬ ንጉሣዊ አገዛዝ ከቀረ፥ መሪው "**ፕሬዚዳንት**" ከሚባል **አባ ሙዳ** ቢባል እንዴት ባማረብን::

ስለ መንግሥቱ አንድነት ከሆነ ግን ከግራኝ ይልቅ ኦሮሞዎች ጐድተውታል፤ ግራኝ አጠቃሎ በአንድ ሃይማኖት (በእስልምና) ሊገዛት ያሰባትን ሀገር እነሱ በስፍር ቁጥር አልባ ጎሳቸው ልክ ከተፏት:: በነሱ ምክንያት "ሀገረ መንግሥት" የሚባለው ክፍል ሳይቀር በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ስር መተዳደር አልቻለም:: ለራሳቸው አንድነትን፥ ለሀገሪቱም

አንድ መንግሥትን ለማምጣት የልጅ ልጆቻቸው ጎንደር ላይ መሠረቱን መጣል፥ ሸዋ ላይ ቤቱን መሥራት ነበረባቸው። ባጭሩም ቢሆን ታሪኩን እንቃኘው።

Codex vindobonensis Palatinus, Aeth. 4, f. 1b.

**እስካሁን ከተገኙት የዜናሁ ለጋላ ቅጅዎች አንዱ።።**

(**ገጽ** 63 **ላይ ተቀድቷል።።**)

# ምዕራፍ ፬

## ትንሣኤ መንግሥት

**ምኒልክ ተወልዶ እልም ባያልም፥**
**ጎበና ፎክሮ ያን ባይተረጉም፥**
**ኢትዮጵያ እምትባል የሰው ልጅ እናት፥**
**በዛሬው ዓለም ውስጥ ቦታም ባልኖራት።**

**የኦሮሞችን ታሪክ የጻፉ አቶ ዓፅመ ጊዮርጊስ (ዓፅሜ/ዓጥሜ)።**

(ከ *Da Zeila alle Frontiere del Caffa, Viaggi di Antonio Cecchi,* 1886)

ለኦሮሞዎቹ አንድነትን ለሀገሪቱም አንድ መንግሥትን ለማምጣት የኦሮሞዎችና የሌሎች ኢትዮጵያውያን የልጅ ልጆች ጎንደር ላይ መሠረቱን መጣል፥ ሸዋ ላይ ቤቱን መሥራት ነበረባቸው::

ኢትዮጵያን እነዚህ ጎብረት አልባ ኦሮሞዎች ሲቆጣጠሯት የማእከላዊ መንግሥት ባለሥልጣኖች መላወስ አልቻሉም ነበረ፥ "*ወሊ ንሱ ኮርማ ታኢ፥ ቡኣፊ ያቢ ደወዱ*" ("ወንዴ ኮርች ሁን፥ ወጪና ወራጁን ከልክል") የሚለውን የሸማግሌዎች ምርቃት እንደ ዓሠርቱ ቃላት ትእዛዝ የሚያከብሩት ይመስል ነበረ:: አቤቶ ነጋሢ ማህል ሸዋን ሰባት ዓመት ከገዛና ሥልጣኑን በሕዝብ ዘንድ ካረጋገጠ በኋላ የማዕርግ ስም ለማስፈቀድ ጎንደር ሄዶ መመለሻውን ኦሮሞዎች ስለዘጉት እዚያው ሞቶ እዚያው ተቀበረ[1]::

ኢትዮጵያን እንደዱሮው ከዳር እስከዳር የሚያስተዳድር መንግሥት ጠፋ:: ሁሉም፥ ኦሮሞዎቹም፥ ክርስቲያኖቹም እስላሞቹም በያዙት ቦታ ጎበዝ እየወጣባቸው ሀገሪቷ የትናንሽ መንግሥታት መጠራቀሚያ ሆነች:: "ሀገረ መንግሥት" የሚባለውም ለስሙ ዘውድና አልጋ ጠባቂ ንጉሥ ጎንደር ላይ ይኑረው እንጂ ባለ ዘውዱ እንኳን ሥልጣን ኖሮት ሊሾም ሊሽር የሚበላው አጥቶ "ለንጉሡ መጽውቱት" የሚባል ለማኝ ሆኖ፥ ጉልበተኞች በጎጃም፥ በጎንደር (በስሜን)፥ በትግሬ፥ በሸዋ ራሳቸውን የቻሉ መንግሥቶች አቋቋሙ:: ኦሮሞዎችም በጊቤ ወንዝ አገሮች የሉባው ዴሞክራሲ ቀርቶ የቄራጭ ፈላጭ መንግሥት ማቋቋም ጀምረው ነበረ::[2]

በዚህ ጊዜ ነው "ብቅል የገደለውን ብቅል ያነሣዋል" እንደሚባለው የጋሎቹና የሲዳማዎቹ (የኦሮሞዎቹና የአማሮቹ) ልጆች ተቀባይነትን ለማግኘት በአቤቶ ያዕቆብ ዐፅም ተንጠላጥለው የኢትዮጵያን መንግሥት "ነበ ዘቀዳሚ መንበሩ" (ከቀድሞው መንበሩ) የመለሱት:: ታሪኩን በአማርኛ ብዙዎች ስለጻፉት እዚህ መድገም አያስፈልግም[3]::

---

1. ጎሩይ ወልደ ሥላሴ (Asfa-Wossen Asserate, *Die Geschichte von Šawā*), p. 38.
2. Huntingford, *The Galla of Ethiopia The Kingdoms of Kafa and Janjero*, London 1955.
3. በዚህ ርእስ ላይ ብዙ ተጽፏል:: ከዚህ በታች ያሉትን በማንበብ መጀመር ይቻላል፥ የብላቴን ጌታ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ* (የፋሺስቶች ወረራ

ለማገናኘት ያህል፥ አፄ ልብነ ድንግል (1500–1537) በግራኝ ጦርነት ከመላ ቤተ ሰቡ ጋራ በሸሸት በነበረበት ጊዜ አንዱ ልጁ አቤቶኑን ያዕቆብ እዚያው እሸዋ ካንድ ቦታ ተደብቆ ቀርቶ ነበረ። የአቤቶ ያዕቆብ አንዱ ልጁ ገራም ፋሲል የሱስንዮስ አባት ነው፥ ሁለተኛው ዘሮቹ ከኦሮሞዎች ጋራ በጦር ሜዳና በጋብቻ ተገናኝተው ሸዋ ላይ መንግሥት ያቋቋሙት ሥግወ ቃል ነው። (ሶስተኛው፥ ተዝካረ ድንግል የአጐቱን የአፄ ሚናስን መንግሥት ሲቀናቀን ተሸንፎ የእቴጌይቱ ዘመዶች ገደል ወረወሩት።)

ከኦሮሞውም ከአማራውም እየተጋቡ፥ ሥግወ ቃል ወይዘሮ ሰንበልትን፥ ወይዘሮ ሰንበልት አቤቶ ኔጋሚን፥ ኔጋሚ ስብስቴን፥ ስብስቴ አብዬን፥ አብዬ አምኃ ኢየሱስን፥ አምኃ ኢየሱስ አስፋ ወሰንን፥ አስፋ ወሰን ወሰን ሰገድን፥ ወሰን ሰገድ ሣህለ ሥላሴን፥ ሣህለ ሥላሴ ኀይለ መለኮትን፥ ኀይለ መለኮት ዳግማዊ ምኒልክን ይወልዳሉ[4]።

የዛሬይቱ የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥት ተመልሶ የተቋቋመው አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሀገሪቱ ድንበር ላይ ከጠላት ጋር ሲዋደቁ በነዚህ ልጆችና በመጨረሻም ምኒልክ ኀይለ መለኮትና ኅበና ዳጨ ነፍጠኞች ትግል ነው።

ትዝታቸው፥

ምኒልክ ተወልዶ እልም ባያልም፥
ኅበና ፎክሮ ያን ባይተረጉም፥
ኢትዮጵያ እምትባል የሰው ልጅ እናት፥
በዛሬው ዓለም ውስጥ ቦታም ባልኖራት።

የሚያሰኝ ነው።

ከአፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ የጠፋን መፈለግ፥ የተናደን መገንባት ተጀመረ። ስለትንሣኤው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ[5]፤

---

ኅትመቱን ያጨናገፈው)፤ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፥ በከፊል፥ Asfa-Wossen Assrate, *Die Geschichte von Šawā*፤ የጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፤ የተክለ ጻድቅ መኮሪያ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፤ እና የባሕሩ ዘውዴ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1884 እስከ 1966*።

4. ለምሳሌ፥ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እኅት ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ "የአድአውን ባላባት ልጅ አቶ ደሞ ቡኔን አግብተው" እንደነበረ አቶ ገብረ ሥላሴ አዳ ያስታውሳሉ፤ *ትዝታ ለመታሰቢያ*፥ ገ. 6–7።

5. ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፥ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፥ ገ. 100።

ከዚህ በኋላ በ፲፰፻፹፬ ዓመተ ምሕረት በዲርማ ደብረ ነጐድጓድን፥ በለገሒዳ አትሮንሰ ማርያምንና ታዕካ ነገሥትን፥ በለገጐራ መካነ ሥላሴን፥ ጥንት በኖራ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት በግራኝ ጊዜ የተቃጠሉትን እያስቆፈሩ ግምቡን አስወጡት። የግምቡም ቁመት ሰባትም ስምንትም ክንድ ሆነ። ነገር ግን ከቀን ብዛት የተነሣ መሬቱ አጥብቆ ውጦታልና እስከ መሠረቱ ለመቆፈር አልተቻለም። ሥራውም ድንጋዩ አራት ማዕዘን የተጸረበ የተቀረጸ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ከዚያውም ብዙ ንዋየ ቅድሳት ወጣ። የወሌም ሰው ይህን ሁሉ ባየ ጊዜ እውነትም የክርስቲያን አገር መሆኑን ተረዳው።

ከዚህ ጥቅስ አራት ነገር እንረዳለን፥ (1) እነዚህ የታወቁ የአማራው አገር ታላላቅ አድባራት በግራኝ ወረራ ጊዜ መቃጠላቸውን (በታሪክም አንብበናል)፥ (2) በኦሮሞዎች ወረራ የቦታዎቹ ስሞች መለወጣቸውን (ዲርማ፥ ለገሒዳ፥ ለገጐራ)፥ (3) "አዲሱ" ትውልድ አዲሶቹን የቦታ ስሞች መቀበሉን፥ (4) ቅርሶች ከመቃብር ለመነሣት ዕድል ማግኘታቸውን።

በሀገርና በመንግሥት መካከል ያለው ልዩነት እንዳይማታ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምኒልክና ጎበና ዳጨ መልሰው ያቋቋሙት ማእከላዊውን መንግሥት እንጂ ሀገሪቷማ ሁል ጊዜም በልጆቿ እጅ ነበረች። የቦታ ስሞችን የለወጡት ራሳቸው ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ ወደኋላ ወደዱሮው እንመልስ ያለ የለም።

የማእከላዊው መንግሥት ትንሣኤ ሸዋ ላይ ይወለድ እንጂ፥ የተፀነሰው ቀደም ብሎ እዚያው እጎንደር ነው። እንደምናየው፥ በጎንደር ዘመነ መንግሥት በኦሮሞዎችና በመንግሥት መካከል ብዙ ጊዜ በጥቅም ምክንያት የረጅም ጊዜ ግጭት ተካሂዷል። ሆኖም ላይ ላዩን "ጋላና ክርስቲያን" ወይም "ኦሮሞና ሲዳማ" የማይገናኙና የማይጣጣሙ ይምሰሉ እንጂ፥ የነፃነቱ አብሮ ኑሮ በማህል ያለውን የዘርና የባህል ልዩነት የሁለት ኩሬን ውሐ የሚገድበውን ግድብ እንደሚያፈርስ ኃይል ቦርቡሮት ውስጥ ውስጡን በባህልም በዘርም ተደበላልቀዋል። አምቻና ጋብቻነቱ እስከ ቤተ መንግሥት ዘልቋል። ኦሮሞዎች እንደነ አዛኝ ሀካኮ በሥርዓቱ ውስጥ ገብተው ሥልጣን ተካፍለዋል። ተጨማሪ ምሳሌ ካስፈለገ እነዚህን ከአፄ ኢያሱ (1676-1698) ታሪክ የቀዳኋቸውን ሁለት ጥቅሶች እንመልከት፥

(1) *ወዳግመ መጽአ ጨዋሂ ዘይብል ወጽአ ጋላ ወፀብአ ለድጎ። ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ዘንተ ነገረ አዘዘ ለጸሐፌ ላሕም ቱሉ ወይቤሎ ሑር ትልዎ ወኢያምስጥከ። ወውእቱኒ ሖረ በሌሊት ወተለዎ ወረከቦ ለጋላ በምድረ ጨ።*

(1) “ጋላ መጥቶ ድንን ወጋው” የሚሉ ትክለኛ ወታደሮች እንደገና መጡ። ይህንን ነገር ንጉሡ ሲሰማ ጸሐፌ ላሕም ቱሉን፥ “ሂድ (ጋሎችን) ተከተላቸው፥ እንዳያመልጡህ” ብሎ አዘዘው። እሱም በሌሊት ሄደና ተከተላቸው፤ ጋሎቹን በምድረ ጨ አገኛቸው[6]።

(2) *ወበውእቱ ወርኀ ሜሞ ለዮሐንስ ሚመተ ጸሐፌ ላህም ዘዳሞት። ወሜሞ ሚመተ ብላቴኖች ጌታ ለጠቢብ ወማዕምር ወለባዌ ፍትሕ ወክቡረ ዘመድ ወነገድ ዘእምነገደ ጋላ ወአድያ ዘውእቱ ባስልዮስ ወልደ ቡናያ ወወልደ እኅቱ ለደጃዝማች ሎፊንስ።*

❖

(2) በዚህ ወር ዮሐንስን የዳሞት ጸሐፌ ላህም ሹመትን ሾመው። ከጋላ ነገድና ከአድያ የሆነውን ጥበበኛውን፥ ዐዋቂውን፥ ፍርድ አስተዋዩን፥ ባለ ተከበሩ ዘመዶች የሆነውን የቡናያን ልጅና የደጃዝማች ሎፊንስ እኅት ልጅ ባስልዮስን የብላቴኖች ጌታ ሹመትን ሾመው[7]።

በዚያን ዘመን የብላቴኖች ጌታ ማዕርግ ከቢትወደድነት ቀጥሎ ነበረ። ግን ጸሐፊው የባስልዮስን ነገድ ባይነግረን የማን ነገድ ይመስለን ነበረ? በስማቸው ምክንያት ኦሮሞዎች መሆናቸውን ሳናውቅ የቀረን ስንቶች ናቸው? የክርስቲያኑ መንግሥት ስንል የኦሮሞዎችና የሌሎቹ ሁሉ ክርስቲያኖች መሆኑን ማስታወስ አለብን።

በደም የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ከተራው ሕዝብ ቤት እስከ ቤተ መንግሥት የሳሳዎችና የነገዶች ግንኙነት ውጤት መሆናችንን የሚያሳየው ያያቶቻችን የጋብቻቸው ታሪክ ያልተጻፈው በኢትዮጵያውያን መካከል ጋብቻ ጉድ ወይም ብርቅ ስላይደለ ነው። የአፄ ምኒልክ ልጅ ወይዘሮ ሸዋረገድ የራስ ጎበና ልጅ የአቶ ወዳጆ ባለቤት እንደነበሩ የተጻፈው የግዥዎች ታሪክ ስለሆነ ነው እንጂ አፄ ምኒልክ አማራ (!) ራስ ጎበና ዳጨ ኦሮሞ ስለሆኑ ያንን እንደ ታሪክ ለመመዝገብ አይደለም። ክቡር ልጅ ሚካኤል እምሩ ራስ ጎበና ዳጨ አያታቸው መሆናቸውን የነገሩን *ኦንድነት* ጋዜጣ ስለጠየቃቸው ነው። ያውም ቢሆን ዘራቸውን ለመቀጠር ሳይሆን ቤተ ሰባቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ትንሣኤ ስላደረገው አስተዋጽኦ ታሪክ ሲያስተምሩን ነው።

በባህልም ረገድ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በነሱና በወረሩት ሕዝብ መካከል ከፍተኛ መደባለቅ ነበረ። ለምሳሌ፥ ክርስቲያኖቹ ስማቸውን “ዘጸ”፥ “ዐስቦ”፥ “ዐምዶ”፥ “መንገዶ”፥ “ተዝካሮ”፥ “ዘሦ”፥ ወዘተ እያሉ በሳብዕ ሲያሳጥሩ እናያለን። የሆነው፥

6. Guidi, *Annales Iohannis I ’Iyāsu I et Bakāffā,* part II, p. 206-7.
7. እዚያው ገ. 170።

ኦሮሞዎች “ጢኖ”፥ “ጥሂቶ”፥ “ሐለብዶ”፥ “በርባዶ”፥ ወዘተ እያሉ ስም የሚያወጡበትን ዘዴ በመውሰድና የራሳቸው በማድረግ ነበረ። በአማርኛ ላይ የሚታየውን የባህላቸውን ጉልሕ ተጽእኖ ትተን ግዕዝን ብንመረምረው የኦሮሞ ባህል ተጠቃሚ ሆኗል። ይሄ የሆነው ኦሮሞዎች የግዕዝ ዓለም ጎረቤቶች ስለሆኑ ሳይሆን፥ እንደ ኦሮሞዎቹ እንደ አዛዥ ጢኖ እና የጎጃምን ታሪክ እንደጻፉልን እንደሠዓሊው እንደ አለቃ ተክሌ የግዕዙ ሥነ ጽሑፍ ባለቤት ስለሆኑ ነው።

የሀገሪቱ ባህል በአዲስ ደም እንደፋፋ ግልጽ ነው። አባ ባሕርይም ቢሆኑ ይኸንን ያህል ዝርዝር የጻፉት ስለባለቤት እንጂ ስለ ጐረቤት ወይም “እጋላ አገር” ሄደው ያገኙት “የመስክ ጥናት” አይደለም።

የየጎሳው ልጆች ያስመሰለን ታሪካዊ አጋጣሚና በቦታ መወሰን ምክንያት ግማሾቻችን ያንዱን ነገድ ቋንቋ፥ ግማሾቻችን ደግሞ የሌላውን ነገድ ቋንቋ ስለምንነጋገር ነው። ለምሳሌ፥ ደምቢያን (ጎንደርን) እና ጎጃምን የወሰዱ ኦሮሞዎች ልጆች ቋንቋ አማርኛ ሆኗል፤ አማራ መስ–ለዋል። የአርሲ ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሐድያ ትውልድ ሆኖ ሳለ ቋንቋው ኦሮሞ ሆኗል፤ ኦሮሞ መስሏል። ይህ መስሎ መገኘት ለጠላት መግቢያ ትልቅ ቀዳዳ ሆኖ እነሆ ሊያተራምሰን ይመላለስበታል።

የምንነጋገረውን ቋንቋ ተከትለን ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈጸሙት ታሪካዊ ድርጊቶች አንዱን ክፍል የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ አንዱን የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ታሪክ እናድርግ ብንል እውነት አትፈቅድልንም። የአያቶቻችን ልጆች መሆናችንን በማያጠራጥር ግምት የምንደርስበትን ያህል የቅድምአያቶቻችን ቋንቋ ምን እንደነበረ አንደርስበትም። ዛሬ የትኛውንም ቋንቋ ወርሰን ብንገኝ ሁላችንም፥ በዚያን ዘመን አነጋገር የጋሎቹና የሲዳሞቹ፥ ወይም በዛሬው አነጋገር፥ የኦሮሞዎቹና የአማሮቹ ልጆች ነን።

በምንናገረው ቋንቋ እየተመራን ከጥንት ዘራችን ልንደርስ የማንችልበት ምክንያት ቋንቋዎቹን ጥምዝምዙ የታሪክ መንገድ ስላሳወራቸው ነው፤ ዕውር ደግሞ መምራት አይችልም፤ ቋንቋዎችን ታሪክ አካፋይ ብናደርጋቸው ሲደናበሩ ለነሱ (ለቋንቋዎቹ) እንደሚመች አድርገው፥ ግማሾቻችንን ከናታችን ግማሾቻችንን ከአባታችን ዘርና ታሪክ ያለያዩናል። በ16ተኛው ምእት ዓመት ኢትዮጵያን የወረሩ ኦሮሞዎችና ሊከለክሏቸው የሞከሩ የቀድሞዎቹ ነባሮች ሁሉም ከሞላ ጐደል እኩል አያቶቻችን ሆነዋል፤ እኛም እንደዚያው ከሞላ ጐደል እኩል ልጆቻቸው ነን።

የምንናገርበትን ቋንቋ ማስረጃ አድርገን ከተፈጸመው ረጂም ታሪክ ውስጥ ኦሮሞዎቹ የፈጸሙትን ዛሬ ኦሮምኛ ለሚናገሩ ሌላውን ለሌሎች ማካፈሉን የምንገፋበት ከሆን መጀመሪያ ታሪኩን ከአያቶቻችን ነጥቀን ለወረስናቸው ቋንቋቸው መስጠት ይኖርብናል። ይህ ደግሞ

“ባለታሪኩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም፤ እኛ ታሪክ የለንም” ማለት ይሆናል።

እርግጥ ኦሮምኛ የሚናገሩ ኦሮሞ የሚባሉ ኢትዮጵያውያንና ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ የግል መጠሪያ ያላቸው ሌሎች ኢትዮጵያውያን አሉ፤ እነዚህ ሰዎች ታሪክ አንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጋቸውን ረስተው ልዩነታቸውን ለማጠንከር ከፈለጉ ከአሁን ይጀምሩት እንጂ ወደ ታሪክ አይሂዱ፤ ታሪክ ያሳቅቃቸዋል፤ ፍላጎታቸውንም ውድቅ ያደርግባቸዋል።

# አባሪ

# Appendix

**በኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ኦሮሞች በሰፊው የጻፉ አለቃ ታዬ::**

(ከ Gustav Arén, *Envoys of the Gospel in Ethiopia*, 1999)

# አባሪ ፩ – Appendix I

## ከአለቃ ታየ ትልቁ መጽሐፍ የተቀዳ

(JE692E, ገ. 548-561, 586-7, 595-600)

“ሌም” ሌሎች ምንጮች፥ “መ” የኢየሩሳሌሙ ቅጂ የአለቃ ታየ መጽሐፍ፡ (JE692E)።
(በጎዳግ ካልገለጽኩ በቅንፍ ያለው የጸሐፊው ነው)

### 17. ስለ ነገደ ጋላ

ስለ ነገደ ጋላ የሚነገር ቁም ነገርና እውነት፥ እውነትና ተረት የሆነ በየአይነቱ ብዙ ልዩ ልዩ ታሪክ አለ። አቶ ዓጽሜ በጻፉት የታሪክ መጽሐፍ ስለ ጋላ ሲናገር እንዲህ ይላል። ጋላ የሚሉት ሕዝብ ካገሩ የወጣበት ምክንያት እጅግ አይታወቅም። ባለታሪኮች እኒህ የጋላ[1] ሕዝብ ከእስያ ፈልሰው ወደ ማዳጋስካር እንደ ተሻገሩ፥ ከዚያም ፈልሰው ቦባሳ አጠገብ ከባሕር ወደብ ተቀመጡ። ቦባሳ ማለት ለከብትም ቢሆን መሠማሪያ ማለት ነው፥ በጋልኛ። ከዚያም ገናሌ የሚባለውን ጅረት ተከትለው ኢትዮጵያ ወጡ ይላሉ።

ካገራቸው ሲወጡ ግን ሁሉ ባንድ ጊዜ አልወጡም፤ የወደደ ወጣ ያልወደደ ቀረ እንጅ[2]፤ ይህ ጋላ የተባለ ሕዝብ ከዚያ ተነስቶ መጣና በባሌ ዳር ገላና በሚሉት ጅረት (ወንዝ)[3] ዳርቻ ተቀመጠ። ላሙንና[4] ፍየሉን በጉን እያረባ እንደ ዘላን ሁኖ ኖረ።

ከመጣም ካዜ ልብነ ድንግል ስመ መንግሥታቸው[5] ወናግ ሰገድ ከሳቸው መንግሥት በፊት 102 ዓመት[6] ሁኖት ነበር። ይህም አዜ ይስሐቅ በነገሡ በ፭ ዓመት በ፮ ሺህ ፱፻፬ዓመተ ዓለም፥ በ፲፬፻፬ ዓመተ ምሕረት

1. መ የገላ።
2. Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis and His Work,* pp. 56-57 and 138.
3. መ።
4. “ላሙን” የሚሉት ግዕዙን ተከትለው ነው፤ በሬም ይጨምራል። ከብቱን ማለታቸው ነው።
5. መ ”ሥጮቸው።
6. መ ዓመ።

ነው፤ የሚሉ አሉ። እውነተኛው ግን የጋሎች ወደ ኢትዮጵያ መውጣት በዛጔ (መራ ተክለ ሃይማኖት ስመ መንግሥቱ ዛጔ[7]) መንግሥት ፲ዓመት በ፱፻፴ ዓመተ ምሕረት ነው።

ፈረንጆች ስለ ጋላ የጻፉት ታሪክ በራስ ዕውቀትና በመመርመር ነው። እኛ ግን አዛኝ ጢኖ የጻፈውን ታሪክ አይተን ነው።[8]

ጋሎች ሲመጡ በጋላኔ ወንዝ (ጅረት)[9] ወጥተው ሐሮ ውላቦ በሚባል አገር ገቡ። በሐሮ ውላቦ ዋናተኛ በዋና የሚቆርጣትና የሚሻገራት ትንሽ ኩሬ ባሕር አለች። ጋሎች አባታችንና ፍጥረታችን ከዚህ ውሀ ወጣነ ይላሉ። ስለዚህም፥ ዑማን ውላቦ ባቲ ይላሉ። ይህም ከውላቦ ውሀ ፍጥረት ወጣ ማለት ነው። ስለዚህ ጋሎች ለውሀ ይሰግዳሉ። ሰውም እንስሳም ከዚያች ውሀ አይጠጣም። ክልክል ነው። ጋላ ሁሉ ከዚያ ለውሀይቱ ይሰግዳል። ከዚያም ሰንጋና ብዙ ፍሪዳ በግም ፍየልም ያርዳሉ።

በሐሮ ውላቡ ልዩ ልዩ ቋንቋ ያላቸው ጥቂት ሕዝቦች አሉ። ዶራስ ይባላሉ። የጋላን ሕዝብ ይመስላሉ። ከሲዳሞ እስከ ውላቡ ፬ቀን፥ ከውላቡ እስከ ቦረን ፭ቀን ያስኬዳል።

ጋሎች ፪ ነገድ ናቸው፤ በርቱማና[10] ቦረና[11] ይባላሉ።
በርቱማ ፮ ልጆችን ወለደ። እነርሳቸውም እኒህ ናቸው፤

፩፥ ከረዩ
፪፥ መረዋ
፫፥ ኢቱ
፬፥ አክቱ[12]
፭፥ ወረንሽ[13]
፮፥ ሁበና[14]

የበርቱማ የበኩር ልጁ፥ ከረዩ ፮ ልጆች ኃይለኞች ወለደ። እነርሳቸውም፤

፩፥ ሊበን

7. ቅንፍ የመ።
8. አዛኝ ጢኖ የጻፉት የሚሉት የትኛውን ድርሰት እንደሆነ አይታወቅም፤ ዜናሁ ለጋላን አስፋፍተው የጻፉት ይመስላል።
9. መ።
10. ሌም "በርቱማ"ን እና "በረይቱማ"ን ያፈራረቋቸዋል።
11. "ቦረን" እና "ቦረና" የአንድ ነገድ ስም ይመስላሉ።
12. መ "አከቱ"ን እና "አክቹ"ን ደጋግሞ ለየብቻቸው ስለሚጽፋቸው የስሕተት ጉዳይ አይመስልም።
13. ሌም "ወረንሻ"ን እና "ወረንጥሻ"ን ያፈራረቋቸዋል፤ አሁን ደግሞ መ "ወረንሽ"።
14. ሌም ሁምበና።

፪፥ ትለሙማ:: ወለሙ[15]
፫፥ ጅሌ
፬፥ አቦ
፭፥ ሉባ
፮፥ ዐለስ ናቸው::

ወለሙ ከ፮ ሴቶች ፮ ወለደ::

፩፥ ሂበኖ
፪፥ ዐበይ
፫፥ አሊ
፬፥ ቃሉ
፭፥ አምቦ
፮፥ ሂዳ
፯፥ ጎራ ናቸው::

ከኢህ ሌላ ደግሞ ለወለሙ በኮ፥ ኖሊኢኑ የሚባሉ ፪ልጆች አሉ የሚሉ አሉ::

ቦረና ፲፩ልጆች ወለደ::

፩፥ ዳጨ
፪፥ ጅሌ
፫፥ ኮኖ — እኢህ
፬፥ ቦች — ትለሙማ ይባላሉ[16]::
፭፥ አካኮ
፮፥ ወቦ — እኢህ
፯፥ ሉባ — ሰደቻ ይባላሉ::
፰፥ ጭሌ
፱፥ ሊቦን
፲፥ ጉድሩ
፲፩፥ ሆኮ ናቸው::

እኢህ ሆኮ ይባላሉ::
ከወለሙ ልጆች ፫ቱ ፊተኞች በወለሙ ስም ይጠራሉ፤ ፬ቱ በወረሰደቻ ስም ይጠራሉ ይባላል::

መረዋ የበርቱማ ሁለተኛ ልጁ ወርድያንን[17] ወለደ::

---

15. ሌም "ቱለማ"፥ "ቱላማ" :: "ወለሙ" የተጨመረው ለእርማት ይሁን አይሁን አይታወቅም::
16. ቁ. 15ን ተመልከት::
17. አንዱ "ን" በስሕተት የገባ መሆን አለበት፤ ቁ. 19ን ተመልከት::

ወርድያን ፫ልጆችን ወለደ። እነርሳቸውም፤

፩፥ አና
፪፥ ዑር[18]
፫፥ አበጢን[19] ናቸው።

እኒህ የመረዋ ልጆች በኃይልና በብዛት ከሁሉ ይበልጣሉ።

ይህም የጋላ ሕዝብ አረማዊ ሕዝብ ነውና እግዚአብሔርን አያውቅም። እግዚአብሔር ለሙሴ ጽፎ ከሰጠው ካ፲ቱ ቃላት ለጋላ የጐደለው መጀመሪያ ትእዛዝ ያንተ አምላክ እኔ ነኝ፤ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ያለው ብቻ ዋና ነገሩ ነውር[20] ከባህርይ ሕግ ጎዶሎነት የሚያስተምረው ሐዋርያ ስላጣ ሁሉን ይፈራልና ዛፉንም ወንዙንም ባሕሩንም ደንጊያውንም ገደሉንም ያመልካሉና ይሰግዳሉም።

ሁለተኛ እሁድን ሰንበተ ጉዳ ቅዳሜን ሰንበተ ጢና እያለ እንደ ክርስቲያን ያከብራል።

ሶስተኛ ምንም ቢሆን በሐሰት አይምልም።

አራተኛ አባት እናቱን አክብሮ በዕድሜ የበለጠውንም ባልንጀራውን ያከብራል። አለዚያ በጨፌ ማለት በሸንጎ ጉባኤ ይፈረድበታል።

አምስተኛ ነፍስ የገደለ በጉማ የነፍስ ዋጋ በመክፈል በእጅግ ብዙ ገንዘብ ይቀጣል። ደግሞ ነገሩ ታይቶ በአዩ በሉባ ተፈርዶበትም የሚሞትም አለ።

ስድስተኛ ምንዝር[21] በጨፌያቸው ወይም በችሎታቸው ከክርስቲያኖች ይልቅ እነሱ መልካም ይፈርዳሉ።

እነዚህም የበርቱማና የቦረን ልጆች የጋላ ነገድ ሁሉ ከሕፃንነት ጀምሮ እስከሽምግልና እንደ ክህነት ያለ መዓርግ አላቸው። ይህ መዓርጋቸው ገዳ ይባላል። ገዳ ማለት እንደ ክህነት ያለ ሹመት ሥልጣንም ነው። ይኸውም ሥልጣናቸው እንደ ዘመናቸው ቁጥር ለ፰ ለ፰ ዓመት ነው። ዘመናቸው በ፰ በ፰ ዓመት ይከፈላል። ገዳ ይሉታል።

በ፰ በ፰ ዓመት የሚከፍሉትም ባሯ ሉቦች ስም እንደ ተጠራ ፭ ናቸው። በ፰ በ፰ ዓመት አንድ ሉባ ተሽሮ ሌላው ሉባ ሲሾም እንደ ሌላው ሕዝብ ንጉሥ ባላባትም[22] ጌታም የለባቸውም። እስከ ፹ዓመት ለሉባ ይታዘዛሉ። ከ፹ ዓመት በኋላ ሌላ ሉባ ይሾማል። የዚያ ጊዜ ለየነገዳቸው ስም ያወጣሉና ይገዘራሉ።

18. ሌም ኡሩ።
19. መ።
20. መ።
21. ዐዕሜ "አመንዝራ"።
22. መ ባለበትም።

ነገሩ እንደኛ ይመስላል። እኛ ዓመት በእየ ወንጌላዊ ስም እንደምንጠራቸው[23]፥ ፩ ማቴዎስ፥ ፪ ማርቆስ፥ ፫ ሉቃስ፥ ፬ ዮሐንስ ብለን ለ፬ ዓመታት ስም እንደምንሰጣቸው[24]፥ እነሱም በ፭ ዓመት አንድ ስም ይሰጣሉ። ፮ውን ዘመን ባ፭ አርበኞች ስም ይጠራሉ። ፮ውን ዘመን ሲጨርስ ተገዝሮ ሉባ ይሆናል።

ይህም ፮ው ዘመን ካ፭ የሚከፍል ያ፭ አርበኞች[25] ስም የሚጠራበት እኒህ ናቸው።

መጀመሪያው፥ ገዳ ቢርመርጂ ነው።[26] ሁለተኛው፥ ሆረታ[27] ወይም ሚልባህ፤ ሶስተኛው፥ ምንችሌ[28] ወይም ሙደና፤ አራተኛው፥ ዱሌ፤ አምስተኛው፥ ሮበሊ ይባላሉ። እነዚህ የጋላ ሕዝብ ሥራት አባ ዱሌች በ፮ በ፮ ዘመን ይመላለሳሉ። የጋላ ታላቁ[29] ሕግ ይህ ነው።

ደግሞ ከዚህ ሌላ ሞጋሳ ኮሉ የሚባል ሥራትና ሕግ አላቸው። ሞጋሳ ለባዕድ ነው። እሱም የጡት ልጅ እንደማለት ያለ ነው። ኮሉ ከጎሳ ወገን ነው። ይህም ረዳት ወይም አዛዥ እንደማለት ነው።

የሕጋቸውም ሥርዓት እንዲህ ነው። ጋላ ከተወለደ ጀምሮ እስከ ሞቱ ድረስ ሕግና ሥርዓት አለው። አባቱ ተገዝሮ ሉባ ሲሆን፥ ልጁ ለ፭ ዓመት ኢትሚኮ ይሆናል።

ቀጥሎ ለ፭ ዓመት ደበሌ ይሆናል። የሕግን ሥርዓት ካባቱ ከሽማግሌችም ይማራል።

ሶስተኛ፥ ጢፎሊ ይባላል፤ ነጻ የወጣ ነው። ይዘፍናል፥ ይጨፍራል፥ የፈቀደውንም ይሠራል። ተው ይህ ከፋ ይህ በጀ የሚለው የለም። በዘፈን በጭፈራ ይጣላሉ ይጋደላሉ። የነጻ ዘመን ነውና ነገር የለበትም[30]።

፬ተኛ ቀኙንዳላ ይሆናል፤ በዕርጋታ በመደመም ይኖራል። ወደ ጨፌ ይሄዳል፥ በሽንጎም ይቀመጣል።

፭ተኛ የቀኙንዳላነቱን ዘመን ከጨረሰ በኋላ ያሮማይ ይባላል። ወደ ጨፌ አይሄድም ወደ ሸንጎም አይወጣም። የቀሩት ወደ ጨፌ ሲሔዱ እሱ በመንደር ይቀራል። ሌባ ቀማኛ[31] ወንበዴ ይሆናል። የማንንም በግና ፍየል

23. መ እንደምጠራቸው።
24. መ እንደምሰጣቸው።
25. መ "ኛት።
26. ጸሐፊዎቹ ገዳን እና ሉባን፥ የሉባውን የተጻውዖ ስምና የሹመት ስም፥ የሉባዎቹን ቅደም ተከተል የሚሰጡት በተለያየ መልክ ነው። ለዚህ ድርሰት መነሻውን የአባ ባሕርይን ድርሰት ማድረግ ይኖርብናል። ገዳ ሥርዓቱ ነው፤ ሉባ ባንድ ዘመን ተገዝሮ 8 ዓመት የሚገዛ ትውልድ ነው። "ቢርመርጂ" ቢርመጂ ነው።
27. አባ ባሕርይ አያውቁትም።
28. ሌም ምስሌ።
29. መ ታሉቁ።
30. መ የለበም።
31. መ ቀመኛ።

እያረደ ይበላል። ብቻ ካንድ በረት ፩ በግ ፩ ፍየል ፩ ሰንጋ እንጂ ፪ አይወስድም።

እንዲሁም እኒህን ፫ መዓርጋት ሲፈጽም ፵ ዘመን ይሆነዋል። ከዚህ በኋላ ይገዘራልና ሉባ ይሆናል።

አዩ ግን ከወገኑ ተመርጦ ወገኑ የወደደውን ይሾማል። ገዳውን የጨረሰ[32] ሉባ ይሾሙታል። አዩም ቦኩን አስመርቆ በጨፌ ይቀበላል። ቦኩ ማለት የወይራ ዱላ ነው። እሱም ቅቤ የጠገበ የተወለወለ እንደ በትረ መንግሥት የከበረ ነው። በሱ ተሹሞ ይመረቅበታል። ፷ ዓመት ተሹሞ ይፈርዳል። ከ፷ ዓመት በኋላ ይሻራል። አይፈርድም፣ ከጨፌም አይደርስም። ሉባ ዱለቻ ይባላል። አዩ በደጁ ከብዙ ሉቦች ጋራ ይፈርዳል።

በ፷ በ፷ ዓመት ጋላ ሁሉ ተሰብስቦ የሚፈርድበት ያለፈውም የ፷ ዓመት ታሪክና ፍርድ የሚነገርበት የተነቀፈው ተነቅፎ አዲስ ሕግ የሚሠራበት ለሚመጣውም የጋላ ሕግና ሥርዓት የሚሰበክበት ቦታውና ጨፌው በቀድሞ ዘመን ቦረና ነበር። ከዚያም የሚፈርደው አባ ሙዳና ይባላል። አባ ሙዳና ማለት መሢሐዊ ወይም የተቀባ ማለት ነው።

ከቦረናም ከወጡ በኋላ እስከዛሬ ከየጎሳው ወደርሱ ስብከቱና ትእዛዙን ሰምተው የሚመለሱ ፪ ፪ ሰው ይልኩ ነበሩ። እነሱም በተመለሱ ጊዜ በእየጨፌው አዩ በክብር ይቀበላቸዋል። እነዚህም ጅላ ይባላሉ። በልብሳቸው ወይም በምልክታቸው የታወቁ ናቸውና በሰልፍ መሀከል ቢሄዱ የሚነካቸው የለም።

ከቦረና ከወጡ ወዲህ የሁሉም ጨፌ መልካ ቦሎ አዋሽ ነበረ። አዩም የሚፈርደው ከጋላን[33] ነበረ። በኋላ ዘመን ጋሎች እስበሳቸው ሲጣሉ ቦታም ሲጠባቸው በሚጥጫም[34] ሲለያዩ በጨፌም ተለያዩ።

32. መ "ሻ።

33. መ።

34. የ"ሚጥጫ"፥ "ሜጥቻ" ትክክለኛ ትርጉም ምን እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም። ቃሉም አንዳንድ ቦታ "መጥቻ" ተብሎ ተጽፎ ይገኛል። ግን የከብት መንጋ መሆን አለበት። "ከግራኝ ወዲህ ሸዋን የተሌማ ጋላ ሜጥቻ አሰረበት።"፥ (EMML 1515 p. 160)። ከዘመቻ በፊት የሚደረግ የከብት ደም ማፍሰስና መቀባት ያለበት አምልኮ በዚሁ ስም ይጠራል። አንድ ምንጭ ክርስቲያኖቹን ሲወቅስ፥ "እንደ ጋላም ደመ መጥቻ ለፈረስ ይቀቡ ያደርጉ ገ'መሩ" ይላል (EMML 144, f. 113a)። አምልኮው ወደ ጦርነት ሲወጡ የሚያደርጉት መሆኑን የልማዱ ታሪክ ያስረዳል። ኦሮሞዎች በንጉሡ ሹምና በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያምፁ ድል የሚያደርጉበትን ዘዴ እንዴት ጋኔን እንደነገራቸው ጸሐፊዎቹ ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ፥ "ይህ ላሎ የሚባል ሰው ቡላ ፍየል ጥቁር በግ ነጭ ላም ቅቤ ይዞ (ከጠንቋይ ዘንድ) መጣ፤ ምን ላድርግ አለው። ከዚህ በኋላ ... እንዲህ አለው፥ በጉን ፍየሉን ላሚን አርደህ ደማቸውን በቅቤ አመድ ለውሰህ ቀድመህ አንተ ግምባርህን ተቀባ፣ ለፈረስህም ቀባው፣ ልጆችህም እንዳንተ ይቀቡ። ሥጋውንም አንተ በፊት

ስለዚህ አዋሽ መልካ ቦሎ የቱለማ[35] ጨፌ ሆነ። የአዩም ያው ገላን[33] ነው። የመጫም ጡሌ ሆነ። እኩሌታ መጫ ነገሥታት አሉበት።

የይቱ ጨፌ ካራ ቀሩርቀሩራ ሆነ።

ከቡርቃ[36] በታች የሐረርጌ ጋላ ጨፌ በሉሎ ነበረ።

እንደዚህም ወሎ አሩሴም በየደጃቸው ጨፌ አደረጉ።

ይኸውም ጨፍያቸው በመሰብሰባቸው ሁከት እንዳይነሳ በዳግማዊ ምኒልክ አዋጅ ተከለከሉ[37]። እንዲህ ስለሆነ ጋሎች በጨፌያቸው የሚፈርዱበት ባጠገባቸው ካለነው ክርስቲያን ነን ከምንለው ይልቅ የነርሳቸው የተሻለ የጸናም ነው።

በጋላ ሥርዓት በሉባ በአዩ በጨፍያቸው ጋላ ያባቱንና የናቱን ልጅ አያገባም። ያጎቱን የእጎቱን ልጅ አያገባም። ሕግ ተላልፎ ቢያገባም እስከሞት የሚያደርስ ብርቱ ቅጣት አለበት። ከወገኑ ከዘመዱ ማግባት በነርሳቸው ዘንድ እርም ነው።

ጥንቱንም አልተጀመረም እንጅ በጨፌ አፍርሰውትም ቢሆን ከሕግ ወጡ ማለት ነው፤ በሕጋቸውም ይፈረድባቸዋል። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል። እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላምና ሕግ ሳይሰራላቸው የበደሉ ሁሉ ያለ ሕግ ይጠፋሉና። ሕግ ተሠርቶላቸውም የበደሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል። ሕግን የሚሰሙ በእግዚአብሔር ዘንድ ጻድቃን አይደሉምና ሕግን የሚሰሩ እነርሳቸው ይጸድቃሉ እንጅ። ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባህርያቸው ሕግ ቢያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው ለራሳቸው ሕግ ናቸው። ሕግንም በማድረግ በልባቸው የተጻፈውን ይገልጣሉ እርስበርሳቸውም ልባቸው ይመሰክርባቸዋል። አሳባቸውም ይገሥጻቸዋል። እግዚአብሔርም በሰው ምሥጢር በሚፈርድበት ቀን በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ ፍርዳቸው ይሆናል እንዳለው የሚሆንበት ጊዜ አለ። ሮሜ 2፡11-17። 1፡42።[38]

ጋሎች በሃይማኖት አረማውያን ናቸው። ብቻ የሐዋርያ ማጣት ነው እንጂ፥ ፩ አምላክ እንዳለ ያውቃሉ፤ ዋቃ ጉራቻ ይሉታል። በተቸገሩና በተጨነቁ ጊዜ ወደ ሰማይ ያያሉ፤ ወደዚያውም ይለምናሉ።

---

በልተህ አብላቸው አለው። ... ላሎም ይህን ነገር ሰምቶ የነገረውን ሁሉ አድርጎ ... አልመጣም ብሎ ካዝማች እንድርያስ ላከ። ከዚህ በኋላ አዝማች እንድርያስ ስማ ሠራዊት ክተት በነጋሪት ብሎ ሰውን ሁሉ ሰብስቦ ተዋጉ። (ላሎ) ድል ነስቶ ላሙን ነድቶ ልጆቹን አስከትሎ ጋላ ከሚባል ዱር ገብቶ ጫት ቡን እየበላ ወተት እየጠጣ ጎጆ ሰርቶ ተቀመጠ" (EMML 144, ff. 107b-108a)።

35. መ "ሉማ።

36. መ ከቡርታ።

37. በሳቢያው ለዐመፅ እንዳይዶልቱ ይሆናል።

38. መ ።

ከጋላ ሁሉ አስቀድሞ የወሎ ጋላ አሰለመ። ቀጥሎ የሜጫ ጋሎች፥ ነገሥታት ነነ የሚሉ፥ ከጊቤ ማዶ ያሉ አሰለሙ። ቀጥለው በሐረርጌ ከተማ ዙሪያ ያሉ ጋሎች ምስሮች በገዙዋቸው ጊዜ በግድ ሰለሙ፤ በኋላም ባጼ ምኒልክ ዘመን እስከ ኢቱ[39] ሰለመ።

አሁንም የቀረው ጋላ ያማራ ወታደርን ስለጠላ[40] ክርስቲያን ከመሆን እስላም መሆንን ይመርጣል። ጋላ አማራን መጥላቱ ገንዘብን በመውደዱና በክፋቱ በመጨከኑ እንቅፋት ሆኖበት ነው እንጂ የእስላም ቢሆን ወይም የክርስቲያን የሃይማኖትን ክፋትና በጕጉት ለይቶ ስላወቀ አይደለም።

## ጋሎች በሴት ቅናትና መጋደል ይቅር ብለው ሕግ የሰሩበት ምክንያት።

(ገ. 555-561)

በወሎ፥ በፊት ገና ሳያሰልሙ፥ አንድ ጅግና ጎበዝ ባገራቸው ነበረ፤ መልካም ቆንጆ ምሽት ነበረችው። አንድ የጨዋ ልጅ መልከ መልካም ገና ከሴት ያልደረሰ ጕበዝ በጎረቤት ነበረ። የዚህ ጅግና ምሽት በዚህ ጕበዝ ፍቅር ተነድፋ ነፍስ አልቀረባትም። ዘወትርም ለምኝታ ትመኘው ነበረች። ከዕለታት አንድ ቀን በተመቸ ቦታ አገኘችው፤ ፈቃድዋንም ለመፈጸም ያዘችው። በጋላ ሥርዓት ያልገደለ ሰው ከሴት አይደርስም ነበረ፤ ይልቁንም ከጉልማሳ ምሽት ምንም አይቀርብ ነበረ።

ስለዚህ እንዲህ አላት፤ የተደረገ ነገር ሳይሰማ[41] አይቀርምና እኔም ገና መራዮን አላወጣሁምና ይህ ነገር ቢሰማ አንች ትነወሪያለሽ፤ ባልሽንም ታስነውሪያለሽ፤ ስለዚህ[42]። አሁን አይሆንም። በኋላ ግን ከዘመቻ ገድዬ በተመለስሁ ጊዜ በግልጥ ወዳጅ አደርግሻለሁ። የጅግና የእገሌ ምሽት ሆነሽ አሁን ከኔ መራዬን ካላወጣሁ ልጅ ጋራ ብትገኝ በኋላ ላንች ታላቅ ኃፍረትና ነውር ይሆንብሻል አላት።

እሱዋ ግን አንድ ጊዜ በክፉ ፍትወት ተነድፋ፥ በሱ ፍቅር እሳት ልብዋ ተቃጥሏልና፥ ይህማ ምን ችግሮህ፤ እኔ አንዱን ልጄን በምሥጢር በንዲህ ያለ ስፍራ እሰድልህለሁ እሱን ግደልና ሰልበህ እያዘፈንህ ና አለችው።

እሱ ግን አዬ ብትጠይኝ ነው እንጂ ይህስ መውደድም አይደለ፤ የዚያን ጅግና ጕበዝ ልጅ ገድዬ በኋላ የተደረገ ነገር ሳይሰማ አይቀርምና ቢሰማ ይገለኛል። እንኳን እኔን ከነዘር አዛጎርቴ ያጠፋኛል አላት።

39. መ ኤቱ።
40. መ ስጠላ።
41. መ ሳይማ።
42. መ ስዚህ።

እሷም ግድ የለህም ይህን ነገር ከኔና ካንተ በቀር ሌላ ሰው ማን ያውቀዋልና ይሰማል ብለህ ትጠራጠራለህና ትፈራለህ አለችው::

እሱም በይ እንግዲያስ ነገርሽ እንዲህ ከሆነ፥ በኋላ ስለ ልጅሽ እንዳይጠትሽ ይህንንም ምሥጢር ለሰው እንዳታወጭ ብሎ በጽኑ መሐላ እንደ ሥራታቸው አማላት:: ከዚህ በኋላ በሩካቤ ሳይገናኙ ሁለቱም በየቤታቸው ሄዱ::

ማታ በጨለማ በቀጠሮው ስፍራ ሂዶ ከዱር ተሸሽጎ ተቀመጠ፤ እሷም ልጅዋን ባንድ ምክንያት ልካ ወደዚያ ስፍራ ሰደደችው:: ልጁም በደረሰ ጊዜ ያዘውና ወደ ሩቅ ስፍራ ወሰደው:: ከዚያም ይህ ልጅ የወንድሜ ልጅ ነውና አደራ ደኅና አድርጋችሁ[43] ተጠንቅቃችሁ[44] ጠብቁልኝና አኑሩልኝ ብሎ ከወዳጅ ዘመድ ቤት አኖረው::

ጊዜው የሽብርና የስርቆት የመግደል ጊዜ ነበርና፥ አባት እናት ቤተ ዘመድም ሁሉ ተሰርቆ ተሸጠ ይሆናል (ወይም ጋዱ ገድሎት ይሆናል)[45] ብለው አልቅሰው ዝም አሉ::

ይህ ጐበዝም ጥቂት ሰንብቶ አንድ ልብስ የፍየል ደም ቀብቶ አንድ ጩቤ ይዞ ወደ ሩቅ አገር ሂጂ ገደልሁኝ፤ ሰለባውን[46] አስጣሉኝ፤ የደም ሸማውን ጩቤውን ግን አመጣሁኝ ብሎ አሳያቸው:: በቤቱ ይዘፈን ጀመረ::

ይህች ሴትም ምንስ ልጃችን ጠፍቶ አዘንተኞች ብንሆን ለርሱም ለጐረቤታችን ሞቱ (ነውና) እንደሰው ሁሉ ሂደን እንኳን ደኅና መጣህ፥ እንኳ ቀናህ እንበለው ብላ ከነ ባልዋ ወደ ቤቱ ሄዱና እንኳ ደኅና ገባህ፥ እንኳ ቀናህ አሉት::

እሱም እንኳ ደኅና ቆያችሁኝ ብሎ እንደ ሥራቱ ስለ ልጃችሁ ሞት *ሐሞቱ ኢሲኒ ኢንዴቢይን ከንጉደቱ ኢሲኒ ያኬኝ* ብሎ አጸናናቸው::[47] ይህም ክፉ አይመልስባችሁ የሚያድግውን ይስጣችሁ ማለት ነው::

ከዚህ በኋላ ተነስታ ከሚዘፍነው ሰው ጋራ ተነስታ[48] ዘፈነች::

ዘፈን ከተፈጸመ ሰው ሁሉ በየቤቱ ተበተነ::

ይህ ጐበዝና ይች ሴት የሚመቻቸውን ጊዜ ሲጠባበቁ ፩ቀን በሩካቤ ተገናኙ፥ ክፉ ፍትወታቸውንም ፈጸሙ:: ከፊተኛው የሚበልጥ እጅግ አጥብቃ ወደደችው::

---

43. መ "ጋቸው:: ይህ በጸሐፊው አማርኛ ልክ ሊሆን ይችላል::
44. መ "ቃቸው:: እንደ ቀኞጥር 43::
45. በኋላ በቅንፍ ጎዳግ ላይ የተጨመረ::
46. መ ሰላ"::
47. መ::
48. መ::

እሱም አንድ ጊዜ ልቧን መዝኖታልና ጥቂት ሰነባብቶ እንቢ አላት:: ምነው ምን ሆንህ አለችው::

ባልንጀሮቸ ይህ አንድ የገደለ ሁለተኛ ያልደገመ[49] እያሉ ሰደቡኝና አሳፈሩኝ አላት::

ይህማ ምን ችግሮህ ደግሞ ሁለተኛውን ልጂን ግደለው ብላ ሰጠችው:: ወስዶም ከወንድሙ ጋራ ጨምሮ (አኑሮት)[50] መጣና እንደ ፊተኛው ገባ፤ ምኞቷንም ፈጸመ::

እንደልማዱ ደግሞ እንቢ አላት:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ እሷም ፫ኛውን ልጅዋን ደግሞ ግደለው ብላ ሰጠችው:: ወስዶም ከወንድሞቹ ጋራ አኖረው:: እንደልማዱም ገደልሁ ብሎ ገባ:: እስዋንም ምሽት አከል አድርጎ ያዘ::

በደረጀም ጊዜ ይህ ጐበዝ ገዳይና ጅግና ሆነ:: እነዚያንም ልጆች እየተመላለሰ እያያቸው በምግብ እያስመቻቸው አደጉ::

ከ፭ ከ፮ ዓመት በኋላ ብርቱ ጉዳይ አለኝና ፯ ቤት ወሎ ይሰብሰብልኝ ብሎ ለሹሙ ለሐዩ ነገረው:: በሁሉም በሐዩ ትእዛዝ ተሰበሰቡ:: ያሚ የሚባል ታላቅ ጉባዔ አደረጉ::

በጉባዔውም መሀከል ይህ ጐበዝ ተነስቶ ቆመ:: ስሙኝ ዘመዶቸ፥ ዋቃ እግዚአብሔር ይስማችሁ[51]::

ጉባዔውም ዝም ብሎ ነገሩን ለመስማት አደመጠ:: *አንዱ ሥራታቸው[52] ጉባዔውንና አገሩን ቆሌውንና አድባሩን ከመረቀ በኋላ፥ ነገሩን እንዲህ ነው ሲል ጀመረ::

የምነግራችሁ ነገር እገሌን የሚያስቆጣ ነውና አስቀድማችሁ እሱን እንዳይገለኝ እሠሩልኝ አለ:: ያ ሰውም ተያዘና ታሠረ::

ነገሩንም ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው፥ የዚህ ሰው ምሽት እሱን በመመኘት በክፉ ፍትወት ተነድፋ በልጆችዋ ያደረገችውን ጭከናና[53] ጕድ ነገር ሁሉ ነገራቸው::

እኔ ግን ልጆቹን አልገደልኩም፤ በመልካም ቦታ እየመገብሁ አሳደግሁ እንጂ፥ ብሎ ሽልሞ አስጊጦ ባጠገቡ አኑሯቸው ነበርና ተነሱ ብሎ በጉባዔው መሀከል አቁሞ፥ እነሆ ልጆችህ ብሎ ላባታቸው አስረከበ::

ልጆቼ ሞቱ ብሎ ተስፋ የቆረጠና በጎዘን ተደቁሶ የነበረ አባትም ድንገት ሳያስበው የልጆቹን መገኘት[54] በጆሮው በሰማ ባይኑም ባያቸው ጊዜ የደስታ ድንጋጤ ደንግጦ እንደ ድንጋይ ሆነ::

---

49. መ ያለ"::
50. መ::
51. "አለ" መጨመር ነበረበት::
52. "እንደ ሥርዓታቸው" ለማለት::
53. መ ጭከ"::
54. መ "ች::

ሰውም ሁሉ በዚህ ሰው ደግነት በዚያች ሴት ጭከናና ክፋት ተደነቀና ተገረመ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ይህ ሰው በጉባዔው መሀከል ተነስቶ ቆመ፥ እንዲህ ሲል፥ ወዳጆቸና ዘመዶቸ ሆይ፥ ደግሞ እስቲ ስሙኝ አንድ ጊዜ ለኛ የሚጠቅመውን ነገር እንድናስብና ሥራት እንድናወጣ እንድናቀናም ልንገራችሁ።

ዕውቀት የሌላቸው እንሰሶችና አራዊቶች እንኳ ለልጆቻቸው ይራራሉ። ስለ ልጆቻቸውም ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ይሰጣሉ። ሰዎች የሚባሉ ፍጥረቶች የኛ ሴቶች ግን ከእንስሳና ከአራዊት እጅግ ይከፋሉ። ይህም ክፋታቸው የሥጋ ፍትወታቸውን ለመፈጸም ልጆቻቸውን ለሞት አሳልፈው እስኪሰጡ የልባቸው መሸፈንና መደንደን ይታያል።

እንዲህ ከሆነ እንግዴህ በንዲህ ያሉ ፍጥረቶች ሴቶች በሚባሉ መቃናትና መጣላት መጋደልም ይቅር። ወንድም ወንድሙን፥ ባልንጀራም ባልንጀራውን፥ ቢቸገር የሚረዳውን፥ ቢጮህ አብሮት የሚወጣውን፥ ቢቆስል የሚያነሳውን፥ ቢሞት የሚቀብረውን በኪህ ጥፎች ምክንያት እንዳይጣላውና እንዳይገድለው እናንት[55] ሽማግሌች ለዚህ ነገር የውል ሥራት አድርጉ። እናቶቻችን ናቸውና ነው እንጂ ሴቶች ከሰው ሊቆጠሩ አይገባቸው ነበረ። እንግዴህ በሴት መቀናናትና መጣላት ይቅር አለ።

ነገሩም በጉባዔው ሁሉ ፊት የተወደደና ያማረ ሆነ። ከዚህ በኋላ ሽማግሌች በሴቶቻቸው ላይ ይህን ሥራት ሠሩ።

አንደኛ ነገር፥ ሴት ልጅ ባባትዋ ቤት ከወንድሞችዋ ጋራ ርስት አትካፈል።

ሁለተኛ፥ በሰው ብትሞት የነፍስ ዋጋዋ የወንድ ነፍስ ዋጋ እኩሌታ ፱ ቁም ከብት ይሁን፥ የወንድ ግን ፲ ቁም ከብት።

ሶስተኛው፥ አባት ሴት ልጁን ሲድር ልጄን ሽጫለሁ[56] ይበል፥ ባልዋም እንደባርያ ቀጥቅጦ ይግዛት። ኮብልላ ሂዳም ከሌላ ሰው ብትወልድ ልጆቿን ጨምሮ መልሶ ወስዶ የግድ ይግዛት።

አራተኛ፥ ከወንድ ባይናፋ[57] ብትያዝ የቅናት ዋጋ ውሽማዋ ለባልዋ አንድ ወይፈን ይስጥ። ለሷም ፩ ሽማና መስታዎት[58] ይስጥ። ይህንን ይዞ ወደ ቤትዋ የሚሄድበት[59] ቀን አራራ ይባላል። ይህም የዕርቅ ቀን ማለት ነው። ለዚህ ላንዱ ወይፈን መናጆ ፯ትም ፲ርም ቁም ከብት አብሮ ወስዶ ከባልዋ በረት ያገባል።

---

55. መ እናት።
56. መ ስ"።
57. "ባይናፋ"? ትርጉሙ ግልጽ ነው፥ ቃሉ ግን የተለመደ አይደለም።
58. ታሪኩ እውነት ቢሆን ድርጊቱ የተፈጸመው በቅርብ ጊዜ ነው ለማለት ይቻላል።
59. መ የምትሄድበት።

እሱም ከጥቂት ባልንጀሮቹ ጋራ ሁኖ አጊጦ ተሸልሞ ይሄዳል። ባለቤቱም ጨዋታና ወግ የሚያውቁትን ሽማግሌች ጠርቶ ጐረቤቶቹንም ሰብስቦ መብልና መጠጥ አቅርቦ እሱም ከምሽቱ ጋራ አጊጦና ተሸልሞ ይቆያል።

ያም እንደደረሰ የውሽማውን ራስ ይስማል። ያመጣውንም አስረክቦ አልፎ ይቀመጣል።

ሽማግሌችም እንግዲህ እናንተ[60] በሁሉ ልትረዳዱ የሚገባችሁ ወንድማማች ናችሁ ይሏቸዋል።

ከዚህ በኋላ ከመልካም ጨዋታ ጋራ መብልና መጠጥ ይቀርባል። እነርሳቸውም በደስታ ሲበሉ ሲጠጡ ሲጫወቱ ውለው ያመጡትን ወይፈን አስረክበው ለመናጆ ያመጡትን ከብቶቻቸውን መልሰው ይዘው ወደቤታቸው ይሄዳሉ።

ከዚህ በኋላ ወደ ውሽማው በግልጥ እየተመላለሰ እንደ ባለቤት ይሆናል። ጦሩን በደጁ አቁሞ ይገባል። ባለቤቱ በሜዳ ኑሮ ሲመጣ የምሽቱን ውሽማ ጦር በደጁ ቁሞ ባየ ጊዜ ወደኋላው ተመልሶ እስኪወጣለት ከጐረቤት ሲጫወት ይቆያል። ወደሩቅ አገር የሄደ እንደሆነም ና ቤቱን ጠብቅ ብሎ ይጠራዋል። የምሽቱ ውሽማ ከቤቱ መጥቶ እንደ ባለ ቤት ሁኖ ባለቤቱ ሲሰራው የነበረውን እየሠራ እስኪመለስ ይቆየዋል[61]።

ጋሎች ይህን ሥራት የሠሩ መቸም ሴትን ጠብቆ ማዳን የለምና ላንዲት ሴት ሁለት ወንድ ቢጠብቃት ይሻላል፥ መቃናትና መጋደል ይቀራል ብለው ነው።

## ስለ ጋላ ትውልድ

(ገ. 586-7)

የጋላ ትውልድ እንዲህ ነው፤ ፊት የጠራናቸው በርቱማ[62] ፮ ቦረን ፲፩ ሁለቱ ወንድማማች ፲፯ ልጆች ወለዱ።

የበርቱማ ልጆች

፩፥ ከረዩ
፪፥ መረዋ
፫፥ ኢቱ
፬፥ አክቱ[63]

60. መ እናተ።
61. መ የ"።
62. ቁ. 10ን ተመልከት።
63. ቁ. 12ን ተመልከት።

፫፡ ወረነሻ
፬፡ ሁበና[64] ናቸው

የከረዩ ልጆች

፩፡ ሊበን
፪፡ ሜጫ
፫፡ ትለሞማ[65]
፬፡ ወለሎ
፭፡ ጅሌ
፮፡ አቦ
፯፡ ሉባ
፰፡ በላዕ ናቸው

የመረዋ ልጆች

፩፡ ወርድያን
፪፡ አሩሲ
፫፡ ኢተ
፬፡ ጥሙጋ

ወርድያን ፫ ይወልዳል

፩፡ አና
፪፡ ዑር[66]
፫፡ አበጢ

እኒህ ሁሉ የመረዋ ልጆች ናቸው። እኒህ የመረዋ ልጆች በኃይልና በብዛት ከሁሉ ይበልጣሉ። ስለዚህም በሁሉ ይገኛሉ።

የኢተ ልጆች

፩፡ ጅሌ
፪፡ ሉባ

የአክቱ[63] ልጆች

፩፡ ጅንጉር
፪፡ ጨፋ

64. "ም" ተውጣ ነው እንጂ "ሁምበና" ነው።
65. ሌም ቱለማ፤ ቁ. 15ንና 16ን ተመልከት።
66. ቁ. 18ን ተመልከት።

የወረነሻ ልጆች

ፅ፥ ሰዩ
ፂ፥ አቡ
ፆ፥ ጫቡ
ፀ፥ ይሉ
ፈ፥ ጉድሩ
ፊ፥ ኩታይ
ፋ፥ አሞሩ
ፐ፥ ሆሮ ናቸው

የሁበና[64] ልጆች

ፅ፥ ራያ
ፂ፥ አዘቦ
ፆ፥ አሸንጌ ናቸው።

እነዚህ ወሎች ያማራ ጐረቤት ስለሆኑ ጋልኛን አጥፍተው ባማርኛ ይናገራሉ። አሸንጌዎች የትግሬ ጎረቤት ስለሆኑ ጋልኛን አጥፍተው በትግርኛ ይናገራሉ።

የቦረን[67] ልጆች፥

ፅ፥ ዳጨ
ፂ፥ ጅሌ
ፆ፥ ኮኖ።
እነዚህ ትሎማ[65] ይባላሉ።

ፀ፥ ቦች
ፈ፥ አካኮ
ፊ፥ ወቦ
ፋ፥ ሉባ።
እኒህ ሰደቻ ይባላሉ።

ፐ፥ ጭሌ
ፀ፥ ሊበን
ፈ፥ ጉድሩ።
እኒህ ሆኮ ይባላሉ።

ፈፅ፥ ሆኮ።

67. ቁ. 11ን ተመልከት።

የዳጨ ልጆች÷

፩÷ ሌቃ
፪÷ ጨለባ::

የጅሌ ልጆች÷

፩÷ ወለጋ
፪÷ ጉማ::

የኮኖ ልጆች÷

፩÷ ሊሙ
፪÷ ጅማ
፫÷ ጌራ::

የቦች ልጆች÷

፩÷ አብቹ
፪÷ ግምብቹ::

የአካኮ ልጆች÷

፩÷ ወበሪ
፪÷ ገላን::

የወቦ ልጆች÷

፩÷ ሉሜ
፪÷ ሊበን::

የሉባ ልጆች÷

፩÷ ሜታ
፪÷ ዋዩ ይባላሉ::

የጭሌ ልጆች÷

፩÷ ጉለሌ
፪÷ ሰላሌ÷[68]

68. ፪ ተረስቶ በኋላ ከ"ሰላሌ" ቀጥሎ ተጽፏል::

የሊበን ልጅ÷

፩÷ አበቲ[69]::

የጉድሩ ልጅ÷

፩÷ ደራ::

የሆኮ ልጅ÷

፩÷ ቦረና[67]::

እኒህ ሁሉ የጋላ አባቶች ናቸው::

## ምዕራፍ

### የወሎ እስልምና እውነተኛው ታሪክስ እንዲህ ነው::
(ገ. 592-594)

የእስላሞች መጀመሪያ ነቢይና ንጉሥ የመሐመድን የልጁን የፋጢማ ባል አሊን አብደርህማን[70] የሚባል ገደለው:: ያሊ ልጅ ከፋጢማ የተወለደው ሐሰን ነግሦ ነበርና በኋላም የሚነግሡ የመሐመድ የፋጢማ የዓሊ ልጆች ናቸውና የአብድ ረህማን[70] ልጆችና ወገኖች ሁሉ የዓሊን ደም ተበቅለው ይፈጁናል ሲሉ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሸዋ በይፋት ተቀመጡ:: ይህም የሆነ በንጉሥ ድግና ሚካኤል ዘመን ነው::

ድግና ሚካኤል ከ፲፮፻፮ (እስከ) ፲፮፻፹፪ ዓመተ ምሕረተ ፳፮ ዓመት ነገሠ:: በሱ ዘመን ውስጥ እኒህ እስላሞች በይፋት ገቡ:: በዚያ ዘመን የነበሩ ተከታትለው የነገሡ ነገሥታትና መኳንንት ካህናትም በስንፍናቸው ዝም ብለዋቸዋልና ብዙ ገንዘብ እየሰጡ በማታለል የነገሥታቱን የመኳንንቱን ልብ አብርደው እኒህ እስላሞች ቀስ ቀስ እያሉ በሸዋ ዳር ለዳር ባልዩ አምባ ባርነባ እስከ ወሎ አገር እያስተማሩ ሰው ሰራሽ ሃይማኖታቸውን ዘረጉና አሰፉ:: ብዙ ያልተማረ ሕዝብን አሰለሙ::

ወሎም በነበረበት ከኒህ እስላሞች ጋራ ተገናኝቶ የእስላምን ሃይማኖት መስማት ጀመረ:: ከዚህም በኋላ ከኒህ እስላሞች ከሉ የሚባል ሸህ መጥቶ አስተማረውና ከወንድሞቹ ተለይቶ÷ እሱ ካሰለመም የእስላም ወገን እየበረታ ሄደ::

---

69. "አበጢ" ይሆን?
70. መ::

ባጼ ዓምደ ጽዮን ደክሞ የነበረ[71] እንደ ገና እየተነሳ አሸቸገረ። ስለ ዚህም በዚያ ዘመን በውድማ አስፈሬ ጊዜ በነገሠ በሁለተኛው (ዓመት)[72] ባንድ ወገን ጋላ ባንድ ወገን እስላም እየተነሳ ቢያስቸግራቸው ጋላን ብቻ ለማጥቃት እኒህ ከይፋትና ከወሌ እስላሞች ለመታረቅ ንጉሡና መኳንንቱ ካህናቱም ተሰብስበው ባንድ ሁነው መከሩ። መክረውም አልቀሩ ከእስላሞች ጋራ ታረቁ[73]።

ዕርቃቸውም ለንጉሥ ሊታዘዙና ሊገብሩ፥ በሃይማኖታቸው ሊኖሩ፥ በየሕዝባቸው በእያገራቸው ሊሾሙ[74]፥ ባገራቸው ውስጥ ያለ ክርስቲያንን እንዳይበድሉ፥ ቤተ ክርስቲያንም ሊጠብቁ እንጂ ላያቃጥሉ፥ በዚህ ውል ክርስቲያኖች በወንጌል እስላሞች በቀሩዓን ተማምለው ውል ሳያፈርሱ በፍቅር ሊኖሩ ታረቁ።

ስለዚህ በይፋት ባርነባ ባሉ እስላሞች አለቃ ወይም ገዥ ተብሎ ወላስማ ተብሎ ከወገናቸው ተሾመ። የወልሰማን ትርጓሜ በኋላ ከእስላሞች ታሪክ ላይ እናመጣዋለን።

ለወሌም ንጉሥ ሰጥቶት ከዋየት ወዲህ ያለን አገር ያዘና ግዛቱ ርስቱም አደረገ። የዚያ አገር ስም ጥንት ላኮ መልዛ ይባል ነበር፤ ወሌ ከያዘው ወዲህ በስሙ ወሌ ተብሎ ተጠራ። ይህ የሆነ በሺ ፲፬፻፷፫ ዓመተ ምሕረት ነው።

ወሌም ገና በሕይወቱ ሳለ አገሩን ለ፯ቱ ልጆቹ አካፍሎ ሰጣቸው። አገራቸውም በየስማቸው ተጠራ።

የሂበኖ ወረሂማኖ ተባለ፤

የቃሉ ወረቃሉ ተባለ። ወረ ማለት አገር ወይም መንደር ማለት ነው።

የዐበይ ዐበይ ቤት፥

የዓሊ ዓሊ ቤት፥

የአምቦ ለገ አቦ[75]፥

የሂዳ ለገ ሂዳ፥

የጎራ ለገ ጎራ ተባለ። ለገ ወይም ለጋ ማለት መልካ ማለት ነው።

ስለዚህም አገሩ በጥቅሉ ወሌ ፯ ቤት ወሌ ይባላል።

---

71. ዓፄ ዓምደ ጽዮን ሲነግሥ በኢትዮጵያ ግዛት ስር የነበሩ የእስላም ሀገሮች አድመው ዐምፀውበት ነበር፤ ይህ ዐመፅ ሳጥናኤል የአምላኩን መንበር ለመቀማት እንደሞከረ ዓይነት ነው ብሎ መታቸው፤ Peruchon, "Histoire des Guerres d' 'Amda Ṣyon, pp. 271-363, 361-493.
72. ውድማ አስፈሬ የነገሠው በ1292-1306 ዓ. ም. ነው።
73. የግብጾችን ታሪክ ይመስላል። መለካውያን (ካቶሊኮች) ቢያስቸግሯቸው ክርስቲያኖቹ ከእስላሞቹ ጋራ ተስማሙ ይባላል።
74. መሾም መሻር የሙሉ ሥልጣን ምልክት ነው።
75. "ም" ተውጣ ነው እንጅ ቃሉ "አምቦ" ነው።

የወሎ እውነተኛ ታሪክ ይህ ነው። የጋኔን ክታብ ተቀበለ፤ አረርጌ ወርዶ የእስላም ክታብ ተማረ፤ ግራኝ ሲመጣ አብሮ መጣ ማለት ግን ፍጹም ሐሰት እንደሆነ በታሪኩ አለመስማማትና በነገሩ ሁሉ ይታያል።

## ስለ ጋላ ተጨማሪ ያፍ ታሪክ

(ገ. 568-9 572-3)

*(አለቃ ታየ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለኦሮሞ ከሚነገረው ያፍ ታሪክ ብዙ ሰብስበዋል። አንዳንዶቹ እንዲህ ሲሉ ይጀምራሉ፤ ጋሎች አባታቸው አራት ወንዶች (ከረዩን፥ ቱለማን፥ መጫን፥ ወሎን) ሶስት ሴቶች (አልኮን፥ ዱረቲን፥ ኢያንቱን) ወልደ። ወንዶቹ የውጭ ሴቶች ቢታጡ(!) አጎቶቻቸውን አገቡ ይሉና ልጆቻቸውን ይዘረዝራሉ። ታሪኩ ከአጀማመሩ ላይ ባይታመንም፥ ስለኦሮሞዎች የሚጽፍ ሰው የልጅ ልጆቹን ዝርዝርና ማን የት እንደሰፈረ የሚሰጥን ምንጭ ሳያጠናው አያልፍም። ስለዚህ ከአለቃ ታየ መጽሐፍ በቀዳሁት ላይ ከዚህ በታች ያሉትን ሁለቱን እጨምራለሁ።*

**<u>አንዱ ታሪክ</u>** (ገ. 568-9)፤

**ከረዩ አያንቱን አግብቶ፥ አሩሲን፥ አያን፥ ቤቶን፥ ይቱን[76] ወለደ።**

**ዳግመኛም የእስላም መሐመድን[77] የየሱፍን[78] ልጅ አግብቶ ትጉሪን[79]፥ ኑሪን ወለደ።**

**አያም አሩሲ ቢሞት እንደ እስላም ሕግ የወንድሙን ምሽት ወርሶ ሱባን፥ ድንጉርጉራን ወለደ። ከንብ ገደል አይመለል ድረስ፥ ከአደል እስከ ጥልጣል[80] ድረስ፥ ከትግሬ በመለስ ይፋትን፥ ምሥራቁን አገር ሁሉ ይዘውታል። ወግግን[81]፥ አሰቦትን፥ ጥቁር ምድርን፥ ጨርጨርንም ሁሉ ይዘውታል።**

---

76. ይቱ "ኢቱ" ነው።
77. "ን" በስሕተት የገባች ይመስላል።
78. "የ" በስሕተት የገባች ይመስላል።
79. ትጉሪ ለታጁራ (ጅቡቲ) ስም የሰጠው የኦሮሞ ነገድ መሆኑ ነው።
80. የአፋሮች ሌላ ስም።
81. ወግግ የአቡነ ሳሙኤል ሀገረ ስብከት ነበረ። ገድላቸውን ስታሊስናስ ኩር አሳትሞታል፤ Kur, *Actes de Samuel de Wagag*. አሰቦት ገዳማቸውን ያቋቋሙበት ደብር ነው። ብዙዎቹን መነኮሳት አሁን በትግሬ ነፃ አውጪ ዘመነ መንግሥት የኦነግ አባላት አረጿቸው።

**ትሎማ አልኮን አግብቶ** የሚጫ አብቹን[82]፥ ዳጨን፥ ሰዶን[83] ወለደ።

ዳግመኛም ከረዩ ቢሞት **የመሐመድን**[77] **የሱፍን ልጅ ምሽቱን ወርሶ** ራያ ያሉትን ጋሎች ወለደ፤ ትሎማ ይባላሉ። ጅሌም የትሎማ ልጅ ነው ይላሉ። ጥንት የዛር ልጅ ነው ይሉት ነበር። በበረት ውስጥ አግኝቶ አሳደገው፤ ስለዚህ የትሎማ ልጅ ተባለ።

**ወሎ ያደል ሴት አግብቶ** ካሉን ወለደና ሞተ።

ዳግመኛም **ትሎማ የወሎን ምሽት ወርሶ** ባቡን፥ ጐራን፥ ኢሉን፥ ቃሉን፥ ካሎን፥ ሂዳን፥ ኩታይን (ወለደ)[84]። እነዚህ ፯ቱ ትሎማ ናቸው። በውርስ ልጅነት ወሎ ይባላሉ።

**ዳጨ የትሎማ ልጅ**[85] **ነው።** ፬ ቤት አብቹን፥ ፭ ቤት ግምብቹን፥ ፮ ቤት ጋላንን ይወልዳል።

ዳግመኛም **ያብቹ ሜጫን**[86] **(ምሽት)**[87] **ወርሶ** ሚታን፥ ቦረናን፥ ሀገረ ደዋሮ ያለውን ሰዶን[88] ይወልዳል። እነዚህም አጨብር፥ ወረዶሮ፥ ኖኖ ይባላሉ።

**ሜጫም ዱረቲን አግብቶ** ጅፋርን፥ ወጌዱን፥ ሊበንን ወለደ።

ኩታይም[89] በሪያን በውርስ ካብቹ ሜጫ ምሽት ወለደችው። እናታቸው ጥቁር ሻንቅላ አይጠ በላ ናት[90]። እነዚህ ሁሉ እስከ ዓጼ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ ፯ ፯ ሁነው በኢትዮጵያ ሁሉ መልተው ከክርስቲያን ጋራ እኩል በኮል ሁነው ኖሩ።

82. አነጋገሩ ሌሎች አብቹዎች ወይም ሌሎች ሜጫዎች ያሉ ያስመስላል።
83. "ሶዶን" ማለቱ ሳይሆን አይቀርም።
84. "ወለደ" አልተቀዳም፤ ተረስቶ ይሆናል።
85. መ ልድ።
86. ቁ. 80ን ተመልከት።
87. ያልተቀዳ።
88. በዚህ አነጋገር ደዋሮ ይባል የነበረው ሶዶ መሆኑ ነው፤ የአቶ ዐፅሜም እምነት እንደዚሁ ነው። ትክክሉን ግን በእርግጠኝነት ማወቅ ያስቸግራል። በየጊዜው ኢትዮጵያን የጐበኙ ምዕራባውያን የነደፏቸው ካርታዎችም እርስ በርሳቸው አይስማሙም። ደዋሮ ግራኝ መጀመሪያ የወጋው የክርስቲያን ግዛት ስለሆነ አዳል አጠገብ መሆን አለበት፤ ወይም ሁለት ሶዶዎች ነበሩ፤ ወይም ሶዶ ከአዳል የሚዋሰን ሰፊ አገር ነበረ። መጠሪያነታቸው ስለቀረው የቦታ ስሞች ሁኔታ ለማወቅ የሚፈልግ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ሰብስቦ ያሳተመውን ማንበብ ይችላል፤ Richard Pankhurst, *The Ethiopian Borderlands*, Lawrenceville (New Jersey) 1997.
89. መ ኩታሪን።
90. ጸሐፊው ሌሎች ሕዝቦች ቀንዳውጣ፥ ውሻ፥ እንቁራሪት፥ አንበጣ እንደሚበሉ የሰሙ አይመስሉም።

**ሌላው ታሪክ** (ገ. 572-3)፤

**ከረዩ አያንቱን አግባና ፲ ወለደ፤ እነሳቸውም እኒህ ናቸው::**

፩፥ አሩሴ
፪፥ ኢቱ
፫፥ ጥሙጋ
፬፥ ጂሌ
፭፥ ሱባ
፮፥ ጅጉርገሩር
፯፥ ጫፋ
፰፥ ራያ
፱፥ አዘቦ
፲፥ አሸንጌ

**ሜጫ አልኮን አግብቶ አስራ አምስት ወለደ፦**

፩፥ ሰዶ
፪፥ አቡ
፫፥ ጫቡ
፬፥ ይሉ
፭፥ ገሩድሩ
፮፥ ኩታይ
፯፥ አሞሩ
፰፥ ሆሩ
፱፥ ሌቃ
፲፥ ጨለባ
፲፩፥ ወሊጋ
፲፪፥ ጉማ
፲፫፥ ሌሙ
፲፬፥ ጅማ
፲፭፥ ጌራ ናቸው::

**ትሎማ ዱረቲን**[91] **አግብቶ አስራ አምስት ወለደ፦**

፩፥ አብቹ
፪፥ ግንብቹ
፫፥ ወበሪ
፬፥ ገላን

91. መ ዱረተን::

ፍ፥ አዳ
ፌ፥ ሉሜ
ፊ፥ ሊበን
ፎ፥ ሚታ
ፏ፥ ዋዩ
ፐ፥ ጉለሌ
ፐ፩፥ ሰላሌ
ፐ፪፥ ዋጁ
ፐ፫፥ አቦቴ
ፐ፬፥ ደራ
ፐፍ፥ ቦረና

ወሎ ፯ ምስቶች አግብቶ ከ፯ ላይ ቤት ሠርቶ ፯ ልጆች ወለደ፤ ስማቸውም እኒህ ናቸው፡-

፩፥ ሂበኖ
፪፥ ዐበይ
፫፥ አሊ
፬፥ ቃሉ
፭፥ አምቦ
፮፥ ሐዳ
፯፥ ጎራ ይባላሉ።

የጋላ ሕዝብ በየነገዳቸው እኒህ ናቸው፤ የከረዩ ልጆች ፲፥ የሚጫ ልጆች ፲ፍ፥ የትሉማ ልጆች ፲ፍ፥ የወሎ ልጆች ፯ በድምሩ በድሙሩ[92] ፸ፍ[93] ነገድ ናቸው።

## የጋላ ሥራትና ሕግ

(ገ. 597-600)

**በኢትዮጵያ ክርስቲያን፥** ክርስቲያን በሚባል ሕዝብ ሕግና ሥራት እየተደነገገ በየጊዜው አይፈጸምም፤ የመንግሥት አዋጅም አያቆመውም። እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም በያገሩ በየደምቡ አረማዊ ቢሆን፥ ክርስቲያንም ቢሆን፥ እስላምም ቢሆን፥ አይሁዳዊም ቢሆን፥ ሁሉ በየወገኑ ጸንቶ የቆመ ሕግ አለው። ከቶ ምንም ቢሆን በጥቂት ነገር በታናሽ ምክንያት ባል ምሽቱን አይፈታም፤ የሚያፋታም[94] የለም።

92. መ።
93. መ። "፸ፍ" መሆን ነበረበት።
94. መ የሚፋታም፤ ዐፅሜ የሚያፋታም።

ጋላ ግን ምንም በምክንያት ቢሆን በረኮ ያገባት ምሽቱን ከቶ አይፈታም። ጋላ በታላቅ ጭንቅ ከምሽቱ ቢለይ እሷም ሂዳ ከሌላ ብትወልድ በኋላ ወደ ረኮ ባልዋ ብትመለስ ልጆችዋን ይዛ ትመለሳለች። ባትመለስም በዚያም ብትሞት ልጆችዋ ለረኮ ባልዋ ሁነው ይሄዳሉ እንጂ ለወለዳቸው አባታቸው አይሆኑም።

ስለዚህም የመጀመሪያ ባልዋ የፈታት ሴት ብትወልድልኝ ልጆቼ ላይሆኑ እያለ አንዳንድ ከጨነቀው በቀር የሚያገባት የለም። ይህም የረኮ ባልዋ የነበረ ቢሞት እኒህ ከውጭ የመጡ ልጆች ዘሩ ያይደሉ እንዲወርሱት ያውቃልና የብርቱ ጭንቅ ነገር ካልሆነ በዋዛ ነገር ክርስቲያን እንደሚባሉ ጐረቤቶቹ የረኮ ምሽቱን አይፈታም።
ማኅተም አልጠፋምና እኒዚያ የውጭ ልጅ እንደ ልጆቹ ትክክል ናቸውና ርስትን ይወርሳሉ። እሱም ከሌሎች ምሽቶች ቢወልድ ዋና ልጁ በኵሩ በጋልኛ አንጋፋ የሚባለው የረኮ ምሽቱ የተወለደው ነው።

ረኮ ማለትም የሕግ የኪዳን የመጀመሪያ ምሽት ማለት ነው። ደግሞ በጋልኛ ጭንቅ ማለት ነው። ከቁባቶቹ ወይም ከሁለተኛይቱ ከረኮ ምንም ታላላቆች ኃይለኞች ልጆች ቢወልድ ዋና ወራሹ የመጀመሪያይቱ የረኮ ምሽቱ ልጁ ነው። ሴት ልጅ ቢወልድ ፈጽማ ወደ ባልዋ ትሄዳለች፤ እንደ እስላም ሥራት በባሏ ወገን ትጠራለች።

ጋላ ከሌላ ጎሳ እንጂ ምንም ቢሆን ከዘመዱ አይጋባም። እንደ ጋላ ዘሩን ቆጥሮ የሚያውቅ የለም። ታላቁ ዕውቀታቸው ዘራቸውን መቁጠር ነው። አባት ለልጁ ትውልዱን ያስተምረዋል። ስለዚህ እስከ ፲ ትውልድ ቢሆን አይጋቡም።

በኢትዮጵያ ፍትሐ[95] ነገሥት እስከ ፬ ትውልድ ሊጋቡ በይነዋል። ዓጼ ዘርአ ያዕቆብ ብቻ በ፯ ትውልድ ሊጋቡ በመንግሥታቸው ሕዝብ ሁሉ አዋጅ ነግረው ነበሩ። ይህም አዋጅ እስከ ዛሬ ከሸዋ በተጉለትና[96] በመንዝ፥ በጐንደር፥ በቤገምድርና በጎጃም፥ ከትግሬ በሐማሴን፥ በሌላም አገር ብዙች ሥራት ይጠብቃሉ፤ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሁሉ ያስቡታል።

በጋላ መጻሕፍት ከተሰጧቸው ከማይጠብቁት ክርስቲያን ነኝ ከሚሉት ጐረቤቶቻቸው ይልቅ የሚሻል ብዙ መልካም ነገር አለበት። ዳሩ አንድ ትልቅ ትልቅ[97] ሁሉን ብላሽ የሚያደርግባቸው ነገር አለ። እሱም እግዚአብሔርን አለማወቅ ነው፤ ማለት ሕጉንና ትእዛዙን በሁሉ ስፍራ መኖሩንም አያውቁም። ሰማዩን እግዚአብሔር ይሉታል። ማን ፈጠረህ ቢሉት ዑመም ይላል። በተቆጡ ባዘኑም ጊዜ ወደ ሰማይ ያያሉና በልባቸው እንዳለ ያስታውቃሉ።

95. መ ፍታ።
96. መ ከተ"።
97. መ።

ጋላ ጥንት ከምሽቱ ወንድ ቢያገኝ ይገል ነበር፥ በፊት እንዳሳየነ። ሰንጋ ካሰረለት[98] ካስታወቀው በኋላ ግን ከምሽቱ ገብቶ ቢያገኘው አንዳች አይለውም። የምሽቱን ውሽማ ጦር ከደጃፉ ቁሞ ባየ ጊዜ እንደ ገባ[99] ያውቃልና ተመልሶ ወደኋላ ይሄዳል።

## በጋላ ሕግ የደም ሥራት

የጋላ የደም ሥራት ባራት ክፍል ይከፈላል።

መጀመሪያ ጨዋ ቢሞት ገዳዩ ፪ ቁም ከብት ይከፍላል።

ሁለተኛ ሴት ብትሞት ፬ ቁም ከብት፤

ሶስተኛ ጠቢብ፥ አንጥረኛ፥ ሸማኔ፥ ፋቂ ባለ እጅ፥ ሁሉ ቢሞት ፰ ቁም ከብት ይከፍላል።

አራተኛ ልጅ አባቱን ቢገል፥ ልጁ የረኮ ምሽቱ ልጅ ቢሆን ያባቱ ወገኖች ድንጊያ ከወገቡ አስረው ከባሕር ይጥሉታል እንጂ እርማቸው ነውና በደም ማፍሰስ አይደበድቡትም። እናቱ ረኮ የሌላት እንደሆነች ግን የናቱ ወገኖች ተቀብለው ወስደው ፪ ቁም ከብት ይክፈሉ እንጂ የሕግ ልጅ አይደለምና አይደብደብ ይላሉ። አባት ልጁን ቢገድልሳ ቢሉ አይገልም ይላሉ።

ስለ ጋላ ከሚነገር ታሪክ ከረጅም ባጭሩ፥ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃናል። ከዚህ ቀጥለን የእናሪያን (ነገር) ታሪክ እንጽፋለን።

## 18. ስለ ነገደ እናርያ[100]

(ገ. 600)

የእናሪያ ሕዝብ ሁሉ የካም ዘር ነው። ነገደ ዮቅጣን መጥተው የነገደ ኮሳን መንግሥት በወሰዱ ጊዜ፥ ሕዝቡንም በጦር አጥፍተው የተረፈውን ባሳደዱ ጊዜ በኢትዮጵያ ደቡብ ዳር ለዳር በወላሞ፥ በሲዳሞ፥ በሆሎ፥ በኮንታ፥ በአሞሮ በዝንጅሮ የሚኖር ሕዝብ ነው። እሱም ከጦር በኋላ ከነገደ ዮቅጣን ነገሥታት ገብቶ ለነሳቸው ተገዝቶ ገብሮ የሚኖር ነው።

ቀድሞ ጋሎች ሳይዙት ሉቅማ፥ ጅማ፥ ሌቃ፥ ትቤ፥ ጉማ፥ ከፋ፥ ይህ ሁሉ የእናሪያ ሕዝብ አገር ነበር። በኋላ ጋሎች እያስለቀቁት የጋላ አገር ሆነ። ይህ ሁሉ ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከዚያም በኋላ እስከ ዘመነ ክርስትና ተያይዞ እንደ መጣ አንድ እናሪያ ተብሎ ከንጉሠ ነገሥት በታች አንድ ንጉሥ ይሾምበት ነበር።

98. መ ከ"።

99. በኋላ የተጨመረ።

100. ይህ ክፍል ስለነገደ እናርያ ነው፥ እዚህ የቀዳሁት ስለ ኦሮሞ ስላለበት ነው።

**ዜናሁ ለጋሻን ወደ እንግሊዝኛ ከተረጐሙት አንዱ ቻርልስ ቤኪንግሃም።**

(ከ *Proceedings of the British Academy,* Vol. 105: 1999 Lectures and Memoirs. )

# ዐባሪ ፪ – Appendix II

## Ethnography of the Galla *(ዜናሁ ለጋላ)*

By Abba Bahriy

In transliterating names and other words, the system I followed is this:

(a) for vowels: “e” for *gi'iz* or first order and *hamis* or fifth order; “u” for *ka'ib* or second order; “i” for *salis* or third order and for *sadis* or sixth order; “a” for *rabi'* or fourth order; and “o” for *sabi'* or seventh order. The “h” has lost the *gi'iz* vovel for the *rabi'*.

(b) for consonants: I have “h” for ሀ, ሐ and ኀ ; “s” for ሰ and ሠ; “’” for አ and ዐ, ignoring both when they come at the beginning of a word; “ch” for ቸ; “tch” for ጨ; “t” for ተ and ጠ; “gn” for ኘ; “j” for ጀ; “ts” for ጸ and ፀ; and “p” for ፐ and ጰ.

Expressions in parenthesis are supplied for the sake of English.

I (hereby) begin to undertake studies[1] of the Galla in order that I may know the number of their tribes, their zeal to kill people, and the brutality of their demeanor. If there is anyone who would say to me, “Why has he written about the wicked ones like the history of the good?”, I will give him an answer, saying to him: “Search in the books, and you will see that the history of Muhammad and the history of the kings of the Muslims have been written, although they are our enemies in religion. Giyorgis Welde Amid[2], too, has written the history of the

1. Lit. “write.”
2. Giyorgis Welde Amid (1205-1273 A.D.) was a Coptic historian who wrote the history of the world from creation to 1260 A.D. Among the Copts he is known as Jirjis Ibn Abi Yãsir Ibn Abû Al-Makarîm Ibn al-‘Amīd al-Makin. The Ge‘ez translation of his work, made in the second half of the thirteenth century, is known by his name.

Zingu'n[3] kings of the Barbarians,[4] who are the Afridon[5] and the other kings of Persia, who are called at this era the Sofi."

**Section 1**

The owner[6] of (this) book says: The Galla appeared from the west[7] and crossed the river of their country, which they call *gelena*[8], to the frontier of Bali[9], in the time of the *Hatse* Wenag Segged.[10] They are the two tribes who are called Bereytuma[11] and Boren.[12]

Bereytuma begot six children. The first was called Kerreyu, the second Merewwa, the third Ittu, the fourth Akkechu, the fifth Werentisha,[13] and the sixth Humbena.[14]

The father of the Boren was called Seppira[15].

Seppira begot Datche, and Datche begot Metcha. Metcha begot Da'ale and Jidda.

And the two brothers gave birth to many tribes, which are the sons of De'ale: Hoko; second, Tchile; third, Obbo; and fourth, Suba.

3. In the world history by Giyorgis Welde Amid, "Zingu'n" (plural of "Zingu'") refers to the Babylonians, e.g., EMML 21, f. 40b, Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. I, p. 23.
4. *'Agam/'ajam* in Arabic is "non-Arab", "pagan", and "Persia."
5. The reference must be to the Farīdun dynasty.
6. I.e. "the author."
7. If the Oromo crossed the frontier of Bale to come to central Ethiopia, they could not have come from west. Ethiopian writers sometimes confuse the names of the cardinal points. Dillmann has references, e.g. Isaiah 11:11, and 45: 6, to some older manuscripts where *"mi'rab"* appears where *"misraq"* is expected; see Dillmann, *Lexicon linguae aethiopicae*, col. 964. The author might have meant to say, "the Galla came to the west."
8. The word probably means "river."
9. Today changed to "Bale."
10. Wenag Segged/Libne Dingel (1508-40) died fleeing from the forces of *Imam* Ahmad Ibn Ibrahim al-Ghazi.
11. Also called "Bertuma."
12. It is not known how the two tribes are related.
13. Also called "Werrensha" and "Werrensh."
14. Also called "Hubbena", with "m" assimilated into "b."
15. In Ge'ez it means a "band of people," from Greek *speira* "military unit;" see Leslau, *Comparative Dictionary of Geez*, p. 509 (col. 1); and n. 28 below.

Jidda begot Hakako, his first-born; second, Gudru; and third, Liben.

Furthermore, Datche begot the Datch--and called them by his own name[16]--the Kono, Becho, and Jille.

And these, too, gave birth to many tribes. Their names are these: the children of Becho are Uru and Ilu; the children of Datch are Soddo[17], Abbo, Galan; the sons of Kono are Seqseq[18], Liben; the sons of Jille are Ela, Abbo, and Li'is.

All these are called Tulema, because they are many.[19] They used to make war together; (but) after a long while, they quarreled with each other and separated from each other, as Abraham and Lot separated when their herds became a multitude, that they said to one another: "Let us separate, so that if you are to the right, I be to the left; or if I am to the right, you be to the left."[20] And it (now) happened as it happened (then).

Similarly, the two tribes of De'ale, who are the Tchile and the Hoko, and also the two tribes of Jidda, Liben and Gudru[21], separated from their brothers and formed unity; and were called *Afre*,[22] in the time of the *luba* which the Boren call Ambisa--the Bertuma[23] call him Robale.

Furthermore, the Hakako, sons of Jidda, and the children of De'ale, Abbo and the Suba, formed unity in the time of the *luba*,[24] called

16. This means "Datch" and "Datche" are the same.
17. Could this mean that the Soddo Gurage got its name from this tribe?
18. There is a region in Gojjam which has this name. It must have received it from Oromo who have since become Amharic speakers.
19. This reasoning gives the impression that "tulema" means many.
20. Gen. 13: 9. Since the allusion is to explain the reason for their separation, we can infer that the separation of the two tribes was caused by their growing number of cattle. The reason the other sources give is "*miticha*."
21. In the text it is usually "Guidru."
22. From *afur* meaning "four". Beckingham and Huntingford have given the English equivalent of most of these Oromo terms in their *Some Records of Ethiopia*, pp. 111-29.
23. Same as "Bereytuma."
24. *Luba* ("the circumcised") is the equivalent of the *messiah* or *hastega* of the Christians.

Birmeje; and were called *Seddecha*.[25] These, too, gave birth to many tribes. These are their names:

The sons of Tchile are Gelam and Webbo/Abbo.
The sons of Hoko are Kiremo, Imuru and Jidda.
The sons of Liben are Waliso, Kutawe and Amiyye.
The sons of Gudru are Sirba, Melol and Tchereqa.
The tribes of Hakako are Abbo, Harsu and Limu.
The tribes of Suba are Hagelebabo and Tchura.
The tribes of Abbo/Obbo are Seyyo, Abono, Tum'e and Leqa.

When all these are allied, they are called Metcha[26]; and when they quarrel, they are called *Afre* and *Seddecha*. When they are all united with the Tulema, they are called Seppira.[27]

Boren,[28] on his side, begot twelve[29] children. The first was Datche, the second Jille, the third Kono, the fourth Becho. These are

25. From "s*edi"* ("three").
26. There is a region in Gojjam which has this name. It must have received it from Oromo who have since become Amharic speakers.
27. See n. 15 above.
28. It seems that Oromo tribes are identified by any one or two of their ancestors; here by Seppira and/or Boren. The name Seppira is enigmatic; see n. 15 above. According to Mersie Hazen Welde Qirqos, the Oromo elders are not familiar with this name, EMML 3749, p. 57. There is a tradition that the ancestors of the Galla are the Portuguese whom *Atse* Gelawdewos settled in the south after the war with *Imam* Ahmad ibn Ibrahim al-Ghazi (Gragn). The Portuguese could have encouraged the "Galla" to revolt against the kingdom which refused to convert to Catholicism. Almeida reports that when Patriarch Dom João Bermudez, their spiritual leader, was expelled from Ethiopia, "God made known to him that the rod and whip which he had first put into the hands of Granh (Gragn) and the Moors (Muslims) of Adel to punish the obstinacy of the Abyssinians, had now been delivered to the Gallas and that they were to be a crueller scourge and almost the total ruin of that contumacious empire. So, the Patriarch, as he came on his way (out of Ethiopia) pronounced many curses on the lands through which he passed, and said, many times that there were certain black ants invading the kingdoms and the provinces of the empire, destroying and wholly devastating it." See Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, p. 135.
29. Possibly a mistake for eleven.

called Tulema. The fifth was Hakako, the sixth Obbo, the seventh Suba--these (three) are called *Seddecha*. The eighth was called Tchile, the ninth Liben, the tenth Gudru, the eleventh Hoko--these (four) are called *Afre*.

**Section 2**

